# መስከረም

STANFORD LIBRARIES

DT 371 MASKARAM
M469

- ሳይንስና ቴክኖሎጂ — ለልማት
- ስለመንደር አንዳንድ መሠረታዊ ባሕርያትና የኢትዮጵያ ሁኔታ
- የሕዝብ ታሪክ ሠሪነትና የግለሰብ ሚና
- ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን

DT
371
M469
NO.25-26
1978

ናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ ፩ ቁጥር
መጋቢት 1978 **25**

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem 515-15 PP 9

ቅጽ 6 ቁጥር
መጋቢት 1978 25

## ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

## ማውጫ

ገጽ


- ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምሥረታው መሳካት . . . . 3
- ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለልማት . . . . . . . . . . . . . . 7

  —ጓበይ ጽጌ

  —ታመነ ታደሰ
- ስለመንደር አንዳንድ መሠረታዊ ባሕርያትና የኢትዮጵያ ሁኔታ . . . . . . . . . . . . . . . . 3 . . . . . . 28

  —በላይነህ አሰጉ
- የሕዝብ ታሪክ ሠሪነትና የግለሰብ ሚና . . . . . . . . . . . . 46

  —ጠና ደዎ
- ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፒሊን . . . . . . . . . . . . . . . . . . 64

  —የቶየ መንገሻ


በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

## የዝግጅት ገጽ

# ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምሥረታው መሰካት

በዓለም ላይ የሚታዩት አገሮች ሁሉ ዛሬ ለሚገኙበት ሁኔታ የበቁት በውስብስብ የታሪክ ሂደት ውስጥ በማለፍ ነው ። ከመካከላቸውም የህልውና ዘመናቸውን በሺህ ዓመታት የሚቆጥሩ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ብዙዎቹ በምዕተ ዓመታት የሚያሰሉ ናቸው ። የተወሰኑትም ዕድሜያቸው በዓመታት ውስጥ የሚካተት ነው ። ኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ የምትደመርና በብዙ ሺህ የሚቆጠር የህልውናና የሉዓላዊ (ሶቨርን) መንግሥትነት ታሪክ ያላት ጥንታዊት አገር ናት ።

ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበት አካባቢ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ፑንት በመባል እንደሚታወቅና ከጥንታዊው የግብፅ ሥልጣኔ ጋር ግንኙነት እንደነበረውም ምልክቶች አሉ ። በተለይም ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ በሁለቱ አካባቢዎች መካከል የንግድ ግንኙነት እንደተመሠረተ የታሪክ ማስረጃዎች ይመሰክራሉ ። ይልቁንም ከ3,500 ዓመታት ገድም ወዲህ ደግሞ ሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር ሆኖ ከግብፃውያን ጋር የተጧጧፈ ንግድ ያካሂድ እንደነበረ ታሪክ ያረጋግጣል ።*

ኢትዮጵያ በሕዝቧና በኋላም በምትገኝበት ጂኦግራፊያዊ አካባቢ በግሪክ ሥልጣኔና እንዲሁም በሮማውያን ሥልጣኔ ዘመናት ታዋቂነት እንደነበራት በታሪክ በሚገባ ተመዝግቧል ። ከሁሉም በላይ የአክሱም ሥልጣኔ ከጥንታዊ የዓለም ሥልጣኔዎች አንዱ እንደነበር ዛሬም ግዙፍ የድንጋይ ቀርጾች፣ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና የሕንፃ ፍርስራሾች ቋሚ ምሥክሮች ናቸው ።

ከዚህ ሁሉ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ እጅግ ረጅም ለሆነ ዘመን የተደራጀ ህልውና የነበረው መሆኑን ነው ። ይህም ህልውናው ከጊዜ ወደጊዜ የተለያየ ቅርፅ ይያዝ እንጂ በሥርዓትና ደንብ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ክፍሎች በየዘመኑ የተነሡ ነገሥታት፣ ሡልጣኖችና ሌሎችም ገዥዎች የበላይነታቸውን የሚያረጋግጡባቸው መንፈሳዊ ስልቶችና የማኅበራዊ ግንኙነት ሥርዓቶች ነበሯቸው ።** በዚህ ረገድ በ15ኛው ምዕተ ዓመት ወደአገራችን እንደገባ የሚነገርለት «ፍትሐ ነገሥት» ወጥነት ያለው ቀደምት የሕግ ሠነድ ሆኖ የተወሰነ ግልጋሎት መስ

---

* Sergew Hable Sellassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History*, Addis Ababa. 1972, pp 21 - 26.

** ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ጉባኤ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ ካደረጉት ንግግር ።



Digitized by Google

ጠቱ ይታወቃል። በ1923 የወጣው ሕገ መንግሥት ደግሞ ለፍጹማዊ የፊውዳል ሥር ዓት በኢትዮጵያ መንሠራፋት ሕጋዊ ዋስትና የሰጠ ሲሆን በ1948 ተሻሽሎ የወጣው ሕገ መንግሥትም በተመሳሳይ ለዘውድ አገዛዙ ሲያገለግል ቆይቷል።

ኢትዮጵያ የዘመናት የመንግሥትነት አኩሪ ታሪክ ያላት አንድዋ ቀደ ምት አገር ስትሆን በአንፃሩ ግን እስከ 20ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ድረስ ለኋላቀር የፊውዳል አገዛዝ ተዳርጋ ኖራለች። በ1966 የአብዮቱ መቀጣጠልም ይህ ሁኔታ ያስከተ ለውና ሊታለፍ የማይችል የታሪክ ግደታ ነበር። በዚህ መሠረት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስ ተዳደር ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የወሰደው አንዱ ዐቢይ የመጀመሪያ እርምጃ የነበረውን ሕገ መንግሥት ማገድ ነው። ይህም የፊውዳሉን ሥርዓት ሕጋዊ ዋስትና ያሳጣው ሲሆ ን ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መመሥረት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

በዚህ መሠረት በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የአረገው ሥርዓት የፖለቲካ ተቋሞች ሕዝባዊ ባሕርይ ባላቸው ተቋሞች እየተተኩ አዲስና ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት እየተገ ነባ መጥቷል። እስካሁን የአዲሱ ፖለቲካ ሥርዓት ዋንኛ አካላት ከሆኑት መካከል የኀ ብረተሰቡ ግንባር ቀደም መሪ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲና እንዲሁም ሕዝቡ ክንዱን ያስተባበረባቸው ልዩ ልዩ ድርጅቶች ህልውናቸው በሚገባ ተረጋግጧል። የሚቀረው የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ቀጥተኛ የሥልጣን መገለጫ የሆነው መንግሥት ብቻ ሲሆን እሱ ንም እውን ለማድረግ በአሁኑ ጊዜ ተገቢው የዝግጅት እንቅስቃሴ በራሱ በሕዝቡ ተሳ ታፊነት በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚቋቋመው አዲሱ መንግሥት ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ለቀጥታ የሥልጣን ባለቤትነት የሚያበቃው ከመሆኑም ሌላ በሁሉም የማኀበራዊ ሕይወት መስኮች ሙሉ ተሳታፊና ወሳኝ የሚያደርገው ነው። ለመንግሥ ታዊ ተግባር አስፈላጊ የሆኑት የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የጣህልና ሌሎችም አካላት ሁሉ ሕዝቡ በምርጫ ከሚያቋቁመውና ሙሉ ሥልጣኑን ከሚገልጥበት አዲስ መንግ ሥት የሚመነጩና ለእሱም ተጠያቂ የሚሆኑ ናቸው። ስለዚሁ መንግሥት አወቃቀር ኢሠፓ በፕሮግራሙ ውስጥ እንደሚከተለው በግልፅ አሥፍሮታል።

> የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መዋቅር በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚገኙትን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግና የብሔረሰ ቦችን አሠፋፈር በማገናዘብ በአንድ ወጥነት የሚደራጅ ነው። በሪፐብሊኩ ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን ከዝቅተኛው የአስተዳደር ክልል እንሥቶ እስከከፍተኛው አገር አቀፍ ደረጃ ድረስ በሕዝብምርጫ ላይ በመመሥረት በሚቋቋሩ አካላት የሚገለጽ ይሆናል።

የኢትዮጵያን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሕጋዊ መሠረት ላይ ለማቋቋም በቅድሚያ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጐት የሚያንጸባርቅ ሕገ መንግሥት ማስገኘት አስፈላጊ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በሰፊው የተያያዝነው ዓቢይ ተግባር ይህንኑ የሚመለ ከት ነው። የሕገ መንግሥቱ ዝግጅት በኢሠፓ የቅርብ ትኩረትና አመራር የተሰጠበት ከመሆኑም ሌላ የሕዝቡ ተሳትፎ ያለበት ነው። በአጠቃላይ በሕዝቡ ለሕዝቡ የሚ ዘጋጅ እንደመሆኑ በኋላም በራሱ በሕዝቡ ለማካይነት የታለመለትን ግብ እንደሚመታ ከወዲሁ እርግጠኛ ለመሆን ይቻላል።



Digitized by Google

በዚህ መልክ ሕገ መንግሥቱ ተዘጋጅቶና ጸድቆ ፣ በእሱም አማካይነት የኢትዮ
ጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሲመሠረት በአገራችን አዲሱ ሕዝባዊ የፖለቲካ
ሥርዓት በተሟላ መልኩ ይሰፍናል ። የሥርዓቱ ዋንኛ አካላት ፣ ማለትም ፓርቲው
መንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች በሚያደርጉት የተቀነባበረ እንቅስቃሴም ፍትሕና የጋራ
ብልፅግና የሰፈነበትን ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የመገንባቱ ጥረት በይበልጥ ፍሬ እያሳየ
እንደሚሄድ እሙን ነው ።

በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ፓርቲው በኅብረተሰቡ ገንባር ቀደም መሪነቱ
የሕዝቡ ፍላጐቶች በሕገ መንግሥቱ መሠረት ተፈጻሚነት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ኃላ
ፊነቱ ይሆናል ። መንግሥት በበኩሉ በየደረጃው በሚዋቀሩት አካላቱ አማካይነት ሕገ
መንግሥቱንና ከእሱም የሚመነጩትን ሕገጋት ተግባራዊ ያደርጋል ። ሕዝባዊ ድርጅቶ
ች ደግሞ የመንግሥታዊ አስተዳደር ጥበብ መቀሰሚያ ትምህርት ቤቶች በመሆን ለአዲሱ
ኅብረተሰብ ግንባታ ሰፊ ድርሻ ይኖራቸዋል ።

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ሕዝቡ በየአካባቢውና በማ
ዕከልም በአንድ ወጥነት በተቀነባበረ መልክ እራሱን በእራሱ የሚያስተዳድር ይሆናል ።
በአካባቢ ደረጃ ተገቢ የሥልጣን አካል በማቋቋም የእራስን ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሕይ
ወት የመምራት መብት ይከበራል ። ከዚያም ባሻገር የየአካባቢውን ሀብትና አቅም
በማቀናጀት የጋራ ኢኮኖሚና ባህል ለመገንባት ፣ የጋራ ደኅንነትን በጋራ ለማስከበር
የሚያስችል ማዕከላዊነት ወይም አንድነት ይኖራል ። አዲሱ መንግሥት በአንድ በኩል
በአካባቢ ፍላጐትና ችሎታ አካባቢን የማስተዳደር ዲሞክራሲያዊ መብት የተከበረበት ፣
በሌላ በኩል ደግሞ ለሁሉም አካባቢ የተመዛዘነ ዕድገት በሚበጅ መልክ የኅብረት ጥረት
የሰፈነበትና አንድ ወጥ አወቃቀር የሚኖረው ነው ።

በሪፐብሊኩ መመሥረት ሙሉ ህልውናው የሚረጋገጠው አዲሱ የፖለቲካ ሥር
ዓት ሁሉም አካላቱ ለአንድ ዓላማ ፣ ማለትም በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ብልፅግና
ለሰፈነበት ኅብረተሰብ ግንባታ የሚቆሙ በመሆናቸው ውስጣዊ ውህደት ያለው ነው ።
ማኅበራዊ ዕድገትን በተቀነባበረ ሁኔታ ለማራመድ ስለሚያስችል ሶሻሊዝምን እውን
ለማድረግ አስተማማኝ ይሆናል ። ስለዚህ ይህ ሥርዓት የተሟላ ህልውናው ይረጋገጥ
ዘንድ ጥራት ላለው ሕገ መንግሥት መገኘትና ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ
ሊኩ በጽኑ መሠረት ላይ መዋቀር ሐቀኛ ዜጎች ሁሉ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ንቁ
የተግባር ተሳትፎ ይጠበቅባቸዋል ።



Digitized by Google

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ
ኢትዮጵያን እንመሠርታለን!



Digitized by Google

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ—ልማት *

ዓቢይ ጽጌ

ታመነ ታደሰ

ታዳጊ ሀገሮች ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ችግሮች የተጋለጡ ፣ በዕድገታቸው እጅግ ወደኋላ የቀሩ መሆናቸው ተደጋግሞ የሚነገር ሐቅ ነው ። እነኝህ ሀገሮች ኋላቀር የሆኑት ምናልባት እንደብረት ፣ ወርቅ፣ መዳብ ፣ ነዳጅ ወዘተ. የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብቶች ስለሌሏቸው ነው ብለን ልንገምት እንችል ይሆናል ። ነገር ግን ፣ ይህ ሳይኖራቸው ከፍተኛው የሥልጣኔ እርከን ላይ ያሉ አገሮች ብዙ ናቸው ። ጃፓን ለዚህ ሁኔታ በምሳሌነት ልትጠቀስ የምትችል አገር ናት ። በሌላ በኩል በብረት ማዕድን ፣ በወርቅ ፣ በሌሎችም ውድና ብርቅ ማዕድናት እንዲሁም በመሬታቸው ልምላሜ የታደሉ ሆነው በሥልጣኔው ምንም ያልገፉ አገሮች በጣም ብዙ ናቸው ። በርካታ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ አገሮች በዚህ ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ ።

የለሙ አገሮች ዛሬ በኢኮኖሚው የተደላደሉ እንዲሆኑ ፣ ኋላቀር አገሮች ደግሞ ኋላቀር ሆነው እንዲቀዩ ያደረገው ምክንያት ምንድንነው ለሚለው ጥያቄ ብዙ መልሶች ቢኖሩም መሠረታዊ ምክንያቶቹ እነኝህ ሀገሮች በውጭ ግንኙነታቸው ለቅኝ አገዛዝና ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ብዝብዛና ጭቆና መጋለጣቸው ፣ በውስጣዊ ሁኔታቸው በኢምፔሪያሊዝም እየተረዱ ማኅበራዊ ዕድገትን በሚያፍኑ የገዥ መደቦች ቁጥጥር ሥር መሆናቸው ነው ። የእነዚህ ሀገሮች ዕድገት መታፈን ዛሬ ጎልቶ ለሚታየውና ለኋላቀርነታቸው አንዱ መገለጫ ለሆነው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕቅማቸው ውሱንነት መንሥኤ ሆኗል ። ይህም የቴክኖሎጂ ዐቅም ውሱንነት ታዳጊ ሀገሮችን በለሙ ፣ በሌላ አነጋገር በቴክኖሎጂ ዐቅማቸው በዳበሩ ሀገሮች ጥገኛ አድርጓቸዋል ።

የለሙ አገሮች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ባለቤት ናቸው ሲባል በነኝህ ሀገሮች ውስጥ በየክፍለ ኢኮኖሚውና ክፍለ

* ከአዲስ አበባ ኢሠፓ ኮሚቴ ለመስከረም ዝግጅት የቀረበ



Digitized by Google

አገልግሎቱ በየደረጃው የሚያስፈልገው የሠለጠነ የሰው ኃይል መጠን በየሙያ ደረጃው ተሟልቶ መገኘቱን ፣ እንደሁኔታው ለሚደረገው የቴክኖሎጂ ግንባታ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራት በማያቋርጥ ሁኔታ ከሙያ ጋር ሥልጠና የሚሰጡ ተቋሞች ተመቻችተው መገኘታቸውን ፣ የኅብረተሰቡን ፍላጐት የሚያረካ ቴክኖሎጂ የቱ እንደሆነ የመምረጥና የመወሰን ችሎታ የዳበረባቸው መሆኑን ፣ አዳዲስ የምርት መሣሪያዎችን አስመስሎ የማበጀቱ ዘዴ በየዘርፉ በመዳበሩና በሁሉም አቅጣጫ የአሠራር መደጋገፍ ሁኔታ መፈጠሩን ፣ የፕሮጀክት ዝግጅትና አፈጻጸም አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች እንደአስፈላጊነቱ መገኘታቸውን ፣ አስፈላጊውን የቴክኖሎጂ መረጃ የሚሰጡ በአሠራራቸው ቀልጣፋና ብቁ ከተለያዩ ኢንተርናሽናል መሰል ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋሞች መኖራቸውን ፣ ለምርምር አድራጊዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠራቸውን ፣ ሕዝቡን ከኋላቀር አመለካከት አላቅቀው ሳይንሳዊ ግንዛቤው የዳበረ ሆኖ ችግሩን ለመወጣት የቴክኖሎጂ ፍላጐቱ እንዲያድግ የሚያደርጉ የተጠናከሩ የሳይንስ ፕሮግራሞች መነደፋቸውን የሚያመለክት ነው ። አንድን ቴክኖሎጂ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ የቴክኖሎጂን ምንነት ከመረዳት ቀጥሎ የሚገኝ ችሎታ ቢሆንም ቴክኖሎጂን በወጉ በመጠቀም የመሣሪያውን ዕድሜ በማራዘም ፣ ምርታማነትን በመጨመር በንዝህላልነት ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማስቀረት መቻሉ ፣ የአገሪቱን ችግር ለይቶ በማውጣት በችግሩ ላይ ምርምር የሚያካሂዱ ተቋሞች በየክፍለ አገልግሎቱና ክፍለ ኢኮኖሚው መኖራቸው ፣ ከነሱም የሚገኘውን ውጤት ከልማት ዕቅዶች ጋር በማጣጣም ቴክኖሎጂን ለልማት የማዋል ሥራ በሚገባ መበልፀጉና በማንኛውም ዘዴ የተገኘውን ትክክለኛ ዕውቀት በጥንቃቄ የመጠቀም ችሎታ መዳበርም የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ወይም ዐቅምን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ናቸው ።

በኋላቀር አገሮች ከነዚህ ሁኔታዎች አንዱ ወይም ሁለቱ ገና በማቆጥቆጥ ላይ ይገኙ እንደሆነ እንጂ ተስተካክለው ሙሉ ለሙሉ አይገኙባቸውም ። ታዳጊ ሀገሮች ከዓለም የምርምር የልማት እንቅስቃሴዎች 2 በመቶ ከፓቴንቱ 0.7 ከመቶ ብቻ ነው ያላቸው ።[1] ይህ ሁኔታ ታዳጊ ሀገሮችን ለ«ቴክኖሎጂያዊ ጥገኝነት» አጋልጧቸዋል ። ሞኖፖሊስቶች በተለይም ድንበር ዘለል ሞኖፖሊስቶች ለታዳጊ ሀገሮች የሚሰጡት ቴክኖሎጂ ተቀባይ ሀገሮችን በመሠረቱ ከቴክኖሎጂ ጥገኝነት የማያወጣ ሲሆን ብዙ ማዕቀበና ግዴታም ያለበት ነው ። ለዚህም አንዱ ምሳሌ የዋጋ ተጽዕኖ ነው ። ታዳጊ ሀገሮች የሚገዙት ቴክኖሎጂ ከዓለም የቴክኖሎጂ ዋጋ የበለጠ ሲሆን አንዳንዴ እስከ 30 ከመቶ በላይ ይሆናል ። በዚህም ምክንያት እነኚህ ሀገሮች በ1982 ብቻ እንኳን ለውጭ ቴክኖሎጂ ማስገቢያ 35,000 ሚሊዮን ዶላር ከፍለዋል ።[2]

ታዳጊ ሀገሮች ከዕለት ወደ ዕለት ለምዕራብ ካፒታሊስት ሀገሮች ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ ምርት ከፍተኛ ዋጋ እንዲከፍሉ ሲገደዱ በአንፃራዊ አነጋገር በዝቅተኛ ቴክኖሎጂ የሚመረተው የእነሱ ሸቀጥ ዋጋ እያሽቆለቆለ ነው ። በእነኚህና በሌሎችም ምክንያቶች ታዳጊ ሀገሮች በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በተዘረጋው የብዝበዛ መረብ ተይዘው በሥርዓቱ ውስጥ እስካሉ ድረስ ከብዝበዛው ለማምለጥ የሚረዳቸው የቴክኖሎጂ ዐቅም ሊኖራቸው አልቻለም ። በመሆኑም የሳይንሳና ቴክኖሎጂ ዐቅም ባለቤት የሆኑ ካፒታሊስት አገሮች ጥሬ ዕቃዎችን ከኋላቀር አገሮች በጣም ርካሽ በሆነ ዋጋ ገዝተው በፋብሪካቸው ፈብርከው ፣ ቀምመውና አበጅተው ጥሬውን ዕቃ ለሸጡላቸው አገሮች ጭምር በብዙ እጅ እጥፍ በሆነ ዋጋ ይሸጡላቸዋል ።

በዚሁ ሁኔታ ኋላቀር አገሮች ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ፣ ካፒታሊስት አገሮች ደግሞ የፋብሪካ ውጤቶች አምራች በመሆን በመካ



Digitized by Google

ከላቸው በተመሠረተው ያልተመጣጠነ ንግድ ካፒታሊስት አገሮች ሲመዘብሩ ፣ ታዳጊ አገሮች ሲመዘበሩ ፣ አብዛኛዎቹ ደሃ አገሮች ይበልጥ ደሃ እየሆኑ ፣ ካፒታሊስት አገሮች ይበልጥ እየበለፀጉ በመሄዳቸው በአሁኑ ወቅት በኢኮኖሚው አንፃር ከፍተኛ ልዩነት ይታያል ።

ታዳጊ አገሮች ከድህነታቸው ለመላቀቅ ወሳኙ መንገድ ተጣጥር ተበድርም ቢሆን ያለ የሌለውን አውጥቶ ወይም በዕርዳታ መልክ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ትላልቅ ፋብሪካዎች ጭምር) መግዛት ነው በማለት በወሰዱት እርምጃ ይበልጥ ተበዝብዘዋል ። ማለትም የተተከለውን ፋብሪካ ለመምራት ተገቢው የሰው ኃይል አለመኖሩ ፣ በየጊዜው የሚያስፈልጉ የመለዋወጫ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ለማምረት አለመቻሉ፣ አንዳንዱም በከፊል የተጠናቀቁ ጥሬ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ የማምረት ዐቅም ማጣቱ ፣ በአጠቃላይ አስፈላጊው መሠረተ ልማት (ኢንፍራስትራክቸር) በአገር ውስጥ አለመገንባቱና እነኝህን ችግሮች ለማቃለል ከሞኖፖሊስቶች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ታዳጊ ሀገሮችን በውጭ ኩባንያዎች ይበልጥ አስመዝብሯቸዋል ። ፋብሪካው ከውጭ መጥቶ ምርት ማምረት ሲጀምር የምርት መሣሪያው የዕልቀት ዋጋ (depreciation) ተተምኖ ፣ የጥሬ ዕቃ ዋጋ ተሰልቶ ፣ አነስተኛ ትርፍ ታክሎበት ሲሰላ አብዛኛውን ጊዜ ዋጋው ከውጭ ከመጣ ተመሳሳይ ዕቃ ከእጥፍ በላይ ከፍ ብሎ ይገኛል ። እንዲሁም ፋብሪካው በዕርዳታ ቢገኝ እንኳን በዕርዳታው ስምምነት ውስጥ የሚጠቀሱት ሐረጎችና አንቀጾች ይበልጥ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮችን ጥቅም የሚያስጠብቁ ስለሆኑ እያደር ለምዝበራ አጋልጠዋቸዋል ። በዚህም ምክንያት ታዳጊ ሀገሮች ለካፒታሊስት ሞኖፖሊስቶች ያላቸው ጥገኝነት ይበልጥ ሊጠናከር ችሏል ።

እዚህ ላይ ቴክኖሎጂን ማሸጋገር አንድን ታዳጊ አገር ይጐዳል ለማለት ሳይሆን ፣ ሽግግሩ ከኢኮኖሚው ግንባታ ጋር የሚጣጣምና በአገሪቱ ውስጥ ከተገነባው የቴክኖሎጂ ዐቅም ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የአብዛኛውን ኅብረተሰብ ፍላጐት የሚያረካ እንዲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጽ ነው ።

ነገሩን ይበልጥ ለማብራራት የሳይንስና የቴክኖሎጂን ፍቺ መስጠቱ አስፈላጊ ነው።

ሳይንስ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ ይህ ነው የሚል አንድ መልስ መስጠት አስቸጋሪ ቢሆንም የሚቀጥለውን ሰፊ ፍቺ መስጠት ይቻላል ። ሳይንስ ማለት

ስለተፈጥሮ ፣ ስለኅብረተሰብና ስለአስተሳሰብ የበለጠ ዕውቀት ለማግኘት የሚካሄድ የምርምር መስክ ነው ። ይህም ለምርምር አመቺ ሁኔታዎችንና የምርምር አካሎችን በሙሉ- ማለትም ሳይንቲስቶችን ከዕውቀታቸውና ከችሎታቸው ፣ ከልምዳቸው ጭምር -፣፣፣ ሳይንሳዊ ተቋሞችን ፣ የቤተሙከራ ( የላቦራቶሪ ) መሣሪያዎችን ፣ የምርምር ዘዴዎችን ፣ የጽንሰሐሳቦችን ፣ የፈርጆችን ፣ የሳይንሳዊ መረጃ ሥርዓትን ፣ ለምርምሩ ቅድመ ሁኔታ መሣሪያ ወይም ውጤት የሆነ ሳይንሳዊ ዕውቀትን በሙሉ ያጠቃልላል ።[3]

ከተጠቀሰው ትርጉም ለመረዳት እንደሚቻለው ሳይንስ ቁሳዊና ሕሊናዊ ገጽታዎች አሉት ። በቁሳዊ ገጽታው ለምርምር የሚረዱ መሣሪያዎች ፣ ተቋሞችንና ሳይንቲስቶችን የሚይዝ ሲሆን በሕሊናዊ መልኩ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና አንድ ገጽ በመሆን አጠቃላይ ዕውቀትን ፣ የሳይንቲስቶች ችሎታንና የምርምር ውጤታቸው የሆነውን ዕውቀት የሚያጠቃልል ነው ። ጠበብ ያለውና የተለመደው የሳይንስ ፍቺ ሳይንስ ሰዎች ስለዓለም ማለትም ስለተፈጥሮ ፣ ስለኅብረተሰብና ስለአስተሳሰብ ያላቸው ሥርዓት ያለው ዕውቀት ነው የሚል ነው ።[4] በአጠቃላይ በዕውቀት መስክ የሳይንስ ልዩ ባሕርይ በተግባር የተገኘውን ዕውቀት በከፍተኛ ደረጃ በማካተት ፣ በማጠቃለል የተ



Digitized by Google

ፈጥርና የማኅበራዊ ክስተቶችንና ሂደቶችን እውነተኛ ውስጣዊ ባሕርይንና ሕግጋትን በንድፈ ሐሳብ መግለጽ ነው ።

እላይ የተጠቀሰውን የሳይንስ ፍቺ የበለጠ ለማብራራት ሳይንስ የሚቀጥለውን ትርጉም ይይዛል ለማለት ይቻላል ።

ሳይንስ ስለተፈጥሮ ሰጥና ስለሰውሠራሽ እንዲሁም ስለኅብረተሰብ ዕድገትና እንቅስቃሴ ሕግጋትና ውስጠ ባሕርያት የሚያሳይ ትክክለኛ አመለካከት ነው ። የሰው ልጅ በሳይንስ ስለተፈጥሮና ስለኅብረተሰብ በየጊዜው ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት ችሏል ። የአገኘውንም ግንዛቤ ጥበብ በተሞላበት ዘዴ በመመርመር ብሎም በተግባር በመፈተን አካባቢውን ይገራበታል ። እንግዲህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሳይንስ ችሎታ ነው፤ ሳይንስ ዕውቀት ነው ፤ ሳይንስ ትክክለኛ ግንዛቤ ነው ልንል እንችላለን ማለት ነው ። የምርት መሣሪያን የኅብረተሰቡን ፍላጐት እንዲያረካ በጥንቃቄ ፣ በሥርዓት በተወሰነ ቅደም ተከተል አስተካክሎ ማበጀት ሳይንስ ነው ስንል ሳይንስ ችሎታ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ስለ አንድ ንጥረ ነገር ወይም ውሁድ ጠቅላላ ጠባይ ዐውቆ እንደ ጠባዩ መያዝና ጥቅም ላይ ለማዋል መቻል ሳይንስ ነው ስንል ሳይንስ ዕውቀት መሆኑን ይገልጽልናል ። በመጨረሻም አካባቢን መርምሮ የተፈጥሮ ሕግጋትን ለምሳሌ ፣ የስበት ሕግን፣ የአየር ግፊትንና እንቅስቃሴን ፣ የብርሃንን ሞገድ ባሕርይ ፣ የማኅበራዊ ችግሮችንና የሥራ አመራርን ምንነትና ሕግጋት ማወቅና በእነዚህም ሕጎች በመጠቀም ለኅብረተሰብ አገልግሎት ማዋል ሳይንስ ትክክለኛ ግንዛቤ መሆኑን ይገልጽልናል ።

ቴክኖሎጂ ሲባል በተለምዶ እንደሚነገረው በነዳጅ የሚሠሩ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የምርት ወይም የአገልግሎት. ጠቀሜታ የሚሰጡ መሣሪያዎችን ብቻ የሚያቅፍ አይደለም ። ቴክኖሎጂ አንድን ሥራ ለማከናወን የሚያስፈልግ ዘዴን ፣ ቅልጥፍናን ፣ ሥርዓትን ፣ የመምረጥን ፣ አስተካክሎ ማበጀትን ፣ መፍጠርንና ሌሎችንም መሰል ሁኔታዎችን ያጠቃልላል ። በመሆኑም ቴክኖሎጂ እንደ ቤት አሠራር ፣ በወንዝ ውሃ በሚገባ መጠቀም ፣ ከበሽታ የመከላከልና ሌሎች መሰል ዘዴዎችንም ያካትታል ።

በአጭሩ ቴክኖሎጂ ሲባል ሰው በእንቅስቃሴው ውስጥ ቁሳዊ ምርትን ለማከናወንና ኅሊናዊ ፍላጐቶቹን (ሥነጥበባዊ ፍላጐቱን ጭምር) ለማርካት የሚገለገልባቸው መሣሪያዎችን የሚያጠቃልል ክስተት ነው ።[5]

ቴክኖሎጂን በተለያዩ መንገዶች ከፋፍሎ ለማየት ይቻላል ። ቴክኖሎጂ በሚውልበት ዓላማ አንፃር የምርትና የአምራች ቴክኖሎጂ በማለት በሁለት መክፈል ይቻላል ። ለምርት ቴክኖሎጂ የሕክምና፣የጦር መሣሪያና የምርምር ቴክኖሎጂዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ። ተግባራዊ በሚሆንበት በምርት መስክ አንፃርም የግብርና ፣ የኢንዱስትሪ፣የመገናኛ ወዘተ· ቴክኖሎጂ በመባል ይከፋፈላል ።[6]

በተጨማሪም ቴክኖሎጂን በሦስት ክፍሎች መለየት ይቻላል ። አንደኛው ባህላዊ ቴክኖሎጂ ወይም በቀል ቴክኖሎጂ ተብሎ የሚጠራው ነው።ሁለተኛው ዓይነት መደበኛ ደረጃ ያለው ዘመናዊ(Standard modern) ቴክኖሎጂ ሲሆን፣በይበልጥ ከያዝነው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ በብዛት ይሠራበት የነበረውን ቴክኖሎጂ ያጠቃልላል ። ሦስተኛው የቴክኖሎጂ ክፍል የተሻሻለ ዘመናዊ (Advanced modern) ተብሎ ይጠራል ። ይህ የተሻሻለ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከመደበኛ ዘመናዊ የሚለየው በውስብስብነቱና በምርታማነቱ ነው ።[7]



Digitized by Google

ቴክኖሎጂ አዳዲስ የሳይንስ ሐሳቦች እየተጨመሩበት ይገነባል ፤ ያድጋል ። በአንፃሩ ቴክኖሎጂ ሳይንሳዊ ምርምር ይበልጥ እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ። በመሆኑም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ግንኙነት ያላቸው የዕድገት መሠረቶች ናቸው ። ቴክኖሎጂ እንዲፈለስፍ ወይም እንዲለወጥ የሚያደርገው የኅብረተሰቡ ፍላጐት ነው ። በመሆኑም ለኅብረተሰቡ ፍላጐት መልስ የሚሰጥ ቴክኖሎጂ ይፈለሰፋል ወይም የነበረው ቴክኖሎጂ አስፈላጊው የሳይንስ ይዘት ይታከልበትና ይለወጣል ። አሊያም ቴክኖሎጂ ከሌላ አካባቢ መጥቶ ተስተካክሎ ከተበጀ በኋላ በሥራ ላይ ይውላል ። ይህም ቴክኖሎጂ በተወሰነ ጊዜ ተገቢውን ግልጋሎት ከሰጠ በኋላ የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለበለጠ ቴክኖሎጂ ይቀሰቅሳል ። በዚህ ዓይነት ቴክኖሎጂ ከትንሽ ወደትልቅ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ የሚያድግ ዲያሌክቲካዊ ሂደት ያለው ክስተት ነው ።

የሳይንስና ቴክኖሎጂን ምንነት ከተገነዘብን በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ዕቅም ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ እንመልከት ። በመጀመሪያ ግን ስለጥንቱ የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ አንዳንድ ነጥቦችን ለመንደርደሪያ ያህል እናንሣ ።

## የቴክኖሎጂ ታሪክ በኢትዮጵያ

ጥንታዊት ኢትዮጵያ ከ4ኛው ምዕት ዓመት እስከ 16ኛው ምዕት ዓመት ድረስ በሥልጣኔአቸው ከታወቁ አገሮች መካከል አንዷ እንደነበረች ብዙ ደራስያን፣ አገር ጐብኝዎችና ሚሲዮናውያን በጽሑፎቻቸው አትተዋል ። ዶ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት «ኢኮኖሚክ ሂስትሪ ኦቭ ኢትዮጵያ» በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ኢትዮጵያውያን ያማሩና የለሰለሱ (ቀጭን) ፈትሎችን ይፈትሉ እንደነበረ ፣ ከጥጥና ከሱፍ የሚሠሩ ልብሶችን ፣ ከበሬ ፣ ከበግ እንዲሁም ከልዩ ልዩ እንስሳት ቆዳዎች ኮርቻዎችን ፣ ጋሻና የጉራዴ ዘገባዎችን ፣ አንፋሮዎችንና ለምዶችን ፣ የመጽሐፍ ሽፋናችን ፣ ከቀንድ መለኪያዎችን ፣ ዋንጫዎችንና የምጥን መያዣ ድጉሶችን ፣ ከብረታብረት የጦርና የእርሻ መሣሪያዎችን ፣ ከወርቅና ከብር የተዋቡ የአንገት ፣ የጣትና የሽማ ጌጦችን ይሠሩ እንደነበረ ገልጸዋል ።

ከእደ ጥበባቱ ቀጥሎ ሊነሱና የጥንት ኢትዮጵያን ሥልጣኔ አጉልተው ለማሳየት የሚያስችሉት የሕንፃና የሐውልት ሥራዎች ናቸው ። በአክሱም ከተማ መሐል አሁንም ቀጥ ብለው ቆመው የሚገኙት የአክሱም ሐውልቶች ፣ በላስታ የሚገኙት ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍለውና ተጠርበው የተሠሩት የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ፣ በጐንደር ከተማ የሚገኘው የፋሲል ቤተ መንግሥት ከጥንት [illegible] ሥራዎች ጥቂቶቹ ናቸው።እነዚህን ሥራዎች ስናነሣ ሐውልቱን ቀጥ አድርጐ ለመትከል የነበረው ችሎታ ለምሳሌ ማዕከላዊ የስበት (የግራቪቲ) ነጥቡን ጠብቆ ሳይዘም እስከአሁን እንዲቆይ መደረጉ በወቅቱ የነበረውን የጂኦሜትሪና የምሕንድስና ችሎታ ለመገምገም የሚያስችል ሲሆን ፣ በሕንፃዎችና በሐውልቶች ላይ ያሉት ንድፎች በዘመኑ የነበረውን ችሎታ ያንፀባርቃሉ ።

እደ ጥበባቱን ፣ ሕንፃዎቹንና ሐውልቶቹን ለመሥራት የጥንት ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ቅርጽና ለአሠራር ምቹነትን ሊሰጡ በሚችሉ መሣሪያዎች የጥንት ባለሙያዎች ይጠቀሙ እንደነበረ አሁንም በሐውልቱና በአብያተ ክርስቲያናቱ ላይ ያሉት ቅርፃ ቅርጽን ምስክርነት በመስጠት ላይ ናቸው።የአክሱምን ሐውልት የሚያህል ነገር ያለዘመናዊ ከባድ ዕቃ አንሺ መሣሪያዎች (ክሬን) ረዳትነት ቀጥ አድርጐ ለማቆም መቻሉን ስናስብ በዘመኑ የነበረውንና አሁን የተረሳውን ቴክኖሎጂ እንድናደንቅ እንገደዳለን ።

እነዚህ ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶቹን ያነሣናቸው የጥንት ኢትዮጵያውያን ሥራዎች፣ በወቅቱ የነበረውን የቴክኖሎጂ ይዘት ከሞላ ጐደል ያስገነዝቡናል ። ዕደ ጥበባቱም

Digitized by Google

ሆኑ ሕንፃዎቹ ከፍተኛ ግምት ሊሰ
ጠው የሚችል ዕውቀት ያላቸው የተለያዩ
ሰዎች ሙያዎች ቅንብር ውጤት እንደነበ
ሩና በተለይ ሕንፃዎቹንና ሐውልቶቹን አስ
ጀምሮ የአሠራር ሂደትን ለመምራትና ለማ
ስጨረስ ከፍተኛ ችሎታ እንደነበረ ለመገ
መት አያዳግትም ።

ኢትዮጵያ የራሳቸው የሆነ ፊደላት ካሏ
ቸው ጥቂት አገሮች ውስጥ አንዷ ናት።
ይህች ሀገር በተለይ በ15ኛው ምዓት ዓመት
በዘርዓ ያዕቆብ አገዛዝ ጊዜ በብራና ጽሑፍ
ከፍተኛ የሥልጣኔ እርከን ተቆናጣ ነበር።[8]
እንደሚታወቀው አንድ ኅብረተሰብ በተ
ለይ ፊደላትን በመቅረጽ ሐሳቡን ፣ ታሪኩ
ንና ሥራውን በጽሑፍ ለማስፈር ከቻለ
ለአካባቢው የነበረው ግንዛቤ ፣ አርቆ የማ
ሰብ ችሎታው የዳበረ ነው ማለት ይቻላል ።

ቴክኖሎጂን እንዲፈለሰፍ የሚያደርገው
የኅብረተሰብ ፍላጐት ነው ። የተፈለሰፈ
ውም ቴክኖሎጂ የዚያን ኅብረተሰብ ፍላ
ጐት አርክቶ እያደር እንደገና የኅብረተሰቡ
ፍላጐት ለሌላ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ እንዲ
ነሣ ያደርጋል ። የኅብረተሰቡ መሠረታዊ
ፍላጐት ካልረካ በስተቀር የቅንጦት የሆኑ
ወይም ከመሠረታዊ ፍላጐት በሁለተኛ
ደረጃ የሚገኙ ነገሮች ለመፈልሰፍ ሁኔታው
በጣም ጠባብ ነው ። ከዚህ በመነሣት እንደ
አክሱም ሐውልት ፣ እንደላሊበላ አብያተ
ክርስቲያናት ወዘተ... የመሳሰሉት ሥራዎች
ሊሠሩ የቻሉት ሌሎች የኅብረተሰቡን ፍላ
ጐት ሊደጉሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች
በወቅቱ ዐድገው እንደነበረም መገመት
ይቻላል ።

በእርግጥ ይህ የጥንት የቴክኖሎጂ ዕድ
ገት በኢትዮጵያ ብቻ የተከሰተ ነበር ለማ
ለት አይደለም ። ዛሬ ታዳጊ አገሮች የሚባ
ሉት እንደሕንድ ፣ ቻይና ፣ እንዲሁም ሌሎች
የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ አገሮችም በቴ
ክኖሎጂ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰው እንደ
ነበረ በርከት ያሉ ተመራማሪዎች ጠቁመ
ዋል ። በዚያን ጊዜ ቴክኖሎጂ በአጠቃላይ
እንደአሁኑ በጥቂት አገሮች ቁጥጥር ሥር
አልነበረም ።[9]

የቴክኖሎጂ ሥርጭት ኢምፔሪያሊስቶች
ከተራ የውንብድና ዘረፋ አንሥቶ እስከ
ወረራ ፣ ከዚያም በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በመ
ዘርጋት ባደረሱት ጥፋት ሊዛባ ችሏል ። የአ
ውሮፓ ቅኝ ገዥ መንግሥታት ዛሬ ታዳጊ
አገሮች በመባል የሚጠሩትን የአፍሪካ፣የእስ
ያና የላቲን አሜሪካ አገሮችን ሀብት ወደ
አገራቸው በማጓጓዝ ካፒታላቸውን አዳብረ
ዋል።ብዝበዛው ቀጥሎ በአንድ በኩል የም
ዕራብ አውሮፓ የካፒታሊስቶቹ ቴክኖሎጂ
ዕድገት እንዲፋጠን በሌላ በኩል በቅኝ የተያ
ዙት አገሮች ቴክኖሎጂ እየቀጨጨና እያደረ
እየጠፋ እንዲሄድ አስተዋጽኦ አድርጓል ።
በአውሮፓ ቅኝነት የተያዙት አገሮች በቴ
ክኖሎጂያቸው ኋላቀር እንዲሆኑና እምብ
ዛም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማይጠይቅ ጠባብ
የምርት ሥራ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ተደ
ረጉ።ለምሳሌ ማሊዢያና ኢንዶኔዥያ የጐማ
ተክል ፣ግብጽና ሱዳን ጥጥ ፣ ሴኔጋል ለውዝ፣
ብራዚል ቡና ፣ ኩባና ፊሊፒንስ ስኳር ፣
ቦሊቪያ ቆርቆሮ ፣ ፔሩ ፣ ቺሊ ፣ ኮንጐና ዛም
ቢያ መዳብ ፤ ኢራቅ ፣ ኢራንና የዓረብ ሰላጤ
አገሮች ዘይት እንዲያመርቱ ተገደዱ ።ይህም
በተለያዩ የኢኮኖሚና የአገልግሎት መስክ
ያሉትን ቴክኖሎጂዎች ትቶ በአንዱ ላይ ብቻ
ማተኮር (ሞኖ ካልቸር) ጤናማ ያልሆነና ቅን
ብር የሌለው «ዕድገት» አስከተለ ። ቅኝ
ገዥዎች የዚህ ዓይነቱ የተዛባ ዕድገት እን
ዲቀጥል ከሚፈልጉበት ዋንኛ ምክንያቶች
መካከል ታዳጊ አገሮችን የማያቋርጥ የጥሬ
ዕቃ ምንጭ ለማድረግ ኋላቀር አገሮች የቴክ
ኖሎጂ ዐቅማቸውን በማዳበርና የሸቀጥ
ምርቶችን በራሳቸው በማምረት ገበያ እንዳ
ይሻሙ ለማድረግ ነው ። የተዛባው ዕድገት
ሥር ሰዶ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ሞኖፖ
ሊስቶች የሚያካሂዱት ቴክኖሎጂያዊ ቅኝ
አገዛዝ ታክሎበት ታዳጊ አገሮችን የቴክ
ኖሎጂ ጥገኛ አድርጓቸዋል ። ዛሬ የብዙ


Digitized by Google

ታዳጊ አገሮች ትግል ከዚህ ጥገኝነት ለመላቀቅ ነው ።

ኢትዮጵያ በቀጥታ በቅኝ ገዥዎች ሥር ባትወድቅም ተዘዋዋሪ ተጽዕኖቻቸው ለቴክኖሎጂው ቀጭጮ መቅረት አስተዋጽኦ አድርጓል ። በአሁኑ ጊዜም የቴክኖሎጂያዊ ቅኝ አገዛዝ ከሚያስከትለው የዕድገት መጫጫት ውጪ አይደለችም ። ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ ያላት ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ፣ የታደለችው ልምላሜ፣ አየሯና ደጋማ መሬቷ በርካታ የወረራ ጥቃቶች እንዲሰነዘሩባት አድርገዋል ። ለምሳሌ ከ1850 እስከ 1888 በአጭሩ በ38 ዓመታት ውስጥ አሥራ አንድ የውጭ ወረራ ጦርነቶችን መክታለች ። በእነዚህ ጦርነቶች ለቴክኖሎጂ ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችሉ የነበሩ ሠርቶ አደሮች ቁጥር ሕይወታቸውን ሰውተዋል ። ለበለጠ ዕድገት ይበጅ የነበረ ሀብትና ንብረትም ወድሟል ።

ከየጦርነቶቹ የተረፈውም ሕዝብ ቢሆን ለሚቀጥለው ጦርነት ላለመሸነፍ በማሰብ ከምርት ክንውን ላይ የበለጠ በጦርነት ዝግጅት ላይ እንደሚያተኩር መገመት ይቻላል ። ጉልማሳው ጋሻ ምከታንና ጉራዴ አስነዛዘርን ይለማመዳል ። በጦርነትም ጊዜ እንደየሁኔታው ወደጦር ሜዳ ይዘምታል ። ሊያመርቱና ቴክኖሎጂን ሊያሻሽሉ የሚችሉ አያሌ ሠርቶ አደሮችም ወረራና አብሮ የሚከተለው የኑሮ መፈናቀል በሚፈጥረው የሀብት መባከን ምክንያት ብዙ ለማምረት አይነሣሡም ።

የአውሮፓ የቴክኖሎጂ አብዮት ውጤት የሆነው የሸቀጥ ምርት እያደር በኢትዮጵያ ከተሞች አካባቢ ያለውን ገበያ በቁጥጥሩ ሥር በማዋሉም የሀገሪቱ የባህላዊ ቴክኖሎጂዎች ውጤት ፈላጊ አጣ ። በዚህ ምክንያት በትላልቅ ከተሞች ይገኙ የነበሩ ቴክኖሎጂዎች ተዘጉ ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ኢትዮጵያውያን እደ ጥበበኞች ከተሞችን ለቀው ገበያ ወደሚያገኙበት ገጠር ገቡ ። ይህን ያላደረጉ የእደ ጥበባት ባለሙያዎች የሥራ መስካቸውን ለመለወጥ ተገደዱ ። ለምሳሌ በሸዋ፣በወለጋና በጋሞ ጉፋ ተጀምረው የነበሩት የብረታ ብረት ማዕድን በማውጣት ብረት የማንጠሩ ሥራ ተቋረጠ ።[10] እነኝህና ሌሎችም መሰል የቅኝ አገዛዝ ተጽዕኖዎች ካፒታሊዝም ትክክለኛው የጥንታዊት ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ዕድገት እንዲጨናገፍ አስተዋጽኦ ማድረጉን ያስገነዝቡናል ።

ሌላው ለኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ መቀጨጭ ምክንያት የሆነው በሀገሪቱ የጉሳዎች የርስ በርስ ጦርነትና ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር የሚያደርሱት ጥፋት ነው ። እንደሚታወቀው በአውጉስቶስ ቄሣር ጊዜ ሮም በሥልጣኔ ገፍታ ነበር ። ሆኖም ይህንን ሥልጣኔ በወቅቱ በሥልጣኔ ያልገፉ ወራሪ የጀርመን የጉትና የስላቭ ጉሣዎች ተራ በተራ እየወረሩ ሥልጣኔውን አውድመውታል ።[11] ከሮም ሥልጣኔ አወዳደቅ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ አይሆን እንደሆነ እንጂ በኢትዮጵያም ውስጥ የጉሳዎች የርስ በርስ ጦርነት በሀገሪቷ ውስጥ ለቴክኖሎጂ ዕድገት መደናቀፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ። የአካባቢው ጉሣዎች ያደረሱት የተደጋገመ ጦርነትና ዘረፋ የአክሱምን ሥልጣኔ እንዲዳከምና እንዲወድቅ አድርጉታል ። ከዚህም በኋላ የገዥ መደቦች የርስ በርስ ጦርነትና የሥልጣን ሽኩቻ እንዲሁም አልፎ አልፎ በአንፃራዊ አነጋገር የቴክኖሎጂ ዕድገት የታየባቸውን በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ አካባቢዎች በዕድገታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበሩ ጉሣዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በቁጥጥር ሥር ማዋላቸው ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ መዳከም ከመንሥዔዎች ውስጥ የሚደመሩ ናቸው ። በርስ በርስ ጦርነቶቹ ታሪካዊ ሥፍራዎች ተደምስሰዋል ፣ የታሪክ ቅርሶች ወድመዋል ፣ አያሌ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ሕይወት ጠፍቷል ፣ ወይም ከሥራቸው ተጓጉለዋል ።[12]

ለኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ መቀጨጭ ከውጭ ወረራ ፣ ከርስ በርስ ጦርነትና ከአውሮፓ

Digitized by Google

ቴክኖሎጂ ተጽዕኖ በተጨማሪ የሀገሪቱ ፊውዳላዊ የመንግሥት ፖሊሲም የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል ። የፊውዳሉ ሥርዓት የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የቴክኖሎጂ ችሎታ በማናናቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለሙያ ዝቅተኛ ግምት እንዲኖር በማድረግ የቴክኖሎጂን ዕድገት አጓቷል ። በሽመና ፣ በሸክላ፣ በብረታ ብረት ፣ በሌጦ ፣ በጽሑፍና በሌሎችም ሥራዎች የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በኅብረተሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ግምት ይሰጣቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ። ለተማሪው ወረቀት ላሽ ፣ ለሸግኔው ቁጢት በጣሽ ፣ ለአንጥረኛው ቀጥቃጭ ፣ ለቆዳ ሥራ ባለሙያው ፋቂ ፣ ለሸክላ ሠሪው ጠይብ የሚሉት መጠሪያዎች ስድብን ያዘሉ ስያሜዎች ናቸው ። አንዳንድ ባለሙያዎች ይህን ማኅበራዊ ተጽዕኖ መቋቋም ተስኗቸው ሥራቸውን በመልቀቅ ወደማይታወቁበት አካባቢ ተሰደዋል ።

የፊውዳሉ የገዥ መደቦች ፖሊሲ የቴክኖሎጂ ሰዎችን በማንቋሸሽ ሀገሪቱን ለውጭ የቴክኖሎጂ ወረራ አጋልጧል ። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የተተከሉት ኢንዱስትሪዎች ለሀገሪቷ ተስማሚነታቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ ጠቃሚ ብሔራዊ የቴክኖሎጂ ዐቅም ሊያስገኙ አልቻሉም ። በመለዋወጫ ፣ በኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ዋጋ፣ለውጭ አማካሪዎች በሚከፈል ደሞዝ ፣ ወዘተ ... አገሪቱ እንድትበዘበዝ አድርገዋል ።

የዚህ ሁሉ ውጤት ዛሬ አብዮታዊት ኢትዮጵያን የቴክኖሎጂ ዐቅም በጣም ኋላቀር ፣ እንዲሁም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ክፍሎች ውስጥ አንዱ እንኳን ጐልቶ የማይታይባት ሀገር እንድትሆን አድርጓታል ። ይህን ሐቅ በበለጠ ለመረዳት ሀገሪቷ በግብርና ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በትራንስፖርትና በመገናኛ ፣ እንዲሁም በጤና አገልግሎት መስኮች ያላትን የቴክኖሎጂ ዐቅም በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን እንመልከት ።

## የግብርና ቴክኖሎጂ

ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረት ነው ። በአሁኑ ጊዜ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት ውስጥ 46% ፣ ከውጭ ንግድ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ 90% ያህሉ የሚመነጨው ከዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ። ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ 86% የሚሆነው የተሰማራው በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ።

የሀገሪቱ የግብርና እንቅስቃሴ በአብዛኛው በኋላቀር ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከክፍለ ኢኮኖሚው የሚገኘው የነፍስ ወከፍ ምርት በጣም ዝቅተኛ ነው ። ከሀገሪቱ ሕዝብ ውስጥ 86% የሚሆነው በግብርና ላይ የተሰማራ ቢሆንም ከዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚገኘው ምርት ሀገሪቱን በምግብ እንኳን ራሷን እንድትችል አላበቃትም ። በአንፃሩ በቴክኖሎጂ በገፉ አገሮች ውስጥ ከሀገሩ ሕዝብ ከ10% የማይበልጠው ብቻ በግብርና ተሰማርቶ የሚያመርተው ምርት ቀሪውን 90% የሀገሩን ሕዝብ መግቦ ለውጭ ገበያ የሚያቀርበው ምርት ይተርፈዋል ።

በየካቲት 1967 የወጣው ሥርነቀል የመሬት አዋጅ ለኢትዮጵያ ገበሬዎች ምርታማነት መጨመር አመቺ የምርት ግንኙነት የፈጠረ ቢሆንም ከአለፈው ሥርዓት የተወረሰው የምርት ኃይሎች ኋላቀርነት የገበሬውን ምርታማነት እንዳይሻሻል አድርጐታል ። የገበሬው ምርታማነት ከፍ ሊል የሚችለው የአስተራረስ ዘዴው ሲሻሻል ፣ ምርቱን ከተባይ ፣ ከአውሬና ከተለዋዋጭ የአየር ጠባይ የሚከላከልበት የተሻለ ዕውቀትና ዘዴ ሲኖረው ፣ ውሱን የሆነውን ጉልበቱን የሚያግዘው የተሻሻለ መሣሪያ ሲያገኝ ፣ እንዲሁም ከጥቂት ዘር ብዙ ምርት በሚያስገኙና ተባይ የመቋቋም ችሎታ ባላቸው ምርጥ ዘሮች ሲጠቀም ብቻ ነው ። በዚህ ረገድ የሀገሪቱ የግብርና ቴክኖሎጂ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለመገንዘብ በክፍለ ኢኮኖሚው የሥራ መገልገያዎች ሁኔታ ፣ የሰው ኃይል ምርታማነትና የምር



Digitized by Google

ምር እንቅስቃሴ ከምን ደረጃ እንዳለ መመልከቱ ይጠቅማል ።

## 1. የሥራ መገልገያዎች

በ1976 በጠቅላላ በሀገሪቱ የነበሩት ትራክተሮች ቁጥር በግምት 7,781፣የእርሻ መሬትን 6.5 ሚሊዮን ሄክታር ነበር።በዚህ መሠረት ለአንድ ሺህ ሄክታር የእርሻ መሬት አንድ ትራክተር ያህል ብቻ ነው የሚደርሰው ። ይህም የሚያሳየው የሀገሪቱ የትራክተር ሥርጭት ዝቅተኛ ፣ አብዛኛው የእርሻ ሥራ የሚከናወነው በባህላዊ ቴክኖሎጂና በሰው ኃይል መሆኑን ነው ።

የማዳበሪያ ሥርጭትም በቂ አይደለም ። ለምሳሌ በ1976 ሥራ ላይ የዋለው ማዳበሪያ 823 ሺህ ኩንታል ነው ። ይህም ለታረሰው የመሬት መጠን 12. ኪሎ ግራም ለአንድ ሄክታር ይደርሳል ። ምንም እንኳን የማዳበሪያ አጠቃቀም ከመሬቱ ጠባይ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ከፍተኛ ምርት ለማግኘት በአማካይ በሄክታር 1 ኩንታል ማዳበሪያ መጠቀም ያስፈልጋል ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ከውጭ የሚመጣው ማዳበሪያ ዋጋው እየናረ በመምጣቱ ገበሬው ከዕውቀቱ ውስንነት በተጨማሪ የተፈለገውን ያህል ማዳበሪያ እንዲጠቀም ለማድረግ አልተቻለም ።

ሌላው በእርሻ ውጤቶች ምርታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚኖረው የሚዘራው ዘር የጥራት ደረጃ ነው ። ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት ለማግኘት የሚዘራው ዘር ለምሳሌ ገብስ 1 ኩንታል በሄክታር ፣ ስንዴ 1 ኩንታል ተኩል በሄክታር ፣ በቆሎ 30 ኪሎ ግራም በሄክታር ወዘተ· ምርጥ ዘር መሆን ይኖርበታል ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በ1976 በመንግሥት እርሻዎችና በገበሬዎች ከተዘራው ውስጥ 0.7 ኪሎ ግራም ብቻ ነበር ምርጥ ዘር የተዘራው።ቀሪው 99 በመቶ አካባቢ የሚሆነው ዘር ጥራት የጐደለው ሲሆን ከዚህ የሚገኘው ምርትም ከፍተኛ እንደማይሆን መገመት ይቻላል ።

## 2. የሰው ኃይል ምርታማነት

የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት ለማስላት የሚያስችል በቂ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ነው ። ይሁን እንጂ አንዳንድ የናሙና ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የገበሬው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የምርት ውጤት ከብር 373 እንደማይበልጥ ይገመታል ።

በክፍለ ኢኮኖሚው ውስጥ የተሻለ መረጃ የሚገኘው በመንግሥት እርሻዎች ስለሆነ የነዚህ እርሻዎች የስድስት ዓመት ምርታማነት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል ።

| | | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 | 1977 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርት ውጤት / ሚሊዮን ብር/ | 152.5 | 206.1 | 206.0 | 180.6 | 156.5 | 168.8 |
| 2 | የሰው ኃይል* / በሺህ ፣ በቁጥር/ | 62.7 | 60.1 | 62.3 | 64.3 | 54.6 | 55.5 |
| 3 | ምርት በነፍስ ወከፍ ፤ /በብር/ | 2,432 | 3,429 | 3,307 | 2,809 | 2,866 | 3,032 |
| 4 | የምርታማነት ኢንዴክስ /1972—100/ | 100 | 141 | 136 | 116 | 118 | 125 |

ምንጭ ፡- በማ· ፕ· ብ· ኮ· ጽ/ቤት የፕላን ክትትልና ቁጥጥር መምሪያ ካዘጋጀው የ6ቱ ዓመታት (1971—76) የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ከኅብርና ልማት መምሪያ መረጃዎች የተቀነባበረ ። (የምርት ውጤት በ1973 ዋጋ)

* የሰው ኃይል ቁጥር ለማግኘት የጽሚ ሠራተኞች ሙሉ ቁጥርና የጊዜያዊ ሠራተኞች ግማሽ ተወስዷል ።

Digitized by Google

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው ከመንግሥት እርሻዎች የተገኘው የነፍስ ወከፍ ምርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው በ1973 እና በ1974 ሲሆን በ1975 እና በ1976 ደግሞ ዝቅ ብሎ ይታያል ። በአጠቃላይ ሲታይ ከ1972—1977 በነበሩት ስድስት ዓመታት የመንግሥት እርሻዎች የነፍስ ወከፍ የምርት ውጤት ከብር 2,432—እስከ ብር 3,429 ሲሆን ይህም ከገበሬው የነፍስ ወከፍ የምርት ውጤት (ብር 373) ጋር ሲነፃፀር እስከ ስምንት ጊዜ እጥፍ ብልጫ ያሳያል ። ለዚህ ከፍተኛ የምርታማነት ልዩነት ዋናው ምክንያት ገበሬው የሚጠቀምበት ቴክኖሎጂ የመንግሥት እርሻዎች ከሚጠቀሙበት ቴክኖሎጂ በጥራትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ መሆኑ ነው ። ለምሳሌ የመንግሥት እርሻዎች በአንድ ሄክታር በአማካይ 142 ኪሎ ግራም ማዳበሪያ ሲጠቀሙ ገበሬው በአማካይ 8.2 ኪሎ ግራም ብቻ ይጠቀማል ። የምርጥ ዘርን አጠቃቀም ያየን እንደሆነ የመንግሥት እርሻዎች በአማካይ 85 ኪሎ ግራም በሄክታር ሲጠቀሙ ገበሬው 0.7 ኪሎ ግራም ብቻ ይጠቀማል ።

እንዲሁም ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት በመንግሥት እርሻዎች ለ115 ሄክታር መሬት አንድ ትራክተር ሲኖር በገበሬው እርሻ ደግሞ ለአንድ ሺህ ሄክታር የእርሻ መሬት አንድ ትራክተር ቢደርስ ነው ።

በአጠቃላይ በተሻሻለ ቴክኖሎጂ መጠቀም ከአንድ ሄክታር የእርሻ መሬት የሚገኘውን ምርት ምን ያህል ከፍ እንደሚያደርገው በሌላም ምሳሌ ማሳየት ይቻላል ። የጤፍ ምርት ለምሳሌ በባህላዊ ቴክኖሎጂ ብቻ በመጠቀም በሄክታር ቢበዛ 8 ኩንታል ገደማ የሚገኝ ሲሆን በአንፃሩ በማዳበሪያ ፣ በምርጥ ዘርና የተሻሻሉ የእርሻ ዘዴዎች በመጠቀም ከሁለት እጥፍ በላይ (ከ20—22 ኩንታል) ማግኘት እንደሚቻል ተረጋግጧል ። እንዲሁም የስንዴ ምርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በሄክታር ከ10 ኩንታል ወደ 35 ኩንታል ከፍ ሊል ይችላል ።

### 3. የምርምር እንቅስቃሴ

የኢትዮጵያን የግብርና እንቅስቃሴ በምርምር ለመደገፍ የተወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ በ1958 የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩትን ማቋቋም ነበር። ይህ ኢንስቲትዩት ሲቋቋም የነበረው ዓላማ በአንድ በኩል የእርሻ ፣ የከብት ርቢና የደን ውጤቶችን ለማበራከት የሚረዳ ብሔራዊ የእርሻ ምርምር ፖሊሲ ለማዘጋጀት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሚወጣው ፖሊሲ መሠረት በተመረጡ የእርሻ መስኮች ላይ የሠርቶ ማሳያ ፕሮግራሞች ለማዘጋጀትና ለማከናወን ነበር ።

ኢንስቲትዩቱ በነዚህ አጠቃላይ ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ስለአዝርዕት ፣ ተክልና ፍራፍሬዎች፣ ስለከብት ግጦሽና መኖ፣ ስለሥጋና ወተት ማሻሻያ፣ ስለ ደን ልማትና እንክብካቤ ፣ ስለእርሻ ምሕንድስና ፣ እንዲሁም ስለእርሻ ኢኮኖሚክስ ምርምሮች አከናውና አንዳንድ ተጨባጭ ውጤቶች አስገኝቷል ።

ሀ/ የአዝርዕትን ማሻሻያ ምርምር በሚመለከት ፣ በስንዴ ፣ በገብስ ፣ በበቆሎ በጤፍና በልዩ ልዩ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬዎች ላይ በተደረገው ምርምር በሽታ የመቋቋም ችሎታ ባላቸው ዝርያዎች በመጠቀምና ልዩ ልዩ ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎችን በሥራ ላይ በማዋል ገበሬው በልማዳዊ ዘዴ ተጠቅሞ ከሚያገኘው ምርት ከሁለት እስከ ሦስት እጥፍ የሚሆን ምርት ለማግኘት እንደሚቻል በሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎች የተካሄደው ሙከራ አረጋግጧል ።

ለ/ የእንስሳትን እርባታ ፣ የግጦሽና የመኖን ምርምር በሚመለከት ፣ በከብቶች ፣ በበጎችና በፍየሎች ላይ በተካሄደው ምርምር የተሻለ የሥጋና የወተት ምርት የሚያስገኙትን ዝርያዎች ለመምረጥ ከመቻሉም ሌላ ከውጭ አገር ከተገኙ ምርጥ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል ጠቃሚ ልምድ ተገኝቷል ።


Digitized by Google

የእንስሳት መኖ ዝግጅትን በሚመለከት ደግሞ በተለያዩ የመኖ ዓይነቶች ላይ የላቦራቶር ሙከራ ከመደረጉ ሌላ ለደጋውና ለቆላው የአየር ጠባይ የሚስማሙ የሳርና የቅጠላ ቅጠል ዓይነቶች ተመርጠዋል ።

ሐ/ <u>የእርሻ ምሕንድስናን ምርምር በሚመለከት</u> ፤ በእርሻ ምሕንድስና የምርምር ዘርፍ ባህላዊ የእርሻ መሣሪያዎች የሚሻሻሉበትን መንገድ ለማጥናት ፤ ልዩ ልዩ መገልገያ መሣሪያዎችን ሠርቶ ለማሳየት ፤ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለማፍለቅና የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን ለማጥናት ጥረት የተደረገ ቢሆንም እንደውሃ መሳቢያ ፤ የእንሰት መፋቂያና የእህል መውቂያ መሣሪያዎች ሠርቶ ከማውጣት በቀር ይህን ያህል ጉልቶ የሚታይ ውጤት አልተገኘም ። ለዚህም ዋናው ምክንያት የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መሆኑ ታውቋል ።

የምርምሩ እንቅስቃሴ ካስገኛቸው ውጤቶች ሌላ የሀገሪቱን የምርምር ዐቅም ለመገምገም ከሚያስችሉት ጠቋሚዎች ዋናዎቹ ለምርምር ሥራ የሚመደበው የበጀት ድርሻና በዚሁ ሥራ ላይ የተሰማራው የሠለጠነ የሰው ኃይል ናቸው ።

ለእርሻ ምርምር ተግባር በየዓመቱ የተመደበው የሙአለንዋይ ወጪ ከሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነፃፀር 0.17% ሲሆን ይህም ኢኮኖሚያቸው በእርሻ ላይ የተመሠረተ አገሮች ከምርምር አጥጋቢ ውጤት ለማግኘት ወጪ ማድረግ ከሚገባቸው 2.5% ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል ።

ይህ ሐቅ ሀገራችን ለእርሻ ምርምር ሥራ የበለጠ ትኩረት መስጠት እንዳለባት የሚያስገነዝብ ነው ። ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በጓድ መንግሥቱ የቀረበው ማዕከላዊ ሪፖርት ይህን ጉዳይ እንደሚከተለው ገልጾታል ፤

ለግብርና ምርታማነት ዕድገት አንዱ ቀድሚያ ሊሰጠው የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ የግብርና ምርምር ሥራን ማጠናከር መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ። ለልዩ ልዩ የሀገራችን ክፍሎች ተስማሚና ውጤታማ የሆኑ ምርጥ ዘሮች በብዛት በምርምር እንዲገኙ ካልተደረገ ፣ በሀገራችን የአካባቢ ልዩ ባሕርይ (ኢኮሎጂ) አኳያ የአዝርትን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያገዙ ሳይንሳዊ የአሠራር ዘዴዎች ካልዳበሩና ለገበሬው በስፋት እንዲዳረሱ ካልተደረገ የግብርና ምርታማነት ፈጣን ዕድገት ተጨባጭ ሊሆን አይችልም ።

ሪፖርቱ በዚህ አኳያ የተወሰደውንና የሚወሰደውን እርምጃ ሲገልጽ የሚከተለውን አስፍሯል ፤

የግብርና ምርምር ማዕከሉችን በሀገራችን ልዩ ልዩ ክፍሎች የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ባሕርይ አንፃር ለማቋቋም የሚቻልበት ዘዴ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲጠና ተደርጓል ። በዚህም ጥናት መሠረት የመጀመሪያዎቹ የግብርና ምርምር ማዕከሎች በጋምቤላ በመተከልና በአሶሳ ሠፈራ አካባቢዎች ፣ እንዲሁም በባሌና በጉጃም አምስት ከፍተኛ የግብርና ምርምር ጣቢያዎች ለማቋቋም የገንባታው ሥራ እየተካሄደ ነው ።

የሰው ኃይልን በሚመለከት በእርሻ ምርምር ላይ የተሰማራው የሠለጠነ የሰው ኃይል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በብስለትም ሆነ በቁጥር ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በቂ ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ባይገኙም ቁጥራቸው በአፋጣኝ እየጨመረ ነው ። ለምሳሌ በ1972 የከፍተኛ ደረጃ ምሩቃን የሆኑ ተመራማሪዎች ቁጥር ወደ 60 የደረሰ ሲሆን በ1975 ከ150 በላይ የሚሆኑ ከፍተኛ ተመራማሪዎች ተሰማርተው እንደነበር ታውቋል ። በ1977 ደግሞ በዚሁ ተግባር ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ቁጥር ወደ 253 ከፍ ብሏል ። የባለሙያዎቹ ቁጥር መጨ


Digitized by Google

መር ለችግሩ መቃለል የሚረዳ መሆኑ ባያ ጠራጥርም ከምርምር ከፍተኛ ውጤት ሊገኝ የሚችለው የባለሙያዎች ልምድና የፈጠራ ችሎታ ሲታከልበት በመሆኑ በዚህ ረገድ ብዙ እንደሚቀር ይገመታል ፡፡

## የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ

የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ውን'ሚና ይጫወታል ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢንዱስትሪ ድርሻ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት 12% የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 8% የፋብሪካዎች ድርሻ፣ ቀሪው 4% ደግሞ የእደ ጥበባትና የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ድርሻ ነው ፡፡

የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በአጠቃላይ ሲታይ ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የተሻለ አደረጃጀት ፣ የሰው ኃይል የሙያ ብቃትና የማምረቻ መሣሪያ ዘመናዊነት ቢኖረውም ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመገንዘብ ይቻላል ፡፡

የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የቴክኖሎጂ ገጽታው ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ የክፍለ ኢኮኖሚውን የካፒታልና የሰው ኃይል ጥምርታ ፣ የመሣሪያ አጠቃቀም ችሎታ እንዲሁም የሰው ኃይል ምርታማነት በአጭሩ ማየት ያስፈልጋል ፡፡

የካፒታልና የሰው ኃይል ጥምርታ (Capital Labur ratio) ፡ በ1976 የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ብር 419 ሚሊዮን የሚገመት የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደነበረው የተገመተ ሲሆን በዚህ ጊዜ በክፍለ ኢኮኖሚው ተሰማርቶ የነበረው የሰው ኃይል 88,866 ነበር ፡፡ ይህም የሚያሳየው ለያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 4,715 የሚገመት ንብረት እንዳለ ነው ፡፡ ከዚህ ውስጥ ለያንዳንዱ ሠራተኛ የሚደርሰው የማምረቻ መሣሪያ ዋጋ ከዚህ ዝቅ ያለ እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የሜካናይዜሽንም ሆነ የአውቶሜሽን ደረጃ ዝቅ ያለ መሆኑን ነው ፡፡

## የኢንዱስትሪ መሣሪያዎች አጠቃቀምና እንክብካቤ

በክፍለ ኢኮኖሚው የሚገኙትን የፋብሪካ መሣሪዎች የአጠቃቀምና የመንከባከብ ችሎታ ከሚያንፀባርቁ ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ 1/ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፣ 2/ የጥገና መመሪያ ፣ 3/ የመፈተሻና የመለኪያ መሣሪያዎች ፣ 4/ የወርክሾፕ ሁኔታዎች ናቸው ፡፡

1. የሠለጠነ የሰው ኃይል ፡ በ1977 በመንግሥትና ከፊል የመንግሥት በሆኑት ፋብሪካዎች ውስጥ ተሠማርተው ከነበሩት 80,334 ቋሚ ሠራተኞች መካከል 1,152 ወይም 1.4% ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ 4,517 ወይም 5.6% መለስተኛ ፕሮፌሽናል ፣ 11,504 ወይም 14.3% ከ9—12 የትምህርት ደረጃ ያላቸው ቀሪው 63,161 ወይም 78.6% ደግሞ ከ8ኛ ክፍል በታች የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው ፡፡ ከፍተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች የተሰማሩበትን የኢንዱስትሪ ዘርፍ የተመለከትን እንደሆነ 4,544 ወይም 80.2% እንደምግብና ጨርቃ ጨርቅ በመሳሰሉት የፍጆታ ዕቃ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ሲሆን ቀሪው 1,125 ወይም 19.8% የልማት ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን በሚያመርቱ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ናቸው ፡፡ ይህም የሚያሳየው በክፍለ ኢኮኖሚው ከተሰማራው የሠለጠነ የሰው ኃይል መካከል በጣም ጥቂቱ ብቻ የከባድ ኢንዱስትሪ አሠራር ልምድ እንዳለው ነው ፡፡

2. የጥገና መመሪያ (maintenance manual)፡ የመሣሪያዎችን ልዩ ልዩ ክፍሎች በቅደም ተከተል ለመፈታታትና መልሶም በትክክል ለመገጣጠም ፣ እንዲሁም የመለዋወጫ መሣሪያዎችን ለይቶ ለማወቅ የጥገና መመሪያ መኖር በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡

ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት በአገራችን ተቋ



Digitized by Google

ቁመው የነበሩት አብዛኞቹ ፋብሪካዎች የጥገና መመሪያና የመሣሪያዎችን የጥገና ታሪክ የሚያሳይ መዝገብ አልነበራቸውም ። በመሆኑም ፋብሪካዎቹ በሕዝብ ይዞታና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በዋሉበት ወቅት ይህንን ደካማ የነበረውን የመሣሪያዎች አያያዝም አብሮ መረከብ ግዴታ ሆኗል ።

በ1972 በብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው ለጥናቱ በናሙናነት ከተመረጡት ሃያ ዘጠኝ ፋብሪካዎች መካከል አብዛኞቹ የጥገና መመሪያ ፈጽሞ የሌላቸው ወይም ያልተሟላ መመሪያ ያላቸው መሆኑ ታውቋል ። ከጥገና መመሪያ አለመኖር ሌላ መሣሪያዎቹ ሲተከሉ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች በየት በየት እንደተዘረጉ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ (wiring diagram) ባለመኖሩ የጥገና ችግር የሚያጋጥማቸው ፋብሪካዎች እንዳሉም ተገልጸአል ።

በሌላ በኩል የጥገና መመሪያ ያላቸው ፋብሪካዎች ቢሆኑም ፣ የነዚህ መመሪያዎች አቀማመጥና ሥርጭት ለአብዛኛዎቹ ቴክኒሺያኖች አመቺ ባለመሆኑ መመሪያዎቹን በሥራ ላይ ለማዋል እንዳልተቻለ ታውቋል ። አንዳንዶቹ መመሪያዎች ቴክኒሺያኖቹ በማይደርሱበት የመዛግብት ማከማቻ ሲቀመጡ አንዳንዶቹ ደግሞ ግለኝነት የሚያጠቃቸው ግለሰቦች በምሥጢር የሚጠቀሙባቸው ሰነዶች ሆነዋል ።

3· <u>የእጅ መሣሪያዎችና ልዩ ልዩ መለኪያ መሣሪያዎች ፣</u>

የጥገናን ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የእጅ መሣሪያዎችና ልዩ ልዩ የመለኪያና የመፈተሻ መሣሪያዎች ተሟልተው መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው ። ውስብስብ የሆነ የማምረቻ መሣሪያዎች ብልሽት ሲያጋጥማቸው የብልሽቱን ቦታ ለይቶ ለማወቅ የመፈተሻ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ ፤ ብልሽቱ ያለበት ቦታ ከታወቀም በኋላ መሣሪያዎቹን ፈታትቶ ብልሽቱን ለማስወገድ የእጅ መሣሪያዎች አስፈላጊ ናቸው ።

በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ በሚገኙት ፋብሪካዎች ባጠቃላይ የተጠቀሱት ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች እጥረት መኖሩ የታወቀ ሲሆን መሣሪያዎቹ በሚገኙባቸው ፋብሪካዎች ደግሞ በአያያዝ ጉድለት ምክንያት ባሉት መሣሪያዎች እንኳን ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት አልተቻለም ።

4. <u>የጥገና ወርክሾፖች፣</u> ይህ ድርጅት አንዳንድ መሣሪያዎች ለመጠገንና ለመሥራት የሚያስፈልጉ በዋተር ኃይል የሚሠሩ ልዩ ልዩ የድጋፍ መሣሪያዎች ያሉበት ክፍል ነው ። በወርክሾፕ ውስጥ ቴክኒሺያኖች የአንዳንድ የመሣሪያ አካሎችን ለማሻሻልና አዳዲሶችን ለመሥራት ይችላሉ ።

በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በአብዛኞቹ ፋብሪካዎች ድጋፍ ሰጪ ወርክሾፖች አሉ ። የወርክሾፖች አያያዝና አደረጃጀት ግን በጣም የተለያየ ነው ። የወርክሾፖች አጠቃቀምም ቢሆን በሠራተኞች የዕውቀትና የልምድ ደረጃ እንዲሁም የፈጠራ ችሎታ ላይ ያልተመሠረተ ነው ። ለምሳሌ አንዳንድ ፋብሪካዎች ውስጥ ብዙዎቹን የመለዋወጫ ዕቃዎች ለመሥራት የሚያስችል የወርክሾፕ መሣሪያና የሠለጠነ የሰው ኃይል ሲኖር በሌሎች ፋብሪካዎች ውስጥ ደግሞ በጣም ውሱን የሆኑ የመሣሪያ አካላትን ብቻ ለመሥራት የሚያስችል ዐቅም መኖሩ ታውቋል ። አጠቃቀሙንም በሚመለከት ያንዳንድ ፋብሪካ ወርክሾፖች በቂ መሣሪያና የሠለጠነ የሰው ኃይልም እያለ በፈጠራ ችሎታ ማነስ የተነሣ ወይም አስተዳደሩ አመቺ ሁኔታዎችን ባለመፍጠሩ ወርክሾፖች በሙሉ ዐቅማቸው የማይሠሩበት ሁኔታ



Digitized by Google

ይታያል ። አንዳንዶቹ ደግሞ ለሌሎች አር አያ ሊሆን በሚችል የፈጠራ ችሎታ በመ ጠቀም ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው የሚ ችሉ ሥራዎች ሠርተዋል ።

## የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የሰው ኃይል ምርታማነት

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕቅም የደረሰበ ትን ደረጃና በየዓመቱ በሚያሳየው ዕድገት ለመጠቀም የሰው ኃይል የምርታማነት ደረጃና ዓመታዊ ዕድገቱ ጠቃሚ መረጃ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል ።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮ ኖሚ የሚገኘውን የሠራተኛ ምርታማነት ሁኔታ ለመገመት የተሟላ መረጃ የሚገ ኝባቸውን በሙሉና በከፊል መንግሥታዊ የሆኑት ፋብሪካዎች በናሙናነት ተወስ ደዋል ።

## ሙሉና ከፊል መንግሥታዊ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሰው ኃይል ምርታማነት

| | | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 | 1977 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርት ውጤት*/በሚሊዮን ብር/ | 790 | 1,067 | 1,213 | 1,302 | 1,368 | 1,484 | 1,472 | 1,847 |
| 2 | የተሠማራው የሰው ኃይል ብዛት | 63,288 | 63,990 | 64,771 | 69,244 | 73,874 | 75,741 | 78,928 | 80,334 |
| 3 | የነፍስ ወከፍ የምርት ውጤት 1÷2 /በብር/ | 12,483 | 16,674 | 18,728 | 18,803 | 18,518 | 19,593 | 18,650 | 22,992 |
| | የምርታማነት ደረጃ /1970—100/ | 100 | 134 | 150 | 151 | 148 | 157 | 149 | 184 |

ምንጭ፦ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስታትስቲክስ ቡለቲን

ከሠንጠረዡ እንደሚታየው በ1971 እና በ1972 የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የሰው ኃይል ምርታማነት ከፍተኛ ዓመታዊ ዕድ ገት አሳይቷል ። ለዚህም ዋናው ምክንያት በ1971 በተጀመረው የምርት ዕድገት ዘመቻ አማካይነት ቀደም ሲል በከፊል ይንቀሳቀሱ የነበሩትን የማምረቻ መሣሪ ያዎች በሙሉ ዐቅማቸው እንዲሠሩ ለማ ድረግ የተደረገው ከፍተኛ ጥረት ነው ። በ1973 እና በ1974 ግን ከምርቱ እንቅስ ቃሴ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ የሰው ኃይል በመቀጠሩ የ1973 ምርታማነት 1% ብቻ ዓመታዊ ዕድገት ሲያሳይ የ1974 ደግሞ 3% ዓመታዊ ቅናሽ አሳይቷል ። በሠንጠረዡ ላይ ከታዩት ስምንት ዓመ ታት ከፍተኛ የምርታማነት ዕድገት የተ መዘገበው በ1977 ሲሆን ለዚህም ዓይነተኛ ምክንያት እንደሙገር ስሚንቶ ፋብሪካ ያሉ አዳዲስ ፋብሪካዎች መከፈት ነው ።

የግልና የኅብረት አነስተኛ ኢንዱስትሪ ዎችና እደጥበባትን በሚመለከት ምርታማ ነትን ለመገመት የሚያስችል በቂ መረጃ ባይኖርም በ1974 የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ዎችና እደጥበባት ማስፋፊያ ድርጅት ከስ

* ከ1970—76 የታየው የምርት ውጤት በ1971 ፣ የ1977 የምርት ውጤት በ1973 ዋጋ የተሰላ ነው ።



Digitized by Google

ታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽህፈትቤት ጋር በመተባበር በአሥራ ሁለት ክፍላተ ሀገር ካደረገው ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት ጥናቱ ባቀፋቸው 822 አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በ1974 የተሰማሩ 12,113 ሠራተኞች የነፍስ ወከፍ ግምታዊ የምርት ውጤት ብር 13,822 እንደነበር ታውቋል፡፡በሌላ በኩል እደ ጥበባት የሚገለገሉባቸው ቴክኖሎጂዎች በጣም ኋላቀር በመሆናቸው ምርታማነታቸውም ከአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በጣም ዝቅ ያለ እንደሚሆን ይገመታል ፡፡

## የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ቴክኖሎጂ

በቁሳዊ ምርት አምራች ዘርፍ ማለትም በግብርናና በኢንዱስትሪ ሰፍኖ የሚገኘው የቴክኖሎጂ ኋላቀርነት በአገልግሎት ዘርፍም በትራንስፖርት ፣ በመገናኛ እንዲሁም በጤና መስኮች ጭምር እንደሚንፀባረቅ ግልጽ ነው ፡፡

በትራንስፖርትና መገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚ በኩል ዘመናዊና ያልተሻሻለ ባሕላዊ ቴክኖሎጂ ጐን ለጐን ይታያሉ ፡፡ ዘመናዊው ከውጭ የመጣው የተሽከርካሪ፣ የባቡር ፣ የመርከብና የአየር ትራንስፖርት ቴክኖሎጂን የሚያጠቃልል ሲሆን ባህላዊው ደግሞ በጋማ ከብትና በሰው ጉልበት የሚጠቀመው የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ነው ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በትራንስፖርትና መገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚ የውጭ ቴክኖሎጂ መርጦ በማስገባት ፣ የተገዙትን መሣሪያዎች በሥራ ላይ በማዋልና ሲበላሹ በመጠገን ከአፍሪካ አገሮች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ዕቅም እንደገነባን ይታወቃል ፡፡ ከዚህ ሌላ ተሽከርካሪዎችን የመገጣጠም ችሎታ ከመኖሩም ሌላ አነስተኛ አውሮፕላኖችንና ጀልባዎችን በሀገር ውስጥ ለመገጣጠም ዝግጅት እየተደረገ ነው ፡፡

በዘመናዊው የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ረገድ ራስን ለመቻል የረዥም ጊዜ ዓላማችን ቢሆንም ለጊዜው ባህላዊውን የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ በማሻሻል የገጠሩን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል ይቻላል፤ ለምሳሌ ከሰው ጉልበትና ከጋማ ከብት የሚገኘውን የማጓጓዝ ዕቅም ምን ያህል ማሻሻል እንደሚቻል ከሚቀጥለው ማነፃፀሪያ ማየት ይቻላል ፡፡

- የሰው ጉልበት፥— አንድ ጠንካራ ሰው 50 ኪሎ ግራም ጭነት ተሸክሞ በቀን እስከ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት መጓዝ ይችላል የሚል ግምት አለ
- የጋማ ከብት፥— አንድ መካከለኛ ጉልበት ያለው ፈረስ 100 ኪሎግራም ጭነት ተጭኖ በቀን 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ይጓዛል ፡፡
- በሰው ጉልበት የሚገፋ ጋሪ፥— አንድ ሰው በጋሪ ላይ 150 ኪሎ ግራም ጭነት አስቀምጦ በቀን እስከ 30 ኪሎ ሜትር መጓዝ ይችላል ፡፡
- በጋማ ከብት የሚጐተት ጋሪ፥— በዚህ ዓይነት የማጓጓዝ ዘዴ አንድ ፈረስ 500 ኪሎ ግራም ጭነት የያዘ ጋሪ እየጐተተ በቀን 30 ኪሎ ሜትር መጓዝ ይችላል ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የሚጓጓዣ ዓይነቶች በማነፃፀር ለመረዳት እንደሚቻለው በሰው ጉልበት እንዳለ በመጠቀም ፋንታ ጋሪ ቢታከልበት የሰውን የማጓጓዝ ዕቅም በሦስት እጥፍ ማሻሻል ይቻላል ፡፡ የፈረስ ጉልበት በጥሬው ከመጠቀም ጋሪ ቢታከልበት በሦስት እጥፍ ይሻሻላል ፡፡ ባለጋሪ ፈረስ ከሰው ጉልበት በአሥር እጥፍ እንደሚሻል ያስረዳል ፡፡

* የሰው ጉልበት እንደሰው ጥንካሬ ይለያል ፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ጠንካራ ሰው ዕቅም ሲባል በሸክም ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች አማካይ የመሸከም ዕቅም ሊወሰድ ይችላል ፡፡ ለምሳሌ እህል ከመኪና እያወረዱ 20 ሜትር ያህል በመጓዝ መጋዘን ውስጥ የሚደረድሩ ሠራተኞች በስምንት ሰዓት ውስጥ የሚያጓጉዙትን የጭነት መጠን መለካት ይችላል ፡፡



Digitized by Google

የጤና አገልግሎትን ሁኔታ በሚመለከት የኢትዮጵያ አምራች ሕዝብ በምግብ እጥረትና አለመመጣጠን እንዲሁም በመሠረታዊ ንጽሕና ጉድለት የተነሣ ገና መወጣት ያለበት የጤና ችግር ሰፊ ነው። ምንም እንኳ ጥቂት የከተማ ነዋሪዎች በዘመናዊ የሕክምና ቴክኖሎጂ ተገልጋይ ቢሆኑም አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ በተሻሻሉ የጤና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ለመሆን አልበቃም።

ቀደም ባሉት ዓመታት ጤና ነክ የሆኑ በርከት ያሉ ምርምሮች የተካሄዱ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በውጭ አገር ዜጎች የተከናወኑ በመሆኑና ተመራማሪዎቹም ወደአገራቸው ከመመለሳቸው በፊት ተተኪ ኢትዮጵያውያንን ስለማያዘጋጁ የምርምሩ ውጤትም በሥራ ላይ ሳይውል የቀረበት ጊዜ ብዙ እንደሆነ ይገመታል።

ከላይ በየዘርፉ ለማሳየት የተሞከረው የሀገሪቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም የሚገኝበትን ደረጃ ሲሆን፣ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከቴክኖሎጂኋላቀርነት ለመላቀቅና በውጭ ቴክኖሎጂ ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በሚመለከቱ በመጠኑ ለመጠቆም እንሞክራለን።

## የሀገሪቱን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ከፍ ለማድረግ

ለአንድ አገር ልማት መፋጠን የተፈጥሮ ሀብትና የሠራተኛ ሕዝብ መኖር አስፈላጊ ናቸው። እነኚህን አቀናጅቶ ከፍተኛ ምርት ለማግኘት ደግሞ የሠራተኛውን ጉልበት የሚያግዙ መሣሪያዎች እንዲሁም ዕውቀትና ዘዴ ያስፈልጋሉ። መሣሪያዎችን የማበጀት፣ ዕውቀትና ዘዴ የማፍለቅ ችሎታ ደግሞ የአንድ አገር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም መለኪያ ነው። ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም የተለያዩ ደረጃና ክፍሎች አሉት። እነሱም

1-ከውጭ አገር በተገዙ መሣሪያዎችና ዘዴዎች በሚገባ የመጠቀም ችሎታ፤

2- ከውጭ አገር ቴክኖሎጂ ለማስገባት ተስማሚውን መርጦና ተደራድሮ የመግዛት ዐቅም፤

3-ቀደም ሲል በተገኙ የሳይንስ ዕውቀቶችና ዘዴዎች በመጠቀም መሣሪያዎችን በሀገር ውስጥ የመሥራት ችሎታ፤

4-አዳዲስ ዕውቀቶችንና ዘዴዎችን ለማፍለቅ የምርምርና ሥርፀት ተግባር የማከናወን ችሎታ ናቸው።

1. ከውጭ አገር በተገዙ መሣሪያዎችና ዘዴዎች በሚገባ ስለመጠቀም፡— በየክፍለ ኢኮኖሚው በየዓመቱ ለልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ ለመለዋወጫና ለጥሬ ዕቃ መግዣ በሀገሪቷ ዐቅም አንፃር ሲታይ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ይወጣል። ከዚህ ውስጥ ሳይንሳዊ የአሠራር ዘዴዎች ባለመጠቀም የተነሣ መጠኑ ቀላል ያልሆነ ገንዘብ እንደሚባክንም አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ከቴክኖሎጂ ጥገኝነት ለመላቀቅና ዕድገትን ለማፋጠን ባለው ገንዘብ በተገቢው መንገድ መጠቀም አስፈላጊ ነው።

እያንዳንዱ የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለመሣሪያዎች፣ ለጥሬ ዕቃዎችና ለመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ ከሚያደርገው ወጪ ውስጥ የተወሰነውን ድርሻ ለሠራተኛ ሥልጠናና ለሥራ አደረጃጀት ማሻሻያ ማዋል ይኖርበታል ሠራተኞችን በማሠልጠንና የሥራ አደረጃጀቱን በማሻሻል የሚገኘውን ጥቅም ለመለካት እንዲቻል ደግሞ በሥልጠናውና በማሻሻያው እርምጃ ምክንያት በጥሬ ዕቃና በመለዋወጫ ዕቃ አጠቃቀም ረገድ የተደረገውን ቁጠባ ወይም በአሠራር ላይ የተገኘውን ቅልጥፍና የመገምገምና የመለካት ባህልም አብሮ መዳበር አለበት።



Digitized by Google

**2. የቴክኖሎጂ ምርጫ ችሎታን በሚመለከት፣**—እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች የሀገራቸውን ኢኮኖሚና ማኀበራዊ እንቅስቃሴ ለማሻሻል ከቴክኖሎጂያዊ ጥገኝነት ለመላቀቅ በሚያደርጉት የትግል ሂደት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በአብዛኛው በውጭ ቴክኖሎጂ ላይ መጠቀማቸው አይቀርም ። የልማት መሣሪያዎች ከውጭ አገር መግዛት፣ የቴክኒክ ዕርዳታ መቀበል እንዲሁም ለአገራችን ተስማሚ የሆነ ቴክኖሎጂ ካላቸው አገሮች በተለይም ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የጋራ ልማት ድርጅቶች ያቋቁማሉ። በመሆኑም የቴክኖሎጂ ምርጫ ችሎታን ማዳበር ከውጭ ጥገኝነት ለመላቀቅ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው ።

በአገር ውስጥ የሌለ ቴክኖሎጂ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በየሀገሩ ያለውን መቃኘት፣ ተስማሚውን መምረጥና የመረጡትንም ከሻጭ ጋር በአቻነት ተደራድሮ ለመግዛት መቻል ያስፈልጋል።እንደሚታወቀው ቴክኖሎጂያቸውን ለሽያጭ የሚቀርቡ የካፒታሊስት ኩባንያዎች ደግሞ በሚያውቁት የማግባባት ዘዴ ሁሉ ተጠቅመው ሽቀጣቸውን ለመሸጥ እንጂ ለገዥው ጥቅም የማሰብ ተልዕኮ እንደሌላቸው ግልጽ ነው ።

አንድ ቴክኖሎጂ ለመምረጥ ደግሞ አያሌ ነጥቦች መታየት ይኖርባቸዋል ። የሚገዛው መሣሪያ ጥንካሬ፣ ጥራትና ዋጋው፣ ጥራቱም መልካምና ዋጋውም ለጊዜው እርካሽ ቢሆን እንኳን እያደር ሊያስከትል የሚችለው ተጽዕኖ፣የመለዋወጫ ዕቃ የመኖር አለመኖር፣የአሠራርና ለጥገና አመቺነት፣ መሣሪያውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገው የኢነርጂ ዓይነትና መጠን እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት መታየት ካለባቸው ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

ትክክለኛ የቴክኖሎጂ ምርጫ ለማከናወን በሚፈለገው የቴክኖሎጂ ዓይነት ብቃት ያላቸውና የገበያውን ሁኔታ የሚያውቁና የመደራደር ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ ። ዛሬ ብዙ ታዳጊ አገሮች ቅን ፍላጐት እያላቸው ገበያ ላይ ያለውን የቴክኖሎጂ ዓይነት መርጦ የመግዛት ችሎታቸው ስላልዳበረ የሻጭ ኩባንያዎችን ምክር በመቀበል ተስማሚ ያልሆነ ቴክኖሎጂ ወደ አገራቸው ሲያስገቡ ይታያሉ ። የተመረጠውን ቴክኖሎጂ በሥራ ላይ ሊያውለው የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ወይም ደግሞ መሳሪያው ቢበላሽ ሊጠግነው የሚችል ባለሙያ ባለመኖሩ ወይም ጥሬ ዕቃ በአገር ውስጥ ባለመገኘቱ የነዚህ ታዳጊ አገሮች በቴክኖሎጂ አቅራቢው አገር ላይ የሚኖራቸው ጥገኝነት እየባሰ ይሄዳል ።

ይህንን ችግር ለማስወገድ አንድ ቴክኖሎጂ ወደ አገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በቴክኖሎጂ አቅራቢው አገር ላይ ወደፊት የሚኖረው ጥገኝነት በጣም አነስተኛ የሚሆንበት፣ ቢቻል ፈጽሞ የማይኖርበት መንገድ አብሮ መጠናት ይኖርበታል ። የውጭ ቴክኖሎጂ የብሔራዊ ጥረት መደጉሚያ እንጅ የጥገኝነት ማስፋፊያ መሣሪያ መሆን የለበትም ።

**3. ቀደም ሲል በተገኙ የሳይንስ ዕውቀቶችና ዘዴዎች በመጠቀም መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ መገልገያዎችን በሀገር ውስጥ የመሥራት ችሎታን በሚመለከት፣**—እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ታዳጊ አገሮች የማምረቻ መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ መገልገያዎችን በሀገራቸው ውስጥ፣ ቢቻል ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ሀብት በመጠቀም ማምረት ቢችሉ ለአገራቸው ቴክኖሎጂያዊ ዐቅም አንድ ከፍተኛ እመርታ ያስገኝላቸዋል ።

በአገራችን ለምሳሌ በቅርቡ የተቋቋመው የትራክተር ፋብሪካና ቀደም ሲል የተቋቋሙት የእጅ መሣሪያዎች ፋብሪካ እያመረቱ የሚያወጧቸው መሣሪያዎች ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና ለእደ ጥበባት ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሰጡ አይጠረጠርም ።


Digitized by Google

ሌላው ሊጠቀስ የሚገባ የኢንዱስትሪ ውጤት ለማንኛውም ግንባታ ተፈላጊ የሆነው የሲሚንቶ ምርት ነው ። በዚህ ረገድ አገራችን በአሁኑ ጊዜ በሲሚንቶ ምርት ራሷን መቻሏ የሚያበረታታ ነው ።

በቅርብ ከሚቋቋሙት የማምረቻ መሣሪያና ልዩ ልዩ መገልገያ መሣሪያዎች ፋብሪካዎች መካከል ደግሞ የመለዋወጫ ዕቃዎች ፣ የኤሌክትሪክ ሞተርና ትራንስፎርመር፣ እንዲሁም የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች ፋብሪካዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው ።

በተለይ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ሞተሮች ማምረት ከተጀመረና በአነስተኛ ዋጋ ማዳረስ ከተቻለ ከዚህ ጋር የተያያዙ አያሌ የሥራ መገልገያዎች (መብሻዎች ፣ መቁረጫዎች ፣ ፖንፖች ፣ ወዘተ) በአነስተኛ ወርክሾፖችና በእደ ጥበባት ሊመረቱ ስለሚችሉ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ከፍተኛ የምርት እንቅስቃሴ ይፈጥራሉ ።

በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለማስፋፋት ከፍተኛ የሙአለንዋይ ወጪና የሠለጠነ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው ። ውሱን የሆነውን ብሔራዊ የገንዘብና የሠለጠነ የሰው ኃይል ዐቅም ለተወሰነ ጊዜ ለመደጎም ዐቅሙ ካላቸው አገሮች ጋር የጋራ የልማት ማኅበር (Joint venture) ማቋቋም አንዱ አማራጭ ስልት ነው ። እርግጥ በጋራ ልማት ማኅበር ሁሉንም ዓይነት የልማት ሥራዎች ማካሄድ አይቻልም ። በተለይ የውጭ አገር ባለንብረቶችን የሚስቡ የጋራ ልማት ማኅበሮች በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ብቻ በመሆናቸው የሀገር ውስጥን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎች ባብዛኛው በአገር ውስጥ ሀብት መገንባት ይኖርባቸዋል ።

4· **የምርምርና የሥርፀት ችሎታን በሚመለከት**፣— ጥንታዊ ኅብረተሰብ ስለ ተፈጥሮ ሕግጋትና ስለአካባቢው ሁኔታ ግንዛቤ ያገኘው ለኑሮው ባደረገው የረዥም ጊዜ ግብታዊና አዝጋሚ የትግል ሂደት ነበር ። በዚህም ምክንያት አንዱ ትውልድ ሲያልፍ ለሚከተለው የሚተላለፍ ዕውቀት እምብዛም ስላልነበረ ሁሉም በአካባቢውና በወቅቱ ብቻ የተወሰነ ቁንጽል ግንዛቤ ከማግኘት አላለፈም ። ያሠራር ዘዴውም ውሱን በሆነው ዕውቀቱ ላይ የተመሠረተ ስለነበር ተፈጥሮ የለገሰችውን እንዳለ ከመጠቀም አልፎ አካባቢውን ለመለወጥና ለማሻሻል ዐቅም አልነበረውም ።

ዛሬ የዓለም ኅብረተሰብ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ግን አዳዲስ ዕውቀቶችና ያሠራር ዘዴዎች በአጭር ጊዜ ለማፍለቅ፣ እንዲሁም አዳዲስ የምርት መገልገያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ለመሥራት የተደራጀ የምርምርና የሥርፀት ተግባር አስፈላጊነት ግልጽ ሆኗል።

በፍሬያማ ምርምር ላይ የዋለ ሙአለንዋይ በአገር ውስጥ ምርት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያስከትላል ። በተለይ ኢኮኖሚው በተመሠረተበት ዋና ዋና ሴክተሮች ላይ ለሚከናወን ምርምር የሚደረግ ወጪ የዚህን ወጪ እስከ 400% ያህል ጥቅም እንደሚያስገኝ የአንዳንድ አገሮች ልምድ ያሳያል ። በሳይንስና ቴክኖሎጂ የገፉ ሀገሮች የወደፊት ሕልውናቸውና ዕድገታቸው የሚረጋገጠው በሚያፈልቁት አዳዲስ ዕውቀትና ዘዴ መሆኑን በመገንዘብ በየጊዜው ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ከፍተኛ የሆነ የሙአለንዋይ ወጪ ያደርጋሉ። ለምሳሌ አንዳንድ ሀገሮች በየዓመቱ ለምርምርና ለሥርፀት ተግባር የሚያደርጉት ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርታቸው ጋር ሲነጻጸር የሚከተለውን ይመስላል ። ሕንድ 0·23%፣ ሐንጋሪ 4%፣ ምዕራብ ጀርመን 1.2% ፣ ጃፓን 0.74%፤ ሶቭዬት ኅብረት 3·2% ። በሀገራችን የምርምርና የሥርፀት



Digitized by Google

ተግባር እስካሁን ባጠቃላይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ጉላ ብሎ የሚታየውን የእርሻ ምርምር እንቅስቃሴ እንኳን ብንወስድ ለዚሁ ተግባር በ1977 የተመደበው የሙአለ ንዋይ ወጪ ብር 13.3 ሚሊዮን ፥ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነጻጸርም 0.17% ብቻ ነው ። ከተያዙት አንዳንድ ጥረቶች ይህ ሁኔታ እየተለወጠ እንደሚሄድ ይታመናል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ የሚጠቀምበትን ባህላዊ ቴክኖሎጂ በምርምር ማሻሻል ይቻላል ። ገበሬው በሚጠቀምበት የእርሻ መሣሪያ ፥ ያስተራረስ ዘዴ ፣ ዘር ፥ የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና እደ ጥበባት የሚጠቀሙበት መሣሪያ ፥ የሥራ አደረጃጀት ፤ ሕዝቡ ባጠቃላይ የሚጠቀምበት የማጓጓዣ መሣሪያ ፥ የጤና አጠባበቅ ዘዴ ላይ መጠነኛ የምርምር ጥረት በማድረግ ጉልህ ውጤት ለማግኘት እንደሚቻል ግልጽ ነው ።

በዚህ ረገድ የሀገሪቱን የምርምርና የሥርፀት አቅም ከፍ ለማድረግ ካለን ፍላጐት አኳያ የሚከተሉት እርምጃዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው እሙን ነው ።

ሀ/ በየዘርፉ ያሉትን የምርምር ተቋሞች በመሣሪያና በሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ማድረግ ፤

ለ/ የምርምር ተቋሞች በሌሉባቸው ዘርፎች እንደአስፈላጊነቱ የቴክኖሎጂ ማሻሻያ የጥናት ቡድኖች ማቋቋም ፤

ሐ/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎች ማዕከል ማቋቋምና መረጃዎችን ለተጠቃሚው በሚያመች መንገድ ማድራጀት ፥

## ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የሀገሪቱ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ የተመሠረተው ባብዛኛው በኋላቀር ባሕላዊ ቴክኖሎጂና ከውጭ አገር በገቡ ጥቂት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ላይ ነው ። ስለዚህ በሀገሪቱ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሰፊ ሚና የሚጫወተውን ባሕላዊ (ልማዳዊ) ቴክኖሎጂ ለማሻሻልና አስፈላጊ የሆኑትን ተስማሚ የውጭ ቴክኖሎጂዎች ለመምረጥ የሚያስችል ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም መገንባት ጠቃሚ ነው ። ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂን ዐቅም ለመገንባት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችና የተነደፈውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች በአሥር ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝርዝር ውስጥ ተመልክተዋል ።
ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፥

1. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ምንጭ የሆኑትን ባለሙያ ሠራተኞችን ፥ መሐንዲሶችንና ሳይንቲስቶችን ማሠልጠን ፥ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችን ከማስፋፋት ባሻገር ልዩ ልዩ ኢንስቲትዩቶችን ማቋቋምና በሥራ ላይ የሥልጠና ፕሮግራም ማካሄድ ያስፈልጋል።
2. በየክፍለ ኢኮኖሚው ተፈላጊና ተስማሚ ቴክኖሎጂ የሚያመነጩ የምርምርና ሥርፀት ተግባሮች የሚያከናውኑ ድርጅቶች ማቋቋም ፥ (የምርምሩ ዓላማ በምርት ሂደትና በአሠራር ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ የሚያስገኝ መሆን አለበት)።
3. በየክፍለ ኢኮኖሚው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሰብሰቢያና ማሰራጫ ማዕከላት ማቋቋም ፤
4. ለየክፍለ ኢኮኖሚው የኮንሰልታንሲ (የአማካሪ) ፥ የኢንጅነሪንግና የዲዛይን ክፍሎች ማቋቋም ፤
5. ከውጭ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን ከአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብትና እንዲሁም


Digitized by Google

ከሀገሪቱ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት አንፃር ተስማሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ለመምረጥና ለመደራደር እንዲሁም ለመቆጣጠር የሚችል ማዕከል ማቋቋም ፤

6· እንደአስፈላጊነቱ በየክፍለ ኢኮኖሚው ተስማሚ ወርክሾፖች ፣ ላቦራቶሮች ፣ የጥገና ማዕከሎች ማቋቋም፣

7· የሀገሪቱን ባሕላዊ ቴክኖሎጂዎች ለመገምገም ፣ ለመምረጥና ለማሻሻል የሚችሉ ድርጅቶች ማቋቋም ፣

8· የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግንዛቤ ፣ አመለካከትና ተግባራዊ ችሎታ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ እንዲሠራጭና እንዲሰርጽ የሚያደርጉ ተቋሞች ማቋቋም።

ከላይ ከተዘረዘሩት ሥልቶች መካከል ረዥም ጊዜና ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቀው የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጣሪ የሆኑትን የሠለጠኑ ሠራተኞች ፣ መሐንዲሶችና ሳይንቲስቶች ማፍራት ነው ። የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማናቸውም ተቋም ግንባታ አስፈላጊ ነው ። የምርምር ፣ የኢንጂነሪንግና የዲዛይን እንዲሁም ሌሎችን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋሞች ለማቋቋም አስፈላጊው የሰለጠነ የሰው ኃይል በቅድሚያ መዘጋጀት አለበት ።

የሠለጠነ የሰው ኃይል መኖር ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ግንባታ መነሻ ቢሆንም ይህንን የሠለጠነ የሰው ኃይል አስተባብሮ የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጣሪ ለማድረግ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን ለማስተዳደር ኃላፊነት የተጣለባቸው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ። በየድርጅቱ ያለውን የሥራ ሁኔታ ለፈጠራ ሥራ አመቺ እንዲሆን በማድረግ ፣ በፈጠራ ሥራ ከፍተኛ ውጤት ላስገኙ ሠራተኞች የማነቃቂያ ሽልማት በማዘጋጀት እንዲሁም በብሔራዊ ደረጃ ክብር ሊሰጠው የሚገባ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሥራ ያከናወኑ ሠራተኞች ለመንግሥት እየቀረቡ ታዋቂነት እንዲያገኙ ሐሳብ በማቅረብ የየድርጅቱ ኃላፊዎች ከሠለጠነ የሰው ኃይል የሚጠበቀውን ውጤት ከፍ ማድረግ ይችላሉ ።

ባጠቃላይ ለፈጠራ ሥራ በተለይም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ግንባታ መንግሥት የሚቀይሳቸው ስልቶችና በየጊዜው የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች የሚፈለገውን ውጤት ለማስገኘት የሚችሉት ስልቶችንና ፖሊሲዎችን በየደረጃው ተግባራዊ የሚያደርጉት አካላት ከወቅቱና ከሁኔታውች ጋር የተገናዘበ እርምጃ ሲወስዱ ብቻ መሆኑ ግልፅ ነው ። ለምሳሌ የሀገር ውስጥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተፈላጊነት እንዲጨምር ለማድረግ መንግሥት ከውጭ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ለማድረግ ፖሊሲ ያወጣል። በሌላ በኩል ግን በመንግሥታዊ ፣ ሕዝባዊና የግል ድርጅቶች ውስጥ በሀገር ውስጥ በተሠሩ ዕቃዎች በመጠቀም ፋንታ በአንዳንድ ሕገወጥ ነጋዴዎች አማካይነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ገበያ ስላገኟቸው ብቻ እነኝህን ለመግዛትና በሥራ ላይ ለማዋል ከተሯሯጡ የመንግሥቱን ፖሊሲ ፍሬያማነት ዝቅ ያደርገዋል ።

ስለዚህ የሀገሪቱን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዐቅም ለመገንባት ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ ብሔራዊ ፖሊሲ መኖር ፣ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች መሟላት ፣ እንዲሁም የተደራጁ መንግሥታዊና ሕዝባዊዎች አካላትና ሰፊው ሕዝብ በቡድንም ሆነ በነፍስ ወከፍ የሚወስዷቸው እርምጃዎችና የሚያፈልቋቸው ዘዴዎች ወሳኝነት ይኖራቸዋል ።



Digitized by Google

# የግርጌ ማስታወሻ

1. Ivan Dmitriyev, "The System of Neo-colonialist Exploitation", *Social Sciences*, Vol. XVII, No. 1, 1986, p. 162.
2. *Ibid*, p. 165.
3. I. Frolov, edt., *Dictionary of Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1984), p. 372.
4. See Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 367. See also A.P. Sheptulin *Marxist-Leninist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1980), pp. 452-453.
5. See Great Soviet Encyclopedia, Vol. 25, p. 446.
6. *Ibid*.
7. See UNCTAD V. Technology Planning in Developing Countries (To/238/1979, p. 3.
8. Claude Sumner, *Ethiopian Philos* V•l. 1 (Addis Ababa: Cntral Prin Press, 1974), p. 33.
9. Walter Rodney, How Europe Un Developed Africa, (Dar es Salaa Tanzania Publishing House,, 1972).
10. Richord Pankhurst *Economic Histor of Ethiopia*, Addis Ababa: Haile Sela sie I University Press, 1968), pp. 261 272.
11. Sidney Painter, *A History of the Middl Ages 284-1500*, Macmillan, Londor Melbourne, 1966, pp. 18 32.
12. Richard Pankhurst *History of Ethiopi* (Teaching Notes), (Addis Ababa Ministry of Educotion, 1970), p. 73

Digitized by Google

# ስለመንደር አንዳ ንድ መሠረታዊ ባሕርያትና የኢትዮጵያ ሁኔታ

በላይነህ አሰጉ

አብዮታችን በደረሰበት ምዕራፍ ዋንኛ
ትኩረቱ አዲሱን ሕዝባዊ ሥርዓት መገን
ባቱ ላይ ነው ። ከዚሁ አኳያ እርምጃዎች
እየተወሰዱም ነው ። በተለይ የአገሪቱ ዕድ
ገት መነሻ የሆነው የግብርና ኢኮኖሚ ባለ
ፈው ሥርዓት በነበረው የመሬት ሥሪት ፣
በኋላቀርነቱና የተበታተነ በመሆኑ የተፈለ
ገውን ያህል ለዕድገታችን አስተዋጽኦ ማድ
ረግ ቀርቶ የዕለት ምግብም ማቅረብ ባለመ
ቻሉ በዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ጠንከር ያለ እር
ምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖአል ። በመንግ
ሥት ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራትና በግል
አራሽ ገበሬዎች የተደረገው ጥረት የማይናቅ
ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ሊያራምደን
አለመቻሉ በገሀድ ታይቷል ። ለምርቱ ዝቅ
ተኛነት አስተዋጽኦ ካደረጉት ምክንያቶች
አንዱ የሕዝቡ አሰፋፈርና የእርሻው ይዞታ
መበጣጠስ ነው። በተለይ አብዛኛው የእርሻ
ምርት የሚገኘው ከግል አራሾች በሆነባት
አገራችን የዚህ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ
አይደለም።ሁኔታውን በሚገባ በማጤን ጓድ
ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢ
ሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብ
ሰባ «የገበሬውን ኑሮ በተጨባጭ ለማሻሻል
በግል የማረስ ምርጫው እንደተጠበቀ ሆኖ
በመንደር የሚሰባሰብበት ሁኔታ እንዲፈ
ጠር ማድረጉ የሀገሪቱን ለም መሬትና የውሀ
ሀብት እንዲሁም ሌሎችንም ቅምጥ ሀብቶች
በሚገባ መጠቀም የሚያስችል ብቻ ሳይሆን
ለአጠቃላዩ የሕዝቡ ማኅበራዊ ዕድገት መሠ
ረታዊ ጥያቄ ነው» በማለት ባስገነዘቡትና
ማዕከላዊ ኮሚቴውም በወሰነው መሠረት
በልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር ቅድሚያ በተሰጣ
ቸው አካባቢዎች በመንደር የማሰባሰቡ እን
ቅስቃሴ እየተካሄደ ነው።ይህም እንቅስቃሴ
እንደ ከዚህ ቀደሞቹ ሁሉ የአድኅሮት ኃይላ
ትን ጩኸት አስከትሏል ። ዛሬ ለአብዮታ
ችን ቅንጣት ታህል በጐ ምኞት የሌላቸውና
የራሳቸውን ጥቅም ብቻ እንጂ የሕዝብ ኑሮ
ተሻሽሎ ማየት የማይፈልጉ ወገኖች በአርሶ
አደሩ ላይ መዓት እንደመጣበት እያስተጋቡ
ናቸው ። «ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆ



Digitized by Google

ናል» እንደሚባለው ይህ ጨኸት ተጠቃሚውን ጭምር ሊያወናብድ ይችላል።በዚህም የተነሣ የእርምጃውን ገጽታ ለማሳየት በአሁኑ ጽሑፍ ውስጥ ስለመንደር ምንነት ፣ በመንደር የመሰባሰብ አስፈላጊነት ፣ በመንደር ምሥረታው ወቅት ሊፈጸሙ ስለሚችሉ ስህተቶችና ሊተኮርበቸው ስለሚገቡ ነጥቦች መቃኘት እንሞክራለን ።

## መንደር ምንድነው ?

አንድ ስለመንደር የተሰጠ ትርጉም እንደሚያመለክተው ፣

በቃሉ ጠባብ አገላለጽ መንደር ማለት የገጠሩ ሕዝብ የሚኖርበት አነስተኛ የግብርና አካባቢ ማለት ነው ። መንደር የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ሰፋ አድርገን ስንመለከት ግን ከአባባሉ የምንገነዘበው ነዋሪዎቹ ገበሬዎች ፣ የእርሻ ሠራተኞችና በአብዛኛው በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ቋሚ መኖሪያ ብቻ ሳይሆን ፣ መንደር ከከተማ ጋር ሲነጻጸር ፣ በገጠር ያለውን ማኅበረ ኢኮኖሚ ፣ ባህል ፣ አኗኗር ፣ ጂኦግራፊያዊና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል የማኅበረ ኢኮኖሚ ፈርጅ መሆኑን ነው ።[1] በዚህ አገላለጽ መንደር ነዋሪውን ፣ አኗኗሩን ፣ አካባቢውን ፣ የተፈጥሮ ሀብቱን ፣ ወንዙን ፣ ተራራ ሸንተረሩን ፣ የደኑንና የመሳሰለውን የተፈጥሮ ሀብቱን ያጠቃልላል። በመሆኑም ስለመንደር የሚደረግ ማንኛውም ትንታኔ እነዚህን ሁሉ ያካተተ መሆን ይኖርበታል ። የገጠሩን ሕይወት በተሟላ መልኩ ማየት የሚቻለውም እንዲህ ሲደረግ ብቻ ነው ። እንደማንኛውም የሰው ልጅ ዕድገት ገጽታ የገጠሩ ሕይወትም ከኅብረተሰብ ዕድገት ጋር እየተለወጠ የሚሄድ በመሆኑ በምርት ኃይሎች ዕድገትና በዚህም ምክንያት ከሚመጣው ማኅበራዊ ሥርዓት አኳያ በብዙ ተለውጧል ፤ ዛሬም እየተለወጠ ነው።በመሆኑም የገጠሩ መንደር አደረጃጀት አንድ አገር የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ፣ የሕዝቡን ታሪካዊ አመጣጥ ፣ ባህሉንና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን ያንፀባርቃል። የገጠሩ አሰፋፈር ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ፣ የቤቱ አሠራር ፣ የሕዝቡ አመጋገብና አለባበሱም ከአካባቢው ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ፣ ከእርሻው ዓይነትና ከሰፋሪው ባህላዊ አኗኗር ጋር የተያያዘ ነው ።

የመንደርን ምንነት በዚህ መልኩ ከተገነዘብን አመጣጡን ከታሪክ አንፃር መመልከት እንሞክር ። ከኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ እንደምንገነዘበው የሰው ዘር በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያው የዕድገት ደረጃ ላይ ይኖር የነበረው በመንጋ ነው። በዚያን ጊዜ ለሕልውናው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የሚያገኘው ከአካባቢው ፍራፍሬዎችን፣ቅጠላ ቅጠሎችንና ሥራ ሥሮችን በመሰብሰብ ነበር ። የተፈጥሮ ችግርንም ሆነ አደገኛ እንሰሳትን የሚከላከልበት መሣሪያና አስተማማኝ ዘዴ አልነበረውም ። ከሌሎች እንስሳት ጋር ሲነፃፀርም ዐቅመ ደካማ በመሆኑ የተፈጥሮ አደጋን ለመቋቋምና ራሱን ከሌሎች አራዊት ለመከላከል በጋራ ከመሰለፍ ሌላ አማራጭ አልነበረውም ። አብሮ የመኖርና የመረዳዳት ጥንስስ በዚህ የዕድገት ደረጃ ጀመረ ለማለት ይቻላል።እያደርም የሰው ዘር በውሀ ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ እንስሳትን መመገብ ለመደ ። የሥጋን ምግብነት ካወቀ በኋላ የምግብ ፍላጐቱን ለማርካት አደን ጀመረ ። አደን በግለሰብ ደረጃ ያውም በድንጋይና በውል ባል ተቀረጸ እንጨት የሚቻል ስላልነበረ መተባበር የግድ አስፈላጊ ነበር ።

የሚለቀም ቅጠላ ቅጠልና ፍራፍሬ እንዲሁም የሚታደን እንስሳ ሁልጊዜ በአንድ አካባቢ እንደልብ አይገኝም። ስለዚህ ቅጠላ ቅጠልና ፍራፍሬ ለመልቀምም ሆነ እንስሳትን ለማደን ከቦታ ቦታ መዘዋወር አስፈላጊ ነበር ። በዚህም ሂደት ሰዎች አንዳንዱ አካባቢ ከሌላው የተሻለ ሆኖ ሲያገኙት ሻል ባለው አካባቢ ብዙ ጊዜ መቆየትና ተመላልሰውም ወደዚያ መምጣት ለመዱ ። እያለም አንዳንድ የአትክልት ዘሮች ተስማሚ አፈር ላይ የሚበቅሉ መሆናቸው ስለተደረሰበት

Digitized by Google

የሰው ዘር በመረጠው አካባቢ መኖርና የጓሮ አትክልት ማብቀል ጀመረ ። ከዚያም የሚያድናቸውን እንሰሶች ከነሕይወታቸው ይዞ በቤቱ አካባቢ እያኖረ ለማዳ አደረገ ። እርሻና የከብት እርባታ መጀመር በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው የዕድገት ለውጥ የተደረገበት ጊዜ ነው ።

ቋሚ የምግብ ምንጭ በመገኘቱ ሰዎች በአንድ በተወሰነ አካባቢ ይሰፍሩ ጀመር ። የመጀመሪያው የሰው ልጅ መንደርም ይህ በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የተመሠረተው የእርሻና የከብት እርባታ መንደር ነበር ። የዚህ መንደር ምሥረታ ከአደን ወደ እርሻ ከተደረገው ሽግግር ጋር የተያያዘ ነው ። የመንደሩ አመሠራረት በዘርና በጎሳ ላይ የተመሠረተ ሲሆን መሬቱም ሆነ ከዚያ የሚገኘው ማንኛውም ምርት የጋራ ንብረት ነበር ። አሠራሩና አኗኗሩ በኅብረት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በኅብረተሰቡ መካከል የኑሮም ሆነ የሀብት ልዩነት አልነበረም። ለእርሻ ፣ ለአደን፣ ለቤት ሥራ ወዘተ. የሚያሰማራው የጎሳው አለቃ ማለትም በዕድሜውና በልምዱ ከኅብረተሰቡ መካከል የተመረጠ ሰው ነው። «የመንግሥት ተቋም ፣ ሥልጣን፣ በኅብረተሰቡ መካከል የማኅበረ ኢኮኖሚ ልዩነት አልነበረም፤ ሁሉም አባላት በክልላቸው በጋራ ያመርታሉ ፣ ከብቶቻቸውን በጋራ ያሰማራሉ ። »[2]

በወቅቱ የነበረው የሥራ ክፍፍል በጾታና በዕድሜ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ሴቶችና ሕፃናት በአካባቢያቸው ባለ ሥራ ላይ ሲሰማሩ ጎልማሶቹ ራቅና ጠንከር ያለውን ሥራ ያከናውናሉ። የእርሻ መጀመር የእርሻ መሣሪያዎችን መኖር አስፈላጊ አደረገ። የሰው ልጅ መሣሪያዎችን ለመሥራትና ለማሻሻል ባደረገው የረጅም ጊዜ ጥረትም እደጥበብ ራሱን የቻለና ዋስተኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ሆና ወጣ ። ለእርሻ ሥራ የእደጥበብ ውጤቶችን መጠቀም የእርሻውን የምርት ውጤት ከፍ አደረገ ። እያንዳንዱ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ከሚበቃ በላይ ማምረት ቻለ። በእደ ጥበብና በእርሻ ውጤት መካከል ልውውጥ ተጀመረ ። እያንዳንዱ ከሚፈልገው በላይ ማምረት በመቻሉና ልውውጥ በመጀመሩ የግል ሀብት ክምችት ተጀመረ ። የጋራ አሠራርና የጋራ ንብረት ቀስ በቀስ ለግል ንብረት ቦታውን ለቀቀ ፤ በዘር ላይ የተመሠረተው መንደርም ቀስ በቀስ በመኖሪያ አካባቢ ላይ ተመሠረተ ። የግል ሀብት እየተጠናከረ በመምጣቱ ኅብረተሰብ በመደብ ተከፋፈለ ። የሕዝብ ብዛት እየጨመረና የሰፋፊ መሬት አስፈላጊነትም እያደገ ሲሄድ አንዱ አካባቢ የሌላውን በኃይል ለመያዝ በአካባቢ መንደሮች መካከል ውጊያ ተጀመረ ። የተሸነፈው አካባቢ ለአሸናፊው የግጦሽና የእርሻ መሬት ሲሆን ምርኮኛው የግል ባሪያ ሆኖ እንዲሠራ በመገደዱ የባሪያ ጌቶች በኅብረተሰቡ መካከል ብቅ አሉ።በኅብረተሰቡ መካከል የነበረው እኩልነት እየጠፋ አንዱ አገልጋይ ሌላው ተገልጋይ እየሆነ ሄደ ። የሌሎችን ጉልበት መጠቀም ሲጀመር የጥንቱ መረዳዳትና የወል አስተሳሰብ በግል ጥቅም ተተካ።የጥንቱ የወል መንደርም በመደብ ጥቅም አኳያ አቀማመጡና አሠራሩ እየተለወጠ መጣ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለው የመንደር ታሪክ ከመደቦች አመጣጥ ታሪክ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ።

የመንደር አመሠራረትና አቀማመጥ የሕዝቡን ታሪካዊ አመጣጥና የተፈጥሮ ሁኔታን የተከተለ መሆኑን ጠቁመናል ። ከዚህ አኳያ አንዳንድ ጥንታዊ መንደሮችን ብንመለከት ለምሳሌ ከአብዮት በፊት «በቻይና» የነበረው የመንደር አመሠራረት ተራራማና ገደላገደል ከሆኑ አካባቢዎች በስተቀር ችምችም ያለ መንደር ነበር ። ይህም የሆነበት ምክንያት በሕዝብ ብዛትና በረጅም ታሪካዊ አመጣጥ ብቻ ሳይሆን ከውሀ ፍለጋና (በተለይም ጥልቅ ጉድጓዶችን ቆፍሮ ውሃ ከማውጣት ልምድ) ከጠላት ለመከላከል ሲባል ነው።»[3] በፈረንሳይ የመንደር አመሠራረት ቀጭን መሥመር የተከተለ ነው ። ቤቶቹ በሞላ

በአንድ በኩል ማለትም መንገድን ፣ ወንዝንና ምንጭን ተከትለው ይሠራሉ ። በጀርመን የጥንቱ መንደር ገዋንዶርፍ (Gewanndorf) የሚባል ሲሆን ቤቶች፣ጎተራዎች ፣ እብያተ ክርስቲያናትና ሌሎች ሕንፃዎች በመካከል ይሠራሉ ። በነዚህ ዙሪያ የአትክልት ቦታ፣ከዚያ የእርሻ መሬት፣ቀጥሎ ግጦሽ መሬት ፣ በመጨረሻ ጠፍ መሬቶችና ደን ይከተላል ። የዚህ ዓይነቱ አመሠራረት የጋራ መሬቶችን በማስተዳደር፣በሰብል ስብ ሰባ ፣ በወልና በግጦሽ መሬት አጠቃቀም ኅብረት እንዲኖር ያስችላል ።[4]

ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት ምሳሌዎች የምንረዳው እያንዳንዱ አገር የራሱ ታሪካዊ አመጣጥና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ያለው በመሆኑ የሕዝቡ ኑሮ አደረጃጀትም ይህንኑ የተከተለ መሆኑን ነው ። ይሁን እንጂ በሁሉም ሁኔታ ይብዛም ይነስ የሰዎች በአንድነት መኖር አለ ። አንድነቱም ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን ትግል በጋራ ለመወጣት በሚያደርገው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ።

ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች የሚታየው የገጠሩ መንደር ሁኔታም እንደየአገሮቹ ታሪካዊ አመጣጥና ዕድገት የተለያየ ነው። በገጠሩ ካፒታሊስት እርሻዎች እየተስፋፉ ሲሄዱ ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ ባለው አንገብጋቢ ፍላጐት የተነሣ አብዛኛውን ጊዜ በካፒታሊስት አገሮች ያለው መንደር በገጠሩ የሚከፈቱ መንገዶችንና ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን የተከተለ ይሆናል ። በገጠሩ ያለው የአነስተኛ ገበሬ እርሻ በትልልቅ ገበሬዎች እርሻ እየተዋጠና በአንድነት እየተጣመረ ይሄዳል ። አነስተኛ ገበሬዎች ውድድሩን መቋቋም ሲያቅታቸው እርሻቸውን ለትላልቅ ባለእርሻዎች እየሸጡ ወደእርሻ ወዝአደርነት ይቀየራሉ ። ወይም ሥራ ፍለጋ ወደከተሞች ይመጣሉ ። የእርሻ ወዝአደሮቹ የሚኖሩበት የገጠር አካባቢም ወደገጠር ከተማነት ይቀየራል ። «የካፒታሊዝም ዕድገት በብዙ አገሮች በተለይ ዛሬ በዩናይትድ ስቴትስና በካናዳ ጐልቶ እንደሚታየው ትላልቅና ትንንሽ እርሻዎች በገጠሩ የተስፋፉበት የተበታተነ አሰፋፈርን ያስከትላል ፤ ይሁን እንጂ አመጣጣቸው ከፊውዳሉ ሥርዓት በሆኑ እንደምዕራብ አውሮፓ ባሉ ካፒታሊስት አገሮች የተበታተነው የገጠሩ አሰፋፈር ከቀድሞው የገጠር መንደር ጋር ጐን ለጐን ይታያል ። »[5]

በሶሻሊስት አገሮች ለገጠሩ መንደር የሚሰጠው ትኩረት አገሮቹ ብዝበዛን ጨርሶ ለማስወገድ ካላቸው ትኩረት የመነጨ ነው ። ስለዚህ የሶሻሊስት አገሮች የመንደር አመሠራረት ለአጠቃላይ የኅብረተሰብ ዕድገት ከሚቀየሰው የልማት ስትራተጂና ለመመሥረት ከሚታሰበው ማኅበረ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተነጥሎ አይታይም ። በዚህም የተነሣ ሕዝቡ ለጋራ ልማት ተንቀሳቅሶ በኅብረት ለኑሮው የሚበጀውን ሁሉ ለማመቻቸት እንዲችል ጠቅላላውን ኅብረተሰብ ማደራጀት የሶሻሊዝም ዓይነተኛ ተግባር ነው ። በዚህ ላይ በመመርኮዝ የገጠሩ ሕዝብ ከሚደራጅባቸው መስኮች አንዱ ገበሬውን ለእርሻ ተስማሚ በሆነ አካባቢ ማሰባሰቡ ነው ።

በሶቭዬት ኅብረት ዓይነተኛ የገጠር መንደሮች ካልኮዝ በሚባሉ የኅብረት እርሻዎችና ሳቭኮዝ በሚባሉ የመንግሥት እርሻዎች አካባቢ የተሰባሰቡ ናቸው ። በ1970 ላይ ከጠቅላላው የገጠሩ ሕዝብ 42% በነዚህ መንደሮች የሚኖር ነበር ። በአንድ መንደርም የኗሪው አማካዩ ቁጥር 1,000 ነው። እነዚህ መንደሮች የገጠሩ አሰፋፈር መሠረት በመሆናቸው በማንኛውም ማኅበራዊ አገልግሎት ቀድሚያ ይሰጣቸዋል ።[6]

እነዚህ የገጠር መንደሮች ይሁኑ እንጂ የቤቱ አሠራር ፣ የሚያገኙት ማኅበራዊ ግልጋሎትና ያሉበት የኑሮ ደረጃ እጅግ ተሻሽሏል ። የሶቭዬት መንግሥት የገጠር ኮንስትራክሽን ድርጅት በማቋቋም መንደሮቹ በዘመናዊ መልክ እንዲ



Digitized by Google

ሠሩ አድርጓል ። በአጠቃላይ በሶሻሊስት አገሮች ዛሬ ያለው የገጠሩ አደረጃጀት ለኅብረተሰቡ አስፈላጊ የሆኑ ማኅበራዊ ገልጋሎቶችን ከማቅረብ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ከካፒታሊስት አገሮችም ቢሆን የተጠቃሚው ወገን ዓይነት ይለያይ እንጂ የመንደሮች ሁኔታ ማኅበራዊ ገልጋሎቶችን ከማቅረብ ጋር የተሳሰረ ነው ። በለሙ አገሮች የገበሬው አኗኗር በብዛት ተለውጧል ። እንደጥንቱ ከከብቶቹ ጋር የሚያድርበትና መኝታው ፣ መመገቢያውና ማብሰያው አንድ የነበረበት ሁኔታ ተለውጧል።

## የኢትዮጵያ ገጠር ሁኔታ

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ያለው የሕዝብ አሰፋፈር የአካባቢው ሕዝብ ከተሰማራበት የግብርና ዓይነት ፣ ከሕዝቡ ታሪካዊ አመጣጥና ባህል ጋር የተያያዘ ነው ። ኢትዮጵያ ያላት የመሬት አቀማመጥ፣ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጣው የአየር ሁኔታ መለያየት የሕዝቡንም አሰፋፈር የተለያየ አድርጎታል ። በአብዛኛው ሕዝብ ሰፍሮ የሚገኘው በደጋማው የአገሪቱ ክፍል ሲሆን ይህ ጠላትን ከመከላከልና በሽታን ከመሸሽ ጋር የተያያዘ ነው ። የእርሻውና የመሬት ሥሪቱም ዓይነት የሕዝቡን አሰፋፈር ይወስናል ። የዝርያ መሬት ይጠቀሙ በነበሩ የሰሜኑ ክፍሎች መሬት በወራሾች መካከል እየተሸነሸነ ስልሄደ አሰፋፈሩ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ እንደሚደርሰው ማሳ መጠን የተጠጋጋ ወይም የተራራቀ ይሆናል። የተቀራረበ በሆነበትም ቢሆን የአንድ መንደር ነዋሪ ቁጥር ብዙውን ጊዜ አነስተኛ ስለሚሆን ለመሠረተ ልማት በሚያመች ደረጃ አይደለም ። እንደ እንሰትና ቡና ያሉ የጓሮ አትክልቶችን በሚያለሙ ክፍሎች በእያንዳንዱ ቤት ዙሪያ እነዚህ ተክሎች ስለሚኖሩና በቤቶች መካከል ያለው ቦታ በተክሎች ስለሚሸፈን መንደሩ የተጠጋጋ ይመስላል ። ይሁን እንጂ በነዚህ አካባቢዎችም ቢሆን ቤቶቹ የተቀራረቡ አይደሉም ። ከብት አርቢው ዘላን ለብዙ ጊዜ በአንድ አካባቢ በሚኖርባቸው ቦታዎች ውሀ ባለባቸው አካባቢዎች ስብስብ ያሉ መንደሮች ሲኖሩ ፣ በአብዛኛው ግን የተበታተነ ነው ። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የገጠሩ አሰፋፈር በአብዛኛው የተበታተነ ሲሆን ሰፋፊ መንደሮች የሚታዩት በገበያዎችና በአስተዳደር ከተሞች አካባቢ ብቻ ነው ።

በመነሻችን እንደጠቀምነው የሕዝቡ አሰፋፈር ታሪካዊ አመጣጡንና የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ያንፀባርቃል ። ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ያለውን የገጠሩን ሕይወት ምን እንደሚመስል የምንገልጸውም ከዚሁ አኳያ ነው ። የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ ቤት መስከረም 1977 ባወጣው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት በኢትዮጵያ ገጠር የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 37,276,563 ወይም 88.70% ነው። «ከጠቅላላው የአገሪቱ ምርት 46 በመቶ ፣ ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 90 በመቶ ድርሻ ያለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው።» [7] የአንድን ኢኮኖሚ ዘርፍ ጠቀሜታ የምንለካው ከጠቅላላው የአገሪቱ ምርት በያዘው ድርሻ ፣ ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠንና ከተሠማራበት የሥራ ኃይል ብዛት ነው። እላይ ከተጠቀሰው አኃዝ እንደምንረዳው በማንኛውም መለኪያ ግብርና በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ አያከራክርም ። የአገራችንም የወደፊት ዕድገት የሚወሰነው በአብዛኛው ለዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ በሚሰጠው ትኩረት ላይ ነው ። በኛ ሁኔታ ለግብርናው ትኩረት እንስጥ ሲባልም ለገበሬው አመራረትና አኗኗር ትኩረት እንስጥ ማለት ነው ። ከዚህ አኳያ ሲታይ የገጠሩ ኑሮ ምን ይመስላል ?

የኢትዮጵያ ገበሬ የሚተዳደረው በእርሻ፣ በከብት ርባታና በቅይጥ ግብርና (እርሻና ከብት ርባታ) ሲሆን የሁሉም ኑሮ ኋላቀር ነው ። «በኢትዮጵያ ግብርና የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት በአራተኛው ሺህ ዓመት ሲሆን የተለያዩ እንስሳትንም ማርባት በዚህን ጊዜ መጀመሩ ይታመናል ።» [8]



Digitized by Google

ኢትዮጵያ በዓለም እርሻ በመጀመሪያ ከተጀመረባቸው አገሮች አንዷ ስትሆን ዛሬ በምትጠቀምበት የእርሻ ዘዴ ግን እጅግ ኋላቀር ከሆኑት አገሮች አንዷ ናት። በእርሻ በሚተዳደሩ በብዙ አካባቢዎች ዋነኛው የእርሻ መሣሪያ በተለያየ መልክ የሚሠራ የእጅ መሣሪያ ሲሆን በተለይም በጣም ኋላቀር በሆኑ አካባቢዎች በሹል እንጨት መገልገል ዛሬም አለ ። ከዚያ ባለፈ የተሻ ሻለው የገበሬው የእርሻ መሣሪያ በበሬ መጠቀም ሲሆን ጥማድ የእርሻ በሬ ያለው ገበሬም ቁጥር ብዙ አይደለም ። ዛሬ የኢት ዮጵያ እርሻ የሚገኝበት ደረጃ ይህ ነው ። በዚህ መልክ የተመረተ ምርት ከራሱ ከገ በሬው ቤተሰብ ፍጆታ አልፎ ሌላውን የኅ ብረተሰብ ክፍል ለመመገብ እምብዛም የሚ ያስችል አይደለም ።

የአገራችን የግብርና ሁኔታ የሚታወቀው በኋላቀር አስተራረሱ ብቻ አይደለም ። የእ ርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት አንዱ ችግር የተበታተነ መሆኑ ጭምር ነው ። ለዘመናት ተንሰራፍቶ በቆየው ኋላቀር የፊውዳል ሥርዓት የመሬት ይዞታ የተነካ መሬት በጥ ቂቶች እጅ በመሆኑና የራሱ መሬት ያለ ውም እየከፋፈለ ለልጆቹ ሲያወርስ ፣ የወል መሬትም በተወላጆች መካከል ሲከፋፈል ፣ ጢሰኛው በየቦታው ትንንሽ ማሳዎችን ሲከራይ በመቆየቱ የገበሬው እርሻ እጅግ የተበጣጠሰና ጊዜና ጉልበትን የሚያባክን ነው ። የገበሬውን እርሻ የተበጣጠሰ መሆን አስመልክቶ በአሥሩ ዓመት መሪ ዕቅድ ላይ እንደተጠቀመው « 94 በመቶ ያህሉ እርሻ በተበጣጠሰ ሁኔታ በግል ገበሬዎች ይዞታ ሥር የሚገኝ ነው ።»[9] የእርሻ ሚኒ ስቴርም ከ1966—1967 ያደረገው ጥናት እን ደሚያመለክተው

በጠቀላላ በአገሪቱ የእያንዳንዱ ገበሬ አማ ካይ እርሻ 2.46 ማሳ ሲሆን - ከጠቅላላው ገበሬ 19.6% አራትና ከዚያ በላይ ማሳ አለው ። . . . በአገሪቱ ካለው ጠቅላላ ይዞታ 40% ብቻ አንዳንድ ማሳ ሲሆን 60% ሁለትና ከዚያ በላይ ማሳ አለው።[10]

የእርሻው መበጣጠስ በአገሪቱ በሞላ የሚ ታይ ቢሆንም በሁሉም ክፍላተ ሀገር ተመ ሳሳይ አይደለም። ጊአርጊ ጋልፔሪን የተባለ ጸሐፊ ኢትዮጵያ ፣ ፓፑሌሺን ሪሶርስ ኢኮኖሚ በተባለው ጽሑፉ እንደገለጸው

በ1970 ዎቹ እ.ኤ.አ. በመጀመሪያ ላይ ሦስትና ከዚያም በላይ ይዞታ ያላቸው የገ በሬ ቤተሰቦች መጠን በሸዋ 45%፣ በትግራይ 59%፣በጉጃም 47% እና በአርሲ 54% ነው። በማሳው መበጣጠስ የተነሣ የይዞታው መ ራራቅ እየተባባሰ በመሄዱ ሁኔታው የም ርት መቀነስንና የጊዜና የጉልበት መባክ ንን አስከትሏል ። በአንዳንድ አካባቢ ገበ ሬው ከሥራው ቀን እስከ አንድ ሦስተኛ ውን ከአንዱ ማሳ ወደሌላው ሊመላለስ ያባክናል ።[11]

ከዚህ የምንገነዘበው የገበሬው የእ ርሻ ምርት ዝቅተኛ የሆነው በኋላ ቀር አስ ተራረሱ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ጊዜውንና ጉል በቱን በአንድ ሥፍራ ለማዋል እንኳን የእ ርሻው አደረጃጀት ባለማመቸቱ ጭምር ነው ።

የእርሻው ሁኔታ በአስተራረሱ ኋላቀርነ ትና በመበጣጠሱ ብቻም አያበቃም ። ከሕ ዝቡ የዕድገት ደረጃ ኋላቀርነትና ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ጨርሶ ባለመለመዱ ደኑ ተመንጥሮ አልቋል ። በደኑ መመንጠር የተነካ አፈሩ እየተሸረሸረ በአንዳንድ ቦታ ንጣፍ ድንጋይ አግጦ የሚታይበት ደረጃ ተደርሷል ። የደኑ መመንጠር የአፈ ሩን ልምላሜ ከመቀነሱ ባሻገር የአፈሩ እር ጥበት እየቀነሰ ፣ የአካባቢው አየር ሁኔታ እየተለወጠ እንዲሄድ አድርጎታል ። በዚህ የተነሣ ከዓመት ዓመት የሚገኘው ዝናም መጠን እየቀነሰ ነው ። የዘነበው ዝናብም ቢሆን ወደመሬት ውስጥ በብዛት እንዲሰ ርግ የሚያደርገው የደን ሀብት ባለመኖሩ ጐርፍ እየሆነ በወንዞች አማካይነት መጠኑ እጅግ የሚያሳስብ ለም አፈር እየጠራረገ ይወርዳል ። ሁኔታው እየገፋ ሄዶ ዛሬ አንዳንድ አካባቢ በተለይም የሰሜኑ ክፍል



Digitized by Google

ወደበረሃነት የመለወጥ አዝማሚያ አሥጊ እየሆነ መጥቷል ። ድርቅ አልፎ አልፎ የሚታይ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደጋገም ክስተት ሆኗል ፡ ባለፉት ሃያ ዓመታት በተደጋጋሚ የመታን ድርቅ ሁኔታ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው ።

በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሣ የኢትዮጵያ ገበሬ ምርታማነት እጅግ ዝቅተኛ ነው ። በእርግጥ የገበሬው ምርታማ አለመሆን የኢትዮጵያ ልዩ ባሕርይ ሳይሆን በአብዛኞቹ ታዳጊ አገሮችም የአለው ሐቅ ይኸው ነው ። የዓለም ምግብ ድርጅት መግለጫ እንደሚያሳየው «በአብዛኛው ታዳጊ አገሮች በእርሻው አካባቢ ያለው 'ትረፈ' ሥራ ከጠቅላላው የሥራ ኃይል ከአንድ አምስተኛ እስከ ሦስት አምስተኛ ይሆናል ። ይህ መጠን በኢንዶኔዥያ 35%፣ በሲሪላንካ እስከ 45%፣ በፊሊፒንስና በበርካታ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች 64% »[12] ነው ። «ኢትዮጵያ ካላት 122.3 ሚሊዮን ሄክታር የመሬት ስፋት በፈረቃም ሆነ ከዓመት ዓመት ታርሶ ለልዩ ልዩ ዓመታዊና ቋሚ ሰብሎች የሚውለው የእርሻ መሬት 15.8 ሚሊዮን ሄክታር (13 በመቶ) »[13] ብቻ መሆኑ አታን ባለው አሠራርና አሰፋፈር አገርን ማልማት ጨርሶ የማይታለም ለመሆኑ አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው ።

እላይ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሣ የገበሬው ምርታማነት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ገበሬው ከጠቅላላው ምርት አብዛኛውን ለራሱ ተጠቅሞ ለገበያ የሚያቀርበው ከ15—20% የሚሆነውን ብቻ ነው ። ይህ ለገበያ የሚቀርበው የምርት መጠን ከአፍሪካ እንኳን የመጨረሻ ከሆኑት አንዱ ነው ።[14] በአጠቃላይ ገበሬው ባለበት ሁኔታና በገጠሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ዘልቀው ባለመግባታቸው

የታዳጊ አገሮች ገበሬ ምርታማነት በኢንዱስትሪ ከበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች አርሻ ጋር ሲነጻጸር ከ20—30 ጊዜ ያነሰ ነው ። አንድ የአውስትራሊያ ወይም የኒውዚላንድ ገበሬ ለ35 ወይም ለ50 ሰው የሚበቃ እህል ሲያመርት አንድ የምዕራብ አፍሪካ ገበሬ የሚያመርተው ከ1.1—1.2 ሰዎች የሚሆን ብቻ እንደሆነ አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ ።[15]

የኢትዮጵያም ከዚህ የራቀ አይደለም ። ለዚህ ነው 85% የሥራ ኃይል ይዞ ዛሬ 15% የማይሞላውን የከተማ ኗሪ መመገብ ያቃተው ። ለዚህ ነው ለአንድ ዓመት የሚበቃ የምርት ክምችት ባለመኖሩ የአንድ በልግ ወይም መኸር ዝናብ መታጣት የምግብ ተመጽዋች የሚያደርገው ።

በከብት እርቢው በኩል ያለው ሁኔታም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም ። «ኢትዮጵያ በከብት ብዛት ከአፍሪካ አንደኛ ስትሆን ፣ የግጦሽ መሬቷ ስፋት ለእርሻ ከሚሆነው ከስድስት ጊዜ በላይ ይሆናል ። »[16] ካላት ጠቅላላ የከብት ብዛት «ወደ 40% የቀንድ ከብቶች ፣ 75% ፍየሎች ፣ 25% በጎች ፣ 20% የጋማ ከብቶችና 100% ግመሎች የሚረቡት በዘላኑ አካባቢ ነው ። - - - ለእርሻ የሚሆኑ በሬዎች በብዛት የሚገኙት ከዘላኑ አካባቢ ከመሆኑም በላይ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ከ60—70% ከብቶች የሚቀርቡት ከዚሁ ክፍል ነው ። »[17] የከብት እርባታውም ቢሆን የሚጠቀምበት የርባታ ዘዴ በኋላ ቀርነቱ ከእርሻው ክፍል የባሰ እንጂ የተሻለ አይደለም ።

ዘላኑ የኅብረተሰባችን ክፍል በአብዛኛው የሚኖረው በጠረፉ አካባቢ ማለትም በቆላማው አካባቢ ነው ። በዚህ አካባቢ ዝናብ በሚጥልበት ወቅት በቂ ሣር ስለሚኖርና ከብቱ የሚበላው እንደልብ ስለሚያገኝ በሚገባ ይራባል ። ይሁን እንጂ በቆላማው አካባቢ የዝናቡ መጠን አነስተኛና የሚዘንበውም ለአጭር ጊዜ ስለሆነ ፣ የድርቁ ጊዜ ያመዝናል ። በመሆኑም ዘላኑ የከብቱን ጭራ ተከትሎ ከዓመት ዓመት ውሀና ግጦሽ ወዳለበት ሲዘዋወር ይኖራል ። በክረምቱ ወራት የእያንዳንዱ ከብት ክብደት



Digitized by Google

ይጨምራል ፣ በጋው ሲመጣ ይከሳና ለልዩ ልዩ በሽታ ይጋለጣል ። ከፊሉም ይሞታል ። ጊኦርጊ ጋልፔሪን ቀደም ሲል በተጠቀመው ጥናቱ እንደገለጸው ከብት እርቢው ገበሬ « በዓመት ከጠቅላላው ከብት 8% የሚሞቱበት ሲሆን ፣ ከጥጆች ደግሞ እስከ 50% ይሞታሉ ። » [18]

የእንስሳቱ አረባብ ዘዴያችን የሚገኝበት ደረጃ እጅግ ኋላቀር ነው ። መንጋው እርስ በርስ በተፈጥሮ መልኩ ከሚራባ በስተቀር ዘር ምርጫ የተለመደ አይደለም ። በዚህ የተነሣ ከከብቱ የሚገኘው የወተትም ሆነ የሥጋ ውጤት በጣም ዝቅተኛ ነው ። የዘላኑ አካባቢ ተለይቶ የሚታወቀው በኋላቀር የአረባብ ዘዴው ብቻ ሳይሆን ከዘመናዊ ገበያ ጋር በሚገባ ያልተያያዘ በመሆኑም ጭምር ነው ። ዘላኑ ኅብረተሰብ በከብት እርባታ ላይ ያለው አመለካከት ለራሱ ኑሮ ከተጠቀመ በኋላ የተረፈው የከብርና ዝና መለኪያ እንጂ የገቢ ምንጭ አይደለም ። ስለሆነም ዘላኑ ክፍል ከብቱንም ሆነ የከብቱን ውጤቶች ለገበያ የሚያቀርበው አንዳንድ ሸቀጦችን ሲፈልግ ብቻ እንጂ ሸጦ በውጤቱ የመጠቀም ዓላማ የለውም ። የዘላኑ ክፍል ከመሐል አገር ገበያዎች ጋር አለመተሳሰር በእንስሳት ሀብታችን በደንብ እንዳንጠቀም ከማድረጉም በላይ ለጐረቤት አገሮች ሲሳይ ሆኗል ። ከውጭ ምንዛሪ ማግኛ በሁለተኛነት ደረጃ የሚገኘው የከብቶች ውጤት የኮንትሮባንድ ማስገቢያና የአገር ውስጥ ገበያ ማዛቢያ ሆኖ ይገኛል ።

በአጠቃላይ ስንመለከት የኢትዮጵያ ገጠር ሁኔታ ኋላ ቀር ነው ። ገበሬው ከዓመት ዓመት ማስኖ የሚያገኘው ምርት ለዕለት ጉርሱና ለዓመት ልብሱ እንኳን አስተማማኝ አይደለም ። የሚኖርበትም ቤት በአብዛኛው አንድ ክፍል ብቻ ከመሆኑም ሌላ እሱም ከብቶቹም የሚያድሩት በአንድ ክፍል ነው ። በንጹህ ውሀ ፣ በሕክምና ፣ በጤና አጠባበቅና በልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ረገድም በአብዮቱ ዓ[illegible] ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ፣ [illegible] ከፍተኛ በመሆኑ የተጠናከረ ጥረት [illegible] ቃል ። በነዚህና በሌሎችም የገጠ[illegible] ችግሮች የተነሣ የግብርናው [illegible] ኖሚ ችግር መፍታትና ትክክለኛ [illegible] ገት ጉዳና ማስያዝ ዛሬ ነገ ተብሎ ቀን ቀጠሮ የሚያዝለት አይደለም ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ለሚገኝበት እጅግ ዝቅተኛ አኗኗር ዋናው ምክንያት በአመራረትም ሆነ በምርት አደረጃጀት ኋላቀር መሆናችን ነው ፣ በአንድ በኩል በሥራ ላይ ያልተሰማራ ጉልበት በገተማም ሆነ በገጠር በዝቶ በሌላ በኩል የማምረት ጥረት ሳይደረግ በረሃብ አለንጋ መገረፍ ፣ በአንድ አካባቢ ገበሬው የሚያርሰው መሬት ሲያጣ በሌላ አካባቢ ድንግል መሬት ተንጣሎ መገኘት ፣ በአንድ በኩል እንኳንስ ለኢትዮጵያ ለአካባቢ አገሮች የተረፉ ወንዞች ከጉመት ዓ[illegible]ት [illegible] በሌላ በኩል ግን ጠብታ ውሀ እጥ[illegible] - - - ይህ ነው ዛሬ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የምትገኝበት እንቆቅልሽ ። ኢትዮጵያን ከምግብ ተመጽዋችነት በዚያም ሳቢያ [illegible] ከሚያደርስባት የአብዮት ቡርቦራ [illegible] መፈታት ያለበት አንዱ ዓቢይ እንቆቅልሽ ይኸው ነው ። የእንቆቅልሹ ዋንኛ መፍትሄም የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብና የኢትዮጵያን ድንግል መሬት በሚገባ [illegible] ለሥራ መታጠቅ እንጂ ሌላ [illegible] ሊሆን አይችልም ።

በዓለም ላይ እጅግ ለምተ[illegible] አገሮችም ዛሬ እኛ በምንገኝበት የዕድገት ደረጃ ላይ በነበሩበት ጊዜ ተመ[illegible] እንደነበረባቸው ከታሪክ [illegible] በትድመ አብዮት ሩሲያ [illegible] ሁኔታ አስመልክቶ ሌኒን ሲ[illegible] ወደ ልመና ደረጃ [illegible] ብሏል ። [illegible] ከከብቶቹ ጋር ነው ፣ [illegible] - - - እየተደጋገመ በ [illegible] መበላሸት የተነሣ ገበሬው [illegible]



Digitized by Google

ተጋልጧል ፤ በሺ የሚቆጠሩ በረሃብና በበሽታ እያለቁ ናቸው ።» [19] ብሏል ። ሌሎችም አገሮች ከመበልፀጋቸው በፊት የነበሩበት ሁኔታ እምብዛም የተለየ አይደለም። ችግሩንም ለመፍታት የተለያዩ አገሮች የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመዋል ። ምዕራብ አውሮፓና ዩናይትድ ስቴትስን የመሳሰሉ ካፒታሊስት አገሮች ካፒታሊስት የዕድገት ጉዳና በመከተል በጥቂት ባለሀብቶች መጠቀሚያነትም ቢሆን ግብርናን ከኋላቀርነት ሲያላቅቁ ሶቭዬት ኅብረትና የምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮች ደግሞ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለብዙኃን በሚበጅ መልክ ዘመናዊ በማድረግ ከኋላቀርነት ማጥ ወጥተዋል ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያም ዛሬ ከምትገኝበት የኋላቀርነት ማጥ እንድትወጣ ገበሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችና የማኅበራዊ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ መሆን ይኖርበታል ። የገጠሩ የመንደር ምሥረታ እንቅስቃሴ ትልቁ ፋይዳም ለዚህ አስቴዋጽኦ ማድረጉ ነው ።

## የመንደር ምሥረታ

የሕዝብ በየአካባቢው ተሰባስቦ መኖር አስፈላጊነት ከኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎች አኳያ መታየት ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ ነው ። ከሁሉም በላይ የሕዝብ በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ መገኘት በዕቅድ ለመሥራት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ። እንደሚታወቀው በአገራችን አብዛኛው የእርሻ ምርት የሚገኘው በግል ከሚያርሱ ገበሬዎች ነው ። እነዚህ የግል አራሾች ከሕዝቡ ፍላጎትና ከገበያ ጋር የተጣጣመ ምንም ዓይነት ጥናት ስለሌላቸው ባስፈለጋቸው ወቅት የፈለጉትን ዓይነት ያውም በዝቅተኛ መጠን ስለሚያመርቱ ፣ በገበያ ላይ ያለው አቅርቦትና ፍላጎት በየጊዜው ይዋዥቃል ። ይህ ሁኔታ በአገር አቀፍ ደረጃ ለፍጆታም ሆነ በፋብሪካ ጥሬ ዕቃነት ሊሸመትና ሊከፋፈል በሚፈለገው የሰብል መጠንና ዓይነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጋል ። በአንፃሩ ገበሬው ሊያገኝ የሚገባው ጥቅምና ግልጋሎትም ይጓጉላል ። ገበሬው በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ ከተገኘ ግን የራሱን ፍላጎት ለማርካትም ሆነ ለአገር ልማት ተገቢ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያመቸዋል ። በአጠቃላይ በዕቅድ ለመሥራትና በተፈጥሮም በአግባቡ ለመጠቀም ያስችለዋል ። ይህ ካልሆነ በተለይ ተፈጥሮን ማልማት ቀርቶ ያለውን መንከባከብ እንኳ ትኩረት አይሰጠውም ። ስለዚህ ገበሬው በአንድ አካባቢ ከተሰባሰበ ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ዘዴን በማስተግር ለመኖሪያ ፣ ለእርሻ ፣ ለከብቶች ማሰማሪያና ለደን የተለያዩ አካባቢዎችን መከለል ይቻላል ።

ሌላው ተሰባስቦ መገኘት የሚሰጠው ጥቅም የኅብረት ክንድን ለጋራ ልማት ከማንግት አኳያ ነው። በዓለም ላይ ዛሬ ለምተዋል ከተባሉት አገሮች መካከል በተአምር የበለጸገ አንድም አገር የለም ። እያንዳንዱ አገር አሁን ካለበት የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰው በተለያየ መልኩ ያለውን የተፈጥሮና የሕዝብ ሀብት አቀናጅቶ በማሠራት ነው።በቅርብ ዓመታት ከአስከፊ ኋላቀርነት እየተላቀቀች የመጣችውን ቻይናን እንመልከት ። ሕዝባዊት ቻይና አብዮት ማካሄድ በጀመረችበት ወቅት የሕዝቡ የዕድገት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነበር ። በገጠሩ ያለው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታም አስከፊ እንደነበረ ይታወቃል ። በዚህ ላይ አገሪቱ ካላት የሕዝብ ቁጥር ጋር ጨርሶ የማይመጣጠን የመሬት ጥበት ነበረባት ። በመሬት መጣበብና በእርሻው ዘዴ ኋላቀርነት የተነሣ የገበሬው ምርታማነት በጣም አነስተኛ ነበር ። ይሁን እንጂ ዛሬ «ቻይናውያን ከዓለም የእርሻ መሬት ሰባት ከመቶ ብቻ ይዘው የዓለምን ሕዝብ አንድ አራተኛ መመገብ ችለዋል ።» [20] የዚህ ምስጢር እምኑ ላይ ነው ? ምን ተአምር ተሠራ ? ቻይና ከአብዮቱ በኋላ የተጠቀመችበት ዘዴ በመጀመሪያ ደረጃ ያላትን የሀብት ምንጭ ጥቅም ላይ ማዋል ነው ። በዓለም በሕዝብ ቁጥር አንደኛ



Digitized by Google

የሆነችው ቻይና በሕዝቧ የሥራ ኃይል በዶ
ንብ ለመጠቀምና ከእርሻ መግሪያና ከግዳ
በሪያ ጀምር ትድሚያ በአገር ውስጥ ለሚገኝ
የሀብት ምንጭ ሰጥታለች ። በዚህ መሠረት
በአንድ ጉልግሳ ዕድሜ ውስጥ ቢያንስ ሕዝ
ቧን በሚገባ መመገብ ችላለች ። ቻይና ይህን
ውጤት ያሳየችው ያላትንም የሥራ ኃይል
አስተባብራ በተፈጥር ላይ በማስማራት እንጂ
ያጋጠማት ተአምር የለም ። አንድ ምሳሌ
እንመልከት ።

ብቻይና ለተደረገው ጥረት አንድ ጥሩ ማስ
ረጃ በሊንሺን የተቆፈረው የቀይ ሰንደቅ ቦይ
ነው ። ሊንሺን ከፍተኛ የውኃ እጥረት ካለባ
ቸው አካባቢዎች አንዷ ናት።በዚያ ከሚገኙ
500 መንደሮች ወደ 370 የሚሆኑት ለመጠጥ
የሚሆን ውኃ ለማምጣት እስከ አሥር ኪሎ
ሜ. መሄድ ነበረባቸው። ይብሱንም ከአሥሩ
ዓመት ውስጥ ዘጠኙን በድርቅ ይመታሉ።የ
ውኃ ጉድጓድ በመቆፈርና የዝናብ ውኃ በማ
ጠራቀም ችግሩን ለመወጣት ጥረት ቢደረ
ግም ጥረቱ ዋጋ አላገኘም።በመሆኑም የቻን
ግሆን ወንዝ በመጥለፍ ወደ መንደሮቹ ለማ
ምጣት ተፈለገ ። ውኃው ያለበት የመሬት
አቀማመጥ ለመስና ቦይ አመቺ አልነበረም።
በዚህ ላይ የመንግሥት ዐቅም ውሱንነት ፤
የባለሙያ እጥረት ፤ የመግሪያ አለመኖር
ሲታይ በብዙዎቹ ዘንድ ፕሮጀክቱ አስቸ
ጋሪ መስሎ ታየ ። ሆኖም ሌላ አማራጭ ስላ
ልነበረ በአካባቢው ያለውን የሰው ኃይል
በማሠማራት ይህ ትልቅ ፕሮጀክት እ.
ኤ.አ. በ1960 ተጀመረ ።

ወጣቱ ትኩስ ጉልበቱን ፤ ሽማግሌዎችም
ደካማ ዐቅማቸውን ሳይቆጥቡ ለዚሁ ሥራ
አዋሉ ። እያንዳንዱ ብርጌድ የራሱን ኮታ
የሥራ ኃይል አዋጣ ። በየጊዜው ከ15ሺህ
እስከ 37ሺህ ሰዎች ሥራው ላይ ይሠማራሉ።
በዚህ መሠረት በተራራው ውስጥ ለውስጥ
180 ቦዮች ቆፍረውና የቻንግሆ ወንዝ
ዋናው ቦይ ብቻ 70 ኪሎሜትር ተጉዞ የሊ
ሺን አካባቢ መንደሮች ለአንዱና ለሁሉ
ከውኃ እጥረት ገላገለ ። ይህ ሥራው አሥር
ዓመት የፈጀው የቀዩ ሰንደቅ ቦይ በድርቅና
በጎርፍ መፈራረቅ ትሰቃይ የነበረችውን የሊ
ንሺን ገፃት ዛሬ የእርሻና የኢንዱትስሪ መን
ደር አድርጓታል ። [21]

አብዮታዊት ኢትዮጵያም ባላት ዐቅም
ከመጠቀም ሌላ አማራጭ የላትም ። ባለፈው
ሥርዓት በገጠሩ በነበረው ፊውዳላዊ የም
ርት ግንኙነትና ኋላቀር የእርሻ ዘዴ የተነሣ
የወረስነው ድህነትንና ኋላ ቀርነትን እንጂ
የረባ ካፒታል አይደለም ። ይሁን እንጂ ሊሠ
ራ የሚችል የሰው ኃይል ፤ ጥቅም ላይ ያልዋለ
ስፊ መሬትና የተንጣለለ የውኃ ሀብት አለን።
ስለዚህ ችግራችንን ለማቃለል እነዚህን ሀብ
ቶች አቀናጅተን መጠቀም መቻል አንደኛ
ውና ዋንኛው የዕድገት ስትራቴጂአችን
መሆን ይኖርበታል ። ለዚህም በቅድሚያ
ሊሠራ የሚችለው የሰው ኃይል በዕቅድ
ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት ሁኔታ ላይ
መገኘትና ዋና የሀብት ምንጭ ከሆነው
መሬትና ከውኃ ሀብት ጋር መገናኘት ይኖ
ርበታል ። ስለዚህ ገበሬው የሚገኝበት የተ
በታተነ አሰፋፈር መልኩን መቀየር አለ
በት ። ገበሬውን በመንደር የማሰባሰቡ
መርሐ ግብር አስፈላጊነት የሚመነጨው
ከዚህ ነው ።

ዛሬ በአገራችን የሚካሄደው የገበሬው
በመንደር መሰባሰብ ዓይነተኛ አስፈላጊነት
የሚመነጨው የኅብረት ክንድን ለጋራ ልማ
ት ከማንሣቱ አስፈላጊነትም ነው ። ለጋራ
ችግር ተባብሮ መሥራት በተለይ በአገራችን
አዲስ ነገር አይደለም ። ገበሬው ቤቱን የሚ
ሠራው ጉልበት ተከራይቶ ሳይሆን በአካባ
ቢው ነዋሪ ኅብረት ነው ። በእርሻውም ቢሆን
በወንፈል፣በደቦ(በጂጊ) መሥራት ከአያት ከ
ቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው።
ደን መንጥሮ፣በረሃ አቅንቶ ለመጠቀም ተመ
ካክሮ መነሣት የነበረና ያለ እንጂ ዘመን አመ
ጣሽ አይደለም ። በኅብረት መሥራት የተጀ
መረውና ያደገው የሰው ልጅ የሥራ ክን
ውን አንድ አካል በመሆን ሲሆን፤መሠረቱም
ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። መተ
ባበርና መረዳዳት የማናቸውም በጉልበት

Digitized by Google



« መንደር ምሥረታው ለሁለንተናዊ ዕድገታችን አመች ሁኔታ የሚፈጥርልን በመሆኑ ተደስተናል »

ሥራ የተሰማሩ ሰዎች ዓይነተኛ ባሕርይ ሆኖ ቆይታል ። በዚህ ጠባብና ቴክኒካዊ መልኩ በኀብረት መሥራት በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ማኅበረ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የነበረና ለሁሌም የሚኖር ነው ። [22]

የገጠሩ ኤኮኖሚያችን አንዱ ደካማ ጐን እያንዳንዱ ገበሬ በምርታማ ሥራ ላይ ሙሉ ጉልበቱን አለማሰማራቱ ነው ። ገበሬው በመንደር መሰባሰቡ የሥራ ኃይሉን በዕቅድ ለመምራት እንደሚረዳውም ይገመታል።ተበታትኖ ባለበት ሁኔታ ሁሉንም ነገር በግሉ ለመወጣት በሚገደድበት ሁኔታ ላይ ስለሚሆን ጉልበቱን አስፈላጊ በሆነና ባልሆነ ነገር ላይ ያባክናል ። ከተሰባሰበ እንደፍላጐቱና እንደሚያመቸው የሥራ ክፍፍል በማድረግ ምርታማነቱን ሊያሳድግ ይችላል ። ከእርሻ ሥራ ውጭም ለጋራ ጥቅም የሚውሉ የመስኖ ቦዮችን በመቆፈር፣ መንገድ በመሥራት፣ ደን በመትከልና በመሳሰሉት የጋራ ሥራዎች ላይ በመሠማራት ለአካባቢው ምርት መጨመር የሚረዱ ተግባራትን ለማከናወን ይችላል ። በትርፍ ጊዜው የእደ ጥበብ ሥራዎችን በመለማመድ ገቢውን ማሳደግ ይችላል ። ይህም በገጠሩ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት ይረዳል ።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች በገጠሩ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት በመመሥረት ኤኮኖሚውን ዘመናዊ መልክ ለማስያዝና ለማጠናከር ያለው የሥራ ኃይል ገበሬው በመሆኑ የገበሬው ኀብረት ወሳኝ ነው ። ሶሻሊዝምን በገጠሩ ብሎም በአገር አቀፍ ደረጃ ለመመሥረት ገበሬው የምርት ውጤቱን ከፍ ለማድረግ የእርሻውን ክፍለ ኤኮኖሚ ዘመናዊ መልክ ማስያዝ ይኖርበታል ። ለዚህም ዕውቀትና ኃይልን አቀናጅቶ መጠቀም ያስፈልጋል ።

በማኅበራዊ መልኩም የገበሬው ተሰባስቦ መገኘት የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው ። ዛሬ ገበሬው የሚኖረው ከዘመናዊ ኑሮ እጅግ ርቆ በመሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም ። በለሙት አገሮች የእርሻ ውጤቱን ለገበያ ለማድረስ በዘመናዊ መንገድ ይጠቀማል ። በኛ ሁኔታ ግን የገበሬው አሰፋፈር እጅግ የተበታተነ በመሆኑ ዘልቀው የሚገቡ የመኪና መንገዶች ሊዘረጉ ቀርቶ የእግር መንገዱም በደግ የሚስኬድባቸው ቦታዎች ብዙ አይደሉም ። በዚህ የተነሣ ምርቱን እንደአስፈላጊነቱ ለገበያ አቅርቦ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን መጠቀም የጀመረው ክፍል ጥቂት ነው ። ምርት ዓላማ ያለው ተግባር ነው ። ገበሬው ይበልጥ ለማምረት የሚገፋፋው ነገር ያስፈልጋል ። ገበሬው ምርትን ለገበያ አቅርቦ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተጠቃሚ ሊሆን ከቻለና ኑሮው ዕለት ከዕለት እየተሻሻለ ከሄደ የበለጠ ያመርታል ።

ገበሬው በአመዛኙ ማይም በመሆኑ ስለግብርና ፣ ስለዘመናዊ የቤት አሠራርና ስለጤና የሚያውቀው ጥቂት ነው ። የቤቱ አሠራር የሚጠቀምበት ቁሳቁስ ፣ የሚጠጣው ውኃ ወዘተ. ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ባህል የተወረሰ በመሆኑ ለጤንነቱ አመቺ አይደለም ። በአንጻሩ ዛሬ የብዙ አገሮች ገበሬ ኑሮ እጅግ ተሻሽሏል ። ለምሳሌ በሕዝባዊት ኮሪያ «ኤሌክትሪክ የሌለበት የገበሬ መንደር የለም ፤ ሬድዮ በገጠሩ ተዳርሷል ። » [23] ሌሎችም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ።ለገበሬ ኑሮ መለወጥ የገበሬው ለጋራ ብልፅግና በጋራ መሰለፍ አማራጭ የለውም ። እያንዳንዱ የአገራችን ገበሬ ባለው እጅግ ዝቅተኛ ዐቅም የልማት አውታሮችን መዘርጋት ቀርቶ ሊያስብም አይችልም ። ስለዚህ መድህኑ ያለ ዐቅሙን አስተባብሮ ባለው የተፈጥሮ ሀብት መጠቀም ነው።

በትምህርትም ረገድ ስፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ 93% ማይም የነበረበት ወቅት የትላንት ትዝታ ነው ። በአብዮታችን አብዛኛው ሕዝብ ከማይምነት እየተላቀቀ ቢሆንም በተለይ በገጠሩ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ለማካሄድ እንኳን የነበረው የማስተማሪያ ማዕከል ምርጫ ችግር የቱን ያህል እንደነበረ በሥራው የተሰማሩ ያውቁታል።በተበታተነ

Digitized by Google



በዕቅድ የተመሠረተ መንደር ለልማት ይበጃል



Digitized by Google

መልክ፣ በመሬሬው ገበሬ መካከል አግባይ ሥፍራ መያዛ እስቸጋሪ ከመሆኑም ሌላ ገበሬው እሩቅ መንገድ በእግሩ እየተጓዘ እን ዲግር መደረጉ በዘመቻው ላይ ያለው ተጽ ዕኖ ቀላል አይደለም ።

እምራቹ ገበሬ የሚያስፈልገው የቀለም ትምህርት ብቻም አይደለም ። ስለዘመናዊ እርሻ ፣ ስለከብት እርባታ ፣ ስለመስኖ አጠቃ ቀም ፣ ስለምግብ አዘገጃጀትና ጤና አጠባ በቅ ዘመናዊ ትምህርት ሊቀስም ይገባል ። ገሬ ባለንበት የዕድገትና የኤኮኖሚ ደረጃ እንኳንስ ተበታትኖ ለሰፈረ ገበሬና በመ ንደር ከተሰባሰበም በኋላ በቂ ባለሙያዎ ችን ለማዳረስ ብዙ ጥረት እንደሚጠይቅን ግልጽ ነው ። ከዕቅም ውሱንነትም ባሻገር በባለሙያ መጠቀም ያለውን ፋይዳ ገበሬው በሚገባ እንዲገነዘብ ማድረግ እራሱም ቀላ ል አይደለም ። ይህንኑ በመረዳት ቀደም ሲል በአጋርፋ ፣ በአርዳይታና በአሥመራ የግብረ ግብልጠኞዎች ተቋቁመዋል ። በነዚህና ወደ ሬት በሌሎችም ተቋሞች በልዩ ልዩ ሙያ የሠለጠኑ ገበሬዎች ወደየአካባቢያቸው እየ ተመለሱ የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የገበሬው ተመቻችቶ መገኘት አስፈላጊ ነው ።

« በመሬት ላይ ያለ ሀብት የሀብት ሁሉ ምንጭ በመሆኑ ፣ የሠራተኛው መደብ የወደ ሬት ዕድል ለዚህ ሀብት በሚሰጠው መፍ ትሄ ላይ የሚወሰን ትልቅ ጥያቄ ሆኗል» [24] ይላል ካርል ማርክስ። ስለዚህ የገበሬውን ኑሮ በተጨባጭ ለመለወጥ ፣ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለአጠቃላዩ ልማት የመ ሬት ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል ። የዚህን አስፈላጊነት በመገንዘብ ልዩ ልዩ አገ ሮች በተለያየ መልክ ለመሬት ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል።በአንዳንድ አገሮች መሬት ለግል አራሾች በይዞታነት ይሰጥና ገባርነት ይወገ ዳል።በሌሎች አገሮች መሬት በጠቅላላ የሕ ዝብ ሀብት ይሆንና ገባርነትን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ብዝበዛ ለሌለበት ለሶሻሊዝም ግን ባታ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ይመቻቻል ።

በሶቭዬት ኅብረት አብዮቱ ለመሬት ጥያቄ የሰጠውን ምላሽ አስመልክቶ ሌኒን የሚከተ ውን ተናግሮ ነበር።«በዚች የገበሬ አገር የመ ጀመሪያ ተጠቃሚ የሆኑት ፣ ከፍተኛ ጥቅም ያገኙትና ወዲያውኑ የተጠቀሙት ጠቅላላ ገበሬዎች ናቸው » [25] በአብዮታዊት ኢትዮ ጵያም የአብዮቱ ሥር ነቀልነት በመጀመሪያ የተረጋገጠው የገጠርን መሬት የሕዝብ ባደረ ገው የ1967 የመሬት አዋጅ ነበር ። በዚህ አዋጅ አግባይነት የኢትዮጵያ ገበሬ የመ ጀሪያውና ከፍተኛው ተጠቃሚ ሊሆን በቅ ቷል ። አዋጁ በባለመሬትና በጪሰኛ መካ ከል የነበረውን የጌታና ሎሌ ግንኙነት እት ብት በጥሷል ። ገበሬውን የራሱ ምርት ተጠ ቃሚ እንዲሆን አስችሏል ። ለገበሬው ወደ ከተማ መፍለስ አንድ ምክንያት የሆነውን የእርሻ መሬት ማጣትን ጥያቄም አስወግ ዷል ።

ይሁን እንጂ መሬትን የሕዝብ ማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም ። ገበሬው ለመሬት የነበረው ጥማትና ትግል ከፍተኛ ቢሆንም መሬት ባገኘ ማግሥት የሚፈለገበትን የሥ ራ ድርሻ ወዲያውኑ ይወጣል ማለትም አይ ደለም ። ገበሬው ኅብረተሰብ የዕቅም፣ የድር ጅትና የዕውቀት ችግር አለበት ። የገጠሩ ኋላቀርነት የመነጨው እርሻ ከኢንዱስትሪ ጋር ሲነፃፀር ካለው ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠ ረት ኋላቀርነት፣ የገጠሩ ሕዝብ የባህል ደረጃ ከከተማው ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ከመሆኑና ገበሬውም በንቃተ ኅሊናው ከሠራተኛው ሕዝብ ኋላ ቀር በመሆኑ ነው ። ስለዚህ በእር ሻው ሶሻሊስት ለውጥ ለማምጣትና በከ ተማና በገጠር ፣ በሠራተኛውና በገበሬው መካከል ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ከሁሉ አስቀድሞ በገጠሩ ቴክኒካዊ ፣ ባህላዊና ርዕ ዮተዓለማዊ አብዮት ማካሄድ ያስፈልጋል ። በዚሁ በኩል ገበሬው ከአግባቡ እንዲስ ለፍ ከተደረገ የሚጫወተው የፖለቲካ ሚና ቀላል አይደለም ። ያታዳጊ አገሮች ገበሬ ለከፋ ብዝበዛ ተዳርጎ የኖረ ከመሆኑም ሌላ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኅብረተሰቡ ክፍል

Digitized by Google

እንደመሆኑ ሊኖረው የሚችለው አብዮታዊ ሚና ሰፊ ነው ። ስለዚህ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚያካሂዱ አገሮች የገበሬውን ድጋፍ ለማግኘታቸው እርግጠኛ መሆን ይኖርባቸዋል ። ገበሬው ያለፈው ሥርዓት ተበዝባዥ በመሆኑ የሥርዓቱን ለውጥ እጅግ የሚፈልግና ለዚህም በሚደረገው ትግል ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ቢሆንም ባለበት የግለኝነት ባሕርዩ ሥርዓቱ ከተገረሰሰና መሬት ካገኘ በኋላ የመርካት አዝማሚያ ሊያሳይ ይችላል ። ሁለተኛ ገበሬው ለኋላቀርነት ተዳርጎ የኖረ መደብ በመሆኑ ስለለውጥ ፣ ስለአስተዳደር ፣ ስለመደብ አሰላለፍ የሚያውቀው በዙም አይደል ። ስለዚህ ገበሬው ራሱን በራሱ በማስተዳደር ፣ የራሱን የልማት ዕቅድ በመንደፍ ፣ ስለጠላቶቹ ማንነትና ምንነት በደንብ በማወቅ በአብዮቱ ውስጥ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማዘጋጀት ከአብዮታውያን ኃይሎች የሚጠበቅ ተግባር ነው ። በእርግጥ ዛሬ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ገበሬ በገበሬ ማኅበር ተደራጅቷል ። የራሱን ዳኝነት በራሱ ተመራጮች ያያል ። አካባቢውን በራሱ ተሳትፎ ይጠብቃል ። ይህ ተግባር ግን ተበታትኖ በሚገኝበት በአሁኑ ሁኔታ በቀላሉ ሊከናወን የሚችል ተግባር አይደለም ። ስለዚህ ገበሬውን በመንደር በማሰባሰብ የፖለቲካ ንቃቱን ከፍ በማድረግ ራሱን በማስተዳደር ረገድ የበለጠ ብቁ እንዲሆን ማገዝ ያስፈልጋል ።

በአፍሪካ ውስጥ ለልማት ያመች ዘንድ ገጠሩን በመንደር በማደራጀት ረገድ በቀደምት ምሳሌነት የምትጠቀሰው ታንዛኒያ ናት ። ታንዛኒያ የመንደር ምሥረታ እንቅስቃሴዋን በተፋጠነ ሁኔታ የጀመረችው የአሩሻ ዲክላሬሽን ከተባለው በ1967 (እ.ኤ.አ) ከተላለፈው የፓርቲ ውሳኔ ወዲህ ነው ። በዚህ ውሳኔ መሠረት የገጠሩ ሕዝብ አዳዲስ ጎጆዎችን እየሠራ በመንደር እንዲሰባሰብ ተደረገ ። በታንዛኒያ የመንደር ምሥረታው ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች የነበሩት ሲሆን ፣ እነዚህም 1ኛ/ የገጠሩን እድገት ቴክኖሎጂ ማሻሻል ፣ 2ኛ/ በገበሬው መካከል እያቆጠቆጠ የመጣውን የኑሮ ልዩነት መግታትና 3ኛ/ ገበሬው በማንኛውም የአካባቢ ችግር ላይ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እንዲኖረው ማስቻል ነበር ። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ መንደር እንደ አንድ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተቋም ስለሚቆጠር የሚተዳደረው የመንደሩን እንቅስቃሴ እንዲመራ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በተመረጠ ምክር ቤት ነው ።---የመንደር ምሥረታው (እ.ኤ.አ) በ1968 ቀስ በቀስ ተጀምሮ ከ1970—1972 ባለው ጊዜ በተፋጠነ ሁኔታ ተካሄደ ።--- በ1976 13 ሚሊዮን ሕዝብ ወይም ከጠቅላላው ሕዝብ 85% በመንደር ተሰባሰበ ። ዛሬ በታንዛኒያ 8ሺህ መንደሮች ይገኛሉ ።[26] እነዚህ መንደሮች በልዩ ልዩ ምክንያት የተጠበቀውን ውጤት ሁሉ ባያስገኙና ድክመት ቢታይባቸውም በአንድ ጥናት እንደተመለከተው የኡጃማ መንደሮች ልዩ ልዩ ግልጋሎቶችን ለማቅረብ አመች ከመሆናቸው ባሻገር ለአገር ግንባታ ፣ ለመከላከያና ለፖለቲካ ቅስቀሳ መሠረት በመሆንም እያገለገሉ ናቸው ።[27] የታንዛኒያ መንደሮች ጠቀሜታቸው ከዚያች አገር ልዩ ሁኔታ አንፃር የሚመዘን ሲሆን ፣ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የተያዘው የመንደር ምሥረታ እንቅስቃሴም ከዚሁ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ። ጥንካሬያችንም ሆነ ድክመታችን መመዘን ያለበት ከምንገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር መሆን ይኖርበታል ። በዚህ መሠረት ጠቅላላው ሕዝባችን ከቆመለት የእኩልነትና የጋራ ብልጽግና ዓላማ አኳያ ኅብረቱና ድርጅቱ የጋራ ተጠቃሚነቱ ሊጠናከር የሚችልበትን ተግባር ሁሉ ማከናወን አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም ። የመንደር ምሥረታውም ይህንኑ መሠረታዊ ዓላማ ተፈጻሚ ከማድረግ የመነጨ ነው ።

## ማጠቃለያ

ማንኛውም ሥራ ከእክል ነፃ አይደለም ። ማንኛውም ከንዋኔ የራሱ ተቃራኒ አለው ።

Digitized by Google

ገበሬን በመንደር ማሰባሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተገልጿል፣ እውነትም ነው ። ይህ ማለት ግን ጥረቱ አንዳችም ችግር የለበትም ማለት አይደለም ። ለጊዜውም ቢሆን ተጨማሪ ጥረት ማድረግን እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው ።አልፎ አልፎ አንዳንድ የግል አኗኗራቸው የተመቻቸው ገበሬዎች ለብዙኃኑ ጠቀሜታ መጠነኛ መሥዋዕትነት መጠየቃቸው ሊጨንቃቸው ይችል ይሆናል ። እነርሱም ቢሆኑ በረጅሙ ጊዜ የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ እስከተደረገ ድረስ ችግሩ እምብዛም አይደለም ። ዋንኛው ዕንቅፋትና በቀላሉ መታየት የሌለበትም በብዝበዛ ላይ ለተመሠረተ የግል ሀብት የቆሙ ኃይሎች የሚነዙት አሉባልታ ነው ። ይህም ቢሆን ተጨማሪ ትግል ይጠይቅ እንጂ ትክክለኛውን ሁኔታ በገሀድ በማሳወቅ ለማክሸፍ ይቻላል ።

የመንደር ምሥረታ የገበሬውን ፈቃደኝነት፣ የሁኔታዎችን መመቻቸት ፣ የቤት መሥሪያ ቁሳቁስን ፣ ወቅትን ወዘተ. በማገናዘብ መካሄድ እንዳለበት አያጠያይቅም ። ከዚህ ውጭ ከተከናወነ የሚያስከትለው ችግር የእርሻ ምርትን በመቀነስ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በመንደሩ ምሥረታ ላይ ተፈላጊ ያልሆነ ስሜት ሊያሳድር ስለሚችል መታረም ያለበት ነው ።

ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ናት ።የስፋቷን ያህል የየአካባቢው ሁኔታ የሕዝቡ ባህልና አኗኗር ይለያያል ። ገበሬው በአንዳንድ አካባቢ ጥራጥሬ በማምረት ሲኖር፣ በሌላው አካባቢ ደግሞ አትክልት በማልማት ፣ ከብት በማርባት ወዘተ. ይኖራል ። ስለዚህ የመንደር ምሥረታው እነዚህን የተለያዩ ባሕርያት ማጤንን የሚጠይቅ ነው ። ለምሳሌ ከብት በሚረባበት አካባቢ በቅድሚያ በቂ መኖና ውሃ ሊገኝ መቻሉን ማረጋገጥ ወሳኝነት አለው ። ከዚህ አንፃር አንድ በታንዛኒያ ካጋጠመ ሁኔታ ትምህርት ማግኘት ይቻላል ።

ምኪንጋ ሊዩ አንድ የክፍለ ሀገር ከተማ አጠገብ የሚገኝ ቀበሌ ነው ። የቀበሌውም መንደርተኞች ብዙ ሰብሎችን በማምረት ቅድሚያ ያላቸው እንደነበሩ ይነገርላቸዋል ። ትምህርት ቤቶችንና ክሊኒኮችን ተባብረ በመሥራት ረገድ ከሌሎች የተሻለ ልምድ አላቸው ። በአካባቢው በብዛት የሚበቅለው የተምር ዛፍ ነው ። በዛፎቹ ውስጥ የሚበቅለውን ሣር በመጠቀም ከብቶች ለማርባት ዕቅድ ወጣ ። ከብት ላላቸው ገበሬዎች ብድርና ዲቃላ ዘሮች ተሰጡ ። እርባታው ጥሩ ውጤት አስገኘ ። የአካባቢው ውጤት ድንቅ ተባለ ። መንደሩም ተራማጁ መንደር እየተባለ ይጠራ ጀመር ። በሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ከምኪንጋ ሊዩ ተማሩ እየተባለ ቅስቀሳ ተደረገ ። በ1971 (እ-ኤ-አ) የከብቱ ቁጥር 340 ደረሰ ። አካባቢው ሊበቃቸው ስላልቻለ ከብቶቹ ለግጦሽ እስከ ስምንት ኪሎ ሜትር መጓዝ ነበረባቸው ። በዚያ ላይ የተወሰኑ የመንደሩ ነዋሪዎች ንብረት የነበሩት ከብቶች በሌሎቹ ገበሬዎች የተምር ዛፍ ላይ ጥፋት በማስከተላቸው ቅሬታ ተፈጠረ ። ስለዚህ የከብት እርባታው እንዲገታ ተደረገ ። [28] ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው ከብት አርቢው በመንደር ሲሰባሰብ ለከብቶቹ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን ነው ። እዚህ ላይ በብዛት ከብት የሚያረባውን ክፍል ጠቀስን እንጂ በኢትዮጵያ ገበሬ ሲባል በቤቱ ውስጥ ቁጥሩ ይብዛም ይነስ የቤት እንስሳት የማያረባ ቢ ኖ ር በጣም ጥቂት ነው ። የሁሉም መንደርተኛ ከብቶች በአንድ ላይ ሲሰባሰቡ ግን ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ።

የከብቶችን ሁኔታ እንደምሳሌ ጠቀስን እንጂ ከመንደር ምሥረታ ጋር ዘለግ ባለ ሁኔታ መጤን ያለባቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው ። ስለዚህ እንቅስቃሴው ዓቅምና ጠቅላላ ሁኔታን እየገመገመ መራመድ የሚጠይቅ ነው ። የተያዘው ጥረትም ከዚሁ አኳያ ደረጃ በደረጃ እንዲከናወን የተቀየሰ ነው ።

ካርል ማርክስ እንዳስገነዘበው « . . . ገበሬው አብዛኛውን የሚፈልገውን በ ራ ሱ

Digitized by Google

ስለሚያመርት ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የሚያገኘው ከኅብረተሰብ ይልቅ ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው መስተጋብር ነው ። » [29] በመሆኑም ገበሬው በባህሉና በዕውቀቱ ውሱን ነው ። በገባርነት ሲማቅቅ የኖረ በመሆኑ ይጠራጠራል ። ስለዚህ ገበሬውን ለማሳመን የሚቻለው በተግባር ብቻ ነው ። ተግባር ደግሞ ጥረትን ይጠይቃል ። ስለዚህ ገበሬውን በመንደር የማሰባሰቡ ሥራ በመንደር ምሥረታ የሚያበቃ ሳይሆን ተፈላጊዎቹን ውጤቶች እስኪያስገኝ ትግሉ መቀጠል ይኖርበታል ።

የመንደር ምሥረታ ወደ ዋናው ግባችን ለመድረስ ጥርጊያ እንጂ በራሱ ግቡ አይደለም ። ዓላማችን በገጠር ሳይንስና ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ኋላቀርነትን ለማስወገድና የጋራ ብልጽግናን ለማስፈን ነው ። ለዚህ እውን መሆን ደግሞ የገበሬው ተመቻችቶ መገኘት አማራጭ የለውም ። በዚህ መሠረት በመንደር መደራጀቱ አንዱ መሠረታዊ ሁኔታ በመሆኑ የየአካባቢውን ልዩ ባሕርይ በማገናዘብ ደረጃ በደረጃ በሥራ መተርጎሙ ተገቢ ነው ።

# የግርጌ ማስታወሻ


1. *The Great Soviet Encyclopedia,* Macmilan, Inc. New York and London, 1974, p. 665.
2. JAN. O.M. Broek & John, W. WEBB; *A Geography of Mankind,* third edition, Mc. Grawhill International Book Company, 1976, p. 203.
3. *The New Encyclopedia Britanica,* Inc. Helen Hemingway Bento, Publishers, 1973-74, Vol. 4, p. 269.
4. *Ibid.,* Vol. 16, p. 28.
5. *The Great Soviet Encyclopedia,* Vol. 23, pp. 212-213.
6. *Ibid.,* p. 213.

የአሥር ዓመት ልማት መሪ ዕቅድ /000 ረቂቅ/፤ጥራዝ አንድ፣የብሔራዊ አብዮታዊ ምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፤ መጋቢት 1975 ፣ ቁጥር 2 ፤ ገጽ 71 ።

8. Georgi Galperin, Ethiopia; *Population Resources Economy,* *Progrcss,* 1981, p. 141.

የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ፣ ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር 3 ገጽ 71 ።

10. Agricultural Sample Survey, Ministry of Agriculture 1974/75, Vol. 1, p. 59.
11. Georgi Galperin, Ethiopia: *Population Resources Economy,* Progress Publishers, 1981, p. 153.
12. *The Role of the State in Socio-economic Reforms in Developing Countries,* Progress Publishers, 1976, p. 133.

ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና . . . / ከላይ የተጠቀሰው / ገጽ 73 ።

14. Georgi Galperin, *op. cit.*
15. *The Role of the State in Socio-economic Reforms in Developing Countries,* Progress Publishers, 1976, p. 133.
16. Georgi Galperin, *op. cit,* p. 198.
17. *The Study of Nomadic Areas for Settlement:* Study Report I, United Nations Development Programme, Addis Ababa, 1983, p. 7.
18. Georgi Galperin, *op. cit.,* p. 199.
19. V.I. Lenin, *Collected Works,* Volume 4, p. 431.
20. William W. Murdich, *op. cit.,* p. 194.
21. የሕዝብ ማስፈር ባለስልጣን በስድስት ሀገሮች ካደረገው የጥናት ሪፖርት የተወሰደ ፤ አ.ኤ.አ. 1979፤ ገፅ 15 17 ።


Digitized by Google

22. *Leninism and the Agrarian Peasant Question,* Progress Publishers, Vol. 1, p. 225.

23. Kim Il Sung, *Selected Works* Volume 4, p. 217

24. K. Marx and F. Engels: *Selected Works,* Vol. 2, Moscow, 1973, p. 288.

25. V.I. Lenin, *Colected Works,* Vol. 30, p. 112.

26. Land Reform, Land Settlement and Cooperatives, Food and Agricultural Organization of the United Nations, No. 1/2; 1981, p. 45-46.

27. African Rural Development Study..., An Analysis of Programmes and Projects in Africa, Unalele, Washington, 1974, Appendix 1, p. 30.

28. Michael Von Freyhold, Ujama Villages in Tanzania, Analysis of a Social Experiment, Monthly Review Press, London, 1979, pp. 157-58.

29. K. Marx and F. Engels, Soch; 2nd ed. Vol. 8, p. 207: *The Great Soviet Encyclopedia,* Vol. 13, p. 603.



Digitized by Google

# በታሪክ ሂደት ውስጥ የሕዝብና የግለሰብ ሚና

ጠና ደዎ

በአገሮች ታሪክ ውስጥ ሕዝባቸውን
ከውጭ ወረራ የተከላከሉና ጀብዱ የፈጸሙ
የፖለቲካ መሪዎች ፥ በምርምር ፥ በጥናትና
በፈጠራ ሥራዎች አዳዲስ ውጤቶችን ያበ
ረከቱ ዝነኛ ግለሰቦች አሉ ። በዚህም ምክ
ንያት ግለሰቦች ብቸኛ ታሪክ ሠሪዎችና ባለ
ቤቶች መስለው ይታያሉ ። ይሁን እንጂ እነ
ዚህ ዕውቅ ግለሰቦች በመጀመሪያ ደረጃ
መፈጠርና መኖር ፥ ከዚያም ያላቸውን ልዩ
ተሰጥኦና ችሎታ እውን ማድረግ የሚች
ሉት በሕዝብ ውስጥ ነው ። ከዚህ አንፃር
ስናየው ደግሞ የግለሰቦቹ ህልውናና ኃይል
ራሱ የሚመሠረተው በዚሁ ሕዝብ ህልው
ናና ዕድገት ላይ ስለሆነ ኀታሪክ ሠሪና ባለ
ቤት ሕዝብ ሆኖ ይታያል ። ስለዚህ በታሪክ
ሂደት ውስጥ የየትኛው ሚና ወሳኝ ነው ?
ወይስ ያንዱ ሚና ከሌላው ያላነሰ ነው ?
በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነትስ እንዴት
ይገለጻል ?

በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ
ሕዝብ ታሪክን ለመሥራት ምንም ዓይ
ነት ድርሻ እንደሌለው ተደርጎ ቀርቧል ።[1]
በፊውዳል ሥርዓተ ማኅበርም ታሪክ
በንጉሦች ፥ በጦር መሪዎችና በመሳሰሉት
ግለሰቦች አማካይነት የሚከናወን የአምላክ
ፈቃድ ውጤት ነው ይባል ነበር ።

የመሬት ከበርቴው ሥርዓት እየወደቀና
ቡርዣው የካፒታሊስቱ ሥርዓት እየተተካ
ሲሄድም የሕዝብን ሚና ዝቅ የማድረጉ
ተግባር አልተገታም ። በ15ኛው ም ዕ ት
ዓመት መጨረሻና በ16ኛው ምዕት ዓመት
መባቻ ላይ ታዋቂ ከነበሩት የቡርዧ ርዕ
ዮተ ዓለም አራማጆች አንዱ ኢጣሊያዊው
የፖለቲካ ጸሐፊ ማኪያቬሊ ታሪክ ለቁሳዊ
ፍላጎትና ሥልጣን የሚደረግ የጥቂት የፖ
ለቲካ ኃይሎች ትግል ውጤት ነው የሚል
ትንተና አቅርቧል።በ18ኛው ምዕት ዓመት
መገባደጃ ላይ ቶማስ ካርሊሌ የተባለው
እንግሊዛዊ ጸሐፊም «ሰው በዚህ ዓ ለ ም
ውስጥ ያከናወነው ታሪክ ሁሉ ከመሠረቱ
. . . የታላላቅ ሰዎች ታሪክ ነው»[2] ብሏል።



Digitized by Google

በ19ኛው ምዕት ዓመት በኖረው ፍሬዴሪሽ ቪልሄልም ኒቸ በተባለው ጀርመናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ አመለካከት ሕዝብ በጥቂት ብልህ ግለሰቦች የታቀደውን እንጂ ራሱ አስቦና ዐቅዶ የሚሠራ አይደለም ። [3] ይህም ማለት ሕዝብ ግለሰቦች በሚፈልጉት አቅጣጫ ለራሳቸው ግላዊ ግብና ፍላጎት ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ ከመታዘዝ ውጭ ምንም ድርሻ የለውም ።

ባለንበት ዘመንም የቡርዧ ምሁራን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ስለሕዝብና ግለሰብ ሚና የሚያቀርበውን ሳይንሳዊ ትንተና ለመቃወም በሚያደርጉት ጥረት የግለሰቦችን ሚና የሚያጋንኑ ንድፈሐሳቦች እያቀረቡ ነው።ለዚህም « የኅብረተሰብ ቁንጮ » (the theory of elite) ንድፈሐሳብ አራማጆች የመጀመሪያና ዋነኛ ተጠቃሾች ናቸው ማለት ይቻላል።በእነርሱ አመለካከት ታሪክ የሚሠራው በኅብረተሰቡ የላይኛውና ከፍተኛው ክፍል (ቁንጮ) ብቻ ነው።ዋልተር ሊፕማን እንደጻፈው የሕዝብ ተግባር ቀረጥ መክፈል ፣ መሥራት ፣ ወደጦርነት መሄድና አስፈላጊም ሲሆን ለመንግሥቱ ፍላጎት (ጥቅም) እራስን መሠዋት ብቻ ነው ። [5]

የሳይንስና ቴክኖሎጂ አብዮት ባስገኘው ዕድገት አንፃር ይኸው ንድፈሐሳብ ወደ ቴክኖክራሲያዊ ቁንጮ ንድፈ ሐሳብ (the theory of technocratic elite) [6] ተሸጋግሯል ። ይህ ንድፈሐሳብ በአንድ በኩል ሕዝብ ምንም ዓይነት ታሪካዊ ድርሻ እንደሌለው ሲገልጽ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መደባዊ ባሕርይ የሌላቸው (ከመደብ ውጭ የቆሙ) መሪዎች ሕዝብን ማስተዳደር አለባቸው ይላል ።

ይሁን እንጂ ጥንትም ሆነ ዛሬ ታሪክን የግለሰቦች ሥራ ብቻ አድርጎ ማቅረብን የሚቃወሙ ምሁራን ነበሩ፤አሉም። ለምሳሌ በ18ኛው ምዕት ዓመት ከኖሩት የፈረንሳይ ታዋቂ ምሁራን መካከል አንዱ ኮንደርሴት የሚከተለውን ብሏል ።

እስካሁን ድረስ ልክ እንደፍልስፍና ወይም ሳይንስ ታሪክ ፣ የፖለቲካ ታሪክም የጥቂት ግለሰቦች ታሪክ ብቻ ሆኗል ። በእውነቱ የሰውን ልጅ ዘር የሚገነቡ ፣ ባብዛኛው በራሳቸው ሥራ የሚተዳደሩ ብዙኀን ቤተሰቦች ተረስተዋል ። የሌላው ቀርቶ የሕዝብ ሙያተኛነትን ሥራቸው ያደረጉ ፣ ለራሳቸው ሳይሆን ለኅብረተሰቡ የሚሠሩ ፣ በማስተማር ፣ በማስተዳደር ፣ በመከላከል ፣ በማዳንና በሌሎችም ተግባር ላይ የተሰማሩ ሁሉ ተረስተዋል ። [7]

ኮንደርሴት ሰፊው ሕዝብ ታሪክ ሠሪ ነው ከሚል ሳይንሳዊ መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም እርሱም ሆነ ሌሎች የ18ኛው ምዕት ዓመት ምሁራን በታሪክ ውስጥ በሕዝብና በግለሰብ ሚናዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በትክክል መረዳት አልቻሉም ። ከታሪክ መገንዘብ እንደሚቻለው በየትኛውም መደባዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ሕዝብ ያለታዋቂ ግለሰቦች አስተዋጽኦ ፣ ያለነሱ ጠቃሚ ሚና (ለምሳሌ በአመራር ተግባር) ታሪክ የሠራበት ወቅት የለም ። በታሪክ ውስጥ የግለሰቦችን ጠቃሚ ሚና መካድ ሥርዓት የለሽ ከንቱ መተራመስን ወይም ሥርዓተ አልበኝነትን መጋበዝና በማዕከላዊ አሠራር ሥር ሊገኝ የሚችልን ውጤት ማጣት ነው ።

በአጠቃላይ የቅድመ ማርክሳውያን የታሪክ ሂደት ተንታኞችም ሆኑ የበስተኋላኞች ቡርዧ ምሁራን ግለሰብና ሰፊው ሕዝብ በታሪክ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና በትክክል አልገለጹትም ። ይህም በሁለት ገጽታዎች ሊታይ ይችላል ። አንደኛው ገጽታ የሰፊውን ሕዝብ ሚና የሚክድ ወይም ዝቅ የሚያደርግ ነው ። ሁለተኛው የግለሰቦችን ሚና የማይገነዘብ ነው ። ሁለቱ ገጽታዎች የተለያዩ ቢሆኑም የሕዝብንና የግለሰብን ውስጣዊ ግንኙነት በትክክል ለማቅረብ ባለመቻላቸው አንድነት አላቸው ።



Digitized by Google

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈሐሳብ የሰፊው ሕዝብና የግለሰብ ሚናዎች ዲያሌክቲካዊ ተንኙነት ያላቸው መሆኑን ይገነዘባል ። ያንዱ ሚና ካለሌላው እውን ሊሆን አይችልም ። ነገር ግን በታሪክ ሂደት ውስጥ በአጠቃላይ ሲታይ የሰፊው ሕዝብ ሚና ወሳኝ ኃይል ነው ። ይሁን እንጂ የግለሰብ ሚናም በሂደቱ ውስጥ እንደተጨባጭ ሁኔታው ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል ። ይህን በሚገባ ለመረዳት ሕዝብ ማለት ምን እንደሆነ ዘርዘር አድርገን ለመመልከት እንሞክር ።

ሕዝብ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ አንዱ ትርጉሙ በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር የግለሰቦችን ጠቅላላ ድምር ወይም ስብስብ የሚያመለክት ነው ። በአንድ ሀገር ፣ ሠፈር፣ ወይም ብሔር (ብሔረሰብ) ውስጥ ያለ ጠቅላላ የግለሰቦች ድምር ማለት ይቻላል ። ሕዝብ የሚለው ቃል ይህን ትርጉም የሚይዘው በተራ አባባል እንጂ በሳይንሳዊ ፍቺው አይደለም ።

በሳይንሳዊ ፍቺው ሕዝብ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ በተወሰነ የታሪክ ወቅት ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በሙሉ ፣ እንዲሁም በወቅቱ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አባል ለሆኑበት ኅብረተሰብ ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ መደቦችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው ። በዚህ ትርጉም መሠረት ሕዝብ በታሪክ ሂደት ውስጥ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያቅፍና በዚህም ምክንያት ታሪካዊ ፍቺ ያለው ነው ።

በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የግል ማምረቻ መሣሪያዎች አልነበሩም ። በተለያዩ አካባቢዎች በሚኖሩት ማኅበረሰቦች ወይም ጐሣዎች መካከል ልዩነት ቢኖርም ባንድ ማኅበረሰብ ወይም ጐሣ አባላት መካከል በጥቅም ፣ በፍላጎትና በማኅበራዊ አቋም ጉልህ ልዩነት አልነበረም ። ስለዚህ ሕዝብ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ማኅበረሰቦች (ጐሣዎች) ውስጥ በጋራ ኃይል ለጋራ ህልውና የሚታገሉትንና የሚሠሩትን አባላት ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ።

ብዝበዛ በሠፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ግን ሕዝብ ማለት መላውን የኅብረተሰብ አባላት የሚያጠቃልል ሳይሆን ለማኅበራዊ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብዙኃን ክፍሎችን የሚያቅፍ ነው ።

*በመደብ በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ሕዝብ የምንለው ቁሳዊ ሀብት የሚፈጥር ነው ። የዕድገት ተጻራሪ የሆኑትን የኅብረተሰቡን ቁንጮና አድሐሪ መደቦችን የሚቃወም ፣ ብዙኃኑን የሚያቀፍና የኅብረተሰቡን ዕድገት የሚያፋጥኑ ማኅበራዊ ቡድኖችን ሁሉ የሚያጠቃልልና አንዳንድ ጊዜም ከሠራተኛው መደብ ያልሆነውን ብሔራዊ ቡርዧውን የሚጨምር ነው ።*[8]

በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሕዝብ ማለት የሥርዓቱ የብዝበዛ ቀንበር ተሸካሚ የሆነው ባሪያ ፣ «ነፃ ዜጎች» እንዲሁም ለኅብረተሰቡ ዕድገትና ለውጥ ጠቃሚ ድርሻ የሚያበረክቱ ቡድኖችና የኅብረተሰቡ ክፍሎች ናቸው ። በመሬት ከበርቴው ፣ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ተበዝባዡ ጭሰኛ፣ በራሳቸው ወዝና ጉልበት የሚተዳደሩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች፤ በዚሁ ሥርዓት ውስጥ በመወለድ እያደጉ የመጡት የቡርዧውና የወዛደሩ መደብ የሥርዓቱን ሕዝብ የሚገነቡ አካላት ናቸው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር በሕዝብ ውስጥ የሚታቀፉ ደግሞ የወዛደሩ መደብ ፣ በራሳቸው ጉልበት የሚተዳደሩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ፣ ለሥርዓቱ መለወጥ አስፈላጊውን ኤኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ተግባሮች የሚያከናውኑ ማኅበራዊ ቡድኖችና ኃይሎች ናቸው ።

በታዳጊ ሀገሮች ወይም በአሁኑ ወቅት በቅድመ ካፒታሊስት ዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ኅብረተሰቦች ውስጥ ሕዝብ በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉት



Digitized by Google

ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም ለኅብረተሰቡ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የማኅብረሰብ አባላት ናቸው ። እንዲህ ባሉት ኅብረተሰቦች ውስጥ በሕዝብ ውስጥ የሚታቀፉ ሠራተኞች ፣ ገበሬዎች በልዩ ልዩ መንገድ በራሳቸው ጉልበት የሚተዳደሩ የኅብረተሰቡ ክፍሎችና አንዳንዴም ብሔራዊ ቡርዧው ናቸው ።

በየሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ የሕዝብ ዋነኛ አካል የየሥርዓቱ ተበዝባዥ መደቦች ናቸው ። የሕዝብ ቁጥር ከበዝባዥ መደብ አባላት ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ብዙ ነው ። ሕዝብ የየሥርዓተ ማኅበሩ ኅብረተሰብ የሚኖርበትንና የሚያድግበትን ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶች የሚፈጥር ፣ ያለው አርጌ ሥርዓት በአዲሱ እንዲተካ አስፈላጊውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት የሚጥል፣ በመደብ ትግል ውስጥ ወሳኝ ሚና በመጫወት አርጌውን አፍርሶ በምትኩ አዲስ ሥርዓተ ማኅበርን ማስገኘት የሚችል ኃይል ነው ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ያለው ሕዝብ ከላይ በተጠቀሱት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ከነበረውና ካለው ሕዝብ በዓይነቱ የተለየ ነው ። በዚህ ሥርዓት የሕዝቡ ዋንኛ የተገነባው በሠራተኛው ፣ በገበሬው ፣ በምሁራንና በሌሎች ሠርቶ አደሮች ነው ። በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ የማምረቻ መሣሪያ በግል የተያዘ ሳይሆን ፡ የሕዝብ የጋራ ሀብት በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው የችሎታውን ያህል ለኅብረተሰቡ ሠርቶ የሥራውን ያህል ያገኛል ። ሁሉም ላንዱ አንዱም ለሁሉም የሚሠራ ስለሆነ የጥቅም ግጭትና ትግል የለም ። በዚህም ምክንያት የምርት ግንኙነት እንቅስቃሴ በማያቋርጥ ሂደት ከሚያድገው የምርት ኃይል ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ነው ። የእያንዳንዱም ሰው እንቅስቃሴ በተናጠል ፣ የኅብረተሰቡ ባጠቃላይ ከኅብረተሰቡ ታሪካዊ እንቅስቃሴ ጋር የሚጣጣም ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉንም ማኅበራዊ አካላትና አባላት የሚያጠቃልል ነው ።

የሶሻሊስት ሥርዓት ሕዝብ ሚና ሶሻሊስት ባልሆኑ ኅብረተሰቦች ውስጥ ካለው ሕዝብ ሚና የሰፋና በዓይነቱ ልዩ የሆነ ነው ። ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሕዝብ ታሪክ ሠሪነትና ባለቤትነት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠ በመሆኑ በማናቸውም ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መስኮች ውስጥ የራሱን ዕድገት (ዕድል) በራሱ የመወሰን መብቱን ጨብጧል ። ይህ አንደኛው ምክንያት ነው ።

ሁለተኛው ምክንያት ሕዝቡ ራሱ በታሪክ ሂደት ውስጥ ያለውን የተሳትፎ መጠንና ዓይነት የሚያመለክት ነው ። ሶሻሊስት ባልሆኑ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ሕዝብ ታሪክን የሚሠራው በአመዛኙ ያልነቃ ማኅበራዊ ኃይል በመሆን ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ግን የራሱን ወሳኝ ሚና ከማረጋገጡም በላይ የዕድገቱን አቅጣጫ የሚገዛውን ሕግ የተገነዘበ ሕዝብ ነው ። የሕዝብን ታሪክ ሠሪነት በበለጠ ለመረዳት በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በባህል መስኮች የሚደረገውን ወሳኝ አስተዋጽኦ ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክር ።

## በኢኮኖሚ ዕድገት የሕዝብ ሚና

ሰፊው ሕዝብ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ኃይል ነው ። በየትኛውም ጊዜና ስልተምርት ውስጥ የቁሳዊ ሀብት ፈጣሪ ነው ። በተለይም በመደብ በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሕዝብ ጉልህ ድርሻ አምራችነት ሲሆን የውጤት ተጠቃሚነቱ ግን እጅግ ውሱን ነው ።

ማንኛውም የኅብረተሰብ ዓይነት ህልውናው ሊጠበቅና ሊያድግ የሚችለው የምግብ ፣ የመጠለያና የመሳሰሉትን መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት ሲችል ብቻ ነው ። እነኝህን ፍላጎቶች የሚያረኩ ነገሮች ሁሉ ሊገኙ የሚችሉት በሰው የማያቋርጥ ሥራ



Digitized by Google

ነው ። ምርት የኅብረተሰብ ሀልውና መሠ
ረትና ለበለጠ ዕድገቱም ዋስትና ሲሆን ፣
እንደየኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ የምርት
ተግባር አከናዋኙ ክፍል ማለትም አምራቹ
ዋነኛና ተቀዳሚ ታሪክ ሠሪ ነው ።

ሰፊው ሕዝብ ላለበት ኅብረተሰብ የም
ግብ ቁሳቁሶችን ያመርታል ። ለምግብነት፣
ለማምረቻ መሣሪያነትና ለልዩ ልዩ ማኅበ
ራዊ አገልግሎት እንስሳትን ያረባል ። የመ
ኖሪያ ፣ የልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጭና የማ
ምረቻ ቤቶችን ፣ ሕንፃዎችን ፣ ድልድዮች
ንና መንገዶችን ይሠራል ። ተፈጥሮአዊ አካ
ባቢ ውን በበለጠ ለመቆጣጠርና ለመግራት
የሚያስችሉ የተሻሻሉ መሣሪያዎችንና ኃይ
ሎችን ያመርታል ። ለመገናኛና ለመጓጓዣ
የሚሆኑ ነገሮችንና ኃይሎችን ይፈጥራል።
በጠቅላላው ሕዝብ ጊዜያዊ የፍጆታ ምርቶ
ችን የሚያመርት ፣ ለበለጠ ዕድገት የሚ
ረዱ የምርት መገልገያ መሣሪያዎችንና የሀ
ብት ከምችትን የሚፈጥርና በዚሁ አንፃር
በአንድ በኩል ምርታማነቱን እያዳበረ ሕይ
ወቱን ወደተሻለ የዕድገት ደረጃ የሚያሸ
ጋግር ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ደረጃ በደረጃ
በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን እየተቀዳጀ የሚ
ሄድ ኃይል ነው ። ባጭሩ ሕዝብ የየትኛ
ውም ሥርዓተ ማኅበር የምርት ኃይል ትል
ቁና ወሳኝ ኃይል ነው ።

በእርግጥ ሕዝብ ቁሳዊ ሀብቶችን ማም
ረት ብቻ ሳይሆን ሰውን ራሱን ይለውጣል።
ባንድ በኩል ያልነበረውን ሰው በመፍጠር
ያለማቋረጥ ተተኪ ትውልዶችን ያዘጋጃል።
በሌላ በኩል ደግሞ ያለው ሰው ራሱ በአዳ
ዲስ ፍላጎቶች የተነካ በልምዱ ፣ በአስተሳ
ሰቡ ፣ በአኗኗሩና በግንኙነቱ ሁሉ እንዲለ
ወጥ ያደርጋል ። በመሆኑም ሕዝብ በታሪክ
ሂደት ውስጥ ላለው ትውልድ የሚያስፈል
ጉትን ማናቸውንም ቁሳዊ ሀብት ከመፍ
ጠር ውጭም ለተተኪው ትውልድ አስፈ
ላጊውን ቅድመ ሁኔታ የሚያመቻች ወይም
መሠረት የሚጥል ነው ። ለዛሬ ብቻ ሳይ
ሆን ለነገም ጭምር የሚሠራ ነው ። አዲሱ
ትውልድ ራሱ ታሪኩን መሥራት የሚጀ
ምረው ከቀድሞው ትውልድ ከተላለፈለት
ቁሳዊ ሀብትና የልምድ ክምችት በመነሣት
ነው ።

ይሁን እንጂ ሕዝብ ምርቱን የሚያመር
ተውና ለተተኪው አዲስ ትውልድ የሚያ
ስተላልፈውን ነገር በፍላጎቱ የሚወስን አይ
ደለም ። ራሱ የሚያመርትበት ሁኔታ ፣ የም
ርት ሥርጭትና ክፍፍሉ ሁሉ እንደ ዕድገት
ደረጃው ነባራዊ ሕግና እንደሥርዓተ ማኅ
በሩ ግንኙነት የሚለያይ ነው ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ስልተ ምርት ውስጥ
ማንኛውም የኅብረተሰቡ አባል ዓቅሙ በፈ
ቀደለት መሠረት ያመርታል ። የተመረተ
ውም በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ
ጥቅም ላይ ይውላል ። በዚህም ሥርዓት
ውስጥ በኅብረተሰቡ ዕድገት ዝቅተኛነት
የተነሣ አንዱ በሌሎቹ ላይ ጥገኛ የመሆን
ሁኔታ ከፍተኛ ነበር ። ይሁን እንጂ በማም
ረት ሂደት ውስጥ ከተፈጥሮ ሕጎች እየተዋ
ወቀ ምርታማነቱን አሳደገ ። ትርፍ ማምረ
ትም ሲጀመር ከዚሁ ጋር የማኅበራዊ ሥራ
ክፍፍልና የግል ማምረቻ መሣሪያዎች ተከ
ሰቱ ። በኢኮኖሚ ራሱን የቻለ ቤተሰብም
ተፈጠረ ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብን በተካው
የባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት ውስጥም ቢሆን
የሕዝብ አምራችነትና ሀብት ፈጣሪነት በይ
በልጥ ዳበረ እንጂ አላከተመም ።በዚህ ሥር
ዓተ ማኅበር ውስጥ ባሪያውና በጉልበቱ
የሚተዳደረው ድሀው የኅብረተሰብ ክፍል
በማኅበራዊ ሥራ ክፍፍል ውስጥ ያላቸው
ድርሻ አምራችነት ነው ። በዚህ ምክንያት
ሥርዓተ ማኅበሩ የተመሠረተበትንና የሚ
ንቀሳቀስበትን ሀብት የሚፈጥር ይኸው
ብዙኃኑ ሕዝብ ነው ። ዛሬ በተለያዩ ሀገሮች
ውስጥ በታሪክ ቅርስነትና መረጃነት ተመ
ዝግበው የሚገኙ ልዩ ልዩ ጥንታዊ ግን
ቦች ፣ ሐውልቶች ፣ ገዳሞች፣ የአምልኮ ቤቶች፣
ሕንፃዎች ፣ ቤተ መንግሥታትና የመሳሰሉት



Digitized by Google

በሙሉ በባሪያውና «ነፃ ነዋሪ» በተባለው
ድሃ ሕዝብ የተሠሩ ናቸው ።

ይሁን እንጂ በግል ማምረቻ መሣሪያ
ባለቤትነት የተነጣ በቀጥታ አምራች የሆ
ነው ሕዝብ የምርቱ ባለቤት ፣ ተቆጣጣሪና
አሳዳሪ መሆን አልቻለም ። እንዲሁም አም
ራች ያልሆነውና ከሰፊው ሕዝብ የማይመ
ደበው የባሪያ አሳዳሪ ወይም የሥርዓቱ ገዥ
መደብ ሕዝቡ ባመረተው ላይ የባለቤትነት
መብቱን ከማረጋገጡም በላይ ባሪያውን
ራሱን እንደግል ንብረት የሚያስተዳድርበት
ሥርዓት ነበር ። አምራቹ ባሪያ የጌታው
ንብረት በመሆኑ በጌታው የተወሰነለትን
የምግብ ድርሻ ብቻ ያገኛል ።

በፊውዳል ሥርዓተ ማኅበርም ው ስ ጥ
ሥርዓቱ የተመሠረተበትን ቁሳዊ ሀ ብ ት
የሚፈጥር ሕዝብ ነው ። የዚህ ሥርዓት ሕዝብ
ጭሰኞች ፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችና በሥ
ርዓቱ ውስጥ ያቆጠቆጡት የካፒታሊስት
ሥርዓተ ማኅበር መደቦች ናቸው ። በፊው
ዳል ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የምርት ክፍ
ፍሉና ሥርጭቱ ከአምራቹ ሕዝብ ፍላጎ
ትና ውሳኔ ውጭ በጥቂት የገዥ መደብ
አባላት የሚከናወን ነው ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥም
የሕዝብ አምራችነትና ሀብት ፈጣሪነት
ጉልቶ የሚታይ ነው ። ከትናንሽ ነገሮች
ጀምሮ እስከ ትላልቅ ፣ ውስብስብና እጅግ
ዘመናዊ ግኝቶች ድረስ ያሉት በሙሉ የሕ
ዝብ ሥራ ውጤቶች ናቸው ። ዛሬ በካፒታ
ሊስቱ ዓለም ውስጥ ያለው የተከማቸ የሀ
ብት ዕድገት የዕልፍ አዕላፍ ሕዝቦች ሥራ
ውጤት ነው ።

ነገር ግን ይህ የተፈጠረው ግዙፍ ሀብት
ለአምራቹ ወይም ለሠራተኛው ሕዝብ የተ
ሟላ ፍላጎት ማርኪያነት አይውልም ። በጠ
ቅላላው ሠራተኛው ሕዝብ በራሱ ጉልበት
ካፒታሊስቱን የከፍተኛ ሀብት ባለቤት አድ
ርጎ ፣ ራሱ ግን ደሀና ችግረኛ ወዛደር ሆኗል።

ማርክስ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የወ
ዛደሩን ሥራ ውጤት አስመልክቶ ሲጽፍ
«ሥራ በእርግጥ ለሀብታም አስደናቂ ነገር
ችን ፣ ነገር ግን ለሠራተኛው ድኅነትን ፣ ለሀ
ብታም ቤተ መንግሥትን ፣ ነገር ግን ለሠራ
ተኛው ደሳሳ ጎጆን ፣ ለሀብታም ቁንጅናን
ነገር ግን ለሠራተኛው አስቀያሚነትን ያስ
ገኛል ። »9 ብሏል ። ምክንያቱም የምርቱ
ከፍተኛ ተጠቃሚ የሚደራጀት ፣
የማከፋፈል ፣ የማስተዳደርና የመቆጣጠር
ኃይል ያለው የማምረቻ መሣሪያ ባለቤት
የሆነው ካፒታሊስቱ ነው ። ስለዚህ በካፒ
ታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበርም ሰፊው
ሕዝብ በሥርዓተ ማኅበሩ የኢኮኖሚ ዕድ
ገት ውስጥ ወሳኝ ሚና ቢጫወትም ዕድገቱ
ግን አምራች ላልሆነው የካፒታሊስቱ
መደብ ጥቅም የሚውል ነው ።

በጠቅላላው ከላይ በተጠቀሱት አራት
ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ በተደረጉት ኢኮ
ኖሚያዊ የዕድገት ሂደቶች ሰፊው
ሕዝብ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል ። በማንኛ
ውም ሥርዓተ ማኅበር ለሚደረጉት ማና
ቸውም ማኅበራዊና ታሪካዊ እንቅስቃሴ
ዎች ዋናው መሠረት ኢኮኖሚ መሆኑ ይታ
ወቃል ። ይህን መሠረት የሚፈጥረውና የሚ
ያንቀሳቅሰው ደግሞ ሰፊው ሕዝብ በመሆኑ
ይህ ሕዝብ በኅብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ
ያለውን ወሳኝ ሚና ማረጋገጥ የሚያስቸ
ግር አይሆንም ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብም ውስጥ የሰፊው
ሕዝብ አምራችነት ጉልቶ ይወጣል ። ኅብ
ረተሰብ እስካለ ድረስ ማምረት የግድ ይና
ራል ። ይህ ሁለንተናዊ ሐቅ ነው ። ነገር ግን
በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የምርት እንቅ
ቃሴ ቀደም ሲል በነበሩት ሥርዓተ ማኅበ
ራት ውስጥ ከነበረው እንቅስቃሴ ጋር ሲነ
ፃፀር ከፍተኛና የተሟላ ነው ። ይህም ያለ
ምክንያት ሳይሆን በሶሻሊስት ኅብረተሰብ
ውስጥ የማምረቻ መሣሪያዎች የሕዝብ በመ
ሆናቸው ነው ። በዚህም የተነጣ በማምረ



Digitized by Google

ትና በምርት ክፍፍሉ መካከል ቅራኔ የለም። ይህም የሚሆነው ሠራተኛው መደብ የዓቅሙን ያህል ሠርቶ የሥራውን ያህል ስለሚያገኝ ብቻ ሳይሆን ፣ የተመረተውን ለማከፋፈል ፣ ለማሠራጨት ፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ስለሚያደርግም ነው ። በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሠራተኛው የገዥ መደብ አባል የሆኑ ጥቂት የሥራ መሪዎች ከመደባቸው ጥቅም አኳያ የሚወስኑትን መፈጸምና ምንዳ ማግኘትን አስወግዶ በእርሱ ተሳትፎና በእራሱ ለጋራ ጥቅምና ዕድገት ይጠቅመኛል ብሎ የሚወስነውን ተግባራዊ ያደርጋል ። ምርታማነቱም ከቅድመ ሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበራት ጋር ሲነፃፀር እጅግ የላቀ ስለሆነ ዕድገቱ ፈጣን ይሆናል ።

## በፖለቲካው መስክ የሕዝብ ሚና

ፖለቲካ በጥቅል መልኩ ሲታይ የመንግሥትን ሥልጣን ለማኖር ፣ ለመጠቀም ወይም ለመለወጥና ለመያዝ በመደቦች ፣ በተለያዩ መንግሥታትና ማኅበራዊ ቡድኖች መካከል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።[10]

መደቦች ባሉባቸው ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ የመደብ ትግል መኖር የማያጠያይቅ ነው ። የመደብ ትግሉ በመሠረቱ የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይል ግጭት መገለጫ ነው ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሕዝብ የምርት ኃይል ወሳኝ አካል ነው ። ያለውን ሥርዓት በማስወገድ በዕድገቱና በግንኙነቱ የተሻለ ማኅበራዊ ሥርዓት ለማምጣት የሚደረገው የሕዝብ ትግል የምርት ኃይሉ ተራማጅ ባሕርያት መገለጫ ሲሆን ካለው የመደብ ሥርዓት የተሻለ እንደማይኖር በማወጅ ይህንኑ ዘለዓለማዊ ለማድረግ የሚታገለው የሥርዓቱ ገዥ መደብ ( በዝባዥ መደብ) የምርት ግንኙነቱን ኅታች ባሕርይ የሚወክል ነው ።

ይህ ትግል እንደየሥርዓተ ማኅበሩ ዕድገት ደረጃ፣ እንደመደቦቹ የግንኙነት ባሕርይ የሚታይ ቢሆንም ባጠቃላይ መልኩ እጅግ ከተበታተነ ፣ በጣም ዝቅተኛና ግለሰባዊ ከሆነ ተራ ተቃውሞ በመነሣት ግልጽ ወይም ይፋ በሆነ ዓመፅ ከአዲሱ የምርት ግንኙነት ፍላጎቱ ጋር የሚጣጣም መደብ የመንግሥት ሥልጣን እስኪጨብጥ ድረስ የሚያድግ ውስብስብ እንቅስቃሴ ነው ። ይህን ረጅምና ውስብስብ ትግል እንደዕድገቱ ባሕርይ ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል ። አንደኛው «የሰላማዊ ጊዜ» ትግል ሲሆን ፣ ሌላኛው በማኅበራዊ አብዮት ጊዜ የሚካሄድ ትግል ነው ።

## የ«ሰላማዊ ጊዜ» ትግል [11]

የሰው በሰው መበዝበዝ በሰፈነበት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የምርት ኃይልና የምርት ግንኙነት ከሞላ ጎደል ተጣጥመው በሚጓዙበት ወቅት ሕዝቡ በፖለቲካው እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሚና እምብዛም ጉልቶ አይታይም ። በዚህ ወቅት ጉልቶና ደምቆ የሚታየው የሥርዓቱ ገዥ መደብ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው ። ይህ መደብ ሕዝቡን በመምራትና በመቆጣጠር ፣ ምርቱንም በማደራጀትና በማስተዳደር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። ሕዝብ ግን ከአምራችነት ሌላ በፖለቲካው እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ የለውም ። ይህ ወቅት የሥርዓተ ማኅበሩ ቅራኔ ያልዳበረበት ፣ ቀደም ሲል ከነበረው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የተሻለ የምርት አደረጃጀት ፣ ማኅበራዊ ግንኙነትና አሠራር የሚታይበት ወቅት ነው ። ወይም የምርት ግንኙነቱ ከምርት ኃይሎች ጋር ከሞላ ጎደል የሚጣጣምበት ወይም ያለመጣጣሙ በፖለቲካው መስክ ጉልቶ የማይታይበት ወቅት ነው ።

ነገር ግን በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ ኅብረተሰብ ታሪካዊ የዕድገት ሂደት ውስጥ በአንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ የሥርዓቱ የምርት ግንኙነት ከምርት ኃይሉ ጋር ዘልቆ መሄድ ይሳነዋል ። በሁለቱ መካከል በሚፈጠረው ግጭት መገለጫነት የመደብ



Digitized by Google

ትግሉ እየከረረ ይመጣል ። የትግሉ መነሻ በጣም ዝቅተኛና ቀላል ከሆነ ደረጃ ነው ። በተበታተነ ወይም በቡድን ሆኖ ግብታዊነት የሚያጠቃው ይሆናል ። በዚህ ወቅት የሚኖረው ትግል ብልጭ ድርግም የሚል ባሕርይ አለው ። በሥርዓቱ ጭካኔና ብዝበዛ በመማረር ባንድ ጊዜ የሚነግ ተቃውሞና ጠብ ሥር የሰደደ አይሆንም ። ሕዝቡ ራሱ የእምቢታና የተቃውሞ ምልክት ማሳየቱ እንጂ መሪና ተባባሪ መደቦችንና ኃይሉችን አስተባብሮ የተነሣበት ወቅት ስላይደለ በቀላሉ በሥርዓቱ ገዥ መደብ የመጨቆኛ ተቋሞች ይታፈናል ።

በእርግጥ ይህ ግን የመደብ ትግሉን ልምድና እንቅስቃሴ የሚያሰፋው እንጂ የሚያጠፋው አይደለም ። ምክንያቱም ሥርዓቱ የብዝበዛ ሰንሰለቱንና መረቡን ዘርግቶ እስከቆየ ድረስ የትግሉ መካረር የማያጠያይቅ ነው ። በሂደቱም ውስጥ የመደቦች ኃይል ሚዛን ቀስ በቀስ እየተለወጠ ይሄዳል ። የገዥው መደብ ኃይል ቀስ በቀስ እየተዳከመ በሰፊው ሕዝብ ኃያልነት ይተካል ።

በተለይ በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የወዝአደሩ ትግል በተለያዩ መልኮችና የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል ። ወዝአደሩ የሚሠራበትን መሣሪያ በማበላሸት ፣ ሥርዓቱን ሳይሆን በቅርብ ሆኖ የሚቆጣጠረውን በመጣለት ፣ የሥራ ማቆም አድማዎችን በማካሄድ ፣ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግና ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን በማቅረብ በሥርዓቱ ላይ ያለውን ጥላቻና ተቃውሞ ይገልጣል ። በትግሉ ሂደትም ውስጥ የሠራተኛውን ኃይል በማሰባሰብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞቹን ለማስከበር ልዩ ልዩ የመረዳጃና የሙያ ማኅበራት ይቋቋማሉ ። ቀስ በቀስም የአዲሱ ሥርዓት (የሶሻሊዝም) መሪዎች ይከሰታሉ ። የፖለቲካ ፓርቲ ይፈጠራል ። ትግሉ ግንባር ቀደም አመራር በመቀዳጀት ሠራተኛውን ለድል የሚያበቃ ኅሊናዊ ሁኔታ ያመቻቻል ። በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰው የወዝአደሩ ትግል ያለውን የካፒታሊስቱን የፖለቲካ ሥልጣንና የምርት ግንኙነቱን በማፈራረስ ወዝአደሩን የፖለቲካ ሥልጣን በማስጨበጥ ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን ኅብረተሰብ ለመመሥረት የሚደረግ እውነተኛ የፖለቲካ ትግል ቅርጽ ይይዛል ።

### በማኅበራዊ አብዮት ወቅት ፤

ማኅበራዊ አብዮት በታሪክ ሂደት ውስጥ ካረጀው ሥርዓተ ማኅበር ተራማጅ ወደሆነው ሥርዓተ ማኅበር የመሸጋገሪያ መንገድ ነው። በኅብረተሰቡ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ውስጥ መሠረታዊ የሆነ የዓይነት ለውጥ የሚያስከትል ማኅበራዊ ክስተት ነው ። [12]

በ«ሰላማዊ» ወቅት ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የቆየው የመደብ ትግል ለማኅበራዊ አብዮት መከሰት ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያዘጋጅ ነው ። እያረጀ የሚሄደው ሥርዓት በፖለቲካ ሥልጣኑ ባንድ በኩል የቀድሞ ተግባሩን በተሟላ መልኩ ማከናወን ይሳነዋል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቅራኔው እጅግ እየተካረረና እየሰፋ ሕዝቡን ባጠቃላይ ለዓመፅ የሚያዘጋጅ ይሆናል ። በዚህ ሂደት ውስጥ እየዳበረ ለሚመጣው የመደብ ትግል ከፍተኛው ቅርጹ የፖለቲካ ትግል ነው ።

የየሥርዓተ ማኅበሩ ገዥ መደብ ሥርዓቱን በመደብ ጥቅሙ አንፃር የሚቆጣጠርበት ፣ የሚያደራጅበትና የሚጠብቅበት ዋነኛው መሣሪያና ቁልፍ የፖለቲካ ሥልጣን ነው ። የበዝባዥ ገዥ መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ባንድ በኩል የሕዝቡን ጉልበት ለመበዝበዝ ሁኔታዎችን የሚያመቻችና የሚያስችል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝብን ትግል ለማፈን የሚያገለግል የሥርዓቱ የተደራጀ ኃይል ነው ። የሥርዓተ ማኅበሩ ገዥ መደብ የሚታገለው ይኸንኑ የፖለቲካ ሥልጣን በዘላቂነት ለማኖር ሲሆን የሥርዓተ ማኅበሩ ተጨቋኝና አብዮታዊ መደብ

Digitized by Google

ደግሞ የሚታገለው የጨቋኙን መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ደምስሶ የአዲሱን ሥርዓተ ማኅበር የፖለቲካ ሥልጣን በቦታው ለመተካት ነው ።

አብዮት የሕዝብ ሥራ ነው ። የአዲሱን ሥርዓት መደብ ወይም መደቦች ጥቅምና ፍላጐት የሚያፍነውን የአሮጌውን ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን በማስወገድ የአዲሱን ሥርዓት ገዥ መደብ ሥልጣን ማስጨበጥ የተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሥራ አይደለም ። የቡርዧ ምሁራን አብዮትን የጥቂት አብዮታዊ ግለሰቦች ድርጊትና ውጤት አድርገው ያቀርባሉ ። በፖለቲካ አድመኞችና በመፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎች የሚከናወን ያስመስላሉ ። ሐቁ ግን ከዚህ የተለየ ነው ። ያለሕዝብ ተሳትፎ የተከናወነ አብዮት የለም ። በእርግጥ ንቁ ግለሰቦች ለኅሊናዊ ሁኔታዎች መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲኖራቸው የሕዝብ ድጋፍና ተሳትፎ ከሌለበት ግን መሠረታዊ የሆነ የሥርዓት ለውጥ ማምጣት አይችሉም ።

«አብዮት የተጨቋኞችና የተበዝባዦች ትንሣኤ ነው ። ሰፊው ሕዝብ የአዲስ ማኅበራዊ ሥርዓት ፈጣሪ ሆኖ በንቃት ፊት ለፊት ለመጋፈጥ የተነሣበት በአብዮታዊ ጊዜ እንጂ በሌላ ጊዜ አልነበረም ።» [13] ማኅበራዊ አብዮት ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከዳር እምቢ በማለት ከበዝባዥ ገዥ መደብ የፖለቲካ ሥልጣን በላይ የሆነ የፖለቲካ ኃይል ያለው መሆኑን የሚገልጽበት ወቅት ነው ። ይህ በእርግጥ የነቃ ወይም በግብታዊነት የሚንቀሳቀስ ፣ የተበታተነና የተለያየ ወይም የተደራጀ እንቅስቃሴ ሊሆን ይችላል ። ለማንኛውም ግን በሥርዓቱ ላይ ያለውን ጥላቻ የሚገልጽበት ብቻ ሳይሆን የተሻለ ሥርዓት ለማምጣት ግልጽ ትግል የሚያደርግበት ነው ። የራሱን ዕድልና ዕድገት ለመወሰን በቆራጥነት የሚታገልበት ወቅት ነው ። ቀደም ሲል «አከብሮትና ፈርቶት» የኖረውን ሥርዓት በኃይሉ ደምስሶ የተነጠቀውን መብቱን ለማስመለስ የሚታገልበት ጊዜ ነው ። ሌኒን እንዳለው የአብዮት ወቅት በፖለቲካ ንቃቱ እጅግ ኋላቀር የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ወይም አባል እንኳን በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት የሚሳተፍበት ጊዜ ነው ። የሰፊው ሕዝብ ንቁና ወሳኝ ተሳትፎ የሌለበት ማኅበራዊ አብዮት አልነበረም ፤ አይኖርምም ።

ይሁን እንጂ በትግሉ መሳካት ሥልጣን የሚጨብጠው የግድ በትግሉ ውስጥ በመሳተፍ ወሳኝ ሚና የተጫወተው ሰፊው ሕዝብ ላይሆን ይችላል ። የባሪያ አሳዳሪን ሥርዓተ ማኅበር ለማስወገድ ባሮችና ድሆች ወሳኝ ትግል አድርገዋል ። ነገር ግን ትግሉ ባስገኘው አዲስ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሥልጣን የጨበጠው ባሪያው ሳይሆን ፣ የመሬት ከበርቴ ነው ። በቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅትም ኋላቀር የሆኑ የፊውዳል ስልተምርትን በማጥፋት ለካፒታሊዝም ጥስትና ያለው የዕድገት ጐዳና ለመጥረግ የቡርዧው መደብ አብዮቱን ያካሄደው ብቻውን ሳይሆን ወዝአደሮችን ፣ ገበሬዎችንና ሌሎች የለውጡ ደጋፊ ኃይሎችን በዙሪያው በመሰብሰብ ነበር ። በአብዮቱ ግብ መምታት ሥልጣን የጨበጠው ግን ሕዝብ ሳይሆን ፣ የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ገዥ መደብ ቡርዧው ነው ። ባጭሩ በማኅበራዊ አብዮት ወቅት ወሳኝ ኃይል ሕዝብ ቢሆንም አብዮቱ የሚያስገኘውን የፖለቲካ ሥልጣን የሚጨብጠው ግን ካዲሱ ሥርዓተ ማኅበር ዕድገትና ባሕርይ ጋር መጣጣም የሚችል ፍላጐት ያለው መደብ ነው ። የኅብረተሰብ ታሪካዊ ዕድገት በጨመረ ቁጥር የየሥርዓቱ ማኅበራዊ አብዮትም ስፋት ፣ ጥልቀትና ውስብስብነት እየጨመረ ይሄዳል ። የሕዝቡም ተሳትፎ ከሥርዓት ወደ ሥርዓት የሚለያይ ቢሆንም ታሪካዊ ዕድገት በጨመረ ቁጥር ድርሻው ይሰፋል ።



Digitized by Google

የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር በፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር የተተካው በሥርዓቱ ገዥ አባላት በጐ ፈቃድ አልነበረም፤ወይም ባልታወቀ ኃይል የተከናወነ የአጋጣሚ ጉዳይ አልነበረም ። ሽግግሩ የተከናወነው በስልተ ምርቱ የምርት ኃይልና የምርት ግንኙነት ቅራኔ መካረር የተነሣ የሥርዓቱ ተበዝባዥ መደብ ማለትም ባሪያውና የተቀሩት የሥርዓቱ ተጨቋኝና ድሀ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባካሄዱት የመደብ ትግል ነው ።

ይህ ዓይነቱም የባሮች ዓመፅ በሲሲሊ ፣ በቻይናና በሌሎችም አገሮች ታይቷል ። ከሁሉም ትልቁ የባሮች ዓመፅ ግን ከአንድ መቶ ሺ ባሮች በላይ የተሳተፉበት ከ71—70 ዓመተ ዓለም በግሪክ የተካሄደው የእስፓርታከስ ንቅናቄ ነው ። [14]

በእርግጥ ዓመፁ ሥርዓቱን ያዳከመ ቢሆንም ብቻውን ወደ መጨረሻው ግብ አላመራም ። ምክንያቱም ዓመፁ የተመራው በነቃና በተደራጀ መደብ ሳይሆን በግብታዊነትና ተከታታይነት በሌለው የሕዝብ እንቅስቃሴ ነው ። ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ ዓመፅ ባንዳንድ መንግሥታት ላይ ውድቀት በማስከተል በውጭ ወራሪዎች እጅ እንዲወድቁ አድርጓል ። [15] ለምሳሌ በባሪያና በባሪያ አሳዳሪዎች መካከል በተደረገ ትግል የተዳከመው የሮማ መንግሥት በዕድገቱ ዝቅተኛና በጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ በነበረው የጀርመን ጐሣ እጅ ወደቀ ። የዚህም ውጤት ከጀርመን ጐሣ ጥንታዊ የጋርዮሽ ግንኙነትና ከሮማው መንግሥት የባሪያ አሳዳሪ ግንኙነት የተለየና ከፍተኛ የሆነ የመሬት ከበርቴ ሥርዓተ ግንኙነት መመሥረት ሆነ ። በሌሎችም አካባቢዎች ባሮች በጌቶቻቸው ላይ ካካሄዱት የጋራና የግል ትግል ጐን የሥርዓቱ የምርት ግንኙነት ለሥራ መነሣሣትን የሚጠብቅባቸው ዘዴዎች (ማስገደል ጭምር) ተግባራዊነታቸው የገድ እየቀነሰ ሲሄድ የሕዝቡ ምርታማነት እጅግ አዘቀዘቀ ። በዚህ ገፊት የተነሣ ቀስ በቀስ የባሪያው ሥርዓት የምርት ግንኙነት በፊውዳላዊ የምርት ግንኙነት መተካት ግዴታ እየሆነ ሄደ ።

የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበርም ወደካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የተሸጋገረው ሰፊው ሕዝብ ባካሄደው መራራ የመደብ ትግል ነው ። ሥርዓቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ገበሬዎችና ሌሎች የተጨቆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል ። በዚህ ረገድ ከ14ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይና በኢጣሊያ የተደረጉት የገበሬ እንቅስቃሴዎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው ። [16] እያደረም የገበሬው ትግል የበለጠ ተጠናክሮና የሌሎች የፀረ ፊውዳል ኃይሎች ትግል ታክሉበት የፊውዳሉ ሥርዓት በፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ገባ ። በዚህ ጊዜ ነው በወቅቱ ተራማጅ የነበረው የቡርዧ መደብ የገጠሩን ገበሬ ፣ በከተማ ውስጥ ያሉ ድሀና ተጨቋኝ ክፍሎችንና ሌሎች ለውጥ ፈላጊ ኃይሎችን በመሰብሰብና በመምራት የራሱን አብዮት ያካሄደው ። ሰፊው ሕዝብ በቡርዧው አብዮት ውስጥ የተጫወተው ሚና ቀደም ሲል በነበሩት ማኅበራዊ አብዮቶች ውስጥ ከተጫወተው ሚና እጅግ ሰፊ ነው ። ቡርዧው አብዮቱን የመራው በልዩ ልዩ የፖለቲካ መስኮች በመደራጀትና ሕዝቡም ለነፃነት፣ ለእኩልነት ፣ ለዲሞክራሲያዊ መብቶችና ለመሳሰሉት ሰብአዊ ጥያቄዎች እንዲነሣሣ በመቀስቀስ ስለሆነ በአንፃራዊ መልክ ሕዝቡ ሰፊና እጅግ የጐላ ተሳትፎ ያደረገበት ነው ማለት ይቻላል ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የውጤቱ ተጠቃሚ ግን አልሆነም ።

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚካሄደው አብዮት ቀደም ሲል ከነበሩት ማኅበራዊ አብዮቶች ሁሉ የተለየ ነው። ዓላማው ያረጀውን የብዝበዛ ግንኙነት በሌላ የብዝበዛ ግንኙነት ለመተካት ሳይሆን ሰፊውን ሕዝብ በፖለቲካ እንቅስቃሴ



Digitized by Google

ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሟላና በተደ ራጀ መልኩ በማንቀሳቀስ የብዝበዛና የጭ ቆና ግንኙነትን አጥፍቶ ሰው ሙሉ በሙሉ በእኩልነት ፣ ባንድነት ፣ በወንድማማችነ ትና በሰላም አብሮ የሚኖርበትን ኮሚኒ ስት ሥርዓተ ማኅበር መመሥረት ነው ።

ሕዝቦች በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ባንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ባሉት መደቦች መካከል በሚደረ ገው ትግል ብቻ የሚወሰን አይደለም ። በተለያዩ መንግሥታት ፣ ማኅበረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የተለያዩ ደረጃዎች ባሏ ቸው ጦርነቶች ፣ ወታደራዊ ግጭቶች የሚ ገለጹ የፖለቲካ ትግሎችም ተካሂደዋል ። አሁንም የሚካሄዱ አሉ ። በተለይም በዘ መነ ኢምፔሪያሊዝም ፣ የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችንና ፋሺዝምን ፣ ቅኝ አገዛዝን፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ፣ ዘረኝነትን በመ ዋጋት ሰላምን ለማስፈን በልዩ ልዩ ሀገሮች ውስጥ ብሔራዊ ነፃነትን ለመጐናጸፍ ሰፊ ው ሕዝብ የሚጫወተው ሚና ጉልቶ የሚ ታይ ነው ። ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ የቅኝ ግዛት ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን የሞት የሽረት ትግል አካሂደዋል ፤ በማካሄድም ላይ ናቸው ። ከፍተኛ የሆኑ ትዕይንተ ሕዝቦችንና የሥራ ማቆም አድማዎችን በማድረግ ፣ የትጥቅ ትግሎችን በማካሄድና በሌሎችም የት ግል ስልቶች ቅኝ ገዥዎችን ድል አድርገው ብሔራዊ ነፃነታቸውን ተጐናጽፈዋል ። አሁንም ኢምፔሪያሊዝም በዓለም ሰላም ላይ ያደረሰውን ሥጋት ፣ የአፓርታይድን የሌሎችንም መሰል የኢምፔሪያሊዝም፣ ዕድሜ ማራዘሚያ መሣሪያዎች ጨርሶ ማስ ወገድ የሚቻለው በዓለም ሠራተኛ ሕዝቦች ጠንካራ ትግል ነው ። በልዩ ልዩ የካፒታሊ ስት ሀገሮች ውስጥ የሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ፣ የሥራ ማቆም አድማዎች፣የፖለ ቲካ ጥያቄዎችና ንቅናቄዎች ሁሉ የዓለም ሠራተኛ ሕዝብ ኢምፔሪያሊዝምንና አድ ኅሮት ኃይላትን ለመታገል የሚጠቀምባ ቸው ልዩ ልዩ የፖለቲካ ትግል ቅርጾች ናቸው ። በእርግጥ የዚህ ትግል ውጤት በቅ ርጹ የየሀገሩ ሕዝቦች ብሔራዊ ድል ሆኖ ቢታይም በይዘቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካፒ ታሊዝምን በመደምሰስ ሰው በሰው ለማይ በዘበዝበት ለሶሻሊስት ማኅበረሰብ ብሎም ለኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ግንባታ አስ ተዋጽኦ የሚያደርግ ነው ።

## የሕዝብ ሚና በባህል መስክ

ባህል በታሪክ ሂደት ውስጥ በኅብረተ ሰብ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተፈጠረ ፣የሚ ፈጠርና ኅብረተሰቡ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ የሚያሳይ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶ ችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ። [17]

ሰው ታሪኩን መሥራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በዕድገቱ የሚወሰን አሠራር ፣ አኗኗር ፣ አመራረት ፣ ግንኙነትና አስተሳ ሰብ ነበረው ፤ አለውም ። እነዚህ ሁሉ በባህሉ ውስጥ የሚታቀፉ ናቸው ። ባህል ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ ቁሳዊና መንፈሳዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል ። ቁሳዊ ባህል የኅብረተሰቡ የማምረት ልምድ ፣ መሣሪያ ውና የመሣሪያ አጠቃቀሙ ፣ የአኗኗር ፣ የአ ለባበስ ፣ የአመጋገብ ፣ የግንኙነት ስልቱና የመሳሰሉት የሚገለጹበት ነው ። መንፈሳዊ ባህል ደግሞ የሰውን ልጅ የሳይንስ ፣ የኪነ ጥበብ ፣ የሥነ ጽሑፍ ፣ የፍልስፍና ፣ የግ ብረገብ ፣ የትምህርትና የሌሎች መሰል መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችንና ውጤቶችን የሚገልጽ ነው ።

በእርግጥ ባህል ለመጀመሪያና ለመጨ ረሻ ጊዜ የተፈጠረ ሳይሆን ልክ እንደሌሎች ማኅበራዊ ክስተቶች ዕድገት አለው ። ለም ሳሌ የጥንት ሰው የሚጠቀምባቸው የማምረ ቻ መሣሪያዎች የተሳሉ ድንጋዮች፣ የተጠረ ቡ እንጨቶችና የሾሉ ነገሮች ናቸው።የሚመ ገበውም ፍራፍሬና ሥራሥር እንዲሁም የእ ንስሳት ሥጋ ነበር። የሚኖርበት ዋሻና ከዚ ያም ሲሻሻል በተለያዩ ደረጃዎች የተሠሩ ጉጆዎች ነበሩ ። ባህላዊ አስተሳሰቡም



Digitized by Google

በጣአትና መለኮታዊ እምነት ላይ የተመሠረተ ነበር።በአሁኑ ጊዜ የሰው ልጅ የሚጠቀምበት የግምረቻ መሣሪያ ግን በቀላሉ በመንቀሳቀስ ብዙ ነገሮችን መሥራት የሚችል ዘመናዊና ውስብስብ ነው ። የአመጋገብ ስልቱም የተሻለ ፣ የሚኖርበት ቤት ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል ፣ ስለተፈጥሮና ስለ ሰብአዊ ፍጡር ያለው አስተሳሰብም የበሰለ ነው ። ነገር ግን የባህል ዕድገት በአጠቃላይ ሲታይ የማያቋርጥ ሂደት በመሆኑ ዛሬ ዘመናዊ ነው ከሚባለው ባህል ውስጥ ወደፊት በሚተካው ትውልድ አስተያየት ኋላቀር የሚባል ገጽታ ይኖራል ።

በዚህ የባህል ዕድገት ሂደት ውስጥ ወሳኙን ሚና የሚጫወተው ሰፊው ሕዝብ ነው ። ነገር ግን አያሌ የቡርዧ ምሁራን ባህልን የሕዝብ ሥራ ውጤት እንዳልሆነ አድርገው ያቀርባሉ ። በእነርሱ አስተሳሰብ ሕዝብ የጉልበት ሥራን የማከናወን ችሎታ እንጂ የሳይንስና የኪነት ሥራዎችን ለመሥራት ተሳትፎ የለውም ። በመሆኑም ባህል የተወሰኑ ሰዎች ብሩህ ሥራ ነው በማለት ይከራከራሉ ። በእርግጥ ስለጉዳዩ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ለሌለው ሰው ይህ አባባል እውነት ይመስላል ። ምክንያቱም በዚህ መስክ ባሉት ግኝቶች ለግኝቶቹ አስተዋጽኦ ያላቸው ግለሰቦች ስምና ታሪክ ብቻ ጐልተው ስለሚታዩ ነው ። ነገር ግን ለባህል (ለምርት) መፈጠርና መዳበር ወሳኙ ግለሰብ ሳይሆን የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግና ባንፃሩ የሚኖረው ሰብአዊ ፍላጐት ነው ። ማለትም የኪነት አምራች ግለሰቦች መሠረት ራሱ ሕዝብ ነው ። «ሕዝብ ቁሳዊ እሴትን የሚፈጥር ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊ እሴትም ምንጭ ነው ። ፈጽሞ የማይደርቅ በጊዜ አንፃርም የመጀመሪያ የሆነ ምንጭ ነው ። [18]

በባህል ዕድገት ሂደት ውስጥ የማኅበራዊ ሥራ ክፍፍል መዳበር ጐላ ያለ ድርሻ ላላቸው ስመጥር ግለሰቦች እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታ ቢፈጥርም መሠረታቸው ሕዝብ ነው ። ሳይንቲስቶች ፣ የኪነ ጥበብ ሰዎችና ሌሎችም ታዋቂ ግለሰቦች የኅብረተሰብ ውጤቶች ናቸው ። የሚወለዱት ከኅብረተሰቡ በኅብረተሰቡ ውስጥ የመሆኑን ያህል የሚኖሩት ፣ የሚያድጉትና ማንነታቸውንም መቅረጽ የሚችሉት በኅብረተሰብ ውስጥ ነው ።

ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ግለሰቦች ለማኅበራዊና ባህላዊ ዕድገት የሚረዱ ባህላዊ ሥራዎችን ለመሥራት በመጀመሪያ ደረጃ ሰፊው ሕዝብ በታሪክ ሂደት ውስጥ ካቆያቸውና ካከማቻቸው ቁሳዊና መንፈሳዊ ሥራዎች መነሣት አለባቸው ። የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች ፣ ሐሳቦች ፣ መሣሪያዎችና ሀብቶች በሙሉ ወዲያው እንደተወለዱ የሚፈጥሯቸው ሳይሆን ፣ ሲወለዱ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚያገኙአቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው ። ለምሳሌ ተረት፣ አፈታሪክ ፣ ቀረርቶ ፣ እንጉርጉሮ ፣ ውዝዋዜዎች ፣ ልዩ ልዩ ቅርፃቅርጾች ፣ ሥዕሎች፣ መሣሪያዎች ፣ የእደ ጥበብ ሥራዎችና የመሳሰሉት ሁሉ ግለሰቦች ካሉበት ኅብረተሰብ የሚያገኙአቸው ባህላዊ ሀብቶች ናቸው ። እነዚህ ሀብቶች የልዩ ተሰጥኦ ባለቤት የሆኑ ግለሰቦችን ለምሳሌ ፣ የሳይንቲስቶችን፣የአርቲስቶችን ወዘተ. የመሥራት፣ የመፍጠር ፣ አዲስ ነገር የማግኘትና የማስገኘት ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ ይሆናሉ ።

ኅብረተሰቡ በደረሰበት ታሪካዊ የዕድገት ደረጃ አንፃር ለግለሰቦች የፈጠራ ሥራ አመች የሆኑ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ተሰጥኦ ያለው ሰው ቢኖርም ሳይታወቅና ውጤት ሳያሳይ ይቀራል ። ዓለም የመፈላሰፍ ፣ የመመራመር ፣ የመፍጠርና የመጻፍ ተሰጥኦ ያላቸውን ብዙ ሰዎች አፍርታለች። እነዚህም ከባሪያው ወይም ከባሪያ አሳዳሪው ፣ ከጭሰኛው ወይም ከመሬት ከበርቴው ፣ ከወዝአደሩ ወይም ከቡርዧው ወይም በእነዚህ መሠረታዊ መደቦች መካከል ከሚገኙ መደቦችና ማኅበራዊ ቡድኖች የተገኙና የሚገኙ ናቸው ። ይሁን



Digitized by Google

እንጂ የሁሉም ሰዎች ተሰጥኦ በገቢር ታይቷል ማለት አይቻልም ። በኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ አንፃር ሁኔታዎች ሳይመቻቹላቸው በመቅረታቸው በነበራቸው ተሰጥኦ ምንም ፍሬ ሳያፈሩ መክነው የቀሩ ግለሰቦች ብዙ እንደሆኑ ይገመታል ። አሁንም ይኖራሉ ። ለወደፊትም ቢሆን ጭቆናና ብዝበዛ እስካልተወገደ ድረስ የሚኖሩ ይሆናሉ ። ስለዚህ ለባህል ዕድገት ዋናው መሠረትና ወሳኙ ኃይል የሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴና ዕድገት ነው ።

## የግለሰብ ሚና

በታሪክ ዕድገት ሂደት የሰፊውን ሕዝብ ሚና ብቻ በማንግት የግለሰብን ሚና ጠቃሚነት ብንተው ስለታሪክም ሆነ ስለ ሕዝብ የሚኖረን አስተሳሰብ የተሟላ አይሆንም። ምክንያቱም በሰው ልጅ ታሪክ ሂደት ውስጥ በግላዊ ባሕርያቸው ከፍተኛ የሆነ ተጽዕና ያሳደሩ ግለሰብ መሪዎች ፣ የኪነ ጥበብና የሳይንስ ሰዎች ፣ የጦር መሪዎችና ሌሎችም አሉ ።

የቡርዧ ምሁራን ማርክሲዝም የሰፊውን ሕዝብ ወሳኝ ሚና ማረጋገጡን ለብቻው ገንጥለው በማየት ለግለሰብ ሚና ምንም ቦታና ግምት እንደማይሰጥ አድርገው ያቀርባሉ ። የግለሰብ ሚና በሕዝብ ታሪክ ሠሪነትና ባለቤትነት በመዋጡ አስፈላጊው ግምት አልተሰጠውም በማለት ይለፍፋሉ።

ማርክሲዝም ሌኒንዝም ስለግለሰቦች ሚና ያለው አቋም የቡርዧ ምሁራን ከሚሉት የተለየ ነው ። የአንድን ክስተት ውስጣዊ ግንኙነትና ቅንጅት ሳያጤኑ እያንዳንዱን ነገር ለብቻው በመመርመር ትርጉም መስጠት ሐሳቡንም ሆነ ትርጉሙን ደካማ ያደርገዋል ።የቡርዧ ምሁራን ትልቁ ስኅተት ከዚህ አንፃር የሚታይ ነው ። የግለሰብን ሚና ከማኅበራዊ ሕይወት ይነጥሉታል ። ከሌሎቹ ነፃ በሆነ ሁኔታ ብቸኛ ሕይወት ማካሄድ የሚችል አስመስለው ያቀርቡታል ። በተጨባጭ ሕይወቱ ያልሆነውንና ሊሆን የማይችለውን በሐሳባቸው እንደሆነ በማድረግ ፣የሆነውንና የሚሆነውን ይክዳሉ ። ከዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ በመነግት ማርክሲዝምን ይከሳሉ ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የግለሰብን ሚናና ሕይወት የሚያጠናው ግን ካለው እውነተኛ ግንኙነትና ተጨባጭ ሕይወቱ በመነግት ነው ። በእርግጥም የአንድን ክስተት (የግለሰብ ሚናን ጭምር) መሠረታዊ ባሕርይ መረዳት ማለት የክስተቱን ሂደት የሚገዙ ነባራዊ ሕግጋትን ምንነትና አሠራር መገንዘብ ነው ።

ግለሰብ አጠቃላይና ግላዊ ባሕርያት አሉት ። ግላዊ ባሕርያቱ በግለሰቡ አካል ፣ ዕውቀትና ልምድ ፣ አስተሳሰብ ፣ በግል አኗኗርና ሥራ (ሙያ) የሚገለጹና ሌላ ማንም የማይጋራቸው ጠባዮቹ ናቸው ። ግላዊ ባሕርያት በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት የሚወሰኑ ቢሆንም እንደግለሰቡ እንቅስቃሴ ሁኔታ የሕዝብን ታሪክ ለማፋጠን ወይም ለመጐተት የሚችል ተጽዕና ይኖራቸዋል ። ይህ ሲባል ግን ግለሰቡ ባስፈለገው ጊዜና ቦታ የፈለገውን ነገር ይሠራል ማለት አይደለም ። ለሚናው ተፈጻሚነት ኅብረተሰቡ የሚፈጥርለት ነባራዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ወሳኝነት አለው ።

በታሪክ ሂደት ላይ ትልቅ ተፅዕና ለማሳደር የተለየ ተሰጥኦ ላለው ሰው ሁለት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ። አንደኛው ይህ ተሰጥኦ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት አንጻር ከማንኛውም ሰው በበለጠ ካለው ማኅበራዊ ፍላጐት ጋር ሊያስማማው ይገባል ። ናፖሊዮን ከወታደራዊ ችሎታው ይልቅ የቬቶቬንን የሙዚቃ ተሰጥኦ ቢኖረው ኖሮ በእርግጥ ንጉሥ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም ነበር ። ሁለተኛው ባንድ ታሪካዊ ወቅት ተፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ችሎታ ባለው ሰው ላይ የኅብረተሰቡም ሥርዓት መንገዱን ሊዘጋበት አይገባም ። [19]



Digitized by Google

ለሳይንስ ፣ ለቴክኖሎጂ ፣ ለኪነ ጥበብና በጠቅላላው ለሰው ልጅ ዕድገት በራሳቸው ግላዊ ተሰጥኦ በመጠቀም ወደር የሌላቸውን ሥራዎች በመፈጸም በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የታላላቅ ግለሰቦች ስም በታሪክ መዝገብ ላይ ሰፍሯል ። ብዙዎቹ ለዚህ የበቁት ግን ያለአንዳች ችግርና መሥዋዕትነት አልነበረም ። ብዝበዛ በሰፈነበትና ማኅበራዊ ትራኔ በከረረበት ሥርዓት ውስጥ ግለሰቦች በተሰጥኦአቸው የሚያስገኙት ውጤት ካሉበት የኅብረተሰብ የዕድገት ፍላጐት አንፃር ተፈላጊ ቢሆንም፣ ከሥርዓቱ የገዥ መደቦች ጥቅም ጋር ሊጋጭ ይችላል ። ምክንያቱም የግለሰቦቹ ሚና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የሚጣጣም ፣ የጭቁናችን የመደብ ትግል የሚያዳብር በዚህም ምክንያት ለበዝባዥ መደቦች መሠረት የሆነውን ጐታች የምርት ግንኙነት መፈራረስን የሚያስከትል ሊሆን ስለሚችል ነው ።

እርጌውን የምርት ግንኙነት እንዳለ ለማቆየትና የሥርዓቱን ዕድሜ ለማራዘም የሚታገሉ የገዥ መደቦች ለግለሰቦች ጠቃሚ ሚና መዳበርና ውጤት ማግኘት እንቅፋት ይሆናሉ ። በዚህም ምክንያት ለኅብረተሰቡ ዕድገት አስተዋጽኦ ለማድረግ በግሉብ ከነበሩበት ሥርዓተ ማኅበር ጋር ትራኔ ውስጥ በመግባት ሕይወታቸውን ያጡና የሥራ ፍሬያቸው የተቀበረባቸው ብዙ ናቸው። ለራሳቸውም ጥቅምና ደስታን ሳይሹ ወይም ለሚሠሩት ነገር ዋጋ ሳይጠይቁ ለሰው ልጅ ዕድገትና ጥቅም ፣ ለዓለም ሰላምና ለሕዝቦች አንድነት መሠረታዊ የሆኑ ዕውቀቶችን ፣ ንድፈ ሐሳቦችን ፣ የጥናትና የትግል ስልቶችን ፖሊሲዎችንና የመሳሰሉትን ጠቃሚ የትግልና የዕድገት መማሪያዎችን ትተውልን ያለፉ አያሌ ናቸው ። ይህን ሐቅ በበለጠ ለመረዳት የፖለቲካ መሪዎችን ሚና በምሳሌነት እንመልከት ።

የፖለቲካ አመራር ባለበት ሁሉ የፖለቲካ መሪ አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ነው። እስከዛሬ ድረስ በዓለም ውስጥ የተከሰቱት የፖለቲካ ድርጅቶች ፣ መንግሥታት ፣ብሔራዊ ክልሎችና ወታደራዊ ኃይሎች ያለመሪ የኖሩበት ወቅት ፈጽሞ የለም። ሌኒን ይህንኑ ሲገልጽ «የራሱ የሆነ የፖለቲካ መሪና ፣ ማደራጀትና መምራት የሚችሉ ዕውቅ ወኪሎችን ሳይፈጥር ሥልጣን የጨበጠ አንድም መደብ በታሪክ ውስጥ የለም» [20] ብሏል ።

የእያንዳንዱ የፖለቲካ መሪ ሚና የሚለካው ካለው የምርት ኃይል ዕድገት አንፃር ለምርት ግንኙነት ባሕርይ ከሚናረው አቋም ነው ። ይህም በመሠረቱ ከሁለቱ አዝማሚያዎች ውጭ አይሆንም ። አንደኛው አዝማሚያ ኋላቀር የምርት ግንኙነትን ለዘለዓለም ለማኖርና የምርት ኃይሉን ዕድገት ለመግታት የሚታገሉትን የፖለቲካ መሪዎች የሚያጠቃልል ሲሆን ፣ ሁለተኛው ግን የምርት ኃይሉ በደረሰበት ዕድገት ደረጃ አንፃር ኋላቀር የምርት ግንኙነቱን በመለወጥ የተሻለና ከፍተኛ የሆነ ሥርዓት ለመመሥረት የሚታገሉ የፖለቲካ መሪዎችን የሚይዝ ነው ። የመጀመሪያው ነባራዊ የሆነ የሰው ልጅ ዕድገትን ፣ ለውጥንና የታሪክን አቅጣጫ የሚፃረር ስለሆነ ፣ አድኃሪ ጐታች ፣ ወይም ወግ አጥባቂ ነው ። ሁለተኛው ነባራዊው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ዕድገትን ወይም መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት የሚታገሉ ተራማጅ ወይም አብዮታዊ የሆኑ ያዲሱ ሥርዓት ገዥ መደብ መሪዎችን የሚያመለክት ነው ። የኅብረተሰብን ዕድገት በመፃረር ሰፊው ሕዝብ ባላወቀውና ባልተገነዘበው መንገድ በማታለልና በማስገደድ ለአድኃሪ ዓላማቸው የተጠቀሙ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች መኖራቸው በዓለም የታሪክ ማኅደር ተመዝግቧል ። እንደዚሁ ዓይነቶች መሪዎች ለዕድገት የቆሙ ኃይሉ



Digitized by Google

ችን ትግል ለማኮላሸት የሚታገሉ ናቸው። ዓላማቸው የታሪክን ነባራዊ ሕግ የሚፃረር በመሆኑ የሕዝባዊ ትግል ግፊት እየጨመረ ሲሄድ በተራማጆች ላይ የአፈናና የጭፍጨፋ እርምጃ ይወስዳሉ። በእርግጥ የእንዲህ ዓይነቶቹ መሪዎች አቋም በታሪክ ሂደት አንፃር ሲታይ በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ ብቻ የሚኖር ቢሆንም በሰው ልጅ ታሪክ ዕድገት ላይ በቀላሉ የማይገመት ጠባሳ የሚያስከትል ነው።

በዚህ ረገድ የጀርመን ብሔራዊ ሶሻሊስት ፓርቲ (ናዚ)እና መሪው አዶልፍ ሂትለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማና በጦርነቱ ውስጥ የፈጸሙትን አፍራሽ ድርጊት እንደዓይነተኛ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል።በአውሮፓ ውስጥ በካፒታሊዝም ላይ ከፍተኛና አጠቃላይ የሆነ ቀውስ በደረሰበት ወቅት ተፋፍሞ የነበረው የመደብ ትግል ያስፈራቸውን ቡርዧዎች በመወከል ሂትለርና ፓርቲው እጅግ አሠቃቂ የሆነ የሰው ልጅ እልቂት ፈጽመዋል ፤ የሰው ልጅ በብዙ መቶ ዓመታት ውስጥ ያካበታቸውን ቁሳዊና ባህላዊ ሀብቶች አውድመዋል። በዚህም ተግባራቸው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ባንዳንድ አካባቢ የዕድገትን ጉዞ አስተጓጉለዋል ማለት ይቻላል።

ዛሬም ቢሆን ኢምፔሪያሊዝም በኢኮኖሚና በርዕዮተዓለም ረገድ የደረሰበትን ቀውስ ለማስወገድና ሕልውናውን ለማቆየት ሲል በወራሪነቱ ፣ በጣልቃ ገብነቱና በጠብ አጫሪነቱ የዓለምን ሕዝብ ሰላም በሥጋት ላይ ጥሏል።

ይህንንም የሚያደፋፍሩ የሥርዓቱ መሪዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። በእርግጥ ሁኔታው በጦር መሣሪያና በወታደራዊ ኃይል የዓለምን ሕዝብ ታሪክ ወደኋላ ለመመለስ ወይም ባለበት ለመወሰን የሚደረግ መፍጨርጨር እንደሆነ ግልጽ ነው። ባሁኑ ወቅትም በሕዝቦች ጥረት የተገኙና የተፈጠሩ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የኢምፔሪያሊስት ኃይላት የሰውን ዘር ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መሣሪያዎች ሆነዋል። ዛሬ ያለነው አንድ አምባገነን የኢምፔሪያሊስት ሀገር መሪ በሚፈጥረው ችግር የዓለምን ሕዝብ ሰላም አደጋ ላይ ለመጣል በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ነው። ይህም በታሪክ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ግልጽ ነው። ሆኖም ኢምፔሪያሊዝምን ከውድቀት የሚያድነው አይሆንም። እነሂትለርም ሆኑ የዛሬዎች የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት መሪዎች የሚፈጽሙት የታሪክ ተፃራሪ ድርጊት ብቻቸውን ሳይሆን ሰፊውን ሕዝብ ራሱን በተለያዩ ዘዴዎች በማታለል ፣ በማጭበርበርና በመደለል ከሞላ ጎደልም ቢሆን ከጐናቸው በማሰለፍ ነው።

በአጠቃላይ አድኅሪ መሪዎች ሕዝብን ለጥፋት ማሰለፍ መቻላቸው ከሚያረጋግጥልን አንዱ ጉዳይ ባንድ የመደብ ትግል ወቅት ለሕዝባዊ ትግሉ ጠንካራ መሪ በተሟላ መልኩ አለመኖር በሕዝባዊ ትግል ላይ ከፍተኛ ጉድለት የሚያስከትል መሆኑን ነው። በአውሮፓ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማና ሂደት ውስጥ የነበሩት ኮሚኒስቶች በወቅቱ በተፈጠረው ነባራዊ ሁኔታ በመጠቀም ሕዝቡን ከጐናቸው አሰልፈው ሥልጣን ለመጨበጥ ቢችሉ ኖሮ የፋሺስቶችና የአጋሮቻቸውን ጦርነት ወደ ሶሻሊስት አብዮት በመለወጥ በብዙ የአውሮፓ ክፍል ሶሻሊዝምን እውን ለማድረግ በተቻሉ ነበር። የዚህ ዓይነቱ አመራር ደግሞ ሁኔታ ፈቅዶ ፣ ሊከሰቱ ከሚችሉ አስተዋይ ፣ ጠንካራና የሕዝብ ጥቅም አራማጅ ከሆኑ ግለሰቦች ጠቃሚ ሚና ውጭ የሚታሰብ አይደለም።

በአጠቃላይ ልዩ ስጦታና ችሎታ ያላቸው የፖለቲካ መሪዎች ጉልህ ድርሻ ግልጽ ሆና የሚወጣው የሥርዓተ ማኅበሩ የምርት ኃይልና የምርት ግንኙነት ቅራኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስና ይህም በመ



Digitized by Google

ደብ ትግሉ መግሪያነት መሠረታዊ የሆነ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ማኅበራዊ አብዮት ማካሄድ በሚያስፈልግበት ጊዜ ነው ። በሂደት ውስጥ የመደቦች የኃይል ሚዛን እየተለዋወጠ በተወሰነ ጊዜ ያርጌውና ያዲሱ ሥርዓተ ኃይላት ለጊዜውም ቢሆን ተመጣጣኝ (እኩል) ሲሆኑ የፖለቲካው መሪ ሚና ወሳኝ ይሆናል ። ሌኒን እንዳለው ነባራዊ አብዮታዊ ሁኔታዎች መፈጠራቸው (ማለትም የገዥ መደቦች በቅራኔ አዘቅት ውስጥ መግባትና ባለው ሁኔታ መግዛት ሲሳናቸው ፣ ሕዝቦች ደግሞ ጭቆናና ብሶታቸው ከሚችሉት በላይ መሆኑና ለነፃነታቸው ቆርጠው ለመታገል እርምጃ መውሰድ መጀመራቸው) ብቻ በቂ አይደለም ። አርጌውን አፍርሶ አዲሱን ሥርዓት በቦታው ለመተካት ሁኔታዎች ከመቸውም ይበልጥ የተመቻቹ መሆናቸውን የሚያረጋግጥና ከዚሁም አንፃር ሕዝብን ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሶ ለድል መብቃት የሚያስችሉ ኅሊናዊ ሁኔታዎች (ንቃት ድርጅትና አመራር) መኖርም እጅግ አስፈላጊ ነው ። ባጭሩ በነባራዊ ሁኔታ በተመቻቸው ሁሉ መጠቀም የሚቻለው ኅሊናዊ ሁኔታ ሲኖር ነው ።

የኅሊናዊው ሁኔታ ውጤታማነት የሚወሰነው በፖለቲካዊ አመራር ችሎታ ነው ። በአመራሩ ሂደት የፖለቲካ አመራሩ የሚቀይሰው የትግል ስልት ፣ የሕዝብን ኃይል የማስተባበርና የማቀነባበር (የማሳተፍ) ችሎታ የትግሉን አቅጣጫ ይወስነዋል ። በጠቅላላው የፖለቲካ አመራሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን በትክክል ማንፀባረቅ የሚችሉ ኅሊናዊ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ችሎታው አናሳ ከሆነ አርጌው የፖለቲካ ሥርዓት እንደገና ራሱን ማጠናከር ይችላይ ፤ አመራሩ ጠንካራ ከሆነ ግን አርጌውን ሥርዓተ ማኅበር በአዲሱ ለመለወጥ የሚያስችል ታሪካዊ ኃይል ይፈጥራል ። በዚህ አንፃር በተለይ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ከፍተኛ ሚና አለው ።

የፖለቲካ መሪዎች ያለሕዝብ ተሳትፎ ብቻቸውን ተአምር ሊሠሩ አይችሉም ፤ ወይም በአንድ ጊዜ ለሁሉም የማኅበራዊ ችግሮች እልባት የሚሰጡ አይደሉም ። ማንኛውም ሥርዓተ ማኅበር የፖለቲካ መሪዎች ጥንካሬ የሚወሰነው ከሰፊው ሕዝብ በሚያገኙት ድጋፍና እገዛ ነው ። ድጋፉን ማግኘት የሚችሉትም እነርሱ ራሳቸው በሚያደርጉት ጥረት ነው ። ከተጨባጩ ሁኔታ አኳያ የሕዝቡን ፍላጎትና ያለውን ማኅበራዊ ግንኙነት ወደላቀ ዕድገት ለማሸጋገር የሚረዳ ፖሊሲ በማዘጋጀትና ለተግባራዊነቱም ሕዝቡን ከዳር እዳር በማንቀሳቀስ ነው ። ስለዚህ ያንድ ፖለቲካ መሪ ኃይልና ጥንካሬ በሕዝብ ጥንካሬና ኃይል ውስጥ ሲሆን የሕዝቡም ኃያልነት በመሪው የላቀ የአመራር ችሎታ የሚገኝና የሚገለጽ ነው ። ይህ ሲሆን ሰፊው ሕዝብና መሪው ባንድ ጉዳና ላንድ ግብ የሚታገሉ ያንድ አካል ሁለት ገጾች ይሆናሉ ።

ስለመሪዎች ጠቃሚ ሚና ሲወሳ አንድ መጠቀስ ያለበት ተጨማሪ ነጥብ አለ ። በታሪክ መዝገብ ላይ የብዙ ፖለቲካ መሪዎች ስም ሠፍሯል ። ይሁን እንጂ ሁሉም በታላቅነት የሚታወቁ አይደሉም ። በቅድመ ማርክሲዝም ታላቅነት ፣ ጀግንነትና ብልህነት በደምና በዘር የሚታላለፍ ተወራሽ ባሕርይ ሆኖ ይታይ ነበር ።

ለምሳሌ በመሬት ከበርቴው ሥርዓት ውስጥ ሰዎች በተፈጥሮ ታላላቅ ሰዎችና ገዥዎች ሆነው እንደሚወለዱ ይታመናል ። በዚህም የተነሣ ንጉሥነት (ንግሥትነት) ልዑልነትና መሳፍንነት በችሎታ ሳይሆን ከዘር ወደዘር የሚተላለፍ ልክ እንደ ንብረት በውርስ የሚሰጥ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥም ለሥርዓቱ መጠበቅና መስፋፋት የሚታገሉ «ችሎታ ያላቸው» የፖለቲካ መሪዎች ተፈጥሯዊ ተሰጥኦ ያላቸው ተደርጉ ሲቀርብ የኅብረተሰቡ ውጤት መሆናቸው ዝቅ ተደርጎ ይታያል ፣ ወይም ጭራሹኑ ይካዳል ። በአጠቃላይ በኢማርክ



Digitized by Google

ሳዊ አስተሳሰብ መሠረት ትልቅነት ፣ ጀግንነት ፣ ብልህነት የታሪክ ውጤት ሳይሆን አብሮ የሚወለድ የተፈጥሮ ባሕርይ ወይም በ«አምላክ» ፈቃድ የሚሰጥ ፀጋ ተደርጐ ይወሰዳል ።

ነገር ግን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ የግለሰብ ታላቅነት የኅብረተሰብ ውጤት ነው ። በእርግጥ የሰዎችን ልዩ ስጦታና ችሎታ መካድ አይቻልም ። ይህ ግን ከሕዝብ እንቅስቃሴና ዕድገት ውጭ ወደ እውንነት ሊለወጥ የሚችል አይደለም ። በዓለም ውስጥ ብዙ ልዩ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ተፈጥረዋል ። የሁሉም ችሎታ ግን በተግባር አልታየም ። ምክንያቱም ልዩ ስጦታና ችሎታ ያላቸው ግለሰብ መሪዎች ችሎታቸውን እውን የሚያደርጉትና የሚያዳብሩት ሕዝቡ ከደረሰበት ዕድገት አንፃር በሚፈጥርላቸው አመች ሁኔታ ውስጥ በመሆኑ ነው ።

በተጨማሪም የመሪዎች ታላቅነት የሚወሰነው ወይም የሚለካው ከሁሉም በላይ በሚናቸው ዓይነት ነው ። ሚናቸው ከሰው ልጅ ታሪካዊ እንቅስቃሴ አኳያ ከሚያስከትለው ወይም ከሚያሳድረው ተጽዕኖ አንፃር ነው ። በማርክሲዝም ሌኒንዝም ሳይንስ መሠረት ታላላቅ ሰዎች በመባል በታሪክ ውስጥ የሚታወቁት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መዳበር ፣ ለኅብረተሰብ ዕድገትና ሰላም ፣ ለሰው ልጅ ነፃነትና እኩልነት ሲሉ በምታልፍ ሕይወታቸው የማያልፍና ወደር የሌለው አስተዋጽኦ አድርገው ያለፉትና የሚያልፉት ናቸው ። ፐሌካኖቭ እንዳለው «ታላቅ ሰው ታላቅ የሚሆነው . . . የጊዜውን ማኅበራዊ ፍላጐት ለማገልገል የሚያስችል ከፍተኛ የሆነ ችሎታ ስላለው ነው[21]

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ሰው በሥራው አማካይነት የራሱን ታሪክ ይሠራል ። ነገር ግን ይህን ታሪክ የሚሠራው በፈለገውና በተመኘው አቅጣጫ ሳይሆን ነባራዊ የዕድገት ሕጎች በፈቀዱለት መሠረት ነው ። በዚህ ታሪክ ሂደት ውስጥ ባንድ በኩል የግለሰብ ፣ በሌላ በኩል የሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ ። በተለይ የሚናዎቻቸው ልዩነት ጐልቶ የሚታየው በመደቦች በተከፋፈሉ ኅብረተሰቦች ውስጥ ነው ።

የሰውን ልጅ ታሪክ በሚገባ ለማወቅም ሆነ ታሪክን በንቁ ተሳትፎ ለመገንባት የሁለቱንም ሚናዎች በትክክል መገንዘብ ያስፈልጋል ። የአንዱን ሚና ከሌላው ገንጥሎ ወይም መሆን ከሚገባው ውጭ አኮስሶ ወይም አጋንኖ ማየት ስሕተት ነው ።

በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ዘላቂውና ወሳኙ ኃይል ሰፊው ሕዝብ ነው ። ነገር ግን ያለማቋረጥ በሚጓዘው የታሪክ ሂደት ውስጥ በኅብረተሰቡ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያስከትሉ ሚናዎችን መጫወት የሚችሉ ግለሰቦች አስፈላጊነትም ሁለንተናዊ ገዴታ ነው ። የሁለቱም ሚናዎች መጣጣም ወይም አለመጣጣም በየሥርዓተ ማኅበሩና በየዕድገት ደረጃው የተለያየ መልክ ቢኖራቸውም ፣ ሙሉ በሙሉ የሚጣጣሙት በኮሚኒስት ሥርዓተማኅበር ውስጥ ነው ።

## የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ


1. *The Great Soviet Encyclopedia,* Vol. 20, p. 213.
2' *The Fundamental of Marxist-Leninist Philosophy*, (Moscow: Progress Publishers, 1982), pp. 398-99
3. *Ibid*, p. 399.
4. *Ibid.*, p. 401.
5. *Civilization and the Historical Process,* (Moscow: Progress Publishers, 1983), p. 139.
6. *The Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy*, p. 401.
7. George Novack, *Understanding History* (New York: Pathfinder Press, 1880), p. 29.




Digitized by Google

8. *The Fundamentals of Marxist-Philosophy*, p. 403.

9. K. Marx, *The Economic and Philosophical Manuscripts of 1844* (New York: International Publishers, 1976), p. 110.

10. *Dictionary of Philosophy*, (Moscow: Progress Publishers, 1984), p. 329.

11. *Fundamentals of Marxism-Leninism*, (Moscow: Foreign Languages Publishing House, 1963), p. 176.

12. *The Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 21, p. 669.

13. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 9, p. 113.

14. *The Fundamental of Marxist-Leninist Philosophy*, p. 444.

15. *Ibid.*

16. *Ibid.*, p. 445.

17. *Dictionary of Philosophy*, p. 94.

18. *The Fundamental of Marxist-Leninist Philosophy*,

19. G. Plekhanov, *Selected Philosophical Works*, (Moscow: Progress Publishers, 1977), Vol. 1, p. 309.

20. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 4, p. 370.

21. G. Plekhanov *Selected Phiosophical Works*, Vol. 1, pp. 308-309.

Digitized by Google

# ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን

የቆየ መንገሻ

በልማት ልንራመድና የተፈጥሮ ችግሮችንም ሆነ ጥገኛ ጠላታችን የሆነውን ኋላ ቀርነትን ልንላቀቅ የምንችለው በአመዛኙ በእራሳችን ጥረት ነው። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ መብትና ግዴታውን ተገንዝቦ፣ አንድነቱን አጠናክሮ፣ በፍላጎት ለሥራ ሲነሣና የተሟላ የሥራ ዲሲፕሊን ሲኖር ነው። ስለዚህ ደግሞ ኅብረተሰባችን ስለሥራ በተለይም ስለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ምንነት የሚኖረው ግንዛቤ ወሳኝነት አለው።

የሰው ልጅ በረጅም ዘመን ታሪኩ ራሱን ከሌሎች ፍጡሮች እየለየ፣ አካባቢውን ለራሱ በሚስማማ መልክ እየለወጠ፣ ተፈጥሮን ለመገራት የቻለው በሥራ ነው። ይህ በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ያለማቋረጥ የታየና የሚቀጥል ሂደትነው። ሥራ የሰው የሕልውና መሠረት ብቻ ሳይሆን የፈጠራና በፈጠራ ውጤቱም ለሰው ልጅ የደስታ ምንጭ ነው።

የሰው ልጅ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመሩ የሚሄዱትን ፍላጎቶቹን ለማርካት ከተፈጥሮ ጋር የማያቋርጥ ትግል ያደርጋል። በትግሉ የተፈጥሮን አስከፊ ገጽታ በቁጥጥሩ ሥር እያዋለ፣ በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበላይነት ይበልጥ እያጠናከረ መጥቷል። ጥንት ከነበረበት ከአውሬነት የማይሻል ኑሮው ወጥቶ፣ በተለይ በሥልጣኔያቸው በገፉ ሀገሮችና በአንዳንድ አካባቢዎች በደረሰበት ዕድገቱ የከፍተኛ ምርምር ውጤቶች ባለቤት ሆኗል። ካለበት መሬት አልፎ በሌሎች ፕላኔቶች ላይ (በቬኑስ፣ ማርስ፣ ሳተርን፣ ጁፒተር ወዘተ -) አስደናቂ የሆኑ የምርምር ተግባራትን እያካሄደ ነው። ይህ ሁሉ ሌላ ታምር ሳይሆን የሰው ልጅ በዕድገት ሂደቱ ያካበተው የሥራ ውጤት ነው። ኤንገልስ «ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው» በማለት እንደ ገለጠው፣ ሰው ለማምረት የሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴና ለሥራ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሳሪያዎች ዕድገት ጋር፣ የሰውነቱን ቅርጽ እየለወጠ፣ ልዩ ልዩ ድምጾችን እያፈለቀና



Digitized by Google

የሚያፈልጓቸውን ድምጾች በተለያየ መልክ በማቀነባበር የሐሳቡ መግለጫ ቋንቋን እየፈጠረ ፣ በዚህም መግባቢያነት ሥራን የበለጠ እያዳበረ ፣ ተፈጥሮን የበለጠ እየገራ በመምጣት ዛሬ ለሚገኝበት የዕድገት ደረጃ ሊበቃ ችሏል ። በአጠቃላይ የኅብረተሰብ ዕድገት የሥራ ውጤት ሲሆን ሥራ ደግሞ በዲሲፕሊን የሚከናወን እንቅስቃሴ ነው ።

የሥራ ዲሲፕሊን በተወሰነ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ባለው የሥራ አደረጃጀት፣ ባህል፣ ስለ ሥራ ያለ አመለካከት፣ የጥቅም ድርሻና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ላይ በመመሥረት ከሥራና ከሥራ ጋር የተያያዙ ማኅበራዊ ግንኙነቶች የሚመሠረቱበትና የሚካሄዱበት ሥርዓት ነው።«የሥራ ዲሲፕሊን ቅንብር ያለው የሥራ እንቅስቃሴ በኅብረተሰቡ ሕግና ሌሎች ማኅበራዊ ወጐች ላይ ተመሥርቶና በእነርሱ በመመራት የሚከናወንበት የአሠራር ሥርዓት ነው።»[2] የሥራ ዲሲፕሊን ዓይነት እንደየሥርዓተ ማኅበሩ የምርት ግንኙነት ይለያያል ።

በአንድ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ በወቅቱ የሚኖር የሥራ ዲሲፕሊን ባሕርይ በወቅቱ በዚያ ሥርዓተ ማኅበር ባለው የምርት ግንኙነት ዓይነት ይወሰናል ። ለምሳሌ በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚኖረው የሥራ ዲሲፒሊን ዐይነት በፊውዳሉ ፍጹምና ግልጽ በሆነ አስገዳጅነት ፣ በማስር ፣ በመደብደብና በመሳሰሉት የኃይል እርምጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው ። በቡርዧው ሥርዓት ውስጥ ለሠራተኛው የሥራ ዲሲፕሊን ማክበር ጥያቄ የዕለት ጉርስ የማግኘት ጥያቄ ሆኖ ይቀርባል ። ማለትም ሠራተኛው የቡርዧውን የሥራ ዲሲፕሊን አክብሮ ካልሠራ ከሥራው በመስደድ ለረሃብና ፣ ለእርዛት ይዳረጋል፣አደጋም ይጠብቀዋል ። በ ዚ ህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የቡርዧው የሥራ ዲሲፕሊን ማስጠበቂያ ዋንኛ መግሪያ ሠራተኛውን ከሥራ ማባረር ነው ። ስለዚህም ሠራተኛው ይህ ዕጣ እንዳይገጥመው ለሥራውና ለአሠሪው ተገዥ መሆን የግድ ይሆንበታል ። ከሥራ ውጤቱ የሚገባውን የጉልበቱን ዋጋ እንደማያገኝ እያወቀ ተግቶ ይሠራል፣ ድርጅቱን ( አሠሪውን ) ይለማመጣል ። ይሁን እንጂ እያደር የሥራ ዋጋውን ያለማግኘቱ ከሚፈጽሙበት በደሎች ጋር በመዳመር ውስጥ ውስጡን ለነፃነት ትግል ያነሣሣዋል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት በሠራተኛው ላይ በየመልኩ የሚፈጸምበት በደል ሠራተኛውን ለትግል በአንድነትና በቁርጠኝነት እንዲነሣሣ ፣ ዛሬ ዓለም አቀፍ ሥርዓት በመሆኑ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ለሚገኘው ለሶሻሊዝም መመሠረት እንዲታገል አድርጐታል ። ነገር ግን ትግሉ ጠንክሮ ብዝበዛውንና ጭቆናውን እስኪያስወግድ ድረስ ፣ በአሠሪው ካፒታሊስት ድርጅት ወይም ግለሰብ በየጊዜው የሚጫንበትን የከረረ የሥራ ዲሲፕሊን ማክበር የግድ ይሆንበታል ።

ሠራተኛው በረጅም ትግልና ከፍተኛ መሥዋዕትነት የካፒታሊስቱን ብዝበዛና ጭቆና ሲያስወግድ እርሱ የውጤቱ ተጠቃሚ ያልነበረበት የሥራ ዲሲፕሊንም አብሮ ያከትማል ። የድካሙ ፍሬ ሙሉ ተጠቃሚ ወደሚሆንበት ወደ ሶሻሊዝም ይሸጋገራል ። በዚህ የታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የሕልውና መሠረትና የዕድገቱ ዋስትና የሆ ነው ሥራ ለብዙኃን ሠራተኛ ሕዝብ ሰፊ ጠ ቀሜታ በሚኖረው መልክ ይደራጃል ። የሥ ራ ዲሲፕሊንም በዓላማው ፍጹም ተለውጦ የብዙኃን ጠቀሜታ ማስገኛ መግሪያ ይሆና ል ። ሶሻሊስት የሥራ ዲስፕሊን ላይላዩን ሲ ታይ ወይም በቅርጹ ከካፒታሊስት ( ዐያ ,ም ከሌሎች የሥራ ዲሲፒሊን ሥርዓቶ[illegible] ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በቀላሉ ስለማይታ ይ ማስተዋልን ይጠይቃል ።

Digitized by Google

# የሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ምንነትና ጠቀሜታው

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ምንድነው? ከካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ዲሲፕሊን አንፃር ለማኅበራዊ ፍትህና ለሠራተኛው ደህንነት ያለው ጠቀሜታ ምንድነው ?

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ብዝበዛ በተወገደበት ሁኔታ ውስጥ ሠራተኛው የራሱን ጥቅም ከፍ ለማድረግ ሊኖረው የሚገባ፣በማንኛቸውም ረገድ በርትቶ የመሥራት ባሕርይ ነው ። በዝርዝር ሲታይ ሠራተኞች ለሥራ ያላቸውን አመለካከትና የተወሰነ ሥራን በተወሰነ ጊዜ በጥራትና በብቃት ለማከናወን የሚያስችሉ ግንኙነቶችን ፣ እያንዳንዱ ሠራተኛ ይህን ባሕርይ አሟልቶ መገኘትን ፣ የተሟላ የሥራ አደረጃጀትን ፣ የሥራ አመራርን ፣ የሥራ መሣሪያዎች መሟላትና መሻሻልን ፣ መሣሪያዎችን በተገቢው መንገድ መያዝና መጠቀምን ፣ ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው ቦታ ማሠማራትን ፣ በአጠቃላይ ለምርትና ምርታነት ዕድገት፣ ለምርት ጥራትና ለኅብረተሰቡ ደህንነት የሚበጀውን ሁሉ በሚገባ የማከናወን ተግባርን ፣ ለዚህ ተግባር ብቁ የሚያሰኝ የሠራተኛነት ባሕርይ ይዞ መገኘትንና በዚሁ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ማስፈንን ያጠቃልላል ።

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ከካፒታሊስቱ «የሥራ ዲሲፕሊን» ፍጹም የተለየ ነው ። በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተ ፣ አዲስና ተራማጅ የሆነ የሥራ ግንኙነት ነው ። ይህ የሥራ ዲሲፕሊን ዛሬ በሶሻሊዝም ከዚያም ወደ ኮሚኒዝም እያደገ የሚሄድ ፣ በራሱ በሠራተኛው ሕዝብ ፍላጎትና አነሣሽነት ፣ በንቃት ላይ የተመሠረተ ፣ ከብዝበዛ ነፃ የሆነ ሥራን በማከናወን ፣ በነፃ ሕይወት ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ሥርዓት ነው ።

ይህ ዓይነቱ የሥራ ዲሲፕሊን ፣ የሥራ ዝንባሌ ፣ የሥራ ባሕል ፣ የሥራ ፍቅር መስፋፋትና መጠናከር ለሶሻሊዝም ግንባታ ከፍተኛ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ያለው ነው ። ሌኒን እንዳለው «እጅግ ጠንካራ የሆነ ድርጅትና የሥራ ዲሲፕሊን ብቻ ነው ሶሻሊዝምን ለመመሥረት የሚያስችለው [3] » ።

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ፣ ከራሱ ከሠራተኛው ፍላጎትና አነሣሽነት የሚመነጭ ነው ። ለሠራተኛው ፍላጎትና የራስ አነሳሽነት መሠረቱ የሠራተኛው ንቃትና አመለካከት መዳበር ፣ የሠራተኛው ስለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ምንነት በቂ ግንዛቤ መኖር ፤ በአጠቃላይ የሠራተኛው ንቃትና ዕውቀት ራሱ በራሱ መነሣት ነው ። ለዚህም ሁኔታ መሟላት ሠራተኛው ስለሥራ ሳይንሳዊ አመለካከት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። የሥራና የፈጠራ ችሎታውን በፍላጎትና በሚገባ እንዲጠቀምበት ፣ ስለሥራ ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጡ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ሠራተኛው የቴክኒክ (የሙያ) ዕውቀት መጨበጡ ያለው አስፈላጊነት ግልጽ ነው ። ይህ ብቻውን ግን አይበቃም። እያንዳንዱ ሠራተኛ አስተሳሰቡ በሳይንሳዊ አመለካከት መታነጽ ይኖርበታል ። ከሁሉ በፊት ከፍላጎትና ከስሜት የመነጨ የሥራ ኃይል መገኘት ፣ ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ጠንካራ መሠረት መጣል ነው ።ሠራተኛው የራሱን ፍላጎት ከኅብረተሰቡ፣ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ከራሱ ጋር አዛምዶና አጣምሮ ማየት ሲችል ፣ «እያንዳንዱ ለሁሉም ፣ ሁሉም ለእያንዳንዱ» የሚለው የማኅበራዊ ኃላፊነት ስሜት በእያንዳንዱ ሠራተኛ አስተሳሰብ ውስጥ ሲዳብርና የሠራተኛው ባህል እየሆነ ሲሄድ ነው የተሟላ የሥራ ዲሲፕሊን እየሰፈነ ሊሄድ የሚችለው ። የማኅበራዊና የግል ፍላጎቶች መጣጣም ፣ እንዲሁም የግል ፍላጎቶች የማኅበራዊ ፍላጎቶችን ፈር የመከተል ሁኔታ ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መገኘት መሠረቶች ናቸው [4] ።

ሠራተኛው ለሥራ የሚኖረው ፍላጎት ፣ አመለካከትና የራስ አነሣሽነት ሁኔታም


Digitized by Google

ከዚህ ማኅበራዊና የግል ፍላጐት መጣጣም ጋር ግንኙነት ያለው ነው ። ሠራተኛው ለማንና ለምን እንደሚሠራ የሚኖረው ግንዛቤ መዳበር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። በሶሻሊስት ሀገሮች የአንድ የሥራ ድርጅት የአደረጃጀት ብቃት፣ ጥንካሬና ዕድገት የሚገመተው የድርጅቱ ሠራተኞች ስለ ሥራ ባላቸው አመለካከትና ዝንባሌ ነው ። ምክንያቱም በሠራተኛው ዘንድ ሶሻሊስታዊ የሥራ አመለካከት መስፈን ለተሟላ የሥራ ዲሲፕሊን መገኘት አንዱ ዋና ቅድመ ሁኔታ ነው ።

በእርግጥ ይህ ዓይነቱን የሥራ ባህል ማስፈን ከባድና የረጅም ጊዜ ትግል ይጠይቃል ። «አዲስ የሥራ ዲሲፕሊን መመሥረት ፣ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ መካከል አዲስ ዓይነት ማኅበራዊ አንድነትን ማጠናከር ፣ አዲስ የአሠራር ዘዴንና ብቁ ሠራተኞችን መለየትና ማወቅ ፣ ዐውቆም በተገቢው የሥራ መስክ ማሰማራት ፣ --- የብዙ ዓመታት ሥራ ነው።»[5] የብዙ ዓመታት ውጤት በተፈለገ መልኩ የሚገኘው ደግሞ የሥራ ክንውን ከመሠረቱ በትክክል ሲወጠንና ሲቀየስ ነው ። በኢትዮጵያም ለዚህ የሚያበቁ ፣ ከሩቅ ግባችን አኳያ የሚበጁ ጅምሮች በየመስኩ በትክክል መወጠንና ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ለነዚህ ጅምሮች ተገዥ ሊሆን የሚችልባቸውንና ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊንን ለማስፈን የሚያግዙ ሥልቶች መቀየስ ይኖርባቸዋል ።

## ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊንን ለማስፈን የሚያግዙ ዘዴዎች

ሶሻሊስታዊ የሥራ ዲሲፕሊንን ለማስፈንና ለማጐልበት የሚከተሉት ሦስት መሠረታዊ ዘዴዎች ሊረዱ እንደሚችሉ ይታመናል ።

1. የቅርብ ክትትል ፣ የቅርብ ክትትል ሲባል በሠራተኛው ላይ ጥፋት ወይም ስህተት ሲገኝ በመንቀፍ የሠራተኛውን ሞራል (የሥራ ስሜት) መንካት ሳይሆን ፣ ስህተቱን ተረድቶ እንዲያርም ፣ እንዲስተካከል የሚያግዝ ፣ ገንቢነት ያለው ማለትም የማስተማር ክትትል ነው ። አንዳንዴ ክትትል የሚያስተምር ሳይሆን የሚያስቆጣ ፣ በሥራውም ሆነ በሠራተኛው ላይ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህም ክትትል ውጤታማነቱ ታይቶ መቀየስ ይኖርበታል ።
2. ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ፣ ይህ ውድድር በሶሻሊስት የምርት ክንውን ውስጥ ወጪን ለመቀነስና ምርትን ከፍ ለማድረግ የሚካሄድ ሂደት ነው ። ይህን ዘዴ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወደፊት በዝርዝር እንመለከተዋለን ።
3. ቁሳዊና ሞራላዊ ማነቃቂያ ፣ ለፈጠራ ፣ ለጥሩ ሥራና ለሠራተኛ ማነቃቂያና ማነሣሻ ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ (ኢንሴንቲቭ) ስልትን አድልኦ በሌለው በተቀነባበረ አሠራርና በማያቋርጥ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግም የሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ተግባራዊ ማድረጊያ ሌላው ዘዴ ነው ። ሠራተኛው ጠንክሮ ለመሥራት ፍላጐት ሊኖረው፣ የፈጠራ ችሎታውንም በይበልጥ ሥራ ላይ ሊያውል የሚችለው በመብቱ ከመጠቀምና ግዴታውን ከመወጣት ባሻገር ያስገኘው ውጤት ሲታወቅለትና ተገቢ ጥቅም ሲያገኝበት ነው ። ይህ ተግባራዊ ሲሆን ሠራተኛው እርካታ አግኝቶ ለበለጠ ውጤት የሚያነሣሣው ከመሆኑም በተጨማሪ ሌሎች ሠራተኞችም አርአያነቱን በመከተል እንዲተጉ የሚጋብዝ ነው ። ስለዚህም በሥራቸው ምስጉንና ዕውቅ ለሆኑ ሠራተኞች ፣ ላስገኙት አኩሪ የሥራ ውጤት ሞራልን የሚገነቡ ልዩ ልዩ የማነቃቂያ ሽልማቶች መስጠት ለበለጠ የሥራ ውጤት የሚያዘጋጅ ጠቃሚ ዘዴ ነው ።[6]

Digitized by Google



የዕድገት መሠረቱ ሠራተኛው በሥራው የሚያሳየው ትጋትና ውጤት ነው

Digitized by Google

የእነዚህና የሌሎችም ተጓዳኝ ዘዴዎች ተግባራዊነት ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈንና መጠናከር የሚረዳና በተግባርም የተረጋገጠ ነው ።

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊንን ለማስፈን የሥራ የቅርብ ክትትልና ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ያላቸውን አስተዋጽኦ ዘርዘር አድርገን እንመልከት ።

በትክክል ለማየትና ለመረዳት እንደሚቻለው ለሥራ ዲሲፕሊን መጓደል የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ለምሳሌ፣ የሠራተኛው የንቃት ዝቅተኛነት ፣ የሥራ አመራርና አስተዳደር የተዛባ መሆን፣ እንዲሁም በሥራ አመራርና በሠራተኛው ማኅበር መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ አለመሆን ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው ። እነዚህም ችግሮች ሊወገዱ የሚችሉት እንደየባሕርያቸው ተስማሚ እርምጃ በመውሰድ ነው ። የእርምጃውም አወሳሰድ የሚፈልገውን ውጤት የሚያስገኘው የሚመለከታቸው ወገኖች በጋራ ሲሳተፉበትና ገንቢነት ባለው መልክ ሲፈጸም ነው ።

ክትትል (ቁጥጥር) ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊንን ለማስፈን አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችለው ፣ ሳያቋርጥ ሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ነው ። በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ የሚፈለገውን ውጤት ሁሉ የሚያስገኝም አይደለም ። በተጓዳኝ ተገቢ የሥራ አደረጃጀትንና እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤት አጠቃቀም መስፋፋትንም ይጠይቃል ። ዓቅም በፈቀደ መጠን ለሠራተኛው የሥራ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግንም ይሻል ። የሥራ ዲሲፕሊን ሊስፋፋና ሊጠናከር የሚችለው ከነዚህ ሁኔታዎች መሻሻልና መስተካከል ጋር ነው ። ከዚህ አንፃር ዕቅድና የሥራ አመራር ሥርዓት ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፋፋት ምን ያህል እንደሚረዱ እንመልከት ።

ትክክለኛ የሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋት ፣ አንድ የሥራ ድርጅት ፣ ያለውን ቁሳዊና የሥራ ኃይል አቀነባብሮና አቀናጅቶ በተገቢው መልክ በማደራጀት ፣ በማስተባበርና በመቆጣጠር የተፈለገውን ግብ ለመምታት የሚያስችል ፣ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ አንድ አስተማማኝ ሥልት ነው ። «በአዲሱ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሥፍራ የሚይዘው የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ በማዳበር ፣ ለሶሻሊዝም ግንባታ ቁሳዊ የቴክኒክና የባህል መሠረት ለመፍጠር በኢኮኖሚው ግንባር የሚካሄደው ትግል ነው ። በዚህ ግንባር የሚካሄደው ትግል ፍሬ ሊያስገኝ የሚችለው የሀገሪቱን ቁሳዊ ሀብት ፣ ገንዘብና የሰው ኃይል በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት ለማስተዳደር ሲቻል ብቻ ነው ። [7]

የሠራተኛውን በጐ ፈቃድና ተሳትፎ አግኝቶ ምርትን ለማሳደግና ጥራትም ለማስገኘት፣ ትክክለኛ የሥራ አመራር ሥርዓት ጉልህ ሚና አለው ። ለተፈለገው ምርትና ምርታማነት የሚያስፈልጉ ነገሮች በተገቢው ጊዜና ቦታ ተሟልተውና ተደራጅተው መገኘት ፣ ለታሰበው ምርታማነትና የምርት ጥራት መገኘት አንዱ መሣሪያ ነው ። ይህ ደግሞ ከተቀላጠፈ የሥራ አመራር የሚገኝ ነው ።«የሶሻሊስት ምርት የሥራ አመራር ፣ ማኅበራዊ ምርትን ለማሻሻልና የሠራተኛውን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ፣ በኢኮኖሚ ሕግጋት ተጨባጭ ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ፣ ለኢኮኖሚውና ከሱም ጋር ለተያያዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ዕድገት የሚደረግ ፣ዓላማ ያለው የሥራ ግፊት ነው ።» [8]

የሶሻሊስት ምርት አመራር እንደካፒታሊስቱ ሥርዓት በግለኛ ፍላጐት ላይ በተመሠረተ ፣ ሥርዓት የለሽ የኢኮኖሚ አሠራር የሚወሰን አይደለም።በዚህ ሥርዓት ምርት፣ ልውውጥና ክፍፍል የሚከናወነው ከግንባር ቀደም ፓርቲ በሚመነጭ ሳይንሳዊ አመራር መሠረት ነው ። ዓላማውም ማዕከላዊው መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት በብሔራዊው ማዕከላዊ የኢኮኖሚ

Digitized by Google

ዕቅድ ላይ በመመሥረት የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታን ማፋጠን ፣ የተመጣጠነ ብሔራዊ የምርት ዕድገት ማስገኘት ፣ የሠራተኛውን ኑሮ ማሻሻል ፣ እንዲሁም ለዚህ የሚበጅ የሥራ አመራር ሥርዓትን ማጠናከር ነው ። ይህ የአመራር ሥርዓት ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈን ቅድመ ሁኔታን የሚፈጥር ነው ።

ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መገኘት ሌላው ቅድመ ሁኔታ በሥራ ዕቅድ አነዳደፍና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረጉ እንቅስቃሴ ሠራተኛው በሰፊው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሊያደርግ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው ። እንደሚታወቀው ከሶሻሊስት የኢኮኖሚ የሥራ አመራር ባሕርያት አንዱና ዋናው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግና እራሱን በራሱ እንዲመራ ማስቻል ነው ። በዚህ መልክ ሠራተኛውን በየደረጃው ለማሳተፍ የሚቻለው ደግሞ ትክክለኛና ከቢሮክራሲያዊ አስተዳደር የተላቀቀ የሥራ አመራር ሲኖር ነው።

በራሱ በሠራተኛው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎና ድጋፍ የተነደፈ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕቅድና የሥራ አመራር መርህ በተግባራዊነቱ ላይ ብዙም ችግር አያጋጥመውም ። ምክንያቱም ዕቅዱ ከመሠረቱ በሠራተኛው በራሱ ፍላጐትና ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ነውና ።

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ከራስ ፍላጐትና አነሣሽነት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ እንደመሆኑ ፣ ሠራተኛውን በዕቅድ አወጣጥና አመራር እንዲሳተፍ የማድረጉ አስፈላጊነት፣በተሠማራበት ሥራና ኃላፊነት የራሱን ፍላጐትና አነሣሽነት ከማስገኘት ጋር የተያያዘ ነው ። ሶሻሊስት ንቃት ያለው ሠራተኛ ወቀሳንና ቅጣትን ፣ ቁጣና ግልምጫን ፣ ከሥራ መባረርን ፣ ወዘተ. ፈርቶ የሚሠራ ሳይሆን የምርቱ ውጤት ለራሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅም መሆኑን ዐውቆ ፣ ሥራውን አክብሮ ፣ ኃላፊነቱን ተረድቶ ፣ ወዶና ፈቅዶ ጠንክሮ የሚሠራ ነው ።

ለተሟላ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ ፣በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሕግ ላይ የተመሠረተ የሥራ አደረጃጀትና አመራር ቅንጅት መገኘት ሊታለፍ የማይችል ሁኔታ ነው።ሳይንሳዊ የሥራ አደረጃጀት ጥሬ ሀብትን ፣ የማምረቻ መሣሪያንና የሰው ኃይልን በተገቢው መንገድ ለመጠቀምና ምርታማነትን ለማሳደግ ፣ የማኅበራዊ ምርት ብቃትን ለማስገኘት የሚያስችል ጠቃሚ ሁኔታ ነው ። ለዚህ ደግሞ መሠረቱ ሶሻሊስት ብሔራዊ ዕቅድ ነው ። ብሔራዊ የኢኮኖሚ ዕቅድና ሳይንሳዊ የሥራ አደረጃጀት የብሔራዊ ኢኮኖሚው ዕቅድና የሳይንሳዊ አመራር ቅንጅት ውጤት ነው ። በእነዚህ ሁኔታዎች አደረጃጀት ሠራተኛው ተገቢ ተሳትፎ እንዲኖረው ከተደረገ ይህ ራሱ የሠራተኛውን የሥራ ፍላጐትና ስሜት የሚስብ ፣ የሚቀሰቅስና የእያንዳንዱን ሠራተኛ የፈጠራ ችሎታ የሚጋብዝ ይሆናል ።

ለሳይንሳዊ የሥራ አደረጃጀት ከሚያግዙ ሁኔታዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ። እነዚህም የተሟላ የሥራ ክፍፍልና የበቂ ትብብር መኖር ፣ ከሥራ ቦታ አደረጃጀትጉን የተሻለ አገልግሎት መፍጠር ፣ የተሻለና ዘመናዊ የአሠራር ዘዴንና የሥራ መሣሪያን አጠቃቀም ማስፋፋት ፣ የሥራ ግምገማን ዘዴ (ጐበዙን ከደካማው ለመለየት የሚያግዝ ትክክለኛ ዘዴ ጭምር) መዘርጋት ፣ እያንዳንዱን ሠራተኛ በሙያው፣ በችሎታውና በዝንባሌው መሠረት ማሰማራት ፣ የሠራተኛውን ሕዝብ ቴክኒካዊ የሥራ ባሕል ደረጃ ለማሳደግ የሚረዱ ዘዴዎችን መፍጠር ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ የማነቃቂያ ዘዴና ቅርፁን በየጊዜው ማሻሻል ናቸው ። [9]

በነዚህ ሁኔታዎች መሟላት ምክንያት የሥራ ውጤት በጥራት ጭምር የሚያረካ ከመሆኑ ሌላ በሠራተኛው ላይም የሚያሳድረው ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊንና ስሜት ከፍተኛ ይሆናል ።


Digitized by Google

በዚህ መልክ የተደራጀና የተቀላጠፈ የሥራ
አመራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባ
ራዊነቱን ማጠናከር ፣ ለሚፈለገው የሥራ
ዲሲ ፕሊንና የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ
መድህን ነው ። በሶሻሊስት ሥራ አመራር
ላይ የሚከሰቱ ድክመቶች ለሶሻሊስት
የሥራ ዲሲፕሊን መዳከም ምክንያቶች ይሆ
ናሉ ። ከእነዚህም የሥራ አመራር ድክ
መቶች መካከል ፣

— በተሟላ መረጃ ላይ የተመሠረተ ትክ
  ክለኛ ዕቅድ የመንደፍ ልምድ ያለ
  መኖር ፣
— ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው የሥራ
  ቦታ ያለማሰማራት ፣
— በባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ መጠቀም
  ያለመቻልና ባንፃሩ «የባለሙያ እጥ
  ረት አለብን» ማለት ፣
— የንብረት አያያዝና አጠቃቀም እንዲ
  ሁም የቁጥጥር ስልት የመቀየስ ድክ
  መት ፣
—የሥራ መሣሪያዎች ስርጭት ፣ አያያዝና
  ቁጥጥር ድክመት ፣
— ትክክለኛ የሥራ አፈጻጸም መለኪያ
  ያለመኖርና ስለዚህም ሥራና ሠራ
  ተኛን በትክክል የመመዘንና የመቆጣ
  ጠር ጉድለት ፣
— የሥራ ማነቃቂያና ማበረታቻ ሥር
  ዓት (ስልት) በአስተማማኝ መልክ
  በትክክል የመቀየስና የማደራጀት
  ድክመትና የመሳሰሉት ይገኛሉ ። [10]

እነዚህ ድክመቶች ከዕቅድና ከሥራ
አመራር ፣ በአጠቃላይም ከሥራ አደረጃ
ጀት መርህ መዛባት ጋር የተያያዙና ከዚህም
የሚመነጩ ናቸው ። በኛ ተጨባጭ ሁኔታ
በእርግጥ ከኋላ ቀርነታችንና ከአድኃሪው
ሥርዓት ቅሪቶች የሚመነጩ ድክመቶች
እንዳሉ ግልጽ ነው ። ሆኖም እነዚህን ቀስ
በቀስ እያስወገዱና የሚፈለገውን ሥር
ዓት እያጠናከሩ መሄድ ቻል ሊባል
የማይገባው የየዕለቱ ተግባራችን መሆን
አለበት ። ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም
ይህን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልፀውታል ።
በአደረጃጀትና በአሠራር ፣ እንዲሁም በሌ
ሎች መልኮች የሚከሰቱ የአሮጌው ሥር
ዓት ቅሪቶች ዛሬም አልጠፉም ። በምንገኝ
በት በሽግግር ወቅት በዚህ እውነታ ውስጥ
መኖር እንግዳ ባይሆንም በአሮጌ ቅሪቶችና
በአዲሱ አካላት መካከል ያለው ቅራኔ
መቀጠል የሚችል አይደለም ። . . .
ይህ ቅራኔ በአዲሱ አሸናፊነት መወገድ አለ
በት ። [11]

ከአጠቃላዩ የሥራ አደረጃጀት ጀምሮ
በየደረጃው የሥራ ዕቅድ ፤ አመራርና አደረ
ጃጀት በየወቅቱ እየታረመና እየተስተካ
ከለ ፣ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር በተገናዘበ
ሁኔታ መራመድ ለድክመት መወገድ አንድ
መንገድ ነው ። ድርጅቶች የሥራ መዋ
ቅራቸውን ፣ የሥራ አመራር ስልታቸውን፣
የሥራ አደረጃጀታቸውን ፣ የሥራ ደንቦቻ
ቸውንና የሥራ አፈጻጸም መመሪያዎቻቸ
ውን በየጊዜው መገምገም ፣ መከታተልና
ብቁነታቸውን መመዘን ይኖርባቸዋል ።
ለበለጠ ምርታማነት አመቺነት ያለው
የሥራ ስልት እየቀየሱ ፣ አመራርን ወቅ
ታዊ እያደረጉ መሄድ ፣ የአሠራርን መሰና
ክሎች ማስወገድ ፤ ተስማሚ መመሪያዎ
ችን ማመንጨት ፣ ጤናማ የሥራ አካባቢ
የሚፈጥር የአመራር ስልት መከተል ፤ ምር
ታማነትን ለማሳደግ የሚረዳ የሥራ ማነ
ቃቂያ ሥልት መቀየስ ፣ ማደራጀትና
ተግባር ላይ ማዋል ወዘተ- ከጥሩ የሥራ
አመራር የሚመነጩ ፣ ለምርታማነትና ለም
ርት ዕድገት ፣ ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን
መጠናከር የሚበጁ ዘዴዎች ናቸው ።

እዚህ ላይ የሠለጠነ የሰው ኃይል አስፈ
ላጊነት ሳይጠቀስ የማይታለፍ ጉዳይ ነው።
የታለመው ግብ ሊመታ የሚችለው ብቁ
ባለሙያዎችም ሲገኙ ነው ። በብሔራዊ
ኢኮኖሚው ግንባታ ትግል ውስጥ የሠለ
ጠነ የሰው ኃይል አስፈላጊነትን ሌኒን ሲያ
ስገነዝብ «በየሥራ ዘርፉ ፤ በየወቅቱና በየል


Digitized by Google




የሥራ ዲሲፕሊን መግለጫው ምርታማነት ነው

Digitized by Google

ምዱ ዘርፍ የተካኑ ባለሙያዎች አመራር ከሌለ ወደሶሻሊዝም የሚደረገው የሽግግር ትግል ውጤት ሊሳካ አይችልም ፤ ምክንያቱም ከካፒታሊዝም ጋር ሲነፃፀር ፣ ሶሻሊዝም ለሥራ ምርታማነት ዕድገት የነቃና ያወቀ ሠራተኛ ሕዝብ በብዛት ይጠይቃልና [12] ።» ብሏል ።

የሥራ አመራር ተግባር በሙያ ከሠለጠኑና ልምድ ካካበቱ ዜጎች የሚመነጭ እንደመሆኑ የማይለየው የሥራ ዲሲፕሊን መስፈንና የምርታማነት ዕድገት ከዚህ ጋር የተቆራኘ ነው ። ካለንበት ኋላቀርነት ተላቀን፣ በኢኮኖሚ ግንባታችን ተራምደን ሶሻሊዝምን ለመመሥረት በሚደረገው የትግል ሂደት ብቁ የሥራ አመራር የሚሰጡ ዜጎች መኖራቸው አስፈላጊ ነው ።

በእርግጥ በሙያ የተካኑ ሰዎችን ማፍራት ጊዜ የሚጠይቅ ተግባር ቢሆንም አስፈላጊነቱ ደግሞ ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊ ጉዳይ ነው ። ይህ ነው በተለይ ታዳጊ ሀገሮች ሶሻሊስት ግንባታ ሲጀምሩ ወይም ለግንባታው መሠረት ለመጣል ሲታገሉ የሚገጥማቸው አንዱ ዓቢይ ችግር ። ለምሳሌ ሶቭዬት ኅብረት በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታዋ መነሻ ወቅት ተደቅኖባት የነበረ አንዱ ችግር ያሸው የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ነበር ። እ. ኤ. አ. በ1927 በታላላቅ እንዱስትሪ ውስጥ ብቻ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በተለየ የሙያ ትምህርት የሠለጠኑ ከ31,000 በላይ የሚሆኑ ሠራተኞች ይፈለጉ ነበር ። በዚያ ዓመት በሀገሪቱ ያሉት ት/ቤቶች በዚህ ደረጃ አሠልጥነው የሚያስመርቋቸው ባለሙያዎች ቁጥር ግን 5,305 ብቻ ነበር ። እንዲሁም በሶቭየት የኬሚካል ኢንዱስትሪ ውስጥ ከሚገኙት ለእያንዳንዱ ሺህ ሠራተኛ ሦስት ወይም አራት ኢንጂነሮች ብቻ ነበሩ ። በአንፃሩ ግን በተመሳሳይ ወቅት በጀርመን ለተመሳሳይ አንድ ሺህ ሠራተኞች 34 ኢንጂነሮች ይገኙ ነበር ። [13]

ይህ ሁኔታ ሶቭየት ኅብረት በወቅቱ ከመሀል አውሮፓ ሀገሮች ምን ያህል ወደኋላ እንደነበረች የሚያመለክት ነው ። ይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩን ተወጥታዋለች ። በቂ የሥራ አመራር ፣ የተቀናጀ የሥራ አደረጃጀትና የሠራተኛው የነቃ ተሳትፎ መገኘት ነው ሶቭየት ኅብረትን ዛሬ ላለችበት የዕድገት ደረጃ ሊያበቃት የቻለው ።

## ሶሻሊስት የሥራ ውድድር

«ሶሻሊስት የሥራ ውድድር (ኤሚዩሊሺን) የሠራተኛውን የፈጠራ ሥራ ፍላጎትና ስሜት በማነሣሣት፤በማንኛውም የሥራ ዘርፍ ሶሻሊስት ምርትን ለማሳደግ የሚረዳ ማኅበራዊ ክስተት ነው ። [14]

ሶሻሊስት የሥራ ውድድር በሶሻሊስት ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ከብዝበዛ ነፃ የሆነ የሥራ አዲስ ባሕርይን የሚገልጽ ተጨባጭ የሆነ ነባራዊ ሕግ ነው ። ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ የምርት ሰድገት መፋጠን ሠራተኛውን ማነሣሻ አንዱ ኃይል ወይም ዘዴ ነው ። ቁሳዊና ባህላዊ ሀብትን በመገንባት እንቅስቃሴ ውስጥ የመጨረሻውን ከፍተኛ የምርት ውጤት ለማግኘት የሠራተኞች የሥራ እንቅስቃሴ የሚገለጽበትን የመጨረሻ ከፍተኛ የሥራ ምርታማነት የሚገኝበት መንገድ ነው ። ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ዕቅድ ግብ መምታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የምርትን መጠንና ጥራት ለማሻሻል ፣ ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያ አጠቃቀምን ለማፋጠን ፣ የማያስፈልግ የሰው ጉልበት ፣ የሥራ ጊዜና ንብረት መባከንን ለመቀነስ የሚደረግ የሠራተኛው የፈጠራ ሥራ መግለጫ ነው ።« [15]

የሥራ ውድድር በካፒታሊስትም ሆነ በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ አለ ። ይሁን እንጂ የውድድሩ አመራርም ሆነ ውጤቱ በየሥርዓቱ የተለያየ ነው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት የሥራ ውድድር የሠራተኛውን ጉልበት የመበዝበዣ ሥልት ነው ። የው



Digitized by Google

ድድር ውጤት የሆነው ምርት ከፍተኛው ድርሻ በአሠሪው እጅ የሚገባ እንጂ ለአምራቹ ጥቅም የሚውል አይደለም ። በመሆኑም የጥቅሙ ባለቤት አምራቹ ሳይሆን ካፒታሊስቱ ነው ። ስለዚህም በዚህ ሥርዓት የሥራ ውድድር አሠሪው ሠራተኛውን በመበዝበዝ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ባለው ፍላጎትና ዓላማ ላይ የተ መሠረተና ለዚህ ሲል ከሚያደርገው ጥረት የሚመነጭ ነው ። ሌኒን ይህን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጾታል ። «በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ውድድር ማለት - - -በብዙኀሀኑ ሠራተኛ ላይ ለማመን የሚያስቸግር ጭካኔና ጭቆና የሚፈጸምበት ፣ የበለጠ ብዝበዛ የሚካሄድበት ፣ አብዛኛው ሠራተኛ በራሱ ፍላጐት ሳይሆን ፤ የማስፈራሪያ መንፈስ ባዘለ ቅስቀሳ ተገዶ የሚወዳደርበት ሁኔታ ነው ። »[16] በዚህ ሥርዓት የሥራ ውድድር ፣ ምርትንና ጥራትን አሳድጎ የሠራተኛውን ሕይወት የሚያሻሽልና ከችግር የሚያወጣ ሳይሆን ፣ ወደባሰ ብዝበዛና የችግር አዘቅት የሚከት ነው ።

በአንፃሩ ግን በሶሻሊዝም የሥራ ውድድር የተለየ ትርጉም ፣ የተለየ ሚና አለው። ሠራተኛው ሙሉ የሥራ ችሎታውንና ስሜቱን በፍላጎት የሚገልፅበት ፣ በውጤቱም ኑሮውን የሚያሻሽበልት ዘዴ ነው ። ሌኒን የሥራ ውድድር በሶሻሊዝም ያለውን ሚናና ከካፒታሊስቱ ሥርዓት የሥራ ውድድር ዓይነት ጋር ያለውን ልዩነት እንደሚከተለው ገልጾታል ።

*. . . ሶሻሊዝም ለመጀመሪያ ጊዜ ለሶሻስት የሥራ ውድድር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ሠራተኛውን ሕዝብ በብዛትና በስፋት በማሳተፍ ልዩ የፈጠራ ችሎታውን በፍላጐትና በስሚት በተከከል በተግባር ሊያሳይና ሊያዳብር የሚችልበት ፣ ለፈጠራ ሥራ የሚያነሣሣበት ሰፊ ዕድልና መድረክ አዘጋጅቷል ።*

*... በዚህ ሥርዓት የሥራ ውድድር ሠራተኛው የሥራ ችሎታውን ሙሉ ለሙሉ በተ ጨባጭ የሚገልጥበት ፣ ለብዝበዛና ለበዝባዥ ቀንጣት ታክል የማይጐበድድበት ፣ መብቱንና ነፃነቱን በአጠቃላይ ሙሉ ሰብዕናውን የሚያስከብርበት የሥራ መስክ ሆኗል ።*[17]

በሶሻሊስት ሥርዓት የሥራ ውድድር ውጤት ባለቤት ራሱ አምራቹና በአጠቃላይም ኅብረተሰቡ ነው ። የሶሻሊስት የሥራ ውድድር ዓላማ የምርትን ጥራትና መጠን በማሳደግ ፣ የሠራተኛውን (ከዚህም ተያይዞ የመላውን ኅብረተሰብ) ኑሮ ማሻሻልና ማበልፀግ በመሆኑ ፤ የውድድር አሸናፊ የሚሆነው ታታሪ ድርጅትም ሆነ ሠራተኛ ፤ የሁለት ጥቅምና ድል ባለቤት ነው ። ይኸውም በአሸናፊነቱ በግል ከሚያገኘው የሥራ ማነቃቂያ ሽልማት በተጨማሪ በኅብረተሰብ አባልነቱም ፤ የራሱ ምርት ውጤት ተጠቃሚ ነው ። በዚህ ሥርዓት የምርት ውጤት እንደካፒታሊስቱ ሥርዓት በጥቂት ግለሰቦች ኪስ የሚገባ ሳይሆን ፤ ለኅብረተሰቡ የጋራ ጥቅምና ብልጽግና የሚውል ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት ሠራተኛው ለሥራ ያለው ፍቅርና የራስ አለኝነት በዚሁ የምርት ባለቤትና የውጤቱ ተጠቃሚ ራሱ አምራቹ በመሆኑ እውነታ ላይ የተመሠረተ ነው ። ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈን ዋና መሠረትም ይኸው ዕውነታ ነው ።

የሥራ ውድድር ባሕርይ የእያንዳንዱ ሠራተኛ በንቃትና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነፃ የፈጠራ ችሎታ መግለጫ ነው ። ለዚህም ነው ለነፃ ችሎታ መዳበር አመቺ ሁኔታን የሚያስገኘው የሥራ ውድድር በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ የተከሰተው በሶሻሊዝም ነው የሚባለው

ለሶሻሊስት የሥራ ውድድር መስፋፋትና መጠናከር ሌላው አጋዥ ማኅበራዊ ሁኔታ የሠራተኛው ንቃትና አመለካከት የላቀ መሆኑ ነው ። በሌኒን አባባል « የኮሚኒዝም መጀመሪያ (መነሻ) ተራ ሠራተኞች ለኅብረተሰቡ የጋራ ፍላጎት ፣ ጥቅምና ደህንነት ማሰባቸውና ለዚህ መቆማቸውን



Digitized by Google

በአስተማማኝ ማሳየታቸው ነው ። » [18]

ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ሠራተኛው ለራሱ ፍላጎትና ጥቅም ብቻ ሳይሆን ዕውቀቱንና ጉልበቱን ለኅብረተሰቡ ፍላጎት በማዋል ፣ በጋራ ተወያይቶና ተረዳድቶ በመሥራት ፣ ዕውቀትንና ልምዱን ለሌሎች ሠራተኞች በማካፈል ባሕል ላይ የተመሠረተ ነው ። በመሆኑም ከምቀኝነት ፣ ከተንኮለኛነት ፣ ከልምድ መደባበቅና ከሌሎችም ጐጂ አዝማሚያዎች የጸዳ ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት የሚታዩት የሥራ ልምድን ፣ የፈጠራ ችሎታንና ዕውቀትን የመደበቅ ድርጊቶች በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ቦታ አይኖራቸውም ። እነዚህ ድርጊቶች የሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ሲዳብር ከዕለት ወደ ዕለት ከሠራተኛው አስተሳሰብ እየጠፉና እየተወገዱ ይሄዳሉ ።

ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ከፍተኛ የምርት ውጤቶችን በማስገኘት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መጠንከር ያለው አስተዋጽኦም ከፍተኛ ነው ።

—በማምረት ተግባር ውስጥ እያንዳንዱ የሥራ ድርጅትና ሠራተኛ በየሥራ ዓይነቱ የተገኘውን አኩሪ የፈጠራ ሥራና የምርት ውጤት ፣ የፈጠራውንም ዓይነት ሆነ ያስገኘውን ውጤት ለኅብረተሰቡ በማስተዋወቅ ፣ ሠራተኛውን (የፈጠራውን ባለቤት) ለበለጠ የፈጠራ ተግባር ከማበረታታቱም በላይ ፣ ሌሎች ሠራተኞችንም ለጥሩ የሥራ ውጤት ያነሣሣል ፣ ይቀሰቅሳል ፤

—በሠራተኛው መካከል የጋራ መደጋገፍና ትብብርን ያጠናክራል ፤ በጋራና በቡድን ለሚገኝ የፈጠራ ሥራ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።፤

—ደካሞችና ሰነፎች የታታሪ ሠራተኞችን አርአያነት እንዲከተሉና የሥራ መንፈሳቸው እንዲነሣሣና እንዲበረታታ ያግዛል ፤ [19] . . . በሶሻሊስት ኢኮ



ቁሳዊና ሞራላዊ ማበረታቻ ለበለጠ ምርታማነት



Digitized by Google

ኖሚ ግንባታ የሥራ ውድድርን ጠቃሚነት ሌኒን ሲገልጽ « በሶቭዬት ኅብረት መንግሥት የኢኮኖሚ ግንባታ ተግባራት ውስጥ የሶሻሊስት የሥራ ውድድር አደራጃጀት ተግባር ቅድሚያ መያዝ አለበት » ብሏል ።

ሶሻሊስት የሥራ ውድድርን ለማደራጀት፣ ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚበጁ መሠረታዊ ዘዴዎችንና መርሖዎችን ሌኒን እንደሚከተለው ገልጧቸዋል ።

—በእያንዳንዱ የሥራ ድርጅት ወይም ሠራተኛ የተገኘውን አኩሪ የፈጠራ ሥራ ውጤትና የፈጠራውን ባለቤት ለሕዝብ በማስተዋወቅ ድርጅቱን ወይም ሠራተኛውን ለበለጠ ፈጠራና ሥራ ማነቃቃት ፣ ሌሎችም ድርጅቶችና ሠራተኞች አርአያነታቸውን እንዲከተሉ ማድረግ ፤

—የውድድሩን ውጤቶች ማለትም አንዱን የፈጠራ ሥራ ውጤት ከሌላው ጋር ማወዳደርና ብቃቱን መለየት ፤

—በውድድር የተገኘው የሥራ ውጤት ሊደጋገም የሚችል መሆኑን ማወቅ ።[21] መርሖዎቹን ተግባራዊ የማድረጉን ሁኔታም ሌኒን « የሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ታላቅ የማሠልጠኛ ት/ቤት ነው»[22] ብሎታል ።

ሶሻሊስት የሥራ ባሕል በዳበረበት በሶቭየት ኅብረት ፣ ሶሻሊስት የሥራ ውድድር በየሥራ ዘርፉ እጅግ በበለፀገ ሁኔታ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ ይገኛል ። በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኮርያም «ዛሬ ከትናንቱ የበለጠ አምርት! ነገ ደግሞ የዛሬውን እጥፍ ለማድረግ ታገል!» በሚሉ መፈክሮች ይገለፃል ። በሩማኒያም «የሀገሩ የምርት ድርጅቶች ቁንጮ ! የብርጌዶች ቁንጮ !» የሚባሉ ስያሜዎች አሉት ። በቼኮዝሎቫኪያም « እንደሶሻሊስት ሥራ! እንደሶሻሊስት ኑር ! »በሚሉ መፈክሮች ይመራል ። በቡልጋሪያ ፣ በሀንጋሪ ፣ ቬትናምና በኩባም እንዲሁ በይዘታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ማስፋፊያና ማጠናከሪያ አገላለጾች አሉ ።

## ለሥራ ዲሲፕሊን መስፈን የሠራተኛ ማኅበራት ሚና

ሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን ሊሰፍን የሚችለው እያንዳንዱ ሠራተኛ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በውል ተገንዝቦ ፣ እርሱ ለኅብረተሰቡ ፣ ኅብረተሰቡም ለእርሱ መሆኑን ተረድቶ ፣ በፍላጎትና በራሱ አነሣሽነት ለራሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅም በንቃት ሲሰማራ ነው ። ይህን ዓይነቱን ሠራተኛ ዜጋ የመቅረፁና የማስገኘቱ ኃላፊነት ከፍተኛው ድርሻ በሠራተኛ ማኅበራት የሚጣልና በነዚህ መድረኮች አማካይነት የሚገኝ ነው ። በማኅበራቱ አማካይነት የሥራ ዝንባሌውና ዲሲፕሊኑ በትክክል የተቀረፀ ሠራተኛ ዜጋ ፣ ኢኮኖሚ ገንቢ ብቻ ሳይሆን አልፎም ሀገርንና ፣ አብዮትን የማስከበር የዓለም ሰላምንና የሠራተኛውን ዓለም አቀፋዊ አንድነትና መረዳዳት መርህ በማስፈን ረገድም ከፍተኛ ድርሻ አለው ።

ሠራተኛው ጥረቱ ፍሬያማ ይሆን ዘንድ በዕቅድ አወጣጥና በአመራር ተሳትፎውን የሚገልፀው በማኅበራቱ አማካይነት ነው ። የሠራተኛው ማኅበራትና የየሥራ ድርጅቱ አመራር አንድ ዓላማና የጋራ ፍላጎት ያላቸው እንደመሆኑ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በመተባበር ላይ የተመሠረተ ነው ። ሁለቱም ወገኖች የኅብረተሰብ መሪ የሆነውን የፓርቲውን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የተሰለፉ ፣ ምርትን በሚመለከት ሁለቱም ወገኖች ለሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሕግጋት ተገዥ ናቸው ። በሶሻሊስት መንግሥትና በሠራተኛው ማኅበራት መካከል ያለው ግንኙነት በተቃርኖ ላይ ሳይሆን በትብብርና በአንድነት ላይ የተመሠረተ ነው ። የራሱ የሠራተኛው መንግሥት ነውና ፣ ይህም በጎ ሁኔታ ለሶሻሊስት የሥራ



Digitized by Google

ዲሲፕሊን መከበር ከፍተኛ አጽስተዋጽኦ አለው ።

ማኅበራቱ ከቀሙለት የእኩልነትና የጋራ ብልፅግና ዓላማ አኳያ በውስጣቸው ያቀፏቸውን ሠራተኞች የማምረት ብቃት የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው ። የሠራተኛ ማኅበራት ለሠራተኛው ሁለገብ የሆነ ሙያና ዕውቀት መቅሰሚያ ፣ የሥራ ፍቅር ማዳበሪያ ፣ የፈጠራ ሥራ ማስፋፊያ መድረኮች ናቸው ። ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚታገሉ የሠራተኞች ማኅበራት መመሪያዎች ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ ፣

—ሠራተኞችን የሥራ አመራር ጥበብ ማስተማር ፣

—የምርት ባለቤትነታቸውን ማስገንዘብ ፣ በመንግሥታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በስፋት እንዲሳተፉ ማድረግ ፣

—ሕጋዊ መብትና ግዴታቸውን ማስከበር ፣

—ለሠራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው የትምህርትና የባህል ማስፋፊያ መድረኮችን ማደራጀት ፣

—በዓለምዓቀፋዊ የሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግና የሠራተኛውን መደብ የትግል አንድነት ማጠናከር ፤ [22]

በሶሻሊስት ሀገሮች የሠራተኛ ማኅበራት ከኢኮኖሚው የሥራ አመራር አካላት ጋር በመተባበር ፣ በየዘርፉና በየደረጃው ባሉ የሥራ ድርጅቶችና ሠራተኞች መካከል ሶሻሊስት የሥራ ውድድርን በማቀድ ፣ በማደራጀትና በመምራት ፣ የሠራተኛውን ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ የፈጠራ ሥራ በማበረታታትና የሙያ ሥልጠናን በማደራጀትና በማስፋፋት ወዘተ. ለሶሻሊስት የምርት ዕድገትና ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈን ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታሉ ። በምርት ተግባር ዘመናዊ የቴክኒክ ዕውቀትና ልምድን በማስፋፋት ፣ በልዩ የፈጠራ ሥራና በሌላም የሥራ ልምድ ግንባር ቀደም ታዋቂነት ያላቸውን ሠራተኞች ለሠራተኛው ሕዝብ በማስተዋወቅ ፣ እነዚህ አዳዲስ የተገኙ የፈጠራ ውጤቶች በየሥራ ድርጅቱ ሊስፋፉ የሚችሉበትን ሥልት በመቀየስ ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በግብርናና በሌሎችም ብሔራዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለተሻለ ምርታማነትና የምርት ጥራት መገኘት የሠራተኛው ማኅበራት የሚያደርጉት ዕገዛ የላቀ ነው ። ከማኅበራት መሪዎችም መካከል ብቁ የሥራ ኃላፊዎች ፣ አደራጆች ፣ አስተባባሪዎች ይፈልቃሉ ። የሠራተኛውን ማኅበራት «የኮሚዩኒዝም ት/ቤት» የሚያሰኛቸው አንዱ ዓይነተኛ ባሕርይም ይህ ነው ።

በአገራችን የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ከኢሠፓ በሚያገኘው አመራር አማካይነት ፣ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ካለበት ኋላቀርነትና ተፈጥሮ ካስከተለበት ችግር ለመውጣት የሚያደርገውን ትግል አስተባብሮ የመምራት ኃላፊነት የተጣለበት የሠራተኛው መድረክ ነው ። በሥሩ ባቀፋቸው ማኅበራት አማካይነት ሠራተኛው መብትና ግዴታውን በትክክል እንዲወጣ ፣ ማንቃት ፣ ማደራጀትና ማንቀሳቀስ ከመኢሠማ የሚጠበቅ ከፍተኛ ተግባር ነው ። ማኅበሩ ከሚታገልላቸው ዓላማዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

የሀገሪቱ ዓቅም በፈቀደ መጠን የሠራተኛው መብትና ጥቅም እንዲከበር ፣ ማኅበራዊ ፍላጐት ደረጃ በደረጃ እንዲሟላ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ፤

. . . ሠራተኛው የሥራ ዲሲፕሊንን ፣ የፈጠራ ችሎታውንና ምርታማነቱን በማዳበር ማኅበራዊ ይዞታን በማስፋፋትና ግለኝነትን በመዋጋት ፣ በተሠማራበት የሥራ መስክ ሁሉ ለምርት መሣሪያዎች አስፈላጊውን እንክብካቤና ጥንቃቄ በማድረግ ፣ ለሀገሪቱ ምርት በጥራትና በመጠን ማደግ ፣ ለክፍፍልም በትገቢው መንገድ ተግባራዊ መሆን የበኩሉን ድርሻ በማበርከትና በአጠቃላይ



Digitized by Google

በብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ያለውን ተሳትፎ ይበልጥ በማጠናከር ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማድረግ ፣

. . . ሠራተኛው የወዛደራዊ ዓለማቀፋዊነትን መርህ በመከተል ፣ . . . ለዓለም ሰላም ፣ ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት ፣ ለሕዝቦች ነፃነትና ለጋራ ብልጽግና የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ማሰለፍ ። [23]

በመኢሠማ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥም የሠራተኛ ማኅበራትን ተግባርና ኃላፊነት ከሚጠቁሙ ነጥቦች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል ፤

ሠራተኛው በድርጅቱ አማካይነት የወዛደሩ ርዕዮተዓለም የሆነውን ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን እንዲያጠና አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ንቃተ ኅሊናውን ማዳበር፣ የሀገሪቱን ዕድገት ለማፋጠንና ምርት እንዲዳብር ለማድረግ እያንዳንዱ ሠራተኛ በንቃትና በፈቃደኝነት በመነሣት በተሰማራበት የሥራ መስክ የሶሻሊስት የሥራ ውድድርን ባህል እንዲያዳብርና ሙያውንም እንዲያሻሽል አመቺ ሁኔታ መፍጠር ፣ በባለቤትነትም መምራት ፤

. . . ሠራተኞች በሚሠሩበት ድርጅት አስተዳደር ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ፤

. . . ሠራተኛው የሀገሪቱን ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ፣ እንዲሁም ከድርጅቱ አስተዳደር ጋር የሚያደርጋቸውን የኅብረት ስምምነቶች በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እንዲያውል ማበረታታትና ማገዝ ፣ ተገቢውን አመራር መስጠት ፤

. . . ሠራተኛው በተሰማራበት የሥራ መስክ ሁሉ የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት በጥንቃቄና በእንክብካቤ ተይዞ በሥራ ላይ እንዲውል ፣ የምርት ውጤት ጥራቱ ተጠብቆ በየጊዜው እንዲዳብርና በትክክል ለኅብረተሰቡ እንዲዳረስ ፣ ምዝበራና ብኩንነትን በመዋጋት የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ፣ [24]

መኢሠማ የሚያወጣቸው ደንቦችና የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች የሠራተኛውን ጥቅም የማስከበርና ሠራተኛውም ለመላው ኅብረተሰብ ታሪካዊ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ለተልእኮው ውጤታማነትም የእራሱ የሠራተኛው የነቃ ተሳትፎ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ። ሠራተኛው ይህን ወሳኝ ታሪካዊ ኃላፊነቱን በብቃት ይወጣ ዘንድም መተማመኛ ሊሆን የሚችለው ማወቅና መገንዘቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ተገቢ ትኩረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው ።

የሥራ ዲሲፕሊን በትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ይመሠረታል ። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ሊወጣው የሚገባውን ኃላፊነት በትክክል ተረድቶ ለሥራ መቆም ሲችል ነው የሥራ ዲሲፕሊን በሠራተኛው ዘንድ እየሠረፀ የሚሄደው ። የማኅበሩ ዓላማ በሠራተኛው ፍላጐት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ የማኅበሩ ፣ የደንቦቹና የውሳኔዎቹ መፈጸም ወይም አለመፈጸም ፣ የሠራተኛው ፍላጎት መሟላት ወይም አለመሟላት ማለት ነው ። መኢሠማ በሥሩ ያሰባሰባቸውን ሠራተኞች ከዚህ አኳያ የባህል ደረጃቸውን ያለማቋረጥ ከፍ እያደረገ መሄድ ይኖርበታል ።

በየሥራ ድርጅቱ የሚገኙ የኢሠፓ ካድሬዎች ፣ የፓርቲው አባላት እና አካላት በሙሉ ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈንና መጠናከር ግንባር ቀደም ኃላፊነት ያለባቸው እንደመሆኑ ፣ በተግባራዊ አርአያነት ቀድመው መገኘት አለባቸው ። ስለ ሥራ ዲሲፕሊን ከመናገር ባሻገር በአርአያነት ማስተማር የበለጠ ውጤት ያለው መሆኑንም መገንዘብ ያሻል ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

የምንገኘው በሽግግር ወቅት እንደመሆኑ በሀገራችን ሶሻሊስታዊ የሥራ ዲሲፕሊንን በተሟላ መልኩ ለማስፈን የማያ



Digitized by Google

ስችሉ ብዙ እንቅፋቶችና ድክመቶች ገጥ መውናል ። የምርት መሣሪያዎች የሕዝቡ በሆኑባቸው ፋብሪካዎችና በመንግሥት እርሻዎች የሥራ ነገንውን ውስጥ ለሶሻ ሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መሰፈን የሚ ረዱ ኢኮኖሚያዊ አመች ሁኔታዎች የተፈ ጠሩ ቢሆንም የሥራ አደረጃጀትና አመራር ችግሮች ለምሳሌ፣ የአመራር ችሎታ ማነስ፣ ብቁ ሠራተኞችን መለየትና አስፈላጊውን ቁሳዊና ማኅበራዊ ድጋፍ ለመስጠት አለ መቻል ፣ የቅርብ ክትትል ጉድለት ወዘተ - መኖራቸው የታወቀ ነው ። በሠራተኛው (በሁሉም ሠራተኞች ባይሆንም) መካከ ልም የአብዮቱን ዓላማ በትክክል መረዳ ትና በራስ አነሣሽነትና ፍላጎት የሥራ ዲሲ ፕሊን ማክበር ችግር ይታያል ። መኢሠ ማም ሆነ መንግሥታዊ የሠራተኛ አስተዳ ደር አካላት እነዚህን ድክመቶች ለማስወገ ድና ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን መስፈን የሚበጁ ሁኔታዎችን ሁሉ ለመፍጠር መታ ገል ይጠበቅባቸዋል ። ይህ ጥረት ደግሞ በመሠረቱ ዘላቂ ውጤት ሊያስገኝ የሚች ለው ለሶሻሊስት የሥራ ዲሲፕሊን እንቅፋት የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ለማስወገድ ጭምር መሆኑ ግንዛቤ አግኝቶ ሊተኮርበት ይገባል ። በዚህ መሠረት በአንድ በኩል ሠራተኛው በንቃት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ታሪካዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለጥ ረቱ ፍሬያማነት ዓቅም በፈቀደ መጠን ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት ማድረግ ተገቢ ይሆናል ። ይህ ከሆነ የሥራ ዲሲፕሊን ሊስ ፍንና የመላውን ሕዝብ ቁሳዊና ባህላዊ ሕይወት ለማሻሻል የሚያስችል ውጤት ለማግኘት ይችላል ። በዚህ መሠረት ለፍ ላጐቶቻችን ሁሉ መርካት በሁሉም በኩል ኃላፊነትን ለመወጣት ያልተቆጠበ ጥረት ከማድረግ ፣ ተግቶ ከመሥራትና በሥራ ውጤት ከመተማመን የተሻለ አማራጭ የለም ።

## የግርጌ ማስታወሻ

1. M. Rosenthal and P. Yudin, etds., *A Dictionary of Philosophy*, p. 234.
2. Great Soviet Encyclopedia, Third Edition Vol. 8.
3. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 289 ።
4. Klause Weise, *What is Work Like in a Nationally Owned Factory,? Information from GDR*, November 1947, p. 23.
5. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 289 ።
6. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 289 ።
7. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የ1977—1976 የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ፣በኢሠፓ መሥራች ጉባኤ የጸደቀ አዲስ አበባ መስከረም 1977 ፤ ገጽ 7
8. M. I. Volkov, edt. *A Dictionary of Political Economy* (Moscow: Progress Publishers, 1985), p. 321.
9. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 321 ።
10. የ10 ዓመት ልማት መሪ ዕቅድ ረቂቅ ጥራዝ አዲስ አበባ መጋቢት 1977 ገጽ 767።
11. ጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበርና የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ፲ኛ



Digitized by Google

መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት አዲስ አበባ ፣ መጋቢት 1977 ቅጽ ፤ 77—02—04/77 ገጽ 20።

12. Mai Volkov, *The Trainning of Personnel for Industry*, Novosti Press Agency, Moscow, 1983, p. 16.

13. ከላይ ለየተጠቀሰው ገጽ 51 ።

14. *A Dictionary of Philosophy* p. 418.

15. Great Soviet Encyclopedia, Third Edition 24, p. 236.

16. V.I. Lenin, *A Great Beginning, How to Organize Competition* Progress Publishers, Moscow, 1978, p. 40.

17. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 40—41 ።

18. A Dictionory of Philosophy, p. 418.

19. Great Soviet Encyclopedia, Vo. 24, p. 237.

21. Fyodor Mevedev, Soviet Trade Unions, Yesterday-Today-Tomorrow (Profizdat Publishers) Moscow, p. 24.

22. የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት መተዳደሪያ ደንብ ፣ አዲስ አበባ ሰኔ 1974 ፤ ገጽ 1—2

23. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ፡ 2—3 ።

25. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ ረቂቅ (1977--1986 አዲስ አበባ ፤ ጳጉሜን 1976 ፤ ገጽ፡ 26—28 ።



Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

8SPP

# መስከረም

▲ የአፍሪካ የኢኮኖሚ ችግርና ለአዲሱ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚደረገው ጥረት

▲ መንደር ምሥረታ ፣ የሦስት ክፍላተ ሀገር ልምድ

▲ የአካባቢ ትምህርት ጠቀሜታ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 6 ቁጥር 26
1978

Digitized by Google

33254

Digitized by Google



# መስከረም

ቅጽ 6 ቁጥር 26
ሠኔ 1978

## ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

## ማውጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገጽ ........................................ 3
- የአፍሪካ የኢኮኖሚ ችግርና ለአዲሱ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚደረገው ጥረት ........................ 9
  —አሕመድ መሐመድ
- መንደር ምሥረታ የሦስት ክፍላተ ሀገር ልምድ ........................ 38
  —በላይነህ አሰፋ
- የአካባቢ ትምህርት ጠቀሜታ ........................................ 65
  —አበበ ወርቁ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

**የዝግጅት ገጽ**

# ዲሞክራሲ፤ ዲሞክራሲ …ሁሉም ዲሞክራሲ?

በሰው ልጅ የፖለቲካ ሕይወት ታሪክ ውስጥ ያለአገባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ ከኖሩት ጽንሰ ሐሳቦች መካከል አንዱና በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀስ የሚችለው «ዲሞክራሲ» ነው። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በተለይ ዛሬ ብዙኀንን የሚበዘብዙና ከሀገራቸውም ድንበር ባሻገር የሌሎች ሕዝቦችን ሀብት የሚመዘብሩ፣ ሌላው ቀርቶ በዘረኛነት ጭምር ግፍ የሚፈጽሙ፣ ከዚህ ሁሉ ተጽዕና ለመላቀቅ የሚታገሉ፣ የሀገርን ሀብት ለመላው ሕዝብ በእኩልነት መጠቀሚያ ያደረጉ፣ ሁሉም ስለዲሞክራሲ ያወሳሉ። ዲሞክራሲ በየዕለቱ ሲነሣ የሚውልና ብዙዎችም ጠንቀቀው የተረዱት የሚመስላቸው፣ ይልቁንም ተራ መገባቢያ ተደርጉም የሚቆጠር ነው። ላይ ላዩን ሲያዩት በእርግጥ ይመስላል። ነገር ግን በጥሞና ሲታይ ይዘቱ መግባባት የሌለበት ከመሆኑም ባሻገር በመሠረቱ በሀገሮች ውስጥና በመንግሥታት መካከል የሚከሰቱ ውዝግቦችና ግጭቶች ከእሱ በትክክል ተግባራዊ አለመሆን የሚመነጩ ናቸው።

ዲሞክራሲ በጥሬ ትርጉሙ፣ ከግሪክ «ዲሞስ» ሕዝብ እና «ክራቲያ» አገዛዝ ከሚሉ ሁለት ቃላት መንጭቶ የሕዝብ ወይም የብዙኀን አገዛዝን ስለማመልከቱ አጠቃላይ ስምምነት ያለበት ቃል ነው። ጥቂቱ ለብዙኀን ተገዢ የሚሆኑበት፣ የዜጎች ነፃነትና እኩልነት የሚከበርበት የሥልጣን ዓይነት ስለመሆኑ መግባባት አልጠፋም። ችግሩ በቀርጽ ይህን ለሚመስሉ ነገር ግን በይዘት ተቃራኒ ለሆኑ ሁኔታዎችም መገለጫ ማድረጉና አጽንተ ማቀያ ለማድረግ መፈለጉ ላይ ነው።

የጽንሰ ሐሳቡ አመንጭ በሆኑት ጥንታዊ ግሪኮች ዘንድ ዜጋ በመባል የሚታወቁት ባሪያ አሳዳሪዎች ሲሆኑ ባሮች ከመገልገያ ቁሳቁስ ተለይተው አይታዩም ነበር። በዚሁ መሠረት የሕዝብ አገዛዝ ወይም የዲሞክራሲ ባለመብትና ተሳታፊ የሚሆኑት ባሪያ አሳዳሪዎች ብቻ ነበሩ። የነበሩትም ሕጎች ይህንኑ ሥርዓት የሚያስከብሩ ሲሆኑ አደነጋገጋቸውም መለኮታዊ ኃይል ባደረባቸው ሕግ አውጭዎች እንደሆነ፣ «የተቀደሱና» ፍጹማዊያም ተደርገው ይቀርቡ ነበር። ይዘታቸው ሲመረመር ግን የባሪያ አሳዳሪዎችን ጥቅም የሚያስከብሩ፣ የእነዚሁ ዜጎች መብትና ግደታ የሚደነግጉ ናቸው።



Digitized by Google

ባለፉት ጥቂት ምዕት ዓመታት የካፒታሊዝም ተሟጋቾች የዲሞክራሲ ዋንኛ አራማ
ጆች አድርገው እራሳቸውን ማቀረባቸው ይታወቃል ። በተለይ 18ኛው ምዕት ዓመት ላይ
በአውሮፓ «ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት» የሚለው መፈክር በቡርዥዋው ግንባር
ቀደምትነት በሰፊው ተስተጋብቷል ። በጊዜው ተንሠራፍቶ ከነበረው የፊውዳል ፈላጭ
ቆራጭ አገዛዝ ለመላቀቅ ሲባል ብዙኃን ለጥሪው ተግባራዊ ምላሽ ሰጥተዋል ፤ ከፍ ያለ
መሥዋዕትነትም ከፍለዋል ። በተካሄደውም ትግል ለማካይነት በ18ኛው ምዕት ዓመት መገ
ባደጃና በ19ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ በምዕራብ አውሮፓ በርካታ ሀገሮች የቡርዧ ሪፐ
ብሊክ መንግሥታት ሊቋቋሙ ችለዋል ። ሰዎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውም ሊደነገ
በቅቷል ። ይህ ካለፈው የሰው ልጅ ታሪክ ጋር ሲነፃፀር ታላቅ የዕድገት እመርታ ነው ።
ሆኖም የታሪክ ጉዞ የመጨረሻው እርከን አይደለም ።

ዛሬ ዋንኛው የቀራኒ ምንጭ ካፒታሊስቶች ሥርዓታቸውን የተሟላ ዲሞክራሲ መገ
ለጫ አድርገው ለማቀረብ መሞከራቸውና የታሪክ ሂደት ግን ይህን የሚደግፍ አለመሆኑ
ነው ። በካፒታሊዝም ሁሉም የመምረጥና የመመረጥ መብት ስላለው የሕዝብ አገዛዝ ሰፍ
ኗል ፤ ከእንግዲህ የቀረ ነገር የለም ይላሉ ።

በእርግጥ በካፒታሊዝም ውስጥ ማንም ለመንግሥት ሥልጣን ወኪሉን ሊመርጥና ሊመ
ረጥም እንደሚችል ተደንግጓል ። ይህ በሐቅ ተግባራዊ ሊሆን ቢችል ኖሮ ብዙኃን የሆኑት
ለፍቶ አዳሪዎች የመንግሥት ሥልጣንን ጨብጠው ጥቅማቸውን ለማስከበር በቻሉ ነበር ።
ነገር ግን በተጨባጭ እንደሚታየው በየካፒታሊስቱ ዓለም የሥልጣን ባለቤትነት በቡርዧው
ጥቅም አስከባሪዎች እጅ ውስጥ በመፈራረቅ የተወሰነ ነው ። ሠራተኛው በልዩ ልዩ
ሕጎችና የተጽዕኖ ዘደዎች ከመራጭነት አልፎ ሥልጣን ለመጨበጥ አልበቃም ።
ሌላው ቀርቶ ለምርጫ ተወዳዳሪነት ብቻ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን የሠራተኛውን
ቅስም የሚሰብር ነው ። እሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ በወጣው «ታይም» በተባለ የአሚሪካ መጽ
ሔት ላይ የሠፈረውን አነስተኛ ምሳሌ እንመልከት ። ፓውላ ሐውኪንስ የተባሉ ሴት ለዩ
ናይትድ ስቴትስ ከፍተኛው ምክር ቤት ለመመረጥ የገንዘብ ችግር ስላጋጠማቸው ላይቀና
ቸው እንደሚችል ታትቷል ። «ብሔራዊው የሪፐብሊካን የከፍተኛ ምክር ቤት ኮሚቴ በቅ
ርብ እንዳስታወቀው የሐውኪንስ ተወዳዳሪነት ከፍተኛ ቀውስ» ገጥሞታል ፤ ምክንያቱም
ከውድቀት ለመዳን እስከ ሠኔ 20 ድረስ 945 ሺህ ዶላር (1,956,150 ብር) ያስፈልጋቸዋልና
በማለት ተገልጿል ። መጽሔቱ በመቀጠል «እንዲህ ዓይነቱ አባባል የተጋነነ ነው ፤ ምክን
ያቱም ሐውኪንስ 3.3 ሚሊዮን ዶላር (6,831,000 ብር) በእጃቸው አድርገዋል ።*» ወዘተ.
በማለት ለምርጫ ውድድሩ ገንዘብ ምን ሚና እንዳለው በመጠኑ ፈንጠቅ ያደርጋል ።

በማናቸውም ኅብረተሰብ ውስጥ ሥልጣን ፤ መብት ፣ ጥቅም ወዘተ ፣ የመሳሰሉት የፍላ
ጐት መገለጫዎች ሁሉ ከኢኮኖሚ ጋር ካለ ግንኙነት ወይም ከምርት ግንኙነት ውጭ ሊታዩ

*"Time" Magazine June 30, 1986



Digitized by Google

አይችሉም ። የኢኮኖሚ ወይም የምርት መገልገያ ባለቤትነት ያለው ወገን በበላይነት ፍላጐቱን ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ ይኖረዋል ።

ለሁንም መልስ ብለን የዩናይትድ ስቴትስ ካፒታሊስቶች «የነፃነት ሞዴል« ብለው የሚመጻደቁበትን ኅብረተሰባቸውን ቃኘት እናድርግ ።

የአሚሪካ ሕዝብ ሠራተኛና እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተራመደ መሆኑ ይታወቃል ። በኑሮ ደረጃም ረገድ አማካዩ ስሌት (በስታቲስቲካዊ መልክ ለነፍስ ወከፍ በመደልደልም ቢሆን) ከፍ ያለ ነው ። ሆኖም አሚሪካ ተቃራኒ ገጽታዎች የሚታዩባት ነች ። በኢኮኖሚ ፣ በማኅበራዊ ፣ በፖለቲካና በመንፈሳዊ ቀራኒ ውስጥ ትገኛለች ። አቻ የሌለው የፕሮፓጋንዳ ሙገሳ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ሊያደናግር ቢችልም ሌላው ቀርቶ የረሀብተኛ ሠልፈኛም የሚታይባት አገር ነች ። «ከምጽዋት ይልቅ ሥራ ይሰጠንና ከረሃብ ነፃ እንሆናለን» የሚለው ጥሪ የጥቂቶች አይደለም ። በሚሊዮን የሚቀጠሩ መጠጊያ የሌላቸው የለአምሮ ሕመምተኞች የሚገኙባትም ነች ። ከጥቂት ወራት በፊት በመረጃ እንደተረጋገጠው በአሚሪካ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሥራ አጥ የሆኑት ዜጎች ቁጥር ከ16 ሚሊዮን በላይ ይሆናል ። በድህነት ክልል ውስጥ የሚደመሩት ደግሞ ከ30 እስከ 40 ሚሊዮን ሲደርሱ ከጥቁር ቤተሰቦች ውስጥ 42% በዚሁ የድህነት ክልል ውስጥ የሚታዩ ናቸው ። ከ3 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች አንገት ማስገቢያ የላቸውም ። ከሁሉም በላይ ጥቁሮችና ሌሎች ህዳጣን ወገኖች በአብዛኛው ለጉስቁልና የተዳረጉ ናቸው ።* እነዚህ ወገኖች ሥራ ፈትነት ፣ በምግብ እራሳቸውን አለመቻል ፣ መኖሪያ አጥተው በረንዳ ማደር ምርጫቸው ሆኖ ነው? ወይስ የዲሞክራሲ መብታቸውን በዚህ መልክ ሊጠቀሙበት ፈልገው ?

በምዕራብ አውሮፓም ሁኔታው እምብዛም የተለየ አይደለም ። 16 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሥራ አጥ መሆናቸው ብቻ በቂ መረጃ ነው ። በአሚሪካም ሆነ በምዕራብ አውሮፓ ድንገት ከሥራ መባረርና ልችግር መዳረግ ሁልጊዜም በስጋት የሚጠበቅ መቅሰፍት ነው ። ይህንን ሁኔታ አብዛኛው ሠራተኛ በሚደረግበት የሥነ ልቡና ተጽዕኖ ምክንያት እንደ እርግማን ከመቁጠር ባሻገር ምሥጢሩን ገና ሙሉ በሙሉ አልተገነዘበም ። ለምሳሌ በአሚሪካ አያሌ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች ሳይቀሩ ገና ከልጅነት በትምህርት ቤት «እኛ ነፃ ኅብረተሰብ ነን ፣ ሁሉም እኩል ዕድል አለው ፣ ፍትሕና እኩልነት የተረ ገጠ ነው» በሚል አስተሳሰብ ስለሚቀረፁ ጠለቅ ብለው አይጠይቁም ።

ከሁሉም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ሠራተኛው ጥቅሙን ሊያስከብር የሚችለው ሲያብርና ሲደራጅ ቢሆንም በአሚሪካ ከተቀጣሪው ሠራተኛ የተደራጀው ከ20% በላይ አለመሆኑ ነው ። ሠራተኛውን እንዳይደራጅ የሚደረግበት ተጽዕኖ በጣም ከፍተኛ ነው ። ቢደራጅም በድርጅቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ደባ ይፈጸምበታል ። አሠሪው የሠራተኛው ሁኔታ ካልጣመው ንብረቱን ዘግቶ ወይም ነቅሎ ወደሌላ የሀገሪቱ ክፍል ወይም ወደሌላ አህጉር እስከ

*"International Affairs", Moscow, Jan. 1986.

Digitized by Google

መሰደድ ይደርሳል ። በዚህ ላይ የሠራተኛውን ድርጅት በመበተን ተግባር ላይ ተሰማር
ተው ለአሠሪዎች በሚሰጡት ግልጋሎት ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኙ ለያሌ ተቋሞች ለሉ ።
በዚህ ረገድ የተሠማሩ የሥነ ልቡና ሊቃውንት ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ጠበብቶች ፣ ጠበቆች
ወዘተ. ለያሌ ናቸው ።*

በአሚሪካ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ምን ያህል ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ እንደ
ደረሰ ለከራካሪ ለይደለም ። ለምሳሌ በሰው ሠራሽ ልብ ሕይወትን እስከማራዘምም ተደር
ሷል ። ይሁን እንጂ የዚህ ውጤት ተጠቃሚ ያው ባለገንዘብ የሆነው የኅብረተሰቡ ክፍል
ሲሆን ደሃው ደግሞ የእራስ ምታት ኪኒን መግዣ እንኳ ከሌለው የመሰቃየት ወይም ሕይ
ወቱን የማጣት «መብቱ» የተጠበቀ ነው ። የቴክኖሎጂ ምጥቀትና በለጠቃላይ የምርት ኃይ
ሎች ዕድገት ሠራተኛውን ወደተሻለ ሕይወት በማሸጋገር ፈንታ ይልቁንም በተቃራኒው
ለሥቃይ እየዳረገው ነው ። የተራቀቁ መሣሪያዎችና ኮምፒዩተሮች የማይናገሩና የማይጋገሩ
ባሮች በመሆናቸው በብዙ መስኮች ሠራተኛውን እየተኩት ነው ። በየካፒታሊስቱ ሀገር ዛሬ
ለሥራ አጥ መበራከት አንዱ ምክንያት ይህ ሲሆን ሠራተኛውም በተስፋ መቁረጥ መንፈስ
በየጐዳናው ለመብቱ ከመዋደቅና የሚፈጸምበትን ተጨማሪ ግፍ ከመጋፈጥ ሌላ ለማራጭ
የቀረው ለይመስልም ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ስደተኞችን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በጣም ለነስተኛ በሆነ ምንዳ
መበዝበዝ ሌላው የአሠሪዎች የትርፍ ምንጭ ነው ። በተለይ ከታዳጊ ሀገሮች ምሁራንንና
ልዩ ልዩ ባለሙያዎችን በማስኮብለል መገልገያ ማድረግ እጅግ ለሳሳቢ እየሆነ የመጣ ጉዳይ
ነው ። በዚህ ረገድ ከለሙ ሀገሮች ሳይቀር በተለይ ወደአሚሪካ የሚደገረው ፍልሰት
በጣም እየናረ ነው ። አንድ «የአሚሪካ ብሔራዊ የሳይንስ ማኅበር የተባለ ድርጅት እንኳን
እንዳመለከተው ባለፈው የአውርፓውያን ዓመት በ1985 ብቻ ከብሪታንያ ወደ አሚሪካ
የኮበለሉት የብሪታኒያ ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች ቁጥር 1001 መሆኑ ታውቋል ።**

በካፒታሊስት ሀገሮች የሀብት ባለቤትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ዋንኛ ተጠ
ቃሚ በማያከራክር ሁኔታ ቡርዧው ሆኖ ሳለ በዚሁ ላይ በመመሥረትም ሕጐችና ልዩ ልዩ
ተቋሞች የቡርዧው ፈቃድ መግለጫና የጥቅሙ ማስከበሪያ በሆኑበት ሥርዓት ውስጥ ዲሞ
ክራሲ ወይም የሕዝብ ለገዛዝ ተግባራዊ ሆኗል ማለት በብዙኃን ለፍተ ለዳሪዎች ማፌዝ
ነው ። ቡርዧው የሥልጣን መሠረትና የልዕልና ምንጭ የሆነውን ኢኮኖሚን በእጁ ለድርጐ
ነፃነት አለ ፣ ማንም የፈለገውን ለመሆን ይችላል ቢል ለሠራተኛው ምን ይበጀዋል? ሠራ
ተኛው ያሻህን ልትል ትችላለህ በተባለ እውን የዲሞክራሲ መብቱ ተጠቃሚ ሆነ ማለት
ነውን ?

የእርሱ መሠረታዊ ጥያቄ ካለበት የኑሮ ጭንቀት ለመላቀቅ ከሀገሩ ሀብት ተካፋይ መሆን
ነው ። ይህ ጥያቄው ግን የቡርዧውን መሠረት የሚያናጋ በመሆኑ በቸልታ ለይታይም ።
ከዚህ ኣኳያ የዲሞክራሲን እውነተኛ ተገባራዊነት መሻት ለቡርዧው « ሕግ ለስከባሪዎች »
እና « ኅብለዊ መብት ጠባቂዎች» እንዳልነበሩ መሆንን የሚያስከትል ነው ።

በካፒታሊስቱ ዓለም ዛሬ ትላልቅ ባለኢንዱስትሪዎችና ፋይናንስ ካፒታል ምርጥ ሊቃ
ውንትን እየገዙ በየመስኩ የፍላጐታቸው ማስፈጸሚያ በማድረግ በዲሞክራሲ ስም ሠርቶ
ለዳሪዎችን በኢሰብለዊነት መዳፋቸው ሥር ጥለዋቸዋል ። የካፒታሊዝም ቀኝ ለክራሪና ወግ

* Henri Alleg, Interview, "New Times" 7, '86 Moscow.
** "Time" Magazine June 30, 1986

ለጥባቂዎች ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለእራሳቸው በልዩ ልዩ መልክ እየተደራጁና ኃይላቸውን እያጠናከሩ ከድንበራቸው ባሻገርም በመዝመት ሠርተአደሮችን በሥነ ልቡና ጦርነትና በተለያዩ ማጥቂያ ዘዴዎች በመጠቀም ለመበተንና ለማዳከም በአንፃሩም ልዕልናቸውን በዘለዓለማዊነት ለማቆየት እየሞከሩ ነው ። የሬጋን አስተዳደር ኒካራጓን ለመውጋት 100 ሚሊዮን ዶላር በቀርቡ እንዲመደብ ማድረጉ አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው ።

በምዕራቡ ዓለም በአያሌው የሚለፈፍለት ዲሞክራሲ ይዘቱና እውነተኛ ባሕርዩ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ሌላው አሳፋሪ ፣ ነገር ግን ገዛድ የሆነው ምሳሌ የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ አገዛዝ እንዳይወገድ የሚፈጸመው ደባ ነው ። በአሁኑ ዘመን በምድር ላይ በግፈኝነቱ አቻ የማይገኝለትን ዘረኛ አገዛዝ ለማንበርከክ የኢኮኖሚ ማዕቀብ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ በብዙዎች ታምናበታል ። ሆኖም ይህ መለስተኛ እርምጃ እንኳን ሥራ ላይ እንዳይውል እንደብሪታኒያና አሜሪካ ያሉት ሀገሮች በእምቢተኝነት ጸንተው ቀይተዋል ። ለምን ይህን አክራሪ አቋም እንደያዙ ለማወቅ ምርምር የሚያሻው ጉዳይ አይደለም። በአጭሩ ጥቅማቸው እንዳይቋረጥባቸው ነው ። ልዩ ልዩ ካፒታሊስት ሀገሮች እጅግ ከፍተኛ ሙአለንዋይ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያላቸው ከመሆናቸውም ሌላ በደራ ንግድ ተሳስረዋል ። ለምሳሌ አሜሪካ በአሁኑ ጊዜ በጥሬ ዕቃነት ከሚያስፈልጓት ሦስት ስትራተጂያዊ ማዕድኖች (ኮባልት ፣ ክሮሚየምና ማንጋኒዝ) ከ80 % በላይ ከውጭ የምታስገባ ሲሆን ከዚህም አብዛኛውን የምታገኘው ከደቡብ አፍሪካ ነው ። በተጨማሪም በእራሷ በአሜሪካና በሌሎችም የምዕራብ ሀገሮች ለዘገጃጀታቸው ለካባቢን የሚበክል በመሆኑ ምክንያት ክልክል የሆኑ በርካታ ብረት ጠቀስ ጥሬ ዕቃዎችን የሚያቀርብላት ዘረኛው የደቡብ አፍሪካ አገዛዝ ነው ።*

ሌኒን እንዳስገነዘበው «ማናቸውም ዓይነት ዲሞክራሲ . . . የምርት ተግባር አገልጋይ ከመሆኑም ሌላ በመጨረሻ ምንነቱ የሚወሰነውም በኅብረተሰብ ውስጥ ባሉ የምርት ግንኙነቶች ነው ።**ዲሞክራሲ የበላይነት ያለው መደብ መገልገያና የፖለቲካ አገዛዝ መሣሪያ ነው ። መደቦች ባሉበት በማናቸውም ኅብረተሰብ ውስጥ ዲሞክራሲ የቱንም ያህል ሁለንተናዊ ባሕርይ ሊሰጠው ቢሞክር ይዘቱ በሚገባ ሲጤን ያለጥርጥር የበላይነት ያለው መደብ ጥቅም ማስጠበቂያ ነው ።

ሶሻሊስት ዲሞክራሲም ከዚህ አጠቃላይ ሕግ ውጭ የሚታይ አይደለም ። ከእሱ በፊት ካሉት የዲሞክራሲ ዓይነቶች የሚለየው የብዙኃን መሣሪያ በመሆኑ ነው ። በባሪያ አሳዳሪ ፣ በፊውዳልና በካፒታሊስት ኅብረተሰቦች ውስጥ ዲሞክራሲ ጥቂቶች ብዙኃንን የሚገዙበት ሲሆን የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዲሞክራሲ ግን በተቃራኒው ብዙኃን ሠርቶ አዳሪዎች የጥቂቶችን ብዝበዛና ጭቆና የሚከላከሉበት ፣ በአጠቃላይ መብትና ጥቅማቸውን የሚያስከብሩበት መሣሪያ ነው ። በዚህ መሠረት የዲሞክራሲ እውነተኛ ትርጉም በተግባር የሚገለጠው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም ። አንዱ ሌላውን በማይበዘብዝበትና በማይጨቁንበት ሁኔታ የብሔረሰብ ፣ የጾታና የዘር ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም ዜጋ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች እኩልነቱ የሚረጋገጠው መብቱ በሕግ ታውቆ ቁሳዊ ዋስትና የሚያገኘው ፣ በመንግሥት አስተዳደር ተግባሮች ውስጥ በአቻነት ተሳታፊ የሚሆነው በሶሻሊስት ዲሞክራሲ ነው ።

* "Africa" Magazine No. 175, March 1986

** ቪ.ኢ. ሌኒን ፤ ስብስብ ሥራዎች ቅጽ 32 ፤ ገጽ 81

Digitized by Google

በሶሻሊስት ኅብረተሰብና ይህንኑ የዕድገት ፈር በቁርጠኝነት በመረጡ ሕዝቦች ዘንድ
የመንግሥት ሥልጣን ፖለቲካ የኛ ብቻ ነው ለሚሉ ፣ ገዥነት ከዘር የሚመነጭ ለሚመስ
ላቸው የበላይነታቸውን ማስፈን ለሚሹ ጥቂት ወገናች የሚተው አይደለም ። በዝባዥ ወገ
ናች ሠርቶአደሮች የመንግሥት ሥልጣንን ማንቀሳቀስ እንደማይችሉ መመጻደቃቸውና የበ
ላይነትን ላለማጣት አምርረው መታገላቸው የታወቀ ነው ። ከዚህ አኳያ በሩሲያ አብዮት
መነሻ ላይ በአንድ ጋዜጣ የተንጸባረቀ አቋም ጥሩ ምሳሌ ነው ።

> እስቲ ቦልሼቪኮች ያሸንፋሉ ብለን ለአንድ አፍታ እናስብ ። ለመሆኑ የሚያስተዳድረን
> ማን ሊሆን ነው? ምናልባት ምግብ ቀቃዮች፣ እነዚያ የጥብስና የኮተሌት ጠበብ
> ቶች? ወይስ የእሳት አደጋ ሰዎች? የበረት ልጆች? እሳት አንዳጆች? ወይስ ምናልባት
> የልጅ ሞግዚቶች የሽንት ጨርቅ ካጣጠቡ በኋላ ወደመንግሥት ምክር ቤት ለስብ
> ሰባ ሊጣደፉ ነው ? ቦልሼቪኮች ከዚህ የዕብደት ምኞታቸው ውልፍጥ የማያሰኝ
> መልስ ከታሪክ ያገኛሉ ። *

ባሪያ አሳዳሪዎች ፣ ፊውዳሎችና ካፒታሊስቶች ሁሉም በየዘመናቸው ከላይ የተጠቀ
ሰው ዓይነት አቋም ማንጸባረቃቸው እውነት ነው ። ሆኖም ሠርቶአደሮች ስለሀገራቸው
ልማት ማቀድ ፣ ውሳኔዎቻቸውን ተግባራዊ ማድረግና ሕይወታቸውን መምራት እንደሚ
ችሉ ታሪክ መስክሯል ።

ዲሞክራሲ በአንድ ዓይነት መልክ ቆሚ ሆና በዘለዓለማዊነት የሚኖር አይደለም ። የቀድ
ሞዎቹ ገዥ መደቦች ዲሞክራሲ አንዱ በሌላ እንደተተካ ሁሉ የካፒታሊስቶች ዲሞክራ
ድሲም በሠርቶአደሮች ዲሞክራሲ መተካቱ የታሪክ ጉዳይ ነው ። ዲሞክራሲ በሶሻሊዝም
ትክክለኛ ትርጉሙ በተግባር የሚገለጥ ቢሆንም ሶሻሊስት ዲሞክራሲ እራሱ ደግሞ መደ
ቦችና የመደብ ቅራኔ ሲጠፉ ይከስማል ። ነባራዊ ሂደቱ ይህ ነው ። ታዲያ የካፒታሊስቶች
«የእኛ አገዛዝ የማይሻር ሞደል ነው ።» ማለታቸው እውነትነት አለውን ? የሰዎች መብት
መሠረታዊ መገለጫ የሆነውን ቁሳዊ ሀብት በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ጥቅማቸውን ለማ
ደለብ እንጂ ላለማጋራት ሲሉ በዓለም ላይ ከፍተኛ ጥፋት እያደረሱ ስለ «ነፃነት» ስለ «ዲሞ
ክራሲ» ስለ «እኩልነት» ወዘተ. አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ መንዛታቸው በታሪክ ፊት የሚያ
ስተዛዝብ ነው ። በመደብ ትግል ይሉኝታ ሊኖር አይችልምና የነቁ የሕዝብ ወገናች እውነ
ቱን ገላልጠ ማሳየት ይኖርባቸዋል ። ሕዝብ በአብዮታዊ ንቃት ከታጠቀ ታሪክ ሠሪነት ነባ
ራዊው ሕግ የበየነለትና ተፈጻሚነቱም ፍጹም የማያጠያይቅ ነው ። ለዲሞክራሲ እንድረስ
ለት ። ዲሞክራሲ ፣ ዲሞክራሲ ስለተባለ ሁሉም ዲሞክራሲ አይደለምና ።

---

*"Novoe Vremya" (New Times) as quoted by Mike Davidow, *Working Versus Talking Democracy*, p. 28 Novosti Press Agency, Mosciw, 1982.



Digitized by Google

# የአፍሪካ የኢኮኖሚ ችግርና ለአዲሱ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚደረገው ጥረት

አሕመድ መሐመድ

## ክፍል 1

አፍሪካ ከጠቅላላው የዓለም የመሬት ቆዳ ስፋት 22.3 ከመቶ በመያዝ ከእስያ ቀጥላ ያለች ታላቅ አህጉር ነች ። ጠቅላላ ስፋቷ 30.33 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን ይህም ከአውሮፓ ከስድስት እጅ በላይ ማለት ነው ። የሕዝቡ ብዛት በ1980 ወደ 469 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከዓለም ጠቅላላ ሕዝብ 10.6 ከመቶ ነው ። አፍሪካ በብዙ ትናንሽ መንግሥታት የተከፋፈለች በመሆኗ ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ ከ20 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላቸው ሀገሮች ስድስት ብቻ ሲሆኑ ከሰሐራ በታች ካሉ ሀገሮች ሃያ አራት የሚሆኑት ደግሞ ከአምስት ሚሊዮን በታች የሕዝብ ብዛት ያላቸው ናቸው ።

የአፍሪካን ሀገሮች የሚያመሳስሏቸው በርካታ ነገሮች አሉ ። አብዛኛዎቹ በእርሻ የሚተዳደሩ ሲሆን የውጭ ንግዳቸው በአንድ ወይም ሁለት ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህም የውጭ ንግድ ከጠቅላላው ብሔራዊ ገቢያቸው 25% የሚሆነውን ይይዛል። አብዛኛው ሕዝብ (80 ከመቶ) በእርሻ የሚተዳደር ሲሆን ከጠቅላላው የእርሻ ምርት 50% የሚሆነው ከእጅ ወደአፍ የሆነ ምርት ነው ። ባጠቃላይ ከጠቅላላው ብሔራዊ ገቢ 50% የሚሆነው ከእርሻ የሚገኝ ነው ። ከ15—20 ከመቶ የሚሆነው ሕዝብ የከተማ ነዋሪ ነው ።

አፍሪካ የተለያዩ በርካታ ብሔረሰቦችና ጎሣዎች የሚገኙባት አህጉር ነች ። ከኢትዮጵያና ላይቤሪያ በስተቀር ሁሉም ሀገሮች የረዥም ጊዜ የቅኝ አገዛዝ ታሪክ ያላቸው ናቸው ።

አፍሪካ በተፈጥሮ ሀብት በጣም የታወቀች ነች ። በዓለም አለ ተብሎ ከሚታወቀው ክምችት (Potential Reserve) 97% ክሮም፣ 85% ፕላቲነየም፣ 64% ማንጋኒዝ፣ 25% ዩራንዩም እንዲሁም በርካታ ብረት፣ ብር፣ ነዳጅ ወዘተ . ይገኙባታል ። በዓለም በውሃ ኃይል ከሚመነጭ ኤሌክትሪክ 1/3 የሚሆነውም በዚሁ አህጉር እንደሚገኝ ይገመታል ።[1] በአሁኑ ወቅት በዓለም ከሚመረተው ወርቅ 75%፣ ክሮሚየም 47%፣ አልማዝ 72%፣ ዩራኒየም 35%፣ ፎስፌት 26%፣ ማንጋኒዝ 23% የሚሆነው ከአፍሪካ ነው ።[2]



Digitized by Google

በ1970ዎቹ ዓመታት ውስጥና በተለይም ከዚያ ወዲህ ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ገብተዋል ። ከ1960—1979 ባለው ጊዜ 19 በሚሆኑ የአፍሪካ ሀገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢ ያደገው ከ1% በታች ሲሆን ባለፉት አሥር ዓመታት 15 ሀገሮች ከዜሮ በታች (Negative) ዕድገት (ማሽቆልቆል) አሳይተዋል ። እንደ ዓለም ባንክ ግምት በ1983 የነበረው የመላው አፍሪካ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ1970 ከነበረው አራት በመቶ ያነሰ ነው ። [3] ለዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት ዝቅተኛነት ምክንያት የእርሻ ዕድገት አነስተኛነት ነው ።

ከሰሐራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች ከ1960—83 የነበረው የነፍስ ወከፍ ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ፡—

<u>ዓመታዊ ለውጥ ከመቶ</u>

| ሀገሮች | 1960-70 | 1970-80 | 1981 | 1982 | 1983* |
|---|---|---|---|---|---|
| ዝቅተኛ ገቢ ሀገሮች | 1.5 | -0.9 | -1.9 | 2.5 | .03 |
| መካከለኛ ገቢ ፣ ነዳጅ ገዥ ሀገሮች | 1.5 | 1.2 | 0.6 | -0.7 | -3.4 |
| መካከለኛ ገቢ ፣ ነዳጅ ሻጭ ሀገሮች | 1.1 | 1.6 | -6.7 | -4.7 | -7.3 |
| ጠቅላላ | 1.3 | 0.7 | -4.0 | -3.3 | 3.8 |

ምንጭ ፡—

ዓለም ባንክ Toward Sustained Development in sub-Saharan Africa, P.10.

ነፍስ ወከፍ የምግብ ምርት አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ከ1960—1970 ባለው ጊዜ 0.2% ነበር ። ይህ ከ1970—82 ባለው ጊዜ በማሽቆልቆል ወደ 0.9% ወርዷል ። ጠቅላላ እርሻን ከወሰድን ነፍስ ወከፍ ምርት በ1960—70 ከነበረው ከ0.2%፣ በ1970—82 ባለው ጊዜ ወደ—1.1% ወርዷል ። [4]

*ግምት

እንዲህ ባለው እጅግ ዝቅተኛ ምርት ላይ በ1984 ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው ድርቅ በመጨመሩ ከ30 በሚበልጡ ሀገሮች ውስጥ ከ182 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ማለትም ወደ 1/3 የሚጠጉ የአህጉሪቱ ሕዝቦች ከፍተኛ በሆነ የረሃብ አደጋ ላይ ወድቀው በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አልቀዋል ። [5]

ይኸው ወቅት ብዙዎቹ ሀገሮች በውጭ ምንዛሪና በበጀት ቀውስ ውስጥ የወደቁበት ነበር ። ለምሳሌ ወቅታዊ የንግድ ሚዛን ጉድለት (Current Account Deficit) በ1970 1.5 ቢሊዮን የነበረው፣ ከ1981—82 ባለው ጊዜ 49 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር ። ብዙዎች ሀገሮች የገቢ ንግድ ቅነሳ በማድረጋቸውና በመጠኑም ቢሆን ሻል ያለ የምርት ዋጋ በማግኘታቸው ምክንያት ጉድለቱ ከ1983—84 ባለው ጊዜ ወደ 27.3 ቢሊዮን ዶላር ዝቅ ሲል በቅቷል ። [6] ከዚህ ከውጭ ምንዛሪ ችግር ጐን ለጐን የውጭ ዕዳም በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መጥቷል ። በ1970 ወደ 6 ቢሊዮን የነበረው በ1984 መጨረሻ ላይ ወደ158 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር ። በ1983 የነበረው ጠቅላላ የውጭ ዕዳ ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርት 50% የሚያክል ነበር ። [7] በ1984 አፍሪካ ለውጭ ንግዷ የምትከውፍለው (Debt Service Ratio) ከውጭ ንግዷ አኳያ ሲሰላ ወደ 22.3 በመቶ የደረሰ ሲሆን በ1985 ወደ 25 በመቶ ይደርሳል ተብሉ ተገምቶ ነበር ። [8] ይህ ችግር በተለይ አንዳንድ ሀገሮችን ከፉኛ የተጠናወተ ነው ። ለምሳሌ ሱዳን በ1983 የውጭ ዕዳዋ 7 ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን ይህም በዚያው ዓመት ከውጭ ንግድ ካገኘችው ገቢ ሰባት እጅ ነበር ። [9] የገቢ ንግድ መጨመር ፣ የውጭ ንግድ አንፃራዊ ድከመት ፣ የዕዳ መቆለልና የክፍያው መጨመር የውጭ ምንዛሪ ክምችታቸውን ስላሟጠጠው በ1982 ብዙዎቹ ሀገሮች የነበራቸው የውጭ ምንዛሬ ክምችት ከአንድ ወር የሚበልጥ የገቢ ንግድ ሊሸፍን



Digitized by Google

የማይችል ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ።[10]

የአፍሪካ ሀገሮች በአሁኑ ወቅት እንዲህ ባለ አስከፊና አሳዛኝ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን በ1980ዎቹ ዓመታት ሁኔታው ከዚህም ሊከፋ እንደሚችል የዓለም ባንክ ያደረገው ግምት ይጠቁማል ።[11]

ከላይ እንደጠቀስነው አፍሪካ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት እያላት እንዲህ ያለ ችግር ላይ የወደቀችው እንዴት ነው? ለዚህ ከተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ መልሶች ይቀርባሉ ። አንዳንዶቹ የአየሩና የጂኦግራፊው ሁኔታ ለዕድገት አመቺ ባለመሆኑ ነው ይላሉ ። ሌሎቹ በከፍተኛ ፍጥነት የሚጨምረውን ሕዝብ ብዛት ምክንያት ያደርጋሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከነዳጅ ዋጋ መናርና በዓለምአቀፍ ደረጃ ከሚታየው የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዝቀዝ የመጣ ነው የሚሉም አሉ። ሌሎች ደግሞ የአፍሪካ መንግሥታት ከነፃነት በኋላ ያተኮሩት የፖለቲካ ውህደትን በማስገኘት ላይ ስለነበረ ለምርት የሚገባው ትኩረት ስላልተሰጠው ነው ይላሉ ። ከንግድና ከምንዛሬ መጣኔ (Trade and Exchange Rate) አንሥቶ እስከ የአስተዳደርና የማኔጅመንት ጉድለት ያሉትን በርካታ የሀገር ውስጥ ፖሊሲዎች መዛባት ምክንያት የሚያደርጉም አሉ ። በዚህ ላይ ሌሎችንም መጨመር ይቻላል ።

የአፍሪካን የአሁኑን የኢኮኖሚ ችግር ምንጭ በተለየ መልክ የሚያዩም አሉ ። እነሱም የዚህን ችግር መሠረታዊ መንሥኤ ለማወቅ የዓለም ካፒታሊስት ሥርዓትን ዕድገት ማጥናት እንደሚያስፈልግ ያሳስባሉ ። በታዳጊ ሀገሮች የሚታየውን ድኅነትና መራቆት የፈጠረው ያው በዳበሩት ሀገሮች ሀብትና ድሎትን የፈጠረው ኃይል እንደሆነ አድርገው ይመለከታሉ ። ስለሆነም ቀደም ሲል የተጠቀሱት ምክንያቶች ራሳቸው ውጤቶች ወይም በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ችግሮች እንጂ መሠረታዊ መንሥኤዎች እንዳልሆኑ ይገልጻሉ ።

የዚህ ጽሑፍ አቀራረብም ይህን ፈለግ የሚከተል ነው ። ጽሑፉ ሁለት ክፍሎች አሉት ። ክፍል አንድ፡አፍሪካ በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበረችበትን ሁኔታ ከዚያም በዚሁ ወቅት የገባችባቸውን ችግሮች ፣ ከነፃነት በኋላም ያቀደችውን ለውጥና የገጠሟትን ችግሮች ፣ ችግሮቿን ለመፍታት ያቀረበቻቸውን ጥያቄዎችና (ለአዲሱ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ምሥረታ የቀረበውን ጥያቄ ጭምር) ፣ ለጥያቄዎቹም ከለሙት ካፒታሊስት ሀገሮች የሚሰጡትን መልሶች ይዘረዝራል ። ክፍል ሁለት ፣ አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን ለመፍታት ከሌሎች ታዳጊ ሀገሮች (የደቡብ-ደቡብ ግንኙነት) ፣ እና ከሶሻሊስት ሀገሮች ጋር (ምሥራቅ—ደቡብ) የሚያደርጉትን ግንኙነቶች እንዲሁም በአፍሪካ ሀገሮች መሀከል ስላለውና መኖርም ስላለበት ግንኙነት የሚዳስስ ነው ።

## ቅድመ ቅኝ አገዛዝ አፍሪካ

በ15ኛው ምዕት ዓመት አካባቢ አፍሪካ በሽግግር ደረጃ ላይ ነበረች ። ይህም ደረጃ ባንድ በኩል በቤተሰብ (በወል) በሚካሄድ የእርሻ ፣ የከብት እርባታና እንዲሁም የዓሣ ማስገር ተግባር ፣ በሌላ በኩል እነዚሁ ተግባራት በመንግሥታትና በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚካሄዱበት ከፊውዳሊዝም ጋር ሊነፃፀር በሚችል ደረጃ መሀከል ያለ ነበር ።[12]

ለምሳሌ በእርሻው መስክ እጅግ ፈጣንም ባይሆን ምርት እየጨመረ በመሄድ ላይ ነበር ። አፍሪካውያን በጊዜው ባለው ደረጃ ስለአካባቢያቸው ደኅና ዕውቀት ነበራቸው ። በመሆኑም ከጊዜውና ከሁኔታ ጋር የሚገጥም ቴክኒክ ይጠቀሙ ነበር ። ባጠቃላይ ስለአካባቢያቸው (ስለኢኮሎጂው) ማለትም ስለአፈሩ ፣ ስለአየር ጠባይ ፣ ስለዕፀዋትና አዝርዕት ፣ ስለእንስሳት ፣ በእነዚህም መካከል ስላሉት በርካታ ግኙኝነቶች ወዘተ. የነበራቸው ግንዛቤ ቀላል አልነበረም ። ይህንንም ዕውቀታቸውን ለግብርና ይጠቀሙበት እንደነበር ይታወቃል። ባንዳንድ ቦታዎች በጊዜው እጅግ ተለምዶው በነበሩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር ። ከእ

Digitized by Google

ነዚህ ውስጥ የእርከን እርሻን ፣ ዘር እየለዋወጡ መዝራትን ፣ በፈረቃ ማረስን ፣ ገልብጦ ማረስን(Green Manuring) ከብት እርባታንና እርሻን አጣምሮ ማካሄድን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ። በጊዜው ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ዕድገት እርምጃ በነበረው በብረት መገልገያ (እንደማረሻ ፣ ገሶ ወዘተ.) በመጠቀም አዳዲስ ዘዴዎች አዳብረዋል ። ተደጋግሞ የታረሰ የእርሻ መሬትን በማሳደር ቁጥቋጦ እንዲለብስ በማድረግ በዚህም ሂደት አፈሩ እንዲዳብር ከዚያም ቁጥቋጦውን እያቃጠሉ እንደገና ማረስን( Shifting Cultivation) መጥቀስ ይቻላል ።[13] በጊዜው የሰው ብዛትና የአካባቢዎች በግል ንብረትንት መያዝ መጨናነቅ ስላልነበር ገበሬዎች በአንድ አዝመራ ወቅት አቃጥለው ያረሱትን ቦታ የሚመለሱበት ከብዙ ጊዜ በኋላ ስለነበር ቦታው እስከዚያ ቁጥቋጦ አብቅሎና አፈሩም ዳብር ስለሚቆያቸው የአፈር መራቆትና አንድን አካባቢ መላልሶ ከማረስ ወዘተ. የሚመጣ ዛሬ የሚታየው ዓይነት ችግር አልነበረም። በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው የአፍሪካ የእርሻ ምርት ዕድገት እያሳየ ነበር ።

በኢንዱስትሪውም መስክ አፍሪካ የነበረችበት ሁኔታ ከሌሎቹ አህጉራት እስከዚህ የሚለይ አልነበረም ። አንድ ጸሐፊ እንደጠቀሙት መፈብረክ (ማኑፋክቸር) የሚለው ቃል የዘመናዊ ፋብሪካዎችን ፣ ማሽናችን ወዘተ. ሁኔታ ስለሚያሳይ የአፍሪካ መፈብረክ ይናቃል ፣ በቂ ትንተናም አይደረግለትም ። ይሁን እንጂ ይህ ቃል የሚጠቀመው በእጅ የተሠሩትን የዕደ ጥበብ ምርቶች ሁሉ እስከሆነ ድረስ የአፍሪካንም ደረጃ በዛሬው ዓይን ሳይሆን ያኔ በነበረበት ደረጃ ማየትና መገምገም ያሻል ። አፍሪካ በ15ኛው ምዕት ዓመት የነበረችበትን ደረጃ ለመገመት እንዱ ጥሩ ዘዴ በጊዜው ይመረቱ የነበሩትን ምርቶች ጥራት በማየትና በማወዳደር ነው ። ከእነዚህ ጥቂቱን ብንጠቅስ ፦

—የሞርኮ ቆዳ በመባል የሚታወቀውና በሰሜን ናይጀሪያና ማሊ በሚገኙ የሀውሳና የማንዲንጋ ዕደጠበብት ይሠሩት የነበረው ከፍተኛ ጥራት ያለው ቀይ ቆዳ

—ከማንቼስተር ጥጥ የበለጠ ጥንካሬ የነበረው የጊኒ የጥጥ ልብስ ፤

—ዝነኛ የነበረው የካታንጋና የዛምቢያ መዳብ ፤

—ዝነኛው የሴራሊዮን ብረት ወዘተ ።[14]

በእርግጥ ጥጥ ማዳወሪያው ፣ ብረት ማቅለጫው ወዘተ. ትንሽ ነበር ። የሸክላ ሥራም በእሽክርካሪ ሳይሆን በእጅ የሚዞር ነበር። ይሁንና በእነዚህና በሌሎች በመሳሰሉት መስኮች ዕድገት እየታየ ነበር ። ባንድ ልዩ ሙያ ላይ የማተኮር ሂደት (Specialization and localization) በተለይ በልብስ ኢንዱስትሪ ጐልቶ ይታይ ነበር። በዚህም ለምሳሌ የልብስ ማቅለም ጥበብ ከልብስ ስፌት እንዲሁም የፈትል ሥራ ከሽመና ወዘተ. እየተለየ በመሄድ ላይ ነበር ። በየመኖሪያ ቤት ውስጥ ማምረት በፋብሪካ ወደ ማምረት በሚደረገው ሽግግር እንደድልድይ የሚቆጠር የጊልድ ሥርዓት(Guild system) በአፍሪካም በማቆጥቆጥ ላይ ነበር ። ለምሳሌ የቲምቡክቱን የልብስ ሰራዎች ጊልድ ፣ የቤኒንን የነሐስና ብርንዝ ጊልድ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል ። ባጭሩ የሥራ ክፍፍልና በተለየ ሙያ ላይ ማተኮር በምርት ላይ የዓይነትም ሆነ የመጠን ለውጥ እያስከተለ ነበር።[15] በሌላ አነጋገር እንደሌላው አህጉር ሁሉ አፍሪካም ከእጅ ወዳፍ ከሆነ ኢኮኖሚ በመውጣት ሂደት ላይ ነበረች ። የተለያዩ ማኅበረሰቦች ከሚያካሂዱት የተረፈ ምርት ልውውጥ አኳያ ንግድም እየተስፋፋ ነበር። በብዙ አካባቢዎች ሸቀጥን በሸቀጥ መለወጥ በገንዘብ አማካይነት ለሚካሄድ ልውውጥ ቦታውን እየለቀቀ ነበር። በሰሜን አፍሪካ ፣ በኢትዮጵያ ፣ በኮንጎ የነበረው የተሻሻለ የገንዘብ ሥርዓት ለነዚህ ሀገሮች ኢኮኖሚ ከአነስተኛ የሸቀጥ ልውውጥና ከእጅ ወደአፍ ከሆነ አመራረት ከፍ ያለ መሆኑን



Digitized by Google

ይመሰክራል ። እንዲያውም ብዙ የአፍሪካ የታሪክ ጸሐፊዎች በ15ኛው ምዕት ዓመት ላይ ዳበሩ የሚባሉት የአፍሪካ አካባቢዎች ለምሳሌም ግብፅ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ኑቢያ፣ሞሮኮ ምዕራብ ሱዳን ፣ ዝምባብዌ ፣ ቤኒን ወዘተ. በጊዜው ከነበሩ የአውሮፓ አካባቢዎች እንደሚወዳደሩ ይናገራሉ ። ይህም አውሮፓውያን ምሥራቅና ምዕራብ አፍሪካ መጀመሪያ በደረሱበት ወቅት የአፍሪካ ዕድገት ከእነሱ ጋር ተወዳዳሪ እንደነበረ አልሸሸጉም ። ለዚህም የቤኒንን ከተማ ዳኞች ሲጎበኙ ያሉትን መጥቀስ ይበቃል ።

ከተማው ትልቅ ይመስላል ። ወደ ውስጥ ሲገባ ያልተነጠፈ ትልቅ - ሰፊ መንገድ ያጋጥማል ። እሱም አምስተርዳም ውስጥ ካለው ዋርሞስ መንገድ ሰባት ወይም ስምንት እጅ ይበልጥ ይሰፋል። ከተማው እጅግ ቀጥ ያሉ - 120 ጫማ ስፋት ያላቸውን ሠላሳ ዋና ዋና መንገዶችንና ለያሊ ትናንሽ ለቁራጭ መንገዶችን የያዘ ነው ። ቤቶቹ በጥሩና በተስተካከለ ሁኔታ ተቀራርበው የተሠሩ ናቸው ። እነዚህ ሰዎች በንጽሕና ረገድ ከዳች በምንም ዓይነት መንገድ የሚያንሱ አይደሉም ። ቤቶቻቸው ጥሩ ተደርገው ስለሚታጠቡና ስለሚወለውሉ ልክ እንደመስታወት ያብረቀርቃሉ ። [16]

## አፍሪካ በቅኝ አገዛዝ ጊዜ

ከላይ በጥቂቱም ቢሆን ለማሳየት እንደሞከርነው አፍሪካ ከቅኝ ገዢዎች መምጣት በፊት መጠነኛም ቢሆን በራስዋ የውስጥ ሂደት ላይ የተመሠረተ ዕድገት ታሳይ ነበር ። ዛሬ ይህ ሁሉ ቀርቶ ኢኮኖሚዋ ጥገኛ ሊሆንና ሌላው ቀርቶ ራስዋን ለመመገብ እንኳን ከማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። መጠኑ ይለያይ እንጂ ይህ ሁኔታ ታዳጊ ሀገሮች ሁሉ በጋራ የገጠማቸው ችግር ነው ። ስለሆነም የዚህን ችግር መንሥኤ ለማየት ከዚህ ቀጥለን ባንድ በኩል የዛሬዎቹ ታዳጊ ሀገሮች በአውሮፓ ለዳበረው ካፒታሊዝም የካፒታል ክምችት ( Capital Accumulation ) ያበረከቱ መሆናቸውንና በሌላ በኩል ደግሞ ካፒታሊዝም በእነዚህ ሀገሮች ያስከተለው የራሱን አምሳያ መፈጠር አለመሆኑን እንመለከታለን ። በሌላ አባባል አውሮፓንና ሰሜን አሜሪካን ያበለጸገው የዕድገት ሂደት ለእነዚህ ታዳጊ አገሮች መራቆትና ኋላቀርነት ምክንያት እንደሆነና በኢንዱስትሪ የዳበሩት ካፒታሊስት ሀገሮችና ዛሬ «ሦስተኛ ዓለም» በሚል ቅጽል የሚታወቁት ሀገሮች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች እንደሆኑ ለማየት እንሞክራለን ።

ከ16ኛው እስከ 18ኛው ምዕት ዓመት የነበረው ጊዜ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር የዳበረበትና የዕድገት ኃይሉን ያጠራቀመበት ፣ የዓለም ገበያ የተፈጠረበትና እየሰፋም የሄደበት ጊዜ ነበር ። ስለሆነም በታሪክ ውስጥ ይህ ጊዜ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። የዚህ ወቅት ዋና ውጤት በምዕራብ አውሮፓ የጥሪት ክምችት መካሄድና ዛሬ ታዳጊ በመባል የሚታወቁት ሀገሮች በአንፃሩ መራቆትና ወደ ጥገኝነት በይበልጥ እየተሳቡ መሄድ ነበር ። በአውሮፓውያን መስፋፋት ቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰቦች የበታችና የወራሪው ኃይል ተገዥ ተደረጉ ። ባንዳንድ አካባቢም (ለምሳሌም በደቡብና ሰሜን አሜሪካ) ነዋሪ የነበሩ ዜጎች ባብዛኛው ተደመሰሱ ፤ በቦታቸውም ወይ ከአውሮፓ በተሰደዱ ነዋሪዎች አሊያም ከየቦታው (በተለይ ከአፍሪካ) በተጋዙ ባሮች ተተኩ ። ይህ የባርያ ጉልበት ለካፒታሊስት ገበያ ጥሬ ዕቃን ፣ የተለያዩ የእርሻ ምርት ውጤቶችን በማቀበል በአውሮፓ ለካፒታል ክምችት ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል ። የጥሪት ክምችቱ «የቅኝ ሀገሩን» ሕዝብ ሀብት በመዝረፍ ፣ በማጭበርበር ፣ በመጨፍጨፍ ወዘተ. የተገኘ ነው ፤ ዘመኑ የሜክሲኮና ፔሩ በስፔናውያን መወረርና መመዝበር ፣ የኢንዶኔዥያ በፖርቱጊዞችና በዳኞች መዘረፍ ፣ የሕንድ በእንግሊዞች የጭካኔ አገዛዝ መበዝበዝና የአፍሪካ የምዕራብ አውሮፓ ባሪያ ነጋዴዎች ሲሳይ መሆን ፣ በአጠቃላይ ከፍተኛ የውን



Digitized by Google

ብድናና የዝርፊያ ድርጊት የተፈጸመትበ ዘመን ነው ። ዛሬ የሚታየው የካፒታሊስት ሥርዓት ብልጽግናና ድሎት ጎሕ የቀደደው በእነዚህ ታዳጊ ሀገሮችና ሕዝቦች በፈሰ ሰው ጉልበት መሆኑን ማርክስ ሲገልጽ እንዲህይላል ።

የወርቅና የብር በአሜሪካ መገኘት የዚያም ለሀገር ሕዝብ ወደ ባርነት መለወጥና በማዕድን ጉድጓዶች ውስጥ መቀበርና መላወስ ለለመቻል ፣ የሕንድ መሸነፍና መዘረፍ መጀመር ፣ የአፍሪካ ወደ ጥቁሮች ማደኛ ክልልነት መለወጥ ፣ እነዚህ ሁሉ የካፒታሊስት ምርት ዘመንን መጀመር ባሕርያት የሚገልጹ ናቸው ።[17]

በዚህን ጊዜ የተፈጸመው ወንጀል ፣ ስርቆትና ዝርፊያ ለኢንዱስትሪው አብዮት አመቺ ሁኔታን እንደፈጠረና ምን ያህል ከፍተኛ ገፊት እንደሰጠ ዛሬ የቡርዧ ምሁራን እንኳን የሚክዱት እንዳይደለ የታወቀው የእንግሊዝ ኢኮኖሚስት ሜይናረድ ካይንስ የጻፈውን ማጤኑ ብቻ ይበቃል ፤

በእርገጥ ድሬክ በጉልደን ሃይንድ (መርከብ) ዘርፎ ያመጣው ሀብተ ለእንግሊዝ የውጭ ሙአለ ንዋይ ምንጭና መሠረት እንደሆነ ይገመታል ።

ኣልሳቤጥ (በወቀቱ የእንግሊዝ ንግሥት) በዚህ መሠረተ ካገኘችው ገንዘብ ውስጥ የውጭ ዕዳዋን በሙሉ ከከፈለች በኋላ ቀሪውን (42.000 ፓውንድ) ለሌቫንት ኩባንያ ለዋለችው ። ከዚህ ከሌቫንት ኩባንያ በተገኘው ትርፍም የኢስት ኢንድያ ኩባንያ ሊቋቋም ቻለ ። ከዚህም ከኢስት ኢንድያ ኩባንያ የተገኘው ትርፍ በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመት ለነበረው የእንግሊዝ የውጭ ግንኙነት መስፋፋት ዋና መሠረት ሆነ ።[18]

ለምሳሌ ከ1750 እስከ 1800 በነበረው ወቅት ብቻ እንግሊዝ ከሕንድ ከ100 እስከ 150 ሚሊዮን ፓውንድ እንደዘረፈች ይገመታል ። ጠቅላላው ሲታሰብ ግን ከቢሊዮን ፓውንድ ስተርሊንግ በላይ እንደሚሆን ፣ በሌላ አነጋገርም ይህ ገንዘብ በ1800

በአውሮፓ ውስጥ, በእንፋሎት ኃይል ከሚሠሩ እንዱስትሪዎች ጠቅላላ ካፒታል ሁሉ እንደሚበልጥ ዐዋቂዎች ይናገራሉ ።[19] እዚህ ላይ በ1770 የእንግሊዝ ብሔራዊ ገቢ 125 ሚሊዮን ፓውንድ ብቻ እንደነበርና በ1790 ጠቅላላው የእንግሊዝ ዘመናዊ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ጠቅላላ ሙአለ ንዋይ 650,000 ፓውንድ ብቻ እንደነበረ ማወቁ የዝርፊያውን መጠን ለማነፃፀር ያስችላል ።[20] ፖርቱጋል ፣ ዳች ፣ ፈረንሳይና ሌሎች የጊዜው ቱጃ ገገሮች ከፍተኛ ዝርፊያ ያካሄዱ ለመሆኑ አያሌ የታሪክ መረጃዎች አሉ ።

የዛሬዎቹ ካፒታሊስት ሀገሮች ባንድ ወቅት የራሳቸው የደረጀ ኢንዱስትሪና ምርት የነበራቸውን ሀገሮች እንዴት ቀስበቀስ እያዳከሙ የሸቀጥ ማራገፊያቸው እንዳደረጉ አሁንም የሕንድ ምሳሌ ጥሩ ማስረጃ ነው ። ለምሳሌ በ1815 ሕንድ 1.3 ሚሊዮን ፓውንድ የሚያወጣ ጨርቃጨርቅ ውጤት ወደ እንግሊዝ ስትልክ እሷ ግን ከእንግሊዝ የገዛችው ሸቀጥ ከ26,000 ፓውንድ አይበልጥም ነበር ።[21] (የቻይናም ታሪክ ከዚሁ የማይለይ ነበር ። በኋላ የአፍሪካም ሁኔታ ተመሳሳይነት እንዳለው እናያለን ።) ይሁንና ውሉ እድሮ የገበያው ሁኔታ የተገላቢጦሽ መልክ ያዘ ። የእንግሊዝ ኢንዱስትሪ ቀስ በቀስ የበላይነትን አገኘ ። ይህን ያገኘውም አንደኛ በሌሎች ሀገሮች ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣል ፣ (ለምሳሌ በሕንድ ላይ 20 በመቶ ስትጥል ፣ እሷ ግን ለሕንድ 3.5 በመቶ ብቻ ትከፍል ነበር ።[22]) ሁለተኛ ደግሞ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ርምጃዎችን እንግሊዝ በመውሰዷ ነበር ። ሆዊት የሚባል ጸሐፊ በ1838 ከታተመ አርዩንታል ሄራልድ ከሚባል ጋዜጣ በመጥቀስ እንግሊዝ በሕንድ ላይ ኃይል መጠቀሟን እንደሚከተለው ይገልጻል ።

ግዛተ አፄአችን የሰው ሐሳብ የሚደመጥበት ወይም በሕግ የሚመራ አይደለም ። በፈቃድ ያገኘነው አንድም የሀገር (የሕንድ)



Digitized by Google

ክፍል የለም ። በመጀመሪያ የተፈቀደልን በባሕር ጠረፍ ላይ ሠፍረን ዕቃዎቻችንን እንድንሸጥ ነበር ። ቀስ በቀስ ፣ አንዳንድ ጊዜ በኃይል በመጠቀም ፣ አንዳንድም በማጭበርበር . . . የሀገሪቱን ጥንታዊ ሉዓላዊነት ደምስሰን ፣ ማንኛውንም የላቀ ኃይላቸውን ባዶውን አስቀረነው ። ከዚያም በመቀጠል በኢንዱስትሪውና በሀገሪቱ ሕዝብ ሀብት ላይ በማተኮር የተቻለንን ያህል ሀብትና ተረፈ ዕቃ ወሰድንባቸው ። 23

ለዚህ ነበር ግሪፍን የሚባለው ጸሐፊ አውሮፓውያን የመስፋፋት እርምጃዎችን በወሰዱባቸው በእነዚያ በመጀመሪያዎቹ ወቅቶች ለተፈጸሙት ድርጊቶች መልክና ቅርፅ የሰጡት ሁለት ነገሮች ናቸው ፤ እነሱም አንደኛ የአውሮፓ በወታደራዊ መስክ በተለይም በጦር መሣሪያ የበላይነት መያዝና ሁለተኛ ደግሞ ከሌሎች አንፃር ሲታይ አውሮፓ የነበረባት ቁሳዊ ድህነት ነው ብሎ የጻፈው ። በዚያን ወቅት አውሮፓ ሀብታም ከነበሩት የምሥራቅ እሲያ ሀገሮች ጋር በእኩልነት ደረጃ ንግድ ልታካሂድ አትችልም ነበር ። ምክንያቱም አውሮፓውያን የሚፈልጓቸውን በርካታ ነገሮች እሲያ ሲኖራት እሲያውያን የሚፈልጉትን ግን አውሮፓ አልነበራትምና ነው ። ግሪፍን ፣ ኩቻል የሚባለውን ጸሐፊ በመጥቀስ ሲያትት ወደ አሥራ ሰባተኛው ምዕት ዓመት ገደማ ሕንድ በኢኮኖሚ ረገድ ከአውሮፓ ይበልጥ የተራመደች እንደነበረች ይገልጻል ። ለምሳሌም ሕንድ በተደራጁ ኢንዱስትሪዎች አማካኝነት እንደ ወርቅና ብር ዕቃዎች ያሉትን የቅንጦት ሸቀጦች ፣ በተጨማሪም ከመስታወት የተሠሩ ዕቃዎች ፣ ወረቀት ፣ የብረት ውጤቶች ፣ መርከቦች ታመርት እንደነበር ያትታል ። ከእነዚህ ዕቃዎች በርካታዎቹንና በተጨማሪም እንደ ጥጥ ልብስ ፣ ሐር ጨርቅ ፣ ቀለማት ፣ የባሩድ መሥሪያ ወዘተ. ያሉትን ወደ ምዕራብ እየላከች በምትኩ ወርቅ ትወስድ እንደነበር ይገልጻል ። 24 እዚህ ላይ ለመረጃ ያህል አንዳንድ ምሳሌዎች ጠቅሰን እንጂ የዘረፋውን ታሪክ ሁሉ ለመዘርዘር አይደለም ። አውሮፓውያን በእሲያ ላይ ዓይናቸውን በመጣል የዚያችን አህጉር ሀብት ለመበዝበዝ ያደረጉትን ጥረትና ያካሄዱትን ዘረፋ ከማርኮፖሎ ታሪካዊ የምድር ጉዞ ጀምሮ እስከ ቫስኮ ዳጋማ የባሕር ጉዞ ፣ ከዚያም ወዲህ እንደብሪትሽ ኢስት ኢንዲያ ኩባንያ ያሉ እረመኔ ድርጅቶች እስካደረሱት መራቆት ድረስ መዘርዘር እጅግ ሰፊ በመሆኑ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሊጠቃለል የሚችል አይደለም ።

ወደ ጀመርነው ርዕስ ማለትም ወደኢንዱስትሪው መዳከም እንመለስ ፤ እንግሊዞች ሕንድን ከወረሩ በኋላ የሕንዶችን ኢንዱስትሪዎች ሆን ብለው እያዳከሙና እያጠፉ የሀገራቸው የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ሸቀጦች ማራገፊያ አደረጓቸው ። ባንፃሩ ደግሞ ለአውሮፓ ኢንዱስትሪ እንደ ጥጥ ያሉ የእርሻ ውጤቶችን (Cash Crops) እያመረቱ እንዲያቀብሉ ግፊት አደረጉባቸው ። በዚህም መሠረት ወደ 1880 አካባቢ የሕንድ ኢንዱስትሪ ዕድገት እየተዳከመ ሄደ ፤ አያሌ እንዱስትሪዎች ተዘጉ። እንደ ዳካ ያሉ በኢንዱስትሪ ከተማነታቸው የታወቁት ከተሞች ጫካ ወረሳቸው የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ሥራ ፈት ሆኑ ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ወደገጠር ተሰደዱ ይህም በገጠሩ ኢኮኖሚ ላይ ውጥረትን በማስከተሉ የእርሻ ምርት እያሽቆለቆለ ሄደ ። ከ1873— 76 የነበረው የእርሻው ምርት ከ1898- 1900 ከነበረው ተመሳሳይ ምርት ጋር [illegible]ፀር እየቆረቆዘ መሄዱን የሚከተለው ሀ[illegible]ብረዥ ያሳየናል ። 25

| ክፍለ ሀገር | ምርት ከመቶ |
|---|---|
| ጋንጃም | — 43 |
| ቪዛጋፓታም | — 48 |
| ቢላሪ | — 20 |
| ታንጆሬ | + 29 |
| ቲኒቢሊ | — 40 |
| ሳሊም | — [illegible]3 |
| ኮይምባተሬ | — [illegible] |

Digitized by Google

ይህ ስንጠረዥ ከ1873—76 የነበረው ገቢ በ1898—1900 ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከ—13 (በሳሌም ክፍለ ሀገር የደረሰው) እስከ—48 (በቬዛጋፖታም ክፍለ ሀገር የታየው) በመቶ ያህል መቀነሱንም የሚያሳይ ነው ። [25] በዚህ ወቅት በደረሰው ከፍተኛ የምርት መውደቅ ብዙ ሰዎች በረሃብ ረገፉ ። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ነበር ቬራ እንስቴይ የተባለቺውን ጸሐፊ በሚከተለው ኃይለ ቃል እንድትጽፍ ያደረጋት ።

የእንግሊዞች ቀድመ ለያተች በጣም ጥንታዊ በሆነ ኑር በሚኖሩበተ ወቀተ እጅግ ገሩም የሆኑ ሻሾችንና ሌሎችንም የቀንጦተ ዕቃዎችና የሱፍ ጨርቆችን በማፈብረክ ወደ ውጭ ለሸያጭ ትልክ የነበረችው ሕንድ በእነዚያው ለውሬና ለረመኔ በሆኑ የእንግሊዝ ተወላጆች ለሠሣሽነተ በተካሄደው የኢኮናሚ ለብዮተ ለመካፈል ለልቻለችም ። [26]

እስካሁን የሕንድን ምሳሌ በሰፊው መጥቀሳችን በርካታ መረጃዎች የሚገኙበት በመሆኑ ባብዛኛው የተጻፈበትና ያነጣነውን ነጥብ ጎላ አድርጎ ለማቅረብ ያስችለናል በማለት እንጂ ሁሉም ታዳጊ ሀገሮች አንዱ እንደ ሕንድ የደረጀ ኢንዱስትሪ እንደነበራቸው አድርጎ ለማሳየት አይደለም ። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል የአፍሪካን ቅድመ ቅኝ አገዛዝ ሁኔታ እንሥተን እንዳየነው እንደዚያ መጠነኛ የሆነ ዕድገት የነበራቸው ሀገሮች እንኳን ሳይቀሩ ከአውሮፓውያን ሥልጣኔ ጋር ከገጠሙ በኋላ ያ ራሱን የቻለ የነበረው የኢኮኖሚ መዋቅራቸው ተፈረካክሶ የእነዚያ ጥገኛ እንዲሆኑና ባብዛኛውም ዕድገታቸው እየተሻሻለ ከመሄድ ፈንታ እያዘቀጠ እንዲሄድ ተደርጓል ። ለዚህ እስቲ ወደ አህጉራችን ታሪክ መለስ ብለን እንይ ።

የአውሮፓውያን ኢሰብአዊ ድርጊት በሌሎችም አህጉራት ላይ የተፈጸመ ቢሆንም በምንም ዓይነት ደረጃና መልክ ቢታይ ከአፍሪካ ጋር አይወዳደርም ።አውሮፓውያንም በ16ተኛው ምዕት ዓመት ያስፋፉት ከፍተኛ የባሪያ ንግድ አብዛኛውን የአህጉራቱን ክፍል ወደ ብጥብጥና ምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ የጣለ ነበር። ከሕዝቡ መጨፍጨፍና በግፍ መገደል የተነሣ የሕዝብ ብዛት መቀነስ ፣ በስምምነት ይኖሩ በነበሩ ጐሣዎች መካከል የእርስ በርስ ጦርነትና መተላለቅ መባባስ ፣ የኢኮኖሚው እያሽቆለቆለ መሄድ ፣ በእርሻ ምርት ራሷን በሚገባ ትችል የነበረችው አፍሪካ የውጭ ተመፅዋችነትዋን ባጠቃላይ የአፍሪካ የአኗኗርና የአመራረት ዘዴ መለወጥ ከዚሁ ከአውሮፓውያን መምጣት ጋር የተያያዘ ነበር ። እታሚልስ ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ ሲጽፍ፡

የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታሊስተ ጥሪተ ክምችተ የአፍሪካ፣የኢስያን ፣ የላቲን አሜሪካን ኅብረተሰቦች ለራሱ ጥቀም እንደሚበጀው አርጉ ለደራጅተለቸዋል ። በአፍሪካ ውስጥ ገልበተ ሳይሆን ለው ራሱ ሽቀጥ ሆና ስለነበር የባሪያ ንግድ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ መቀነስን በተለይም የኅብረተሰቡ ወጣትና ጠንካራ አባል የነበሩተ እየተገዙ መወሰዳቸውን አስከተለ ። የዚህም ውጤት የእርሻንና የዕደ ጥበብን መዳከምና መቀርቀዝ ማስከተል ነበር ። ከዚህ ሌላ የባሪያ ንግድ ትርፍ የሚያስገኝ ተግባር ሆና መገኘቱ በጐሣዎችና ቡድኖች መካከል የእርስ በርስ ንጭትንና ውጊያን መባባስ አስከተለ።አፍሪካ በራስዋ ኃይል የምትተዳደርበተ ወቀተ ማከተም የጀመረው በዚህን ጊዜ ነበር ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ አፍሪካ በምዕራባውያን ኢኮኖሚና ኅብረተሰብ - እንዲሁም በእነሱ ሥርዓት የካፒታል ክምችት ፍላጎት መሠረት ቅርጽ መያዝ ጀመረች ። [27]

ደርጅቶ የነበረው የእርሻ ምርት እየወደቀ ለመሄዱ ቀጥሎ የተመለከተው ከአልጀሪያ የእርሻ ውጤት የተገኘ መረጃ ጥሩ ምሳሌ ነው ።



Digitized by Google

## የአልጀሪያ ነፍስ ወከፍ

## የእርሻ ውጤት [28]

| ዓመተ ምህረት | 1863 | 1911 | 1938 | 1954 |
|---|---|---|---|---|
| ጥሬ ጥሬ በኪሎ | 1,000 | 377 | 731 | 202 |
| ቀንድ ከብት (በቁም) | — | 0.2 | 0.1 | 0.8 |
| በግ (በቁም) | 4.5 | 1.5 | 0.1 | 0.7 |

አፍሪካ ከአውሮፓ ጋር የቀረፀ ግንኙነት የጀመረችው ከ18ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ማለትም ገና ቅኝ አገዛዝ ከመጀመሩ በፊት መሆኑን ቀደም ሲል ጠቅሰናል። ይህ፣ በመጀመሪያ በንግድ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ውሎ አድሮ ለአፍሪካ በኅበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካም ጥገኛ መሆን መንገድ ከፋች ሊሆን ችሏል። በዚህም በመጀመሪያው ወቅት አውሮፓውያን ለአፍሪካ የሚሸጡት ዕቃ እምብዛም አልነበራቸውም። የአውሮፓውያን ንግድ የተመሠረተው ከሕንድ ወደቦች ገዝቶ መልሶ አፍሪካ ውስጥ በመሸጥ፣ ወይንም ከተለያየ የአፍሪካ ክፍል (ለምሳሌ ከምዕራብ አፍሪካ ከሞሮኮ፣ ሞሪታንያ፣ ሴኔጋል፣ ጋምቢያ፣ አይቮሪኮስት፣ ቤኒን፣ ወዘተ.) ወደ ሌላ የአፍሪካ ክፍል ወስዶ በመሸጥ ላይ ነበር። ታዲያ አፍሪካ ወደቅኝ አገዛዝ ዘመን ስትገባ ቀደም ሲል በሕንድ ምሳሌ እንዳየነው ሁሉ የነበረው ሁኔታ የተገላቢጦሽ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ጥሬ ጥጥ ወደ ማቀበልና ልብስ ወደ መግዛት ዞራ ነበር። አውሮፓ ከውጭ ንግዷ የቴክኖሎጂ ዕድገት ስታተርፍ አፍሪካ ግን ያላትንም አጣች። ይህም የሆነው አንደኛ በባሪያ ንግድ ጊዜ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶችና ጉልማሶች ከመጋዛቸውና ከመጊጠማቸው የተነካ ካለፈው ትውልድ የመጣውን ሆነ የራስን ፈጠራ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፉ በመደናቀፉ፣ ሁለተኛም የአፍሪካ ገበያ በአውሮፓ በተመረቱ ዕቃዎች እየተጥለቀለቀ ሲሄድ በሀገር ውስጥ ይመረቱ የነበሩና ቀደም ሲል የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ያረኩ የነበሩ ምርቶች እየወደቁ መሄዳቸው ነበር። ከእነዚህ ከአውሮፓ በገፍ እየተመረቱ ከሚመጡ ዕቃዎች የደረሰባቸውን ውድድር (አንዳንዶም ቀጥተኛ ተጽዕኖ) ሊቋቋሙ ባለመቻላቸው የሀገር ውስጥ ውጤቶች ተፈላጊነታቸው እየቀነሰ ሄደ። በመሆኑም የሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂ አብሮ ወደቀ። ሰዎች የአባቶቻቸውን ቀላል ቴክኒኮች እንኳን እየረሱ በመሄዳቸው ከመሻሻል ፈንታ እያሽቆለቆለ፣ ከመስፋት ይልቅ እየጠበበ፣ ባንዳንድ ሁኔታም ጭራሽኑ እየጠፋ ሄደ። እንዲህ ዓይነቱ ተጽዕኖ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉትን ቀርቶ እንደ ኢትዮጵያ ያሉትን ነፃ ሀገሮችን እንኳን ሳይቀር እንዴት ሊያዳክም እንደቻለ ፓንክረስት እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

*በ1880 ፡ ፡ ፡ «የሐረር የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ከውጭ በሚመጡ ርካሽ ብረታ ብረቶች ውድድር የመሸነፍና የመዋጥ ዕድል ገጠመው። ከዚህም የተነሣ ፡ ፡ ፡ በሀገር ውስጥ የሚሠሩ የብረታ ብረት ውጤቶች ከውጭ በመጡት ውድድር እየተዳከሙና እየተሸነፉ ሄዱ።* [29]

በእንዲህ ያለ ሁኔታ የሀገር ውስጥ ምርቶች እየወደቁ ቴክኖሎጂው እየተዳከመ ሲሄድ የሀገሬው የዕደ ጠበብት ቁጥር እያነሰ ሄደ። ለምሳሌ በአልጀሪያ በ1850 ወደ መቶ ሺህ የነበሩት በ1951 ቁጥራቸው ቀንሶ 3500 ብቻ ሆነ። [30] በዕደ ጥበብ ሙያ ይተዳደሩ የነበሩ ሰዎችም ወደ እርሻ በመሰማራታቸው በወቅቱ የነበረውን የመሬት ማጣበብ አባባሱት። ይህም የእርሻ ምርት እንዲቀንስ፣ የመሬት ኪራይ ይበልጥ ከፍ እንዲል፣ የገጠር ሥራ ፈት ቁጥር እንዲጨምር አደረገ። እንግዲህ የሀገር የምርት ውጤቶችና ብሎም እነሱን የሚያመርቱ ቴክኖሎጂዎች ቦታ እያጡ ሲሄዱ ከውጭ የመጡ አዳዲስ የምርት ውጤቶችና ቴክኖሎጂዎች በቦታቸው እየተተኩ ሄዱ። ከፍ ያለ ገቢ ያላቸው የገዥ መደብ አባላት በሥልጣኔ የዳ



Digitized by Google

በሩ ሀገሮችን የአለባበስ ፣ የአመጋገብና በአጠቃላይ የምዕራባውያን የአኗኗር ዘዴ ይበልጥ እየተከተሉ ሄዱ ። በተለይም አብዛኛውን የሀገር ሀብት በእጃቸው ያደረጉ ከተሜዎች ከፍተኛና መካከለኛ መደቦች የሀገር ውስጥን ምርት እየተው (እየናቁ) የውጭ ዕቃዎችን ወደ መግዛት ይበልጥ ሲያዘነብሉ የሀገር ውስጥ ገበያ «የምርት ገበያተኞችን» ፍላጐት ወደ ማሟላት ማዘንበሉ ግዴታ ሆነ ። የውጭና የሀገር ውስጥ ከበርቴዎችም ይህንን ከውጭ የሚመጣውን ዕቃ በሀገር ውስጥ በማምረት የሀ[illegible] ገበያ ለመያዝ መቻላቸውን በመረዳት ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም (Import Substituting Industries) [illegible] ይህ ዓይነቱ ስትራቴጂ [illegible] በኋላም በስፋው የቀጠለ ነው ።

እንግዲህ ፊት ከውጭ ይመጡ የነበሩ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት ሲባል እነሱን የሚያመርቱ ቴክኖሎጂዎችን የግዴታ ከዚያው ከውጭ ማምጣት አስፈለገ ። ይህም እንደጠቀ[illegible]ው መውደቅ የያዘውን የሀገር ውስጥ [illegible]ኖሎጂ ጭራሽ መጥፋት ፣ የአፍሪካንን ይበልጥ በባዕድ ቴክኖሎጂ ጥገኝነት ሥር መውደቅ እያስከተለ ሄደ ። በተለይም ባለኢንዱስትሪዎች ገበያ እንዳይነጠቁና ጥሩ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲችሉ የግዴታ እነዚያኑ ዓይነት ዕቃዎች የሚያመርቱ ቴክኖሎጂዎችን ከማስመጣት በስተቀር የሀገር ውስጥን ለማሻሻል ፣ ወይንም የውጭውን ከሀገሪቱ የሰውና ቁሳዊ ሀብት ጋር እንዲጣጣም አድርጎ ለማደራጀት ወዘተ. ሙከራም አላደረጉም ። ይህም አፍሪካውያን ቴክኖሎጂዎች የማጥናታቸውንና የማዳበራቸውን ችሎታ የሚያሳድግ አልነበረም።

በዚህ መልክ ነበር የባዕድ ቴክኖሎጂዎችንም ሆነ የተመረቱ ዕቃዎችን ዝም ብሎ ( Passively ) ወደ ሀገር ማስገባት የቀጠለው ። ማሺኖች ፣ ፋብሪካዎች ፣ ኤክስፐርቶች ፣ ኬሚካሎች ፣ ነዳጅ ፣ ሸቀጣ ሸቀጥ ማዳበሪያ ፣ መድኃኒቶች ወዘተ. መግባት ያዙ ። ውሎ ሲያድርም ከሕፃናት መጫወቻ አሻንጉሊት እስከ አይሮፕላን ፣ ከሽቶ እስከ ማዳበሪያ ፣ በቁጥርም ፣ በዓይነትም በርካታ ዕቃዎች እየገቡ ፣ የገቢ ንግድ በጣም እያደገ ሄደ ።

እነዚህን ለማስመጣት እንዲችሉ ደግሞ የግዴታ በልዋጭ የሚላክ ነገር መኖር ነበረበትና አውሮፓውያን የሚፈልጓቸውን እንደጥጥ ፣ ቡና ፣ ሻይ ፣ ቃጫ ፣ ትንባሆና የመሳሰሉ ምቶርችን በይበልጥ እያመረቱ መላክ ቀጠሉ። በአህጉሩ ውስጥ ለባዕድ ሸቀጦች ያለው ፍላጐት እየጨመረ በሄደ መጠን ከምግብ እህሎች ይልቅ ከላይ ለጠቀስናቸው ምርቶች (Cash Crops) ቅድሚያ በመስጠቱ በእነሱ ላይ ይበልጥ እየተደገፉ መሄድ ቀጠለ ። በመሆኑም ዛሬ አፍሪካ የምትመገበውን አታመርትም ፣ የምታመርተውን አትመገብም ።

እንግዲህ የሕንድንም ምሳሌ እንዳየነውና የአፍሪካም ሁኔታ እንዳረጋገጠልን ፣ ከአውሮፓውያን ጋር መገጣጠሙ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያስከተለው የታዳጊ ሀገሮች የኢንዱስትሪ መሠረት ተደምስሶ ፣ ጥሬ ዕቃ አቀባይና የምዕራባውያን ሸቀጥ ማራገፊያ መደረጋቸውን ነው ። ማርክስ ከመቶ ዓመት በፊት እንደገለጸው ፣ የዚህ ውጤት ፣

የአዲስ ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል መፈጠር ሲሆን ክፍፍሉም የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ዋና ማዕከል ከሆኑት ጥቅምና ፍላጐት ጋር የሚገጥም ነበር ። ይህም ክፍፍል የምድሪቱ አንድ ክፍል ባብዛኛው የእርሻ ምርት አካባቢ እንዲሆንና የኢንዱስትሪ ምርት አካባቢ ለሆነው ለሌላኛው ክፍል ጥሬ ዕቃ እንዲያቀብል የሚያደርግ ነው ።[31]

ዛሬ ላለው የተዛባ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መሠረቱ ይህ ሲሆን ፤ ወደፊት በዚህ ጽሑፍ ለምናነሣው የአዲሱ ዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት ጥያቄ መሠረታዊ ነጥብ ስለሆነ ልብ ማለቱ ጠቃሚ ነው ።



Digitized by Google

ይህን ርዕስ ከማለፋችን በፊት ስለአፍሪካ ዕድገት መጨናገፍ ጉዳይ አንድ መታወስ ያለበት ነጥብ አለ ። አፍሪካ በጊዜው የተጨናገፈበት ኢንዱስትሪና ዕውቀት ፣ (Skill) በዛሬ ዓይን ሲታይ ትንሽ ሊሆን ይችላል ። ግን ቁም ነገሩ ይህ አይደለም ። ቁም ነገሩ ያንኑ ትንሽ ዕድገት ራሱን በቻለ መልክ ማራመድ እንዳትችል መደረጉ ነው ። ባንድ ደረጃ ላይ ከዕድገት መገታት የግዴታ የሚቀጥለውን እርምጃ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለመረማመድ አለመቻልን ያስከትላል ። አፍሪካም ለአምስት ምዕት ዓመታት የገጠማት ይህ ነው ። አንድ ጸሐፊ እንዳለው ከመጀመሪያው የንግድ ግንኙነት ጀምሮ አፍሪካ ያጋጠማት ትልቁ ችግር የዕድገት ዕድል መነፈግ ነው ። ይህ ከሁሉም በላይ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ነው ።

ይህን ሁሉ ስንል አንዳንድ ሰዎች አውሮፓውያን ካፒታሊዝምን ወደ እነዚህ ታዳጊ ሀገሮች በማስፋፋት ሥልጣኔን አምጥተው የለም ወይ ? ይላሉ ፤ ቅኝ ገዥዎችም የሚሉት ይህንኑ ነው ። ግን ጥያቄው እሱ አይደለም ። ጥያቄው ካፒታሊዝም ወደሌሎች ሀገሮች ተዛምቶ ያፈራው የራሱን አምሳያና ከምንጩ መዳበር እንደያዘው ዓይነት የዕድገት ሕይወት የተሞላበት ካፒታሊዝም ነው ወይስ አይደለም ? የሚል ነው ። መልሱ ግልጽ ነው። አይደለም ። ካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ካፒታሊስት ሥርዓት በተስፋፋባቸው ሀገሮች ውስጥ ሁሉ ቢዳብርም ፣ ይህ ባንድ መልኩ የተጨናገፈ ፣ ወደነፃ ዕድገት ለማደግ ኃይሉ የተሰለበ ሲሆን ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ አሁን ድረስ የሚዘገንኑ ወንጀሎችን የፈጸመ ፣ እስከዛሬ ታዳጊ ሀገሮች ሊወጡት ወደአልቻሉት የተንጋደደና የተዛባ የኢኮኖሚ መዋቅር ውስጥ የከተታቸው ነው ።

የካፒታሊስት ኅብረተሰብ በሁለት ዋና ዋና መደቦች (በቡርዧና ወዝአደር) የተከፋፈለበት ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው ። እንግዲህ ካፒታሊዝም በአፍሪካ አድጓል ለማለት የአፍሪካ ቡርዧና ወዝአደር መደቦች በኅብረተሰቡ ዋና መደብ ሆነው መውጣታቸውን ማሳየት መቻል ያስፈልጋል ። የምናየው ግን ሁለቱም መደቦች ጠንክረው አለመውጣታቸውን ነው ። በየሀገሩ ብቅ ብቅ ሊሉ የቻሉት ጥቂት የአፍሪካ የንግድ ሰዎች በውጭ ሰዎች ላይ የተደገፉና ጥገኛ የሆኑ ፣ ለታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ፣ እርሻዎች ወዘተ. የሚያውሉት የራሳቸው በቂ ካፒታል የሌላቸው ፣ ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ በመሆናቸው በእውነተኛ አጠራር ቡርዧ ልንላቸው የሚገቡም አይደሉም ። የወዝአደሩንም መደብ ስናይ ሁኔታው ብዙ ተለይቶ አናገኝም ። ቅኝ ገዥዎች ጥሬ ዕቃ ለማግበስበስ የሚያስችሏቸውን እንደ ማዕድን ያሉትን እንጂ ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት ፍላጐት ስላልነበራቸው የወዝአደሮች ቁጥር ከመላው ኅብረተሰብ አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው ። በመሆኑም ሁለቱም መደቦች መሠረታዊ ሆነው ሊወጡ አልቻሉም።

ካፒታሊዝም እስከዚህም አለመስፋፋቱን እያንዳንዱን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወስዶ ማየትም ይቻላል ። ለምሳሌ እርሻን እንውሰድ ። ካፒታሊዝም በመነጨበት ሀገር (በአውሮፓ) በእርሻ ላይ ከፍተኛ አብዮታዊ ለውጥ አስከትሏል ። አፍሪካ ውስጥ ግን አንድ ጸሐፊ እንዳለው ፣ ብዙኃን አፍሪካውያን ከቅኝ አገዛዝ በፊት የሚገለገሉበት መጣሪያ ዶማ ሲሆን ከቅኝ አገዛዝ በኋላም ያው ዶማ ነው ። እርግጥ በጥቂት አካባቢዎች ባብዛኛው ለካፒታሊስቱ ገበያ ጥሬ ዕቃ የሚያመርቱ ዘመናዊ እርሻዎች ፤ ትራክተሮች ወዘተ. ይገኛሉ ። እነዚህም ቢሆኑ ካለው የቴክኖሎጂ ጥገኝነት የተነሣ በርካታ ችግሮችን አዝለው የሚገኙ ናቸው ።

ቀደም ሲል በገፍ የሚመረቱ የአውሮፓ ሸቀጦች ፣ የአፍሪካን ኢንዱስትሪዎች



Digitized by Google

እንደልብስ ተብረታ ብረት ፣ የሸክላ ሥራን እንኳን ሳይቀር እንዳዳከሙ አይተናል ። እርግጥ ይህ በአውሮፓም ተፈጽሟል ። ሆኖም እዚያ እርጌው ባዲስ ሲተካ እዚህ ግን ማጥፋት እንጂ መተካት አልነበረም። በአውሮፓ ጥምር ማሽኖች አደጥበበኛችን ከሥራ አፈናቀለዋል ። ሆኖም ከዚያ ለዳዲስ ማሽኖች ለሁን ላለው ሥልተምርት መሠረት ሆኑ ። የገበሬ ዕደጥበበኞች እንደ ወዛደሮች ሆነው ወደ ፋብሪካ ተሸጋገሩ ። ... ዳሩ ግን በአፍሪካ የተከናወነው ሳያሸሽሉ ማጥፋት ነው ። ...የፖለቲካ ነፃነት በተገኘበት ወቅት የተረፈው ጥበበኝነት የአፍሪካን ሕዝብ እውነተኛ ፍላጎት ከማርካት ይልቅ ወደቱሪስቶች መስህብነት ዝቅ ብሎ ነበር ።[32]

በትራንስፖርት ረገድም ብንሄድ በቅኝ አገዛዝ ጊዜ የተሠሩት መንገዶች፣ ሐዲዶች ወዘተ. የአፍሪካውያንን ጥቅምና ፍላጎት እንዲያሟሉ ሆነው ሳይሆን ቅኝ ገዥዎች ለአስተዳደር ፣ ለወታደራዊ እንቅስቃሴ ፣ ለውስጥና ውጭ ንግድ እንዲያመቻቸው ተደርጎ ነው ። ስለሆነም መንገዶችና ሐዲዶች ወደ ባሕር የሚያመሩና ወርቅና ብር፣ ቡናና ጥጥ የሚያጓጉዙ ፣ ለውጭ ነጋዴዎች ንግድን የሚያመቻቹ ነበሩ ። ስለዚህም ነው የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ እንደወጡ በሀገራቸውም ውስጥ ሆነ በሀገሮቻቸው መካከል የተለያዩ አካባቢዎችን የሚያገናኙ መንገዶች ያልነበሯቸው ። ይህም ለኢኮኖሚ ዕድገታቸው እስከ ዛሬ ድረስ እንቅፋት ሆኗል ።

በትምህርትም መስክ ለውጡ ባብዛኛው ጉጂ መልኮችን አቅፎ መሆኑን እናያለን። እዚህ ላይ አስቀድመን መጥቀስ የሚገባን ሐቅ አለ ። ይህም ቅኝ ገዥዎች ከመምጣታቸው በፊት በተለያየ መልክና ደረጃ ትምህርት በአፍሪካ እንደነበርና እነሱ እንዳላመጡት ነው ። እርግጥ በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ትምህርት ባብዛኛው መደበኛ አልነበረም ። ሆኖም በጊዜው ለአፍሪካ ፍላጎት ተስማሚና ከኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ኑሮ ፣ በቁሳዊም በሆነ መንፈሳዊ ረገድ ፣ በቅርብ የተሳሠረ ፣ ለኅብረተሰቡም ብቁና የተሟሉ ዜጎችን የሚያፈሩ ነበር ። አንዳንድ የአፍሪካ ትምህርት መደበኛም ነበር። ከከፍተኛ ትምህርት ሌላ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚታዩት እንደ ግብፅ አልገዛር ፣ እንደ ሞሮኮው ፌዝ ፣ እንደ ማሊው ቱምቡክቱ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል ። በሀገራችንም ለዘመናት በየገዳማቱ ይሰጥ የነበረው ትምህርት በወቅቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነበር ።

አውሮፓውያን ወደአፍሪካ ሲመጡ ያደረጉት የዱሮውን ትምህርት የጣጠ ፣ ወይንም የተካ ሌላ ዓይነት መደበኛ ትምህርት ማቋቋም ነው ። ትምህርቱም ከአፍሪካ ኑሮ ፣ አካባቢና ፍላጎት የመነጨ ባለመሆኑ ዛሬ ድረስ ጠንቅ የሆኑ ጉጂ መልኮችን መያዙ ግዴታ ነው ። አንድ ጸሐፊ እንዳለው ፣

ትምህርቱ ወጣቶቹ በራሳቸው እንዲተማመኑና በአፍሪካዊነታቸው እንዲኮሩ ተደርጎ የተቀየሰ (የተተለመ) አልነበረም ። ዳሩ ግን አውሮፓዊና ካፒታሊስታዊ ለሆነ ነገር ሁሉ የተለየ ስሜት እንዲፈጥሩ ተጽዕና የሚያሳድር ነበር ። . . .ስለዚህም የነበረው ትምህርት ረገጠ ለመገዛት ፣ ለመጨቆን ፣ ለመበዝበዝ ፣ የኀሊና ውዥንብር ለመፍጠርና ኋላቀርነትን ለማስፋፋት የተቀየሰ ነበር ።[33]

## አፍሪካ ከነፃነት ባኋላ

እስካሁን ያደረግነው ትንተና እንደሚያሳየን አውሮፓውያን ወደ አፍሪካ ያስፋፉት ካፒታሊዝም የተጣመመና የዕድገት ኃይሉ የተሰለበ ነው ። በእሱ ላይ ያሞናፖል ካፒታሊዝም ተብታቢ የሆነ ተጽዕና በመታከሉ እነሆ ዛሬ አንድ ጸሐፊ ትቶሉ እንደሚገልጸው ገና በልጅነት ዕድሜው የመጃጀትና የመበስበስ ምልክቶችን እያሳየ ነው ።



Digitized by Google

የአብዛኛዎቹ የታዳጊ ሀገሮች ካፒታሊዝም ልዩ የሆነ የተዛባ ታሪክ አለው ። በሕፃንነት ጊዜ ያለውን ስቃይና ተስፋ የመቁረጥ ደረጃ ያለፈ ቢሆንም በወጣትነት ዕድሜ ለሚታዩ ብርቱነትና ወኔ አልበቃም ። ገና በለጋነቱ የሽምግልናና የመጃጀት ባሕርያት ያሳይ ጀመረ ። በቀድሞ ኢንዱስትሪ ኅብረተሰብ ውስጥ ከሚታየው የኢኮኖሚ ዕድገት መገታት በተጨማሪ የሞኖፖል ካፒታሊዝም የተለያዩ የተጽዕና ዓይነቶች ተጫኑበት ።[34]

የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ባብዛኛው ያበቃ ቢሆንም ቀደም ሲል ያየነው ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል በታዳጊ ሀገሮች ላይ የፈጠረው ችግር አሁንም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አማካይነት እየተካሄደ ነው ።

በቅኝ አገዛዝ ወቅት የታዳጊ ሀገሮች ጥገኝነት ፍጹማዊ ነበር ። ይህም በአስተዳደር፣ በወታደር፣ በሕግ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ የቅኝ ገዥው የበታች ጥገኛ በመሆን የተረጋገጠ ነበር ። ሀገሮች የፖለቲካ ነፃነታቸውን እያገኙ ሲሄዱ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት እያከተመ መጣ ። ግን ይህ በራሱ የጥገኝነት ግንኙነቱን አላስቀረውም ። እንዲያውም የዱሮ ግንኙነቶች እንደተጠበቁ ሆነው አዳዲስ የጥገኝነት መልኮች ተፈጠሩ ፤ አሊያም ቀደም ያሉ የጥገኝነት መልኮች በአዲስ መልክ ተደራጁ ። እነዚህን በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር መካሄድ የያዙትን የጥገኝነት መልኮችና የገቢ ወደ ውጭ መፍለስ (Income Drain) ችግር በተለያዩ መልኮች እንደሚከተለው ማየት ይቻላል ።

የመጀመሪያው ቀጥተኛ የኢኮኖሚ ጥገኝነት የሚባለው ነው ። ይህም ዋና ዋና የኢኮኖሚ ተቋሞች በባዕድ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ሀብትነት ሲያዙ ወይም ቁጥጥር ሥር ሲወድቁ የሚመጣ ነው ። ይህ ዓይነቱ ጥገኝነት ከፊት የተላለፈ (ከቅኝ አገዛዝ) በከፊልም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተፈጠረ ሲሆን ሁኔታው በሀገሬው ሕዝብ ጉልበት የተፈጠረውን ተረፈ እሴት የባዕድ ሞኖፖሊስቶች እንዲበዘብዙ የሚያስችል ነው ። አብዛኛዎቹ ሀገሮች ነፃ ሲወጡ በየሀገራቸው የሚካሄደው የማዕድን ቁፈራ ሥራ የእርሻ፣ የጅምላ ንግድና ሌሎችም አያሌ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በውጭ ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር እንደሆኑ ቀሩ ። ነፃ ከወጡም በኋላ የተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮች በተለይ ፊት ቅኝ ግዛት እስከዚህም ያል ነበራቸውና ኋላ ኢኮኖሚያቸው እየተጠናከረ ሲሄድ እንደተቀሩት ካፒታሊስት ሀገሮች የጥሬ ዕቃና ገበያ እንዲሁም ካፒታላቸውን የሚያውሉበት መስክ ፍለጋ በተያያዙት እንደ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ምዕራብ ጀርመን፣ ጃፓን ባሉ ሀገር ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር እየዋሉ ሄዱ ። የውጭ ካፒታል በእነዚህ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትርፍ ያገኛል ። ለምሳሌ ከ1975 እስከ 1980 ከምዕራብ አውሮፓ ብቻ ወደእነዚሁ ሀገሮች የገባው ካፒታል $ 10 ቢሊዮን ሲሆን በትርፍ መልክ የወጣው ግን $ 17 ቢሊዮን ነበር ።[35] በ1980 ብቻ የምዕራብ ሞኖፖሎች ከአፍሪካ ያገኙት ትርፍ ወደ $ 25 ቢሊዮን ይገመታል ።

የታዳጊ ሀገሮች ጥገኝነት ጉልቶ የሚታይበት ሌላው መስክ ንግድ ነው ። የንግድ ጥገኝነት የሚያመለክተው ታዳጊ ሀገሮች ባንድ በኩል የንግድ ግንኙነታቸው ከጥቂት ካፒታሊስት ሀገሮች ጋር መሆኑና በሌላ በኩል ደግሞ ጠቅላላ ኢኮኖሚያቸው በየጊዜው በሚለዋወጠው (በሚዋዥቀው) በካፒታሊስት የዓለም ገበያ ላይ ጥገኛ መሆኑ ነው ። የንግድ ግንኙነታቸው ከጥቂት ካፒታሊስት ሀገሮች ጋር መሆኑ ቀጥተኛ የኢኮኖሚ ግንኙነት ካልነው የመነጨ ነው ። ቁልፍ የኢኮኖሚ ተቋሞች በባዕድ የተያዘ ሀገር ሙሉ በሙሉም ይሁን ባብዛኛው የንግድ ግንኙነቱን የሚመሠርተው የካፒታሉ (የኢኮኖሚ ተቋሞች) ባለቤት ከሆነው ሀገር ጋር ይሆናል ። የሚያመርተው ለዚያ ሀገር ፍላጎት ሲሆን ባንፃሩም ለእነዚህ ሀገሮች ሸቀጥ ገበያ ይሆናል ። ዛሬ ታዳጊ ሀገሮች በመባል ከሚጠሩት ውስጥ የፈረንሳይ ቅኝ


Digitized by Google

የነበሩ ባብዛኛው ከፈረንሳይ ፤ በእንግሊዝ ሥር የነበሩ ባብዛኛው ከእንግሊዝ ጋር ፥ በአሜሪካ ተጽዕኖ ሥር ያሉ ከአሜሪካን ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ የሚያሳየን ይህንኑ ሐቅ ነው ።

የንግድ ግንኙነትን ካንድ ወይም ሁለት ካፒታሊስት ሀገሮች ጋር ብቻ ማድረግ በር ካታ ችግሮች አሉት ። አንደኛ በሁለት በዓ ቅም በማይመጣጠኑ ሀገሮች መካከል ግን ኙነት ሲኖር ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ጠን ካራው ሀገር በደካማው ላይ ተጽዕኖ ሊያደ ርግ ፥ የልውውጡ ሁኔታ ለእሱ (በዋጋም ፥ በመጠንም ፥ በጊዜም) እንዲያመች ሊያደ ርግ ይችላል ። ከዚህ አልፎም በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተጽዕኖ ማሳደሪያ ዘዴ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል ። ታዳ ጊው ሀገር በራሱ ሀገር ውስጥ ችግር ብቻ ሳይሆን በደረጀው ሀገር ውስጥ ከሚፈጠር ችግርም (ለምሳሌ በዳበሩ ሀገሮች ውስጥ ከሚደርስ የኢኮኖሚ ቀውስ) የተነሣ ጉዳት ሊደርስበት ይችላል ።

በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ ንግድ በብሔራዊ ኢኮኖው ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ በመ ሆኑ የዓለም ገበያ ሁኔታ ተለዋዋጭነት በጥገኛው ሀገር ኢኮኖሚው ውስጥ የሚያሳ ድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።በዚህየተነሣ ም የዓለም ገበያ ሁኔታ ተለዋዋጭነት በጥገ ኛው ሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል ።ለምሳሌ በኬንያ ፥ ኡጋንዳ፥ታን ዛኒያ፥ሱዳን፥ኢትዮጵያ ወዘተ. የውጭ ንግድ 20%የሚሆነውን ገበያ ነክ ምርት(Monetary Sector) ይይዛል ። እንደ ሞሪሽየስና ዛም ቢያ ላሉ ሀገሮች ይህ ቁጥር ወደ 50% ይደር ሳል ። ባብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች የገጠር ገቢ ወደ ውጭ ከሚላክ የእርሻ ምርት የሚ ገኝ ነው ። ከዚህ የተነሣ በውጭው ንግድ ላይ የሚደርስ ችግር በቀጥታም ሆነ በተዘ ዋዋሪ በርካታ የኅብረተሰቡን ክፍል የሚ ነካ ይሆናል ። ከዚሁ አኳያ የሚታይ ሌላው ነገር ከ60—95% የሚሆነው የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ፍጆታ ከገቢ ንግድ የሚመጣ መሆኑ ነው ። ታዳጊ ሀገሮች የገቢ ንግዳቸውን ለመሸፈን ባብዛኛው የሚደገ ፉት አንድ ወይም ሁለት ጥሬ ዕቃ(Primary Commodity) ለዓለም ገበያ በማቅረብ ነው። የቅርብ ጊዜ መረጃ ካላቸው 34 ሀገሮች 24 ያሀሉ ከ90—100% የውጭ ንግዳቸው ባንድ ወይም ሁለት ጥሬ ዕቃ ላይ የተመሠ ረተ መሆኑን ያሳያል ። የዚህ ዓይነቱ ጥገኝ ነት ለከፍተኛ ጥቃት እንደሚያጋልጥ ግልጽ ነው ። በተለይ ለጥሬ ዕቃዎች ያለው ፍላ ጎት ከገቢ ጋር በተመጣጣኝነት የሚያድግ ባለመሆኑ ባብዛኛው ቴክኖሎጂ ውጤት (Synthetics) መተካት ስለያዙ የጥሬ ዕቃ ዎች ንግድ ጥሩ ዕድገት አያሳይም ። ለም ሳሌ ጥሬ ዕቃዎች በዓለም ንግድ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በ1955 38% ነበር ። ይህ በ1976 ወደ 19% ዝቅ ሊል በቅቷል ። ከአ ቅርቦት በኩልም ሲታይ ችግር አለ ። በተ ለይ የእርሻ ውጤቶች ለአየር ሁኔታ መለ ዋወጥ ፥ ለበሽታ ወዘተ. የተጋለጡ ናቸው።

ታዳጊ ሀገሮች በውጭ ንግዳቸው የተጠ ናከረ ድርጅት ስለሌላቸው ለጥሩ ዋጋ የመ ደራደር ዓቅማቸው አነስተኛ ነው ። ስለሆ ነም በዳበሩ ሀገሮች ገበያ ሞኖፖል ባሕ ርይ በጣም ይጠቃሉ ። በዚህ ላይ አብዛኛ ዎቹ አንድ ዓይነት ምርት ለገበያ ስለሚያ ቀርቡ እርስ በርስ ተፎካካሪ ይሆናሉ።ይህ ሁሉ በመደማመር የውጭ ንግዳቸውን ከፍ ለማድረግም ሆነ ለምርታቸው ተመጣጣኝ ዋጋ የማግኘት ችሎታቸውን ያሳንሰዋል ፤ የንግድ ሁኔታንም(Terms of Trade)እየተ በላሸ መሄድ ያስከትላል ። የእነዚህ ሀገ ሮች ምርት ዋጋ ቢጨምርም እንኳን የሚ ገዙት ዕቃ ዋጋ ይበልጥ ስለሚጨምር መጎ ዳታቸው አይቀርም ። አንድ የታንዛኒያ ባለ ሥልጣን የሀገራቸውን ችግር ሲገልጹ በ1963 አንድ ትራክተር ለመግዛት አምስት ቶን ቃጫ ማምረት ነበረብን ፤ በ1970 ግን ይህንኑ ትራክተር ለመግዛት 10 ቶን ማም ረት አስፈልጓል ብለዋል ። [36] ዛሬ ከዚህ ብሶ ይገኛል ። ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት ችግር የጥሬ ዕቃዎች ዋጋ መዋዠቅ ነው።



Digitized by Google

ለምሳሌ የጥሬ ዕቃዎች ዋጋ (ዘይትን ሳይ
ጨምር) በ1980 በ14.8% ከፍ አለ ። ምንም
ያህል ሳይቆይ በ1981 በ15.6% ዝቅ አለ ።
ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በአንዲት ታዳጊ ሀገር
ገቢና ብሎም በዕድገት እንቅስቃሴዋ ላይ
ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳይ በቀላሉ መገ
መት ይቻላል ።

ታዳጊ ሀገሮች የውጭ ንግዳቸው በሚ
ፈልገው መጠን ማደግ እያቃተው ሲሄድ
ባንፃሩ ግን የገቢ ንግዳቸው በከፍተኛ ፍጥ
ነት እያደገ ነው ። ለምሳሌ ከ1970—79
ባለው ጊዜ የውጭ ንግድ በ1.7% ሲያድግ
የገቢ ንግድ ግን ያደገው በ8.3% ነበር። ይህ
በውጭ ምንዛሪ ላይ የሚያስከትለውን
ችግር ተመልሰን እናየዋለን ።

ከላይ ካነሣናቸው ሁለቱ የጥገኝነት
መልኮች ሌላ እንደ ቴክኒካዊ ጥገኝነትና
የፊናንስ ጥገኝነት ያሉትን መጥቀስ ይቻ
ላል ። ቀደም ሲል የአፍሪካና ሌሎችም
ታዳጊ ሀገሮች እንዴት የሀገራቸው ቴክኖ
ሎጂ ተዳክሞ የምዕራባውያን ቴክኖሎጂ
ጥገኛ ሊሆኑ እንደበቁ ገልጸናል ። ሆኖም
ይህ የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ባሁኑ ጊዜ ይዞ
የሚገኘውን መልክና አንዳንድ ችግሮች
መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል ። ቴክኒካዊ ጥገ
ኝነት ስንል ባንድ በኩል በቁሳዊ መልኩ
ማለትም ቴክኖሎጂን ፣ ፓቴንት ፣ ላይሰንስ
(ፈቃድ) እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናት
ውጤቶችን ወደሀገር ማስገባትን ሲሆን ፣
በሌላ በኩል ደግሞ በሕያው መልክ ለም
ሳሌ ኤክስፐርቶች ፣ አማካሪዎች ፣ አስተማ
ሪዎች ወደ ሀገር ማምጣትን ፣ ተማሪዎችን
ለእስኮላርሽፕ መላክን ወዘተ. ያጠቃልላል።
ዛሬ በዚህ ረገድ ያለው ችግር በታዳጊ ሀገ
ሮች ውስጥ ያለው የምርምርና የዕድገት
ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተ
ነሣ በእነዚህ ከውጭ በሚመጡት ቴክኖ
ሎጂዎች ተጠቅሞ ራሱን የቻለ የቴክኖ
ሎጂ መሠረት መፍጠር አለመቻል ነው ።
በዳበሩ ሀገሮች ያሉትና የቴክኖሎጂዎቹ
ባለቤት የሆኑት ድንበር ዘለል ኩባንያ
ዎች (Transnational Corporations) በዚህ
ረገድ ታዳጊ ሀገሮች የሚገጥማቸ
ውን ችግር የሚያባብሱ ፣ በዚህ በቴክ
ኖሎጂ ያላቸው ሞኖፖል እንደተጠበቀ
እንዲቆይ የሚሹ ናቸው ። ለምሳሌ አንድ
ኢንዱስትሪ ሲቋቋም ለእሱ የሚያስፈል
ጉት መለዋወጫ ዕቃዎች ፣ ሞተሮች ወዘተ-
ከላኪው ሀገር እየመጣ የሚተካበት እንጂ
ታዳጊው ሀገር ራሱን ችሎ እነዚህን ሁሉ
በራሱ የሚያካሂድበትን ሁኔታ መፍጠር
አይሹም ። ብዙውን ጊዜም ማኔጅመንቱና
የቴክኖሎጂው አመራር ከራሳቸው ሀገር
በመጡ ባለሙያዎች (ስፔሻሊስቶች) ሥር
እንዲሆን ያደርጋሉ ። ሌላው በዚህ ረገድ
የሚታየው ችግር ከዳበሩ ሀገሮች የሚመጡ
ቴክኖሎጂዎች ከታዳጊው ሀገር ፍላጎት ጋር
የሚገጥሙ አለመሆናቸው ነው ። በዚህ
ረገድ ጎልቶ የሚታየው እነዚህ ቴክኖሎጂ
ዎች ጉልበትን ለመቆጠብ ታስበው የተ
ሠሩ ስለሆነ ከጉልበት ይልቅ ካፒታል የሚ
ጠቀሙ ናቸው ። ታዳጊ ሀገሮች ደግሞ ችግ
ራቸው የሰው ኃይል አይደለም ። እንዲያ
ውም ዋና ዓላማቸው ለዜጎቻቸው አምራች
እንዲሆኑ የሚያበቃቸው ሥራ መፍጠር
ነው ። ለታዳጊ ሀገሮች ምርጫው እጅግ
ውድና ዘመናዊ የሆነ ቴክኖሎጂ አምጥቶ
በጥቂት ሰዎች ብቻ ማምረት ሳይሆን በር
ካታ የሀገሪቱን ሰዎች የሚያሳትፍ ቀለል
ያለ ቴክኖሎጂ ነው ። እርግጥ አንዳንድ ልዩ
ምርቶች (ኬሚካል ፣ ነዳጅ ማጣሪያ ወዘተ-)
የረቀቀ ቴክኖሎጂ መሻታቸው ግድ ይሆ
ናል ። ግን እንደ ጨርቃጨርቅ ባሉ ኢን
ዱስትሪዎች በቀላሉ ቴክኖሎጂ መጠቀም
ይቻላል ፤ አስፈላጊም ነው ።

ባጭሩ የኋላቀር ሀገሮች ኢኮኖሚ የተን
ጋደደና የዳበሩ ሀገሮች ጥገኛ ከመሆኑ የተ
ነሣ የሚደርስበትን ጉዳት ከላይ ያነሣናቸ
ውን ነጥቦችና ሌሎችንም በማከል በሰፊው
ማተት ይቻላል ። ለጊዜው ግን በዚህ እና
ቁምና ራሳቸው ኋላቀር ሀገሮችም ሆኑ ያዳ
በሩት ሀገሮች ችግሩን እንዴት ያዩታል ?
ለማስወገድስ ምን ጥረት እያደረጉ ነው ?
ወደሚለው እናምራ ።



Digitized by Google

እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ በተባበሩት መንግሥታት አጠቃላይ ስትራቴጂ ሥር ሁለት የየአሥር ዓመት የዕድገት መከፋዎች (Development Decades) ተደርገው ሦስተኛው አሁን በመካሄድ ላይ ነው። ካለፉት የምናየው ውጤት ግን የችግሩን መባባስ እንጂ መቀነስ አይደለም። ሌላው ጥረት ደግሞ የአሁኑ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ራሱ የችግር ምንጭ ስለሆነ በአዲስ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመተካት የሚደረገው ጥረት ነው።

የዛሬዎቹ ኋላቀር ሀገሮች ችግር በአውሮፓ ከዳበረው ካፒታሊዝም ጋር የተያያዘና አሁንም ችግሩ እንዲቀጥል ግድ ረግ የያዘው ያው የተዘረጋውና ዛሬም ድረስ አቆራኝቶአቸው ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓት መሆኑን ካፒታሊስት ሀገሮች ወይ ጥራቹት ይክዳሉ፤ አሊያም ያ ለዛሬው ችግር ምክንያት እንዳልሆነና ይልቁንም ችግሩ ያለው በራሳቸው በኋላቀር ሀገሮች ዘንድ እንደሆነ ሊያቀርቡ ይሻሉ። በዚህ ረገድ ዋና ምክንያት አድርገው የሚቆጥሩት የኋላቀር ሀገሮችን የሕዝብ ብዛት ዕድገት መጠን ነው። ሱሳን ጆርጅ የምትባል ጸሐፊ ይህን ስትገልጽ እንዲህ ትላለች።

«ምዕራባውያን ለሦስተኛው ዓለም ችግር ዋንኛው ተጠያቂ አድርገው የሚያቀርቡት ሕዝቡን ራሱን ነው። ምዕራባውያን ስለዓለም ረሃብ ለአንባቢያንና ለተመልካቾች ለዘውትረው የሚያቀርቡት በርግጥም ብቸኛው ምክንያት በደሃው ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብ ቁጥር እየናረ መሄዱን ነው።»[37]

ኋላቀር ሀገሮች ቢራቡ፣ ቢቸገሩ ራሳቸው በራሳቸው ላይ ያመጡት ጣጣ ስለሆነ በዚህ አማካኝተው ስለዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት መዛባትና ስለመለወጡ አስፈላጊነት ሊያነሡ እንደማይገባቸው የሚከራከሩ አሉ። ካፒታሊስት ሀገሮች የሚያቀርቡት ትንተና ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ነው። «የዓለም ሀብት (ምግብን ጨምሮ) የተወሰነ ነው። ዓለም ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ከሆነው ከኋላቀር ሀገሮች የሕዝብ ዕድገት መጠን የተነሣ ተጣባለች። ኋላቀር ሀገሮች የሕዝብ ብዛታቸው ስለሚያስከትዳቸው ከዓለም ሀብት ከቀን ወደቀን ይበልጥ ለፍጆታ ሊያውሉ ይሻሉ። ይህም ሁኔታ ይህን ሁሉ ሆድ መመገብ የማትችለውን መሬት አደጋ ላይ እየጣለ ነው።... ድህነትና ረሃብ ሊጠፉ የሚችሉት ሦስተኛ ዓለም ከመጠን ያለፈውን የሕዝብ ዕድገት መጠን ሲቆጣጠሩ ነው።»

ይህ ትንተና የሚከተለውን የማልትስ አባባል ያስታውሰናል።

ሰው በተጣበበት ዓለም ውስጥ አንድ ሰው ቢወለድ ማግኘት የሚገባውን፣ ለሕልውናው የሚያስፈልገውን የዕለት ጉርስ ከወላጆቹ ሊያገኝ አይችልም። ኅብረተሰቡም የሱን ጉልበት የማይሻ እስከሆነ ድረስ ፍርፋሬ እንኳን የመጠየቅ መብት ይለውም ተፈላጊ አይደለምና።[38]

የሕዝብ ብዛት ጉዳይ በተለያየ መድረክ የተነሣና ያወዛገበ ጉዳይ ነው። በነሐሴ ወር 1974 የተባበሩት መንግሥታት ስለዓለም ሕዝብ በቡካሬስት ከተማ ስብሰባ አካሂዶ ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ ብዙ ሀገሮች የመጀመሪያውና መሠረታዊው የዓለም ሕዝብ ብዛት ምክንያት ያለው በኋላቀር ሀገሮች ሀብት መበዝበዝ፣ መራቆትና ኋላቀር መደረግ እንደሆነ ገልጸዋል። በዚሁ ስብሰባ ላይ የቫቲካን ተወካይ «የዓለም ሕዝብ ብዛት ችግር ምክንያት የሀብታሞች ራስ ወዳድነት እንጂ የድሆች መራባት አይደለም» ብለዋል። ባጭሩ ስብሰባው ችግሩ የዓለም ሀብት በሚዛናዊ ሁኔታ አለመዳረስ መሆኑን አምኖበታል።[39]

የሌሎች መራቆት፣ መራብ፣ ባለጸጋ ለሆኑት ሀገሮች ኃይልና የበላይነትን ስለሚሰጣቸው በሆነው ባልሆነው በማድበስበስ ያለውን ሥርዓት መቆየት ይደግፋሉ። እንደዩናይትድ ስቴትስ ያሉ ባለጸጋ ሀገሮች ምግብን ልክ እንደጠብመንጃ በእጃቸው ያለ መሣሪያ አድርገው ያዩታል። የዩናይ



Digitized by Google

ትድ ስቴትስ የእርሻ ኃላፊ የሆኑት ኤርል ባዝ ይህንኑ ሲገልጹ «ምግብ መሣሪያ ነው፤ በአሁኑ ወቅት አንዱ የመደራደሪያችን ዓይነተኛ ቁልፍ ነው» [40] በማለት ገልጸውታል ። የሲ.አይ.ኤ ሪፖርት የሦስተኛው ዓለም ረሃብ ለዩናይትድ ስቴትስ የሚሰጠውን ኃይል ያለምንም ሀፍረት እንዲህ ሲል ገልጾታል ፡ « በሦስተኛው ዓለም የተከሰተው የምግብ እጥረት ለዩናይትድ ስቴትስ ከዚህ ቀደም ያልነበራትን ዓቢይ ኃይል ያጐናጽፋታል ። » [41]

የዓለም ሀብት ምንጭ የተወሰነ ነው የሚለውን ቀደም ሲል ያነሣነውን አባባል እንዲያው ለነገሩ እንቀበል ቢባልም እንኳን ቀናው ጥያቄ መሆን ያለበት ዛሬ ማን ? ምን ያህሉን እየተጠቀመበት ነው ? ለምንስ ዓይነትስ ተግባር ነው ? የሚል መሆን ይኖርበታል ። ላዘር ሞጁስ ይህን ሁኔታ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል ።

—ሦስት አራተኛ ኋላቀር የዓለም ሕዝብ 6.5% የዓለም ገቢ ያገኛል ።

—የዳበሩ ሀገሮች ነፍስ ወከፍ ገቢ የኋላ ቀር ሀገሮች ከ18—20 እጅ ነው ።

—ኋላቀር ሀገሮች አሁን ያለውን የጥሬ ሀብት 80% የያዙ ሲሆን ከጠቅላላ የኢንዱስትሪ ምርት ድርሻቸው 7% ነው ።

—የዓለም ሕዝብ አብዛኛው በረሃብ ሲሰቃይ ከዓለም ሕዝብ 6% ብቻ የሆነው የዩናይትድ ስቴትስ ሕዝብ 55% የሆነውን የዓለም የተፈጥሮ ሀብት እየተጠቀመ ነው ። ለምሳሌ ያህል በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ የአየር ማቀዝቀዣ መሣሪያዎች ብቻ (Air Conditioning Plant) የሚጠቀሙት ኤሌክትሪክ ሕዝባዊት ቻይና ከምትጠቀምበት ጠቅላላ ፍጆታ ይበልጣል ። [42]

በተጨማሪም በመሣሪያ አሽቅድድም ላይ የሚወጣውን ወጭ እስቲ እንይ ።

—በ1962 በመላው ዓለም የሚሊታሪ ወጭ $ 120 ቢሊዮን ነበር ። ይህ የጠቅላላው ኋላቀር ሀገሮች ዓመታዊ ገቢ 2/3 ነበር ።

—በ1967 ይህ ወጭ ወደ $ 182 ቢሊዮን ፤ በ1974 ወደ $ 210 ቢሊዮን ከፍ አለ ። ይህ መጠን በወቅቱ ለደሀ ሀገሮች ከተሰጠው ዕርዳታ 20 እጅ የሚበልጥ ነበር ። ወጭው እየጨመረ በመሄድ በ1975 $ 300 ቢሊዮን ፤ በ1979 $450 ቢሊዮን፤ባሁኑ ወቅት ከ$ 500 ቢሊዮን በላይ ሆኗል ።

ቀድሞ የምዕራብ ጀርመን ቻንስለር የነበሩት ዊሊ ብራንት በ1980 ለኋላ ቀር ሀገሮች የተደረገው ዕርዳታ በዚያን ዓመት ለሚሊታሪ ወጭ ከተደረገው 5% እንደማይሆን ከጠቀሱ በኋላ ለመሣሪያ የሚወጣው ወጭ ጥቂቱ ለዕድገት ዕርዳታ ቢውል ምን ያህል ለውጥ እንደሚያመጣ እንደሚከተለው ይገልጻሉ ።

—የግማሽ ቀን የሚሊታሪ ወጭ ብቻ የዓለም ጤና ድርጅትን ጠቅላላ የወባ ማጥፊያ ወጭ ሊሸፍን ይችላል ።

—ዘመናዊ ታንክ አንድ ሚሊዮን ዶላር ያወጣል፤ይህ ለ 10.000 ቶን ሩዝ መጋዘን ይሠራል ። በዚህም ይባክን የነበረውን ከ 4,000 ቶን የሚበልጥ ለማትረፍ ይቻላል ።

—ይህንኑ ያህል ገንዘብ ለ 30,000 ሕፃናት 1,000 መማሪያ ክፍል ሊሠራ ይችላል ።

—በአንድ ተዋጊ ጀት ዋጋ (20 ሚሊዮን ዶላር) 40,000 የገጠር ፋርማሲዎች ማቋቋም ይቻላል ።

—የአንድ ዓመት የዓለም የሚሊታሪ ወጭ 1/50 ብቻ የምግብ ምርት እጥረት ያለባቸው ሀገሮች በ1990 ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የእርሻ መሣሪያዎችን ሊያሟላ ይችላል ። [43]



Digitized by Google

አሁን ያለው የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት የተዛባ ፥ የኋላቀር ሀገሮችን ችግር ማባባስ እንደያዘ ፥ ስለአዲሱ የኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚነሡ ጥያቄዎች ከሰላም፥ ከጦር መግሪያ ትንሳና ከሰው ልጆች ደኅንነትና ብልጽግና ጋር የተያያዙ መሆናቸውን የሚጠቁሙ በርካታ ምሳሌዎች በመጥቀስ ማሳየት ይቻላል ። «ደቡብ» በሚል መጠሪያ የሚታወቁት ኋላቀር ሀገሮች ይህ ሥርዓት እንዲለወጥ ፥ ሚዛናዊ አሠራር እንዲኖር ሲጠይቁ «ሰሜን» በመባል የሚጠሩት የበለጸጉ ካፒታሊስት ሀገሮች ግን ይህ እንዲሆን የሚሹ አልሆኑም ። በዚህ ረገድ የተደረገውን ጥረት፥ አሁን ያለበትን ሁኔታ፥ በየጊዜው የገጠሙትን ችግሮች ቀጥለን እንይ ።

ኋላቀር ሀገሮች ነፃ መውጣት እንደያዙ ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓት የተዛባ መሆኑን ይበልጥ እየተገነዘቡ ፥ ይህም እንዲስተካከል እየጠየቁ መጡ ። በ1955 በባንዱንግ የተካሄደው የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች ስብሰባ ኢኮኖሚ ጥያቄዎችን ያነሣ የመጀመሪያው የታዳጊ ሀገሮች ስብሰባ ነበር ። ይህ ስብሰባ በመሠረቱ የፖለቲካ ነፃነት እንቅስቃሴ ቢሆንም ፥ በመጠኑም ቢሆን ያነሣቸው የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ኋላ እየተጠናከሩና ቅርጽ እያበጁ «የሦስተኛው ዓለም» ጥያቄዎች ሊሆኑ በቅተዋል ። ይሁንና አዲስ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ጽንሰ ሐሳብ እንዲጠናከር የረዱት በ1960ዎቹ ዓመታት ውስጥ የተካሄዱ ስብሰባዎችና ውይይቶች ናቸው ለማለት ይቻላል ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው ።

—የተባበሩት መንግሥታት የንግድ ዕድገት ጉባኤ (UNCTAD) እንዲጠራ ያስቻለው የ1961 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ፤

—የ77 ቡድን (Group of 77) በመባል የታወቁትና አሁን ከመቶ በላይ የሚሆኑ የአፍሪካ፥የእስያና የላቲን አሜሪካ መንግሥታት የተቋቋሙበት የመጀመሪያው የአንክታድ (UNCTAD) ስብሰባ ፤

—በ1967 ፥ በጥቅምት ወር በአልጀርስ የተደረገው የታዳጊ ሀገሮች የኢኮኖሚ ስብሰባ ፤

—በ1961 በቤልግሬድ ፥ በ1964 በካይሮ ፥ በ1970 በሉሳካ ፥ በ1973 በአልጀርስ የተደረጉት የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባዎች ፥

—በ1964 በጄኔቭ ፥ በ1968 በኒውዴልሂ ፥ በ1972 በሳንቲያጎ ፥ በ1976 በናይሮቢ ፥ በ1979 በማኒላ የተደረጉ የአንክታድ ስብሰባዎች — አዲስ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲቋቋም ጥሪ ያቀረቡ ናቸው ።

ይሁንና ለዚህ ዓይነቱ ጥሪ መነሻ ተደርጎ የሚታወቀው በ1973 በአልጀርስ የተደረገው የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባ ነው ። ከዚህም ጥሪ ተከትሎ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በ1974 ከስድስተኛው ልዩ ስብሰባ ላይ ስለአዲስ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም መግለጫና የድርጊት ፕሮግራም አወጣ ። ከዚህም በኋላ ቃሉ ዓለምአቀፍ ተቀባይነትን አገኘ ። የመግለጫውን መግቢያ ባጭሩ እንጠቅሳለን ።

እኛ የተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገሮች ማንኛውም ሀገር በሚከተለው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት ልዩነት ሳይደረግ ፥ እኩልነትንና ሉዓላዊነትን የሚያስከብር ፥ በጋራ ጥቅምና ትብብር ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን የሚያጠናክር ፥ ኢእኩያዊነትንና አድልአዊ አሠራርን የሚያስወግድ፥ በበለጸጉና በታዳጊ ሀገሮች መካከል ያለውን የሰፋ ልዩነት የሚያቀራርብ ፥ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ የሚጠቅም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትን የሚያፋጥንና ሰላምና ፍትሕ እንዲዳብሩ የሚያደርግ አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት ያለንን ቁርጠኛ አቋም እንገልጻለን ።[44]



Digitized by Google

ይህ መግለጫ ከወጣ ወዲህ አዲሱን የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት የመመሥረቱ ጥያቄ በኢምፔሪያሊስትና በታዳጊ ሀገርችም መካከል አወዛጋቢ ጉዳይ ሆኗል ። በመሠረቱ በኢምፔሪያሊስትና በታዳጊ ሀገሮች መካከል ያለውን ዓለምአቀፍ ፍጥጫና ውዝግብ በተለያዩ ስያሜዎች ለመሸፈን የሚደረግ ጥረት አለ። የዳበሩ ሀገሮችን በጅምላ ሰሜን ፣ ኋላቀር ሀገሮችን ደቡብ የሚለው ክፍፍል ከነዚህ ዓይነት ስያሜዎች አንዱ ነው። ይህንኑ ክፍፍል በሌሎች በተለያዩ ስሞች የሚጠሩ አሉ። ለምሳሌ ደሀና ሀብታም (Poor and Rich) የበለጸጉና በማደግ ላይ ያሉ (Developed and Developing) መሐልና ዳርቻ (Center and Periphery) ወይም ሦስተኛ ዓለም የሚሉ መጠሪያዎች አሉ ። ደቡብ የሚለው ቃል በ1950ዎቹ ሰር አሊቨር ፍራንክ በተባሉ በዋሽንግተን የእንግሊዝ አምባሳደር የተፈጠረ ቃል ሲሆን ፣ እኚህ ሰው በዚያን ጊዜ ሰሜንና ደቡብ የሚል ክፍፍል ሙሉ ሲያደርር በዓለም ፖለቲካ ውስጥ ምሥራቅ ምዕራብ የሚለውን ቃል ይወዳደራል ብለው ነበር። ሰሜን ደቡብ የሚለው ክፍፍል ከጥላ ጉደል መልከአ ምድራዊ አተገማመጥን የተከተለ ሲሆን ከዚህ ትንሽ ለየት ይላል ። ለምሳሌ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ ከምድር ወገብ በታች ሲሆኑም በዚህ ውስጥ ሰሜን በሚለው መጠሪያ ሥር ይጠቃለላሉ ።

በተጨማሪም ይህ የጅምላ መልከአ ምድራዊ ክፍፍል ኢምፔሪያሊስቶች በቅኝ አገዛዝ ወቅትና ከዚያም ወዲህ ታዳጊ ሀገሮችን በመበዝበዝ ያደረሱትንና የሚያደርሱትን ጥፋት ፣ በዚህም ምክንያት ያለባቸውን ተጠያቂነት ወደ ሶሻሊስት ሀገሮችም የሚላከክ በመሆኑ ለእውነተኛ ነፃነት የቆሙና የታዳጊ ሀገሮችን ችግር በትክክል የተረዱ ሁሉ አይቀበሉትም ። በተባበሩት መንግሥታት ሆነ በሌሎች ዓለምአቀፋዊ እንዲሁም አህጉራዊ ስብሰባዎች ላይ ታዳጊ ሀገሮች ለነፃነታቸው መከበርና ከብዝበዛ ለመላቀቅ የሚያቀርቧቸውን ትክክለኛ ጥያቄዎች ሶሻሊስት ሀገሮች ይደግፋሉ ። ይህን ጉዳይ በዚህ ጽሑፍ ሁለተኛ ክፍል በሰፊው ለመመርመር እንሞክራለን ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ደቡብ—ሰሜን የሚለውን ስያሜ የምንጠቀምበት በኢምፔሪያሊስትና በታዳጊ ሀገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ትርጉሙ ነው ።

አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዛሬ በሰፊው የሚነገር ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ስለጽንሰ ሐሳቡ ያለው ግንዛቤ ግን የተለያየ ነው ። በምዕራባውያን ዘንድ የተለመደው (ግርከሳዊ ያልሆነ) ምላሽ (መፍትሔ) ጉብታዊ የገበያ ሁኔታን መጠናከር የሚደግፍ ነው ። ይህ «መፍትሔ» ሸቀጦች ፣ ገንዘብ ፣ ምርት ፣ መሣሪያዎች እንደልብ ቢዘዋወሩ ፣ የንግድ ካፒታል እንደልብ መንቀሳቀስ ቢችል ፣ ለንግድ መስፋፋት ዕንቅፋት የሚሆኑት ሁኔታዎች ቢወገዱና ታዳጊ ሀገሮች በግዛታቸው ውስጥ ለውጭ ኩባንያ አሠራር አመቺ ሁኔታን ቢፈጥሩ (Open Door) ያለውን የውጭ ንግዳቸውን ቢያስፋፉ ፣ የገንዘብን ምንዛሬ ዋጋ ዝቅ ቢያደርጉ ፣ በአጭሩ የዛሬዎቹን ካፒታሊስት ሀገሮች የዕድገት ፈር ቢከተሉ በእነሱ አምሳያ ማደግና መስተካከል የሚችሉ መሆኑን ይገልጻል ።

ይህ ዘዴ ሦስተኛ ዓለም ባለበት የተንጋደደና ጥገኛ የሆነ ኢኮኖሚ ታሪካዊ ምክንያቶችንና አሁን ድረስ ያለውን የባዕድ ተጽዕኖ ይዘነጋል ። ይህን «መፍትሔ» የዓለም ባንክና ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ላለፉት ፵ ዓመታት ሲደግፉና ሀገሮችም እንዲከተሉት ሲገፋፉ ቢኖሩም ዛሬ የኋላቀር ሀገሮች ኢኮኖሚ ሁኔታ እንደሚያሳየው ዘዴው ችግሩን ያባባሰ እንጂ ያሻሻለ ሆኖ አልተገኘም ።

ሌሎች በመፍትሔነት የሚቀርቡ ዘዴዎች የላይኛውን የሚቃወሙ ፣ ሆኖም በመካከላቸው ከፍተኛ ልዩነት የሚታይባቸው ናቸው ። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ታዳጊ ሀገሮች ከካፒታሊስቱ ዓለም ጋር በን



Digitized by Google

ገድ ፣ በፊናንስ ያላቸውን ግንኙነት ፍጹም መበጠስ ለወደፊት ዕድገት የግድ መጓላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው የሚል ዘዴ ነው። ሌላኛው ደግሞ በተመረጡ መስኮች ራስን ከካፒታሊስት ሀገሮች ማላቀቅን (Selective Delinking) የሚደግፍ ነው ።

ይህ ዘዴ ታዳጊ ሀገሮች ከራሳቸው የዕድገት ዓላማ በሚገጥም መንገድ ከሚስማማቸው ሀገር ጋር የንግድም ሆነ ሌላ ግንኙነት መመሥረትን የሚያመለክት ነው ። የዚህ ዘዴ ደጋፊዎች ዓለምአቀፍ ንግድና ሙአለ ንዋይ ለሁለቱም ወገን ይበጃል ይላሉ ። ስለሆነም የመዋቅር መሻሻል (Structural Reform) መደረጉን ማለትም በገበያ ሁኔታ ላይ ቁጥጥር መደረጉን፣ጥቅምም ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ለሁሉ እንዲዳረስ እርምጃ መወሰዱን ፣ የገንዘብ ዕርዳታ መደረጉን ፣ ለታዳጊ ሀገሮች ጥቅም የሚሆን የንግድ አቅጣጫ መቀየሱን ይደግፋሉ ። ይህም በመተባበር እንጂ በመጋጨት እንደማይሆን ይገልጻሉ ። በተባበሩት መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት ያለው (በሰፊው የምናየው) ይህኛው ነው ።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን እርምጃዎች መውሰድ ጠቃሚነቱ ባያጠራጥርም በዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ መሠረታዊ የማኅበራዊ ግንኙነቶችና የምርት መዋቅር ለውጥ ካልተካሄደ በስተቀር በኢንተርናሽናል ንግድና ፊናንስ ውስጥ የሚደረግ የጥገና ለውጥ ዘላቂ መፍትሔ አይሆንም ፤ ይልቁንም «በሽታውን ሳይሆን የበሽታውን ምልክቶች ለማስወገድ እንደመጣር ይሆናል የሚልና ሌላ ዘዴ የሚያቀርብ አለ፣ ይህኛው የማርክሲስቶች አቋም ሲሆን አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ወደ ሶሻሊስት የዕድገት አቅጣጫ ማምራት የሚኖርበት መሆኑን የሚያሳይ ነው ።

እንግዲህ በሚቀጥሉት ገጾች መጀመሪያ ታዳጊ ሀገሮች በአጠቃላይ (የደቡብ ክፍል) ምን ምን ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙላቸው እንደጠየቁ በሰፊው እናያለን ። ቀጥለንም ባንድ በኩል በተባበሩት መንግሥታትና ባንዳንድ ቡድኖች በኩል ችግሩን ለመፍታት የቀረቡ ሐሳቦችን ፣ በሌላ በኩል የለሙ የካፒታሊስት ሀገሮች ለችግሩ ያላቸውን አመለካከትና የሰጡትን ምላሽ እናያለን ።

## የታዳጊ ሀገሮች ጥያቄ

አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት ታዳጊ ሀገሮች የሚያቀርቡት ጥያቄ የደቡብን ክፍል የምርት ዋጋ ፣ የሰሜኑን የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ዋጋ ፣ የሰሜኑ ቴክኖሎጂና ኢንዱስትሪዎች ወደ ደቡብ ክፍል የሚተላለፉበትንና የሚስፋፉበትን ሁኔታ ፣ የዓለምን የገንዘብ ሥርዓትና ተቋሞችን አሠራር ፣ ውሱንነት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ የመጠቀምን ወዘተ. ጥያቄዎች ያዘለ ነው ። ጥያቄዎቹን አንድ ባንድ አንሥቶ በሰፊው ማውሳቱን ለጊዜው በመተው በሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ላይ በማተኮር ሁኔታውን ለማየት እንሞክራለን ።

ሀ· ወደ ዳበሩ ሀገሮች ገበያ ለመድረስ ስለመቻል ጥያቄ ፤

ለ· በዓለም የገንዘብ ሥርዓት ውስጥ የተቋሞች ለውጥ ስለማስፈለጉ ጥያቄ ፤

ወደ ዳበሩ ሀገሮች ገበያ መግባት ስለመቻል ጥያቄ ቀደም ሲል ኋላቀር ሀገሮች በዓለም ገበያ ላይ በሸማችነትም ሆነ በሻጭነት ደካማ አቋም እንዳላቸውና በዚህም እንደሚጠቁ ከዚህ በላይ ተመልክቷል ። በተለይም የንግድ ልውውጥ ሚዛን(Terms of Trade) ወይም የታዳጊ ሀገሮች የውጭ ንግድ የመግዛት ዓቅም እየወደቀ መሄድ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እየጣላቸው ነው ። በዚህ ላይ በታዳጊ ሀገሮች የተፈበረኩ ሸቀጦች ወደ ሀገራቸው በብዛት እንዳይገቡ በኢንዱስትሪ የዳበሩ ሀገሮች በታሪፍና በመሳሰሉት የሚያደርጉት ገደባ ወይም እገዳ ኋላቀር ሀገሮች ንግዳቸውን እንዳያስፋፉና ለሸቀጦቻቸው ገበያ እንዳያገኙ ዕንቅፋት



Digitized by Google

ሆኗል ። ኋላቀር ሀገሮች ደግሞ ከዕርዳታ ይልቅ የዚህ ዓይነቱ የንግድ ግንኙነት ቢስፋፋላቸው ይሻሉ ። ምክንያቱም ንግድ በሀገራቸው ውስጥ የተሻለ የሥራ ዕድል ስለሚከፍትና እንደዕርዳታም ብዙ ተጽዕኖ አያስከትልምና ነው ።

ንግድን በሚመለከት የታወቀው ዓለም አቀፍ ድርጅት የታሪፍና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት ( Genral agreement on Tarrif and Trade ) የተሰኘው ሲሆን ይህ በ1947 የተቋቋመ ተቋም ዓላማው በዓለም በሚነገዱ ዕቃዎች ላይ የሚጣለውን ታሪፍና እንዲሁም ለንግድ ዕንቅፋት የሚሆኑ ሌሎችን ነገሮች ለማስወገድ መጣር ነው ። ስምምነቱ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት ባይችልም ቢያንስ በመርህ ደረጃ ለታዳጊ ሀገሮች መድረክ የሚሆን ሐሳብ አቅርቧል ። ይህም አንድ በንግድ ድርድር ልዩ አስተያየት እንዲደረግለት ( Concesion ) የሚፈልግ ሀገር እሱም በበኩሉ ተመሳሳይ አስተያየት ማድረግ አለበት የሚል ነው ። ከዚህም ሌላ በ1973 በቶኪዮ የጸደቀውን አጠቃላይ አመች የንግድ ቀጣና ሥርዓት ( Generalized System of preference ) ተብሎ የሚጠራውንም አውጥቷል። የዚህም ዓላማ በተለይ ከታዳጊ ሀገሮች ለሚመጡ ምርቶች ተስማሚ ታሪፍ (Preferential Tarrif ) መስጠትን የሚያመለክት ነው ። ይሁንና የታሪፍና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት በተግባር ያስገኘው ውጤት አጥጋቢ አይደለም ። ለምሳሌ አጠቃላይ አመች የንግድ ቀጣናን ብንወስድ ችግር የሚገጥመው የትኞቹ የታዳጊ ሀገር ሸቀጦች ተስማሚ ታሪፍ ያገኙ የሚለውን ጥያቄ መወሰኑ ሲሆን ይህን የሚወስኑት ደግሞ የዳበሩ ሀገሮች መሆናቸው ነው።የዳበሩ ሀገሮች የሚመርጡአቸው ሸቀጦች ኋላቀር ሀገሮች የሚፈልጓቸው ላይሆኑ ይችላሉ ። ስለሆነም ነገሩ ዞር ዞር ጠቃሚነቱ ለዳበሩ ሀገሮች ይሆናል ማለት ነው ። ለምሳሌ የአጠቃላይ አመች የንግድ ቀጣና ሥርዓት ሐሳብ ይዘት ባብዛኛው በጉልበት ኃይል (Labour intensive) የተመረቱትን ምርቶች ከድርድር ወጭ ያደርጋል ። ኋላቀር ሀገሮች የሚሹት ደግሞ የእነዚህን ዓይነቶች ምርቶች ወደለሙት ሀገሮች ሊላኩ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲወሰን ነው ። ስለዚህም ነው የዚህ ዓይነቱን ድርጅት አሠራር መሻሻል አጥብቀው የሚጠይቁት ።

አጠቃላይ የንግድ ቀጣና ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ አጠቃላይ የንግድ ሥርዓት መርህ ቢወሰድም ሀገሮች በየግላቸው የጋራ የንግድ ስምምነት ያደርጋሉ ። ይህም እንደከፊል ተስማሚ ወይም አመች ሥርዓት(Partial System of Preference) ሊታይ ይችላል ። ለምሳሌ ምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች ባብዛኛው የቀድሞ ቅኝ ሀገራቸው ከነበሩት ጋር የሎሜና የያውንዴ ኮንቬንሽን የተሰኙ የንግድ ስምምነቶች (Preference ) አበጅተዋል ።

ወደዳበሩ ሀገሮች ገበያ የመድረሱ ጥያቄ አንዱ መልክ የዋጋን መረጋጋት የሚመለከት ነው ። ይህም በሁለት ዘዴዎች ሊካሄድ ይችላል ። የሚለዋወጡት ዕቃዎች በተመጣጠነ ሁኔታ ዋጋቸው መጨመሩን (ወይም አብሮ መጓዙን ) የሚከታተል ነው ። ሁለተኛው ቢያንስ ዋና ዋና ለሆኑ የኋላቀር ሀገር ሸቀጦች ዓለምአቀፋዊ ክምችት ( Stock ) መፈጠር ነው ። ይህም ከፍተኛ ምርት (ገበያቸው ከሚፈልገው በላይ) ሲመረት ትርፉን በማስቀመጥ የዋጋን መውደቅ መከላከል ፣ በአንፃሩ አቅርቦት ሲያንስ ተገዝቶ ከተከማቸው አውጥቶ በመሸጥ የዋጋን መዋዠቅ መቆጣጠር ነው ። ከዚህም ሌላ ዓለምአቀፍ የሸቀጥ ስምምነቶች ሊደረጉ ይችላሉ ። ለምሳሌም ዓለም አቀፍ የቡና ስምምነትን ፣ የኮካ ስምምነትን ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል ። የዚህ ዓይነቱ ስምምነት የሚያስገኘው ውጤት በሸቀጡ ባሕርይ ይወሰናል ። ለምሳሌ ሸቀጥ እንደነዳጅ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ከሆነ ታዳጊ ሀገሮች አመች የሆነ ስምምነት ሊደራደሩ ይችላሉ ማለት ነው ።



Digitized by Google

ባጠቃላይ ደቡብ ወደሰሜን በሚልካቸው ሸቀጦች በኩል የሚገጥሙትን ችግሮችና እነሱንም ለመፍታት የሚቀርቡትን ሐሳቦች ወደፊት እንመለከታቸዋለን ። ቀጥለን የዓለም የገንዘብ ሥርዓትን እንመልከት ።

የንግድ ፣ የቴክኖሎጂ መተላለፍ ወዘተ. ጉዳይ በዓለም የገንዘብ ሥርዓት ላይ የተደገፈ ነው ። የረጋና የታወቀ ፣ የማይዋዥቅ የገንዘብ የልውውጥ መጣኔ ንግድንም ሆነ ሙአለ ንዋይን ያራምዳል ። ባንፃሩ የሚዋዥቅ ከሆነ ደግሞ ያዳክማል ።

የዓለም የገንዘብ ሥርዓት የተጠነሰሰው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በ1944 በብሪተን ውድስ( Briton Woods )በተደረገው ስምምነት ነው ። ዓላማው በ1930ዎቹ የነበረውን የገንዘብ ዋጋ መቀነስ ውድድር (Devalution Convertability) አንዱን ገንዘብ ከሌላው በመምረጥ የሚፈጠረው የልውውጥ ችግር እንዲወገድና ኢንተርናሽናል የኢኮኖሚ ግጭት እንዳይደገም ለመከላከል ነበር ። በእንዲህ ያለው ሥርዓት መቋቋም ከፍተኛ ተሰሚነት ያገኙት ዩናይትድ ስቴትስና በአነስተኛ ደረጃም እንግሊዝ ነበሩ ። ምክንያቱም አንደኛ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት አውሮፓ ኢኮኖሚዋ ሲንኮታኮት አሜሪካ ግን ከጦርነቱ ከፍተኛ የማምረት ዓቅም ይዛ ልትወጣ መቻልዋ ነው ። ከዚህም ሌላ በጊዜው ጀርመን ፣ ኢጣልያንና ጃፓን ጠላት ሀገሮች ተደርገው ይታዩ ነበር ። ታዳጊ ሀገሮች ደግሞ ባብዛኛው ገና ቅኝ ሀገር በመሆናቸው በጊዜው በስብሰባው የተካፈሉት ሕንድ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ግብፅ ፣ ላይቤሪያና ነፃ የነበሩ የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ብቻ ነበሩ ። ሶሻሊስት ሀገሮችም በፖለቲካና በርዕዮተዓለም ምክንያቶች በነገሩ አልተሳተፉም ። ሶቭዬት ኅብረት መጀመሪያ ላይ በብሪተን ውድስን ስብሰባ ላይ ብትሳተፍም አልዘለቀችበትም ። በጊዜው በስብሰባው ላይ ከነበራቸው ተቃውሞ መካከል በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ውስጥ ለአባላት ድምፅ ለማከፋፈል የተወሰደውን አሠራር ፣ ሁለተኛ ብሔራዊ የወርቅና የውጭ ምንዛሬ ይዞታ እንዲያሳውቁና ከፊሉን ወደ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ቢሮ ወደዩናይትድ ስቴትስ እንዲያዛውሩ መጠየቃቸውን ፣ ሦስተኛ አባላት የውጭ ምንዛሬ ችግራቸውን ለማስወገድ ብድር ስለሚወስዱበት ሁኔታ የተደረሰበት ስምምነት ትክክለኛ ወይም ሚዛናዊ አለመሆኑን የሚመለከቱት ይገኙባቸዋል ።[45]

በብሪቶን ውድስ ስምምነት መሠረት ሁለት ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ተቋቁመዋል ፤ እነዚህም ኢንተርናሽናል የገንዘብ ልውውጥ ሥርዓትን ለመቆጣጠር ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ፣ ችግር ያለባቸውን ታዳጊ ሀገሮች በዕድገት ጥረታቸው ለመርዳት በሚል የዓለም የልማት ባንክ (IBRD) ናቸው ። በዚሁ ስብሰባ ላይ እያንዳንዱ አባል የሚያዋጣው የገንዘብ መጠን ፣ ከሚከማቸው ገንዘብ ማውጣት የሚችልበት ሁኔታና እንዲሁም የየአባላቱ የድምፅ ኃይል ተወስኗል ።እንዲሁም ለኢንተርናሽናል ልውውጥና ለክምችት (Reserve) መፍጠሪያ መስፈርት እንዲሆን ዶላር ስታንዳርድ ( Dollar standard ) የተሰኘው ጸድቋል ።

በዚህን ወቅት ሀገሮች ከወርቅ ይልቅ ዶላር መያዝን ይመርጡ ነበር ። ምክንያቱም ዶላርን ወዲያውኑ ወደፈለጉት ነገር ለመቀየርና ወለድም ሊያገኙበት ይችሉ ስለነበር ነው ። በዚህም ዶላር የዓለም ገንዘብ ሆነ ። ይህም ለዩናይትድ ስቴትስ የዓለም ገንዘብ የመፍጠር ዓቅም አስገኘላት ። የገንዘብ ሥርዓት መረጋጋት( Stability )በዩናይትድ ስቴትስ የገንዘብ ፖሊሲ ( አመራር ) ላይ የተወሰነ ሆነ ። ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል ይህ የዶላር ሥርዓት ከሞላ ጎደል ሲሠራ ቆየ ፤ ከዚያ ወዲህ ግን የአሜሪካ ኢኮኖሚ መዳከም ሲያሳይ ዶላርም መዋዠቅ ያዘ ። አሜሪካ በ1960ዎቹ እንዲሁም በ1970ዎቹ መባቻ ላይ በቬትናም ታካሂዶ የነበረው ጦርነት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር አስከተለባት ። ጦርነቱ ያስከተለው ችግር ከሌሎች የካፒታሊዝም ችግሮች (የሥራ አጥ ብዛት መጨመር የሸቀ



Digitized by Google

ጦች ገቢያ አጥቶ መከመር ወዘተ. ) ጋር ተዳምሮና አባብሷቸው የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ዕድገት እያንተተውና ለከፍተኛ ቀውስ እያጋለጠው መጣ። አሜሪካ ይህን ችግር ለመቋቋም በማሰብ በ1972 ወርቅን በዶላር መቀየሯን አቆመች። ለዶላር ሥርዓት መዳከም ሌላው ምክንያት አሜሪካ ከአውሮፓና ከጃፓን አንፃር ያላት የኢኮኖሚ ጥንካሬ እየተዳከመ መምጣቱ ነው። በኢንዱስትሪ የዳበሩ ሀገሮችን በሚያቅፈው የኢኮኖሚ ትብብርና ዕድገት ድርጅት (DECD) ጠቅላላ ምርት ውስጥ የአሜሪካ ድርሻ ከ60% ወደ 40% ዝቅ ሲል የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክና የጃፓን ከፍ ብሏል።[46] ይህ የምርት ድርሻ ዕድገታቸው ግን ገንዘባቸው ተመጣጣኝ ሚና እንዲጫወት አላስቻለም። ይህም በመሆኑ በአሜሪካ በኩል በሚታየው እጥረትና (Deficit) በሌሎቹ ዘንድ በተከማቸው ትርፍ (surplus) መካከል ቅራኔ እየከረረ ሄደ። ቻርልስ ደጎል በጊዜው ሲታ[illegible]ሙ እንዳመለከቱት አሜሪካ እጥረቷን ተጨማሪ ገንዘብ በማተም የምትወጣበት ሁኔታ እንዲሁ ያለ ችግር ሊቀጥል የሚችል ነገር አልነበረም። በመሆኑም የአሜሪካ የወርቅ ክምችት እየወደቀ፣ ሌሎች ሀገሮች እጅ ያለው የዶላር መጠን እያደገ ሄደ። ከዚሁ አኳያ በዶላር ላይ የነበረው እምነት (እንደተፈለገው) ሊለወጥ መቻሉ፣ (Convertebility) እየወደቀ ሄደ።

የዶላር ሥርዓት መውደቅና መዋዠቅ የሸቀጥ ላኪ ሀገሮችን እውን ገቢ ( real value) መውደቅን አስከተለ። ለምሳሌ ከ1979—1980 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በኢንዱስትሪ በዳበሩ ሀገሮች ውስጥ ከነበረው የገንዘብ ምንዛሬ ዋጋ ቅነሳ የተነሣ ታዳጊ ሀገሮች ከ13 እስከ 14 ቢሊዮን ዶላር በየዓመቱ ሊያጡ በቅተዋል።[47] በመዋዠቁ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቋቋም የመንግሥት የጋራ የገንዘብ ክምችት ለመፍጠር በተደረገው ስምምነት መሠረት በ1968 የጋራ ገንዘብ እንዲከማች የተደረገው በዶላር ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ ዓለም አቀፍ ልውውጥን እንዲያግዝና የተጠቀሰውን ዓይነት ችግር ለማቃለል ነበር። ይሁንና ይህ የተፈጠረው ገንዘብ (SDR) ክፍፍሉ ባብዛኛው ለሀብታም ሀገሮች ያደላ ስለነበር የታዳጊ ሀገሮችን ችግር ሊያቃልል አልቻለም።

ቀደም ሲል እንዳየነው የውጭ ምንዛሪ የታዳጊ ሀገሮች አንዱ ከፍተኛ ችግር ነው። ስለዚህም የገንዘብ ክምችት ከመፍጠር ጋር በአመቺ ሁኔታ ብድር ማግኘት የመቻል ጥያቄ ሌላ ቁልፍ ቦታ የያዘ ነበር። በተለይ ወለድ መክፈሉ ራሱ ለብዙ ሀገሮች ከባድ ሸክም እየሆነ በመሄድ የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን እያሟጠጠ መሆኑ በጣም አሳሳቢ ነገር ነበር። ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ብቻ የታዳጊ ሀገሮች የውጭ ብድር ሃያ እጅ የጨመረ ሲሆን ባሁኑ ወቅት ከ580 ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። በ1970ዎች መጨረሻ ላይ 90 ቢሊዮን ደርሶ የነበረው ዓመታዊ ክፍያ ታዳጊ ሀገሮች በአዲስ ሙአለ ንዋይ መልክ ወደሀገራቸው ከሚያስገቡት በላይ ሆኗል።[48] እንዲህ ያለውን ችግር አሳሳቢነት በማጤን ነበር አራተኛው የአንክታድ (UNCTAD) ስብሰባ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊያቀርብ የበቃው።

—29 ኋላቀር ሀገሮች ያለባቸው ዕዳ እንዲሠረዝላቸው ፤

—አብዛኛዎቹ ከፉኛ የተጎዱ ሀሮች የሚከፍሉት የካፒታልና የወለድ ክፍያ ከ1980 በኋላ እንዲከፍሉ እንዲሸጋገርላቸው ፤

—የአጭር ጊዜ የንግድ ዕዳ ወደ ረዥም ጊዜ (25 ዓመት) እንዲለወጥ ፤

—በአጠቃላይ የብድር ችግር ለመወያየት የአበዳሪና ተበዳሪ ሀገሮች የጋራ ስብሰባ እንዲደረግ ወዘተ. ናቸው።

ሌላው ጥያቄ ኋላቀር ሀገሮች በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በዓለም አቀፍ የልማት ባንክ አመራር ውስጥ የተሻለ ድምፅ እንዲኖራቸው፣ ማለትም ድምፅ የመስጠት



Digitized by Google

ድርሻቸው እንዲጨምር የሚል ነው። ከዚሁ ጋር በገንዘብ መዋዠቅ ምክንያት የሚደርስ ውን ጉዳት ለመቋቋም የሚሰጠው የመደጎሚያው ገንዘብም ክፍፍል አሁን እንዳለው በኮታ ሳይወሰን የታዳጊ ሀገሮች ችግር እየታየ ክፍፍሉ ሰፋ እንዲል የሚጠይቀው ይገኝበታል ።

## የለሙ ካፒታሊስት ሀገሮች መልስ

ከለሙት ሀገሮች የሚሰጠውን መ ል ስ በተለያየ መልክ ማየት ይቻላል ።

1- ከተባበሩት መንግሥታት በኩል ከሚ ደረገው ጥረት ፤

2- በራሳቸው ፈቃድና አነሣሽነት ጥረት ከሚያደርጉ ቡድኖች ፤

3- እንዲሁም ከተለያዩ መንግሥታት ከሚቀርበው ድጋፍና ተቃውሞ አን ፃር ማየት ይቻላል ። ቡድኖች የሚያ ደርጉት ጥረት ራሱ ከተለያየ አመለ ካከትና እምነት የሚነሣ በመሆኑ እን ደገና ሊከፋፈል ይችላል ።

ከፍፍሉቹን ሁሉ አንድባንድ አንሥቶ ማየቱ ሰፊ በመሆኑ ጭርአሳችን በቂ ገለጻ ይሰጣሉ ብለን የምንገምታቸውን ብቻ እና ቀርባለን ።

በተባበሩት መንግሥታት አስተባባሪነት ከተካሄዱት ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ሁለት ስብሰባዎች በኋላ ለአዲሱ ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚደረገው ክርክር እያ ደገ ሄዶ በ1968 በመስከረም ወር የተባ በሩት መንግሥታት ባቀረበው ጥያቄ መሠ ረት በተድሞው የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር በሌስተር ፒርሰን የሚመራ አንድ የታወቁ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን በልማት ተደጋ ፊዎች (Partners in Development) በመ ባል የሚታወቅ ሪፖርት አቀረበ ። ሪፖርቱ ለዓለምአቀፍ ዕድገትና የውጭ ዕርዳታ አዲ ስ መሠረትና አመለካከት ይሰጣል የተባለ ነበር ። የሪፖርቱ ዋና ሐሳብ ሀብት ከሀብ ታም ወደ ደሀ ሀገሮች እንዲተላለፍ ይጠይ ቃል ። በዚህም ረገድ ለታዳጊ ሀገሮች የለሙ ሀገሮች የሚሰጡት አስፈላጊው ዕርዳታ በ1968 ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርታቸው 0.39% የነበረው እስከ 1975 ባለው ጊዜ ድረስ ወደ 0.7% ከፍ እንዲል ጠይቋል ።

ይህ ሪፖርት በጊዜው በመንግሥታትና ምሁራን አካባቢ ከፍተኛ ውይይትን ቀስ ቅሶ ነበር ። ለተባበሩት መንግሥታት ሁለ ተኛው የአሥር ዓመት ስትራቴጂ እንዱ መንደርደሪያ ነበር ። ብዙ የዳበሩ ሀገሮችም ሐሳቡን በመርህ ደረጃ ደግፈውታል ። ይሁ ንና በዚያን ጊዜ የዳበሩ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገታቸው በደኅና ሁኔታ እየተካሄደ ቢሆ ንም (ለምሳሌ ከ1960—73 ድረስ 5 % እያ ደገ ነበር) የተጠየቀውን ዕርዳታ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም ። ሀገሮቹ ከጨመረው ምርታቸው ብቻ እንኳን 1/30 ኛውን ቢሰጡ በፒርሰን ሪፖርት የቀረበው የ0.7% ዕርዳታ ጥሪ ሊሟላ ይችል ነበር ። ነገር ግን በ1970 ዎቹ የዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ዕርዳታ ከጠቅላላ ብ ሔ ራ ዊ ምርታቸው ውስተ ከ0.35% አይበልጥም ነበር ።[50]

የፒርሰን ሪፖርት ከወጣ ከአሥር ዓመት በኋላ ሌላ የታወቁ ሰዎች ቡድን ብቅ አለ። ይህም በቀድሞው የምዕራብ ጀርመን ቻንስ ለር በዊሊ ብራንት የሚመራው ሲሆን ፣ ይህም ቡድን በተራው ሰሜን—ደቡብ የተ ሰኘ ሪፖርት አቀረበ ። ብራንት ሪ ፖ ር ታ ቸውን የሚጀምሩት በመግሪያ አሽቅድድም ላይ የሚባክነውን ሀብት በአኃዝ በማሳየት ከዚህ እጅግ አነስተኛው እንኳን ለዕድገት ቢውል የኋላቀር ሀገሮችን ችግር ም ን ኛ እንደሚያቃልል በመጥቀስ ነው ። የብራንት ሪፖርት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው

የመጀመሪያው ለታዳጊ ሀገሮች ዕድገት አመቺነት አላቸው የሚባሉ አዳዲስ ሐሳቦ ችን (Innovation) የሚያቀርብ ነው ። ከዚ ህም አንዱ የዓለም ዕድገት መዋጮ (World Development Fund) ማቋቋም ሲሆን ይህም የምዕራብ ፣ የምሥራቅ ፣ የደቡብ የነ ዳጅ አምራች ሀገሮችን (OPEC) የሚያቅፍ



Digitized by Google

ነው ። ዓላማው ለነዳጅ ፣ ለኢኮኖሚ ጥምረት (Integration) ለሰሜን ደቡብ ንግድ ወዘተ. አስፈላጊውን ብድርና ድጋፍ መስጠት ይሆናል ። ከዚህም ሌላ የቀረበው ሐሳብ የዕርዳታ ምንጭ መፍጠርን ይጠይቃል ። ለምሳሌም በዓለምአቀፍ ንግድ ፣ በመግሪያ ንግድ፣ በነዳጅ ፍጆታ ፣ በዓለምአቀፍ ትራንስፖርት ፣ እንዲሁም እንደባሕር ዓሣ ማጥመድ፣ ከባሕር ነዳጅ ማውጣት ፣ ከባሕር ወለል ማዕድን ማውጣት ፣ ህዋውን ለሳተላይት መጠቀም ፣ ወዘተ . ባሉ የጋራ ሀብቶችና ግልጋሎቶች ላይ ቀረጥ በመጣል የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው ። በሪፖርቱ ስሌት መሠረት ንግድ ብቻውን በወቅቱ በነበረበት መጠን ላይ እንኳን ወደ 1300 ቢሊዮን ዶላር ሊያስገኝ ይችላል ። [51]

የዕርዳታውን ምንጭ ለማስፋት ሌላው ሐሳብ ደግሞ እጅግ ድሀ ከሆኑት በስተቀር ሁሉም ሀገር ለዕርዳታ መዋጮ እንዲያደርጉ የሚጠይቀው ነው ። በሪፖርቱ መሠረት ዕርዳታ ሰጭ የዳበሩ ሀገሮች የዕርዳታቸውን መጠን ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርታቸው ከ0.35% ወደ1% ከፍ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል ። [52]

ሪፖርቱ የእርሻን ምርትን ስለመጨመርና የዓለምን ሕዝብ ረሃብ ስለመቀነስ አስፈላጊነት ያሳስባል ። የእርሻን ምርት ለመጨመር ይረዳሉ ተብለው የሚገመቱ በርካታ ዘዴዎችን ከጠቀሰ በኋላ ዓለምአቀፍ የእህል ክምችት እንዲፈጠር ይጠይቃል ።

በንግድ ረገድ ታዳጊ ሀገሮች ያለባቸውን ችግር የዛምቢያን ምሳሌ በመጥቀስ የዋጋ መረጋጋትን አስፈላጊነት ይገልጻል ። ዛምቢያ 94 % የውጭ ምንዛሪዋን የምታገኘው ከመዳብ ነው ። በሚያዝያ ወር 1974 አንድ ቶን መደብ በ3074 ዶላር ስትሸጥ ቆይታ ያውዓመት ሳያልቅ የመዳብ ዋጋበ መውደቁ አንድ ቶን በ1290 ዶላር ልትሸጥ ተገደደች። ይህም በኢኮኖሚዋ ላይ ከፍተኛ ቀውስ በማስከተሉ ብሔራዊ ገቢዋ በ15% ወደቀ ። [53] እንዲህ ያለውን ችግር ለመቋቋም 1ኛ የሸቀጦችን መነሻ ዋጋ (Floor price) መወሰን 2ኛ የዋጋ መዋዠቁን ለመቆጣጠር የሸቀጥ ክምችት (buffer stock) መፍጠር፣ 3ኛ ከጥሬ ዕቃ ይልቅ የተዘጋጁ (Processed) ምርቶችን ማቅረብ እንደሚረዳ ሪፖርቱ በሰፊው ያትታል ።

በተለይ ሦስተኛውን ነጥብ ሪፖርቱ ሲያብራራ ታዳጊ ሀገሮች የተዘጋጁ ምርቶችን ለማቅረብ ቢቻላቸው ይህ የተሻለ የሥራ ዕድል ለዜጎቻቸው እንዲፈጥሩ ፣ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ ወዘተ. ያስችላቸዋል ። አንከታድ ሸቀጦችን በናሙናነት በመውሰድ በ1975 ባካሄደው ጥናት እነዚህን ሸቀጦች የሚያመርቱ ሀገሮች ምርታቸውን በጥሬ ከማቅረብ ይልቅ በተዘጋጀው መልክ ሊያቀርቡ ቢችሉ ወደ 72 ቢሊዮን ተጨማሪ ገቢ እንደሚያገኙ፣ በሌላ አገላለጽ ሸቀጦች በጥሬነታቸው ከሚሸጡ ይልቅ ተዘጋጅተው ቢሸጡ አንድ ተኩል እጅ ተጨማሪ ገቢ እንደሚያስገኙ ይጠቁማል ። [54]

ከዚያም በተጨማሪ ኋላቀር ሀገሮች በሽያጭ ፣ በትራንስፖርትና በማከፋፈል ተግባር ተሳትፎ ማድረግ ቢችሉ ይህ ደግሞ የበለጠ ጥቅም ያስገኝላቸዋል ። በዚህ ረገድ ዋነኛው ችግር በታሪፍና ታሪፍ ባልሆኑ ዕንቅፋቶች የሚፈጠረው ነው ። ለምሳሌ ጥሬ የዘምባባ ዘይት (Crude palm oil) ወደ ምዕራብ አውሮፓ (EEC) ሲገባ 4% ታሪፍ ይጣልበታል። ይኸው ምርት በከፊል ዝግጁ ቢሆን ታሪፉ ወደ 12% ከፍ ይላል ። [55] ሌላው ችግር የሸቀጦች የማጓጓዣ ዋጋ ጉዳይ ነው ። የማጓጓዣ ዋጋም እንዲሁ ከጥሬ ዕቃዎች ይልቅ ዝግጁ ለሆኑ ምርቶች የተወደደ ይሆናል ። እንዲያውም አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የማጓጓዣ ዋጋ በሁለትና ሦስት እጅ ይጨምራል ። [56] በእነዚህ ሁሉ ችግሮች ምክንያት ታዳጊ ሀገሮች ለሚያመርቱት ምርት ሸማቹ ከሚከፍለው የሚያገኙት ከ25% ያነሰ ነው ። [57] ይህም ማለት ቡና አውሮፓ ውስጥ 1 ብር ቢሸጥ



Digitized by Google

ከዚህ ውስጥ ለአምራቹ ሀገር የሚደርሰው 25 ሳንቲም ይሆናል ማለት ነው ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በዓለም ገበያ ታዳጊ ሀገሮች በምርታቸው ተገቢውን ዋጋ ለማግኘት ያለባቸውን ችግር ነው ።

ከላይ ከጠቀስናቸው በተጨማሪ ለአንዳንድ ምርቶች ማካካሻ ዘዴ (compensatory financing scheme) እንዲኖር ሪፖርቱ ይጠይቃል ። ይህም ማለት አንዳንድ ምርቶችን ለረዥም ጊዜ ማከማቸት ስለማይቻል (ለምሳሌ ሙዝ) በጊዜው በተገኘው ዋጋ መሸጥ ግዴታ ይሆናል ። ከዚህም ሌላ በድርቅ ፣ በአዝርዕት በሽታ ወዘተ. ምርቱ በድንገት ሊቀንስ ይችላል ። ይህ ሲሆን የአምራቾች ገቢ ክፉኛ ይወድቃል ። እንዲህ ባለው ሁኔታ የሚጎዱ ሀገሮችን መደጎም ያስፈልጋል ።

ሪፖርቱ ንግድ ለሁለቱም ወገኖች (ለሰሜንም ለደቡብም) የጋራ ጥቅም እንዳለው ለሰሜኑ ክፍል ያሳስባል ። ከደቡብ ጋር ያለው ንግድ በሰሜኑ ክፍል ከፍተኛ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር በአኃዝ የተደገፈ መረጃ በማቅረብ ይገልጻል ። ለምሳሌ የነዳጅ ዋጋ ሲጨምርና የሰሜኑ ኢኮኖሚ መዳከም (Recession) ሲባባስ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ታዳጊ ሀገሮች ከነዳጅ አምራች ሀገሮች የባንክ ክምችት በመበደር ከሰሜኑ የገዙት ሸቀጥ ከ1973-7 ድረስ በየዓመቱ ከሚሊዮን ለሚበልጡ ሰዎች የሥራ ዕድል ከፍቷል ።[58] ከዚህም ሌላ ዋጋው ዝቅተኛ በመሆኑ ከደቡብ ሸቀጥ መግዛት በሰሜኑ ክፍል የዋጋ መናርን ለመቆጣጠር ይረዳል። በተጨማሪም በታሪፍና በመሳሰሉት ዕንቅፋቶች ደቡብ ወደሰሜን ሸቀጥ መላክ ካልቻለ የሰሜኑን ዕቃ ሊገዛም ሆነ ያለበትን ዕዳ ሊከፍል እንደማይችል ያሳስባል ። በ1977 ጃፓን ፣ አሜሪካ ፣ ምዕራብ አውሮፓ (EEC) 1/3ኛ የሚሆኑ ሸቀጦችን ወደውጭ የላኩት ወደደቡብ እንደሆነና ጃፓን ብቻዋን 46% እንደላከች በመጠቀም የደቡብ ገቢ ማደግ ለሰሜኑም ጥቅም እንደሆነ ይገልጻል ።[59]

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓትን በሚመለከት የልውውጥ ምጣኔ መዋዠቅ ታዳጊ ሀገሮችን እንደሚጎዳ በመጥቀስ በዚህ ረገድ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንዲተባበር ያሳስባል ። ከዚህም በተጨማሪ በገንዘብ መዋዠቅ ምክንያት የሚደርስን ጉዳት ለመደጎም የሚያስችል አዲስ የገንዘብ ክምችት (SDR) እንዲፈጠርና ክፍፍሉም ለታዳጊ ሀገሮች እንዲያዳላ ይጠይቃል ። እንዲሁም የብሪቶን ውድስ ስምምነት የጊዜውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ስለሚያንፀባርቅ አሁን ከሚገኘው ከተለወጠው ሁኔታ ጋር በሚገናዘብ መልክ ይለወጥ ፣ ታዳጊ ሀገሮች በዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓት ውስጥ ተሰሚነት ያለው ሚና ይኑራቸው ፣ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት በታዳጊ ሀገሮች ላይ ከመጠን ያለፈ ቁጥጥር ከማድረግ ይቆጠብ የሚሉ ማሳሰቢያዎች ይገኛሉ ።

ሪፖርቱ በሌሎች በርካታ መስኮችም መደረግ ስለሚኖርባቸው ለውጦች ያትታል። በመጨረሻ ላይም የዓለም መሪዎች ከደቡብም ከሰሜንም ተሰብስበው በእነዚህ ችግሮች ላይ እንዲወያዩና ለሰው ልጅ ህልውና መጠበቅ ፣ ለኑሮው መሻሻልና የተሻለ ፍትሕ ለሚሰጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት እንዲወያዩ ይጠይቃል ።

የመጀመሪያው የርዕሰ መንግሥታት ስብሰባ በጥቅምት ወር 1981 በካንኩን (ሜክሲኮ) ተካሄደ ። በስብሰባው ላይ የ22 ሀገሮች መንግሥታት መሪዎች ተገኝተዋል። በዚህም ስብሰባ ላይ በተባበሩት መንግሥታት የተላለፈውን ጥሪ ሁሉም ለመደገፍ ተስማሙ ። ይሁን እንጂ በተግባር ሲታይ ይህ ምንም ማለት አልነበረም ። ዩናይትድ ስቴትስ የካንኩን ስብሰባ ሲቃረብ ከታዳጊ ሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት ከራሷ ጥቅም ጋር በሚስማማ ሁኔታ ሊመራ የሚገባበትን ፖሊሲ አበክራ በመግለጽ የፖለቲካውን አየር መመረዝ ጀመረች ። አሁን ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓት ተጠብቆ መቆየቱን የምትፈልግ መሆኑን በተለያየ መልክ ማሳሰብ ቀጠለች ። ከታዳጊ ሀገሮች ጋር



Digitized by Google

ባላት ግንኙነት ለካፒታሊስት ሥርዓት ትድጊያ እንደምትሰጥ፣ ዕርዳታ የሚያገኙት ከሷ ጋር ወዳጅነታቸው የጠበቀ ሀገሮች ብቻ እንደሆኑ፣ ለእሷ የስትራቴጂና የኢኮኖሚ ጥቅም አስፈላጊ የሆኑ ክልሎችን እንደምትጠብቅ ወዘተ. በተለያዩ መድረኮች ማሰማት ያዘች። ከዚህም አልፋ ታዳጊ ሀገሮች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች ውስጥ ኢምፔሪያሊዝምን በማውገዝ በሚያሰሙት ድምፅ ምክንያት የምትሰጠውን ዕርዳታ እንደምታቆም ታስፈራራ ጀመር። በቅርቡም ለምሳሌ ከዩኔስኮ እንደወጣችና በሌሎችም ላይ ማስፈራራቱን እንደቀጠለች ይታወቃል። የዳበሩ ሀገሮች ከጠቅላላ ብሔራዊ ገቢያቸው መጀመሪያ 0.7% ከዚያም 1% ዕርዳታ ይሰጡ የሚለውን ጥሪ በመርህ ደረጃ እንኳን ካልተቀበሉት ጥቂት ሀገሮች አንዷ አሜሪካ ናት። አንዳንድ የስካንድኔቪያን ሀገሮች ከ0.7% አልፈው ዕርዳታ ሲያደርጉ አሜሪካ የሰጠችው ዕርዳታ በ1960 0.5.% አካባቢ ሲሆን በ1970ዎቹ ጭራሽ ዝቅ ብሎ 0.27% ሊሆን በቅቷል። በተለይ አሜሪካ ታዳጊ ሀገሮች በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ በዓለምአቀፍ የልማት ባንክና በአጠቃላይ የንግድና ታሪፍ ስምምነት ውስጥ ምንም ዓይነት ተሰሚነት እንዲኖራቸው አትፈልግም።

ለአዲሱ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ አሜሪካ አደናቃፊ ሐሳቦችን በማቅረብ የታወቀች ናት። በ1960 የመጀመሪያው የአንክታድ (UNCTAD) ስብሰባ አጠቃላይ አመቺ የንግድ ቀጣና ሥርዓት መቋቋሙን አሜሪካ ተቃውማለች። የሰጠችውም ምክንያት ነፃ ንግድን ያናጋል የሚል ነበር። በ1972 በተደረገውም ስብሰባ ታዳጊ ሀገሮች የሚያመርቷቸው ሸቀጦች በለሙ ሀገሮች እንዲሸጡ አመች ሁኔታ መፈጠርንም አልተቀበለችውም። ታዳጊ ሀገሮች በ1974 በስድስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ስብሰባ ላይ አዲሱ ሥርዓት ስለሚቋቋምበት ሁኔታ አርቅቀው ያቀረቡትን ሐሳብም አልደገፈችውም። በ1976 ፓሪስ ውስጥ በተደረገው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ስብሰባ ላይ ታዳጊ ሀገሮች ስለብድር ለመወያየት ፈልገው አሜሪካ የተለመደ የአደናቃፊነት ድምጿን አሰምታለች። በ1979 በየዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ስብሰባም ላይ ታዳጊ ሀገሮች ያቀረቡትን የገንዘብ ዕርዳታ መጠን የመጨመር፣ እላይ የተጠቀሰው በገንዘብ መዋዠቅ ምክንያት የደረሰን ጉዳት ለመቋቋም የሚሰጠው የመደጎሚያ ገንዘብ እንደየ ሀገሮች ችግር እየታየ የማደላደል ጥያቄም ተመሳሳይ ዕድል ገጥሞታል። በ1980 የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ፣ የ77 ቡድን የዓለም የገንዘብ ልውውጥ መጫኔ ሥርዓት እንዲኖረው፣ በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በዓለምአቀፍ የልማት ባንክ ውስጥ በውሳኔ አሰጣጥ ታዳጊ ሀገሮች ያላቸው ተሳትፎ ሚዛናዊነት እንዲያገኝ፣ እነዚህ ሁለቱ ድርጅቶች የተቋቋሙበት የስምምነት ውሎች እንዲሻሻሉ በማለት ያቀረቡት ሐሳብ ፍሬ አልባ ሆነ።

ባጠቃላይ እስካሁን እንዳየነው ለአዲሱ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት መቋቋም የሚደረገው ጥረት በተጨባጭ ምንም ያህል እንዳልገፋ፣ በኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በተለይም በአሜሪካ ዘንድ ድጋፍ እንደሌለው አይተናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የታዳጊ ሀገሮች ችግር ግን እየተባባሰ መጥቷል። ይህም ታዳጊ ሀገሮች መሠረታዊ ችግራቸውን ለማስወገድ በመሠረቱ በውጭ ዕርዳታ ላይ መተማመን እንደሌለባቸው እያስገነዘባቸው ነው።

በአሁኑ ወቅት ከሁሉም ይልቅ የአፍሪካ ሀገሮች ያጋጠማቸው ችግር የባሰ መሆኑ ግልጽ ነው። አስቀድመን እንዳየነው ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ኢኮኖሚያቸው እየተዳከመ፣ የውጭ ዕዳ እየተከመረባቸው፣ ከዚያም አልፎ አብዛኛዎቹ ዜጎቻቸው በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ነው። ስለዚህ ጥያቄው ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አሳሳቢና የሰውን ልጅ ህልውና የሚመለከት ሆኖ

Digitized by Google

ተርፏል ። የአፍሪካ መሪዎችም ይህን በመገንዘብ ፣ በብሔራዊና በጋራ ራስን መቻል መርህ ላይ የተደገፈ የዕድገት አቅጣጫ እየቀየሱ ነው ። ከዚህም ሌላ በደቡብና በሰሜን መካከል በሚባለው ግንኙነት ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ታዳጊ ሀገሮች እርስ በራሳቸው በመካከላቸው (ደቡብ—ደቡብ) ያለውን ግንኙነት ማጠናከር አስፈላጊ ነው የሚለው ሐሳብ እየተጠናከረ ነው ። በዚህ ጽሑፍ ሁለተኛ ክፍል መጀመሪያ በደቡብ—ደቡብ ፣ ቀጥሎም በምሥራቅ—ደቡብ መካከል ያለውን ግንኙነት ካየን በኋላ በአፍሪካ ሀገሮች መካከል ስላለውና መኖርም ስላለበት ግንኙነት በሌጎስ መርሐ ግብር (Lagos plan of Action) ላይ በመመሥረት እንመለከታለን ።

# የግርጌ ማስታወሻ


1. Jocelyn Murry ed., Cultural Atlas of Africa (Oxford: Phaidon Press Ltd., 1981), p. 16.
2. Calculated from UN Statistical Year Book, 1979/80 and UN Year Book of World Energy Statistics, 1980 and from the Legos Plan of Action, p. 7.
3. The World Bank, Toward Sustained Development in Sub-Saharan Africa, A Joint Programme of Action, Washington D. C., 1984, p. 1. See also ECA, Survey of Economic and Social conditions in Africa 1983-84, Addis Ababa, 1984. The World Bank, World Development Report, 1983, 1984, 1085. U. N. Economic and Social Survey of Africa 1958-1983.
4. The World Bank, Towards Sustained Development, p. 77.
5. ECA, Survey, p. 44.
6. Ibid, p. 18.
7. ECA Survey p. 127.
8. Ibid, p. 128.
9. The World Bank, Toward Sustained Development, p. 13.
10. Professor Adebaye Adedeji, "A Preliminary Assessment of the Economic Performance of Africa in 1982 and Prospects for 1983: End of year statement, ECA, Addis Ababa, 29 December 1982, p. 1.
11. The World Bank, Towards Sustained Development, p. 9.
12. Walter Rhodney, *How Europe Underdeveloped Africa* (Dares Salam: Tanzania Publishing House, 1976), p. 46.
13. Ibid, p. 48.
14. " p. 50.
15. " p. 51.
16. " p. 81.
17. Karl Marx, Capital, A Critique of political Economy, Vol. 2, (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 705.
18. John M. Keynes, Quoted by Keith Griffin, "Underdevelopment in History in the Political Economy of Charles K. Wilber (Ed.) (New York: Random House, 1973), p. 72.
19. Ernest Mandell, Marxist Economic Theory, Vol. 2 (New York: Monthly Review Press, 1968), p. 443-444.
20. Ibid.
21. Ibid, p. 446.
22. Ibid, p. 447.
23. Leo Huberman, Man's Worldly Goods (New York: Monthly Review Press, 1963), pp. 166-67.
24. Keith Griffin, p. 73.
25. Ibid, p. 74.
26. Vera Anstey, Quoted by Paul Baran, The Political Economy of Growth (New York: Monthly Review Press, 1957), p. 293.
27. Cadman Ata Mills, African Development, Vol. 1 No. 1 1976, p. 51.
28. Keith Griffin, p. 76.
29. Richard Pankhurst, Economic History of Ethiopia 1800-1935 (Addis Ababa: Artistic Printers Ltd., 1968), p. 272.




Digitized by Google

30. E. Mandel, p. 473.

31. K. Marx, p.

32. W. Rhodney, p 262.

33. Ibid, p. 264.

34. P. Baran, p.

35. Valentin Schetinin et al, A New International Economic Order, Its advocates and Opponents (Balkan State Printing House, 1983), p. 27.

36. Mohamed Bedjaoui, Towards a New International Economic Order (New York: Halmes and Meier Publishers, 1979), p. 35.

37. Susane Greorge, How the Other Half Dies. The Real Reasons for World Hunger (London: Penguin Books, 1976), p. 61.

38. Mohamed Bedjaui, p. 45.

39. Ibid, p. 46.

40. Ibid, p. 33.

41. Ibid.

42. Ibid, p. 27.

43. Willy Brandt, North-South. A Programme for Survival, Report of the Independent Commission on International Development Issues, (The M & T Press, Cambridge Massachussets, 1980), p. 14.

44. U.N. General Assembly Resolution, No. 3201 (S-V1), 29th Plenary Meeting, New York, 1974.

45. W. Brandt, p. 202.

46. Ibid, p. 203.

47. V. Schetinin, p. 13.

48. Ibid, p. 14.

49. Jyoti Shankar Singh, Towards a Fair *Redistribution of World Resources* (New York: Praeger Publishers. 1977), p. 52.

50. W. Brandt, p. 224.

51. Ibid, p. 245.

52. " p. 242.

53. " p. 145.

54. " p. 142.

55. Ibid.

56. Ibid, p. 143.

57. Ibid, p. 144.

58. Ibid, p. 67.

59. Ibid, p. 70.

Digitized by Google

# መንደር ምሥረታ
# የሦስት ክፍላተ ሀገር ልምድ

በላይነህ አሰጉ

የመንደር ምሥረታ በሀገራችን የዕድገት ትልም ውስጥ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው ። በዚሁ መሠረትም ቅድሚያ በተሰጣቸው የሀገራችን ክፍሎች እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ። ለመሆኑ እንቅስቃሴው በተጨባጭ ምን ይመስላል ? ይህ ጽሑፍ በሦስት ክፍላተ ሀገር ማለትም በሐረርጌ፣ በአርሲና በባሌ ውስጥ በዐሥር አውራጃዎች፣ በሃያ ሁለት ወረዳዎች፣ በሃምሳ መንደሮች ጉብኝት በማድረግ ፣ ነዋሪዎችንና የሥራ ኃላፊዎችን በማነጋገር ለጥያቄው ተገቢ መልስ ለመስጠት ይሞክራል ።

በሦስቱም ክፍላተ ሀገር ካደረግነው ጉብኝትና ውይይት ለመረዳት እንደተቻለው የመንደር ምሥረታው አስፈላጊነት በአካባቢው ከሚታየው ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግር የመነጨ ነው ። እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር በነዚህም አካባቢዎች የነበረው ኑሮ የተበታተነና ኋላቀር ነው ። በነበረው የመሬት ሥሪት ችግር በአንዳንድ ቦታዎች ገበሬው እጅግ ተጣቦ ሲኖር በሌሎች አካባቢዎች ሰው ያልሰፈረባቸው ሰፋፊ መሬቶች አሉ። የአየሩ ንብረት የተለያየ በመሆኑ ሕዝቡ የሚኖርበት የግብርና ዓይነትም የዚያኑ ያህል የተለያየ ነው ። ከባሌ በስተቀር ደኑ በብዛት በመመንጠሩ የአፈር መሸርሸርና የአየር ለውጥ በብዛት ይታይባቸዋል። በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ ሦስት ክፍላተ ሀገር ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ጋር የሚመሳሰሉ ቢሆንም የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕርይም አላቸው ። ከሁሉም በላይ በነዚህ ክፍላተ ሀገር በኩል ኢትዮጵያን የምታዋስነው ሶማሊያ ካላት የመስፋፋት ፍላጎትና ከዚሁ ዓላማ በመነሣት በሰርጎ ገቦች አማካይነትም ሆነ በቀጥታ ወረራ ለረጅም ጊዜ ጥቃት ስታደርስ ቆይታለች። ይህም ያስከተለው ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠንቅ እነዚህን አካባቢዎች ከሌሎች ለየት ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ ነው ። በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች የሚካሄደው የመንደር ምሥረታ ፣ ሀገር አቀፍ ከሆኑ ምክንያቶችና ከአካባቢዎቹ ልዩ ባሕርይ የመነጨ ነው ።

## ለመንደር ምሥረታ ያነሣሡ ምክንያቶች

ግብርና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት ነው። ምክንያቱም በኢትዮጵያ አብዛኛው ሠራተኛ የተሰማራበት ፣ የሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገኝበትና ለወደፊቱም ለብዙ ጊዜ የምንተማመንበት ክፍለ ኢኮኖሚ በመሆን ነው። ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የግብርና ኢኮኖሚያችን ተገቢው ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል ። ሀገሪቱ ያላት የመሬት ስፋት በውል ተጠንቶ ለልዩ ልዩ ሰብሎች ማልሚያ ፣ ለመኖሪያ ፣ ለግጦሽና ለደን - - - ተስማሚ የሆነው ክፍል ተለ



Digitized by Google

ሉሉ አይገኝም ። በነበረው የመሬት ሥሪትና በክፍለ ኢኮኖሚው ኋላቀርነት የተነሣ የገበሬው አሰፋፈር ለዘመናዊ እርሻ አመች አይደለም ። እያንዳንዱ ገበሬ በተወለደበትና አያት ቅድመ አያቱ በኖሩበት አካባቢ ከመኖር በስተቀር አካባቢ መርጦ ተስማሚ ቦታ ላይ መስፈር አንዳንዴ ብቻ የሚከናወን በመሆኑ በአብዛኛው ዛሬ ገበሬው ያለበት አካባቢ ጥንት አባቶቹ የኖሩበት ነው ። በዚህ የተነሣ አንዳንዱ አካባቢ ተደጋግሞ እየታረሰ አፈሩ አላግባብ ሲባክን ፣ ደኑ ሲጨፈጨፍ ፣ ሌላው አካባቢ ገና ድንግል ነው ። የገበሬው አሰፋፈር የተበታተነ በመሆኑ እያንዳንዱ ገበሬ መሬቱን እንደፈለገው ለእርሻ ፣ ለግጦሽ ፣ ለቤት መሥሪያ ስለሚያውለው ፣ ያለንን መሬት በሙሉ ከልሉ መጠቀም ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ።

በዚህ ላይ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገቱ ኋላቀር በመሆኑ ምርታማነቱ ዝቅተኛ ነው ። ገበሬው የሚያመርተው ከራሱ ፍጆታ እምብዛም ያለፈ አይደለም ። ሁኔታውን ለመለወጥ ገበሬውን ስለዘመናዊ አስተራረስ ማስተማር ፣ ልዩ ልዩ ምርጥ ዘሮችን እንዲጠቀምና አካባቢውን እንዲንከባከብ ተገቢ አገልግሎት ማቅረብ ይገባል ። ዛሬ አብዮቱ በፈጠረው አመች ሁኔታ የግብርና ሚኒስቴር የልማት መምሪያ እስከ አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ድረስ ደርሷል ። ይሁን እንጂ እነዚህ የግብርና ልማት ሠራተኞች ባላቸው ዓቅም የተቻላቸውን አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ገበሬው አኗኗሩ ሰብሰብ ብሎ ሲገኝ ነው ። አለበለዚያ በተበታተነ ገበሬ መሐል ተፈላጊውን የግብርና ዕውቀትና አገልግሎት ለማዳረስ እጅግ አስቸጋሪ ነው ። ገበሬው በመንደር በተሰባሰበባቸው አካባቢዎች ግን የግብርና ሚ/ቤት በአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ደረጃም ቢሆን በእያንዳንዱ መንደር በመዘዋወር ትምህርት በመስጠት ፣ የልዩ ልዩ አገልግሎት ጣቢያ በማቋቋም የሚደረገው ጥረት ገበሬውንና የግብርና ባለሙያዎችን ይበልጥ አገናኝቷል ። በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት በሐረርጌ ፣ በአርሲና በባሌ በእያንዳንዱ የገበሬ መንደር አለበለዚያ በአገልግሎት ደረጃ ቢያንስ ቢያንስ ችግኝ ጣቢያዎች አሉ ። ገበሬውም በዚህ ሥራ በቀጥታ ይሳተፋል ፣ ከልማት ሠራተኞችም ጋር ይወያያል ። ይህ ከመሰባሰብ የሚገኝ ጥቅም ነው ።

በሀገራችን ጐልቶ ለሚታየው የምግብ እህል ምርት ዝቅተኛነት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ የገበሬው የሥራ ባህል አለመዳበርና የምርታማነት ዝቅተኛነት ነው ። ገበሬው በተወሰነ ሰዓት ተነሥቶ ወደ እርሻው ሄዶ የተወሰነ ሰዓት ሠርቶ የመመለስ ባህል ገና አላዳበረም ። ሲያሰኘው በሌሊት ተነሥቶ እስኪደክመው ይሠራል ፤ አለበለዚያም እርፍዶ ይነሣል ። በተለይ ለአዝርዕት ምርት ከሚውለው የእርሻ መሬት በአማካይ ከ95 በመቶ በላይ ፣ እንዲሁም ከሚገኘው ምርት ከ92 በመቶ በላይ ድርሻ ያለው የግል ገበሬ እርሻ * በሆነባት ሀገራችን የሚታየው የሥራ ባህል አለመዳበር ጉዳቱ ከፍተኛ ነው ። የገበሬው በመንደር መሰባሰብ ለሥራ ባህል መዳበር ጥሩ አስተዋጽኦ አለው ። ይህንን በማስመልከት በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ፣ በሐረር ዙሪያ አውራጃ ፣ ከኮምቦልቻ ወረዳ በከምቦልቻ ከተማ 8 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ያለችው የወረ መሐመድ መንደር ነዋሪና የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር ሊቀ መንበር የሆኑት ጓድ አሕመድ ኡስማን እንዲህ ብለዋል ፣ « ገበሬው ተበታትኖ ይኖር በነበረ ጊዜ እያንዳንዱ ገበሬ ለሥራ የሚወጣው በፈለገው ሰዓት ነበር ። በዚህ አካ

---

*የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ (000 ረቂቅ) ጥራዝ አንድ፣ ብሔራዊ አብዮታዊ ምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ አዲስ አበባ ፤ መጋቢት 1975 ፤ ገጽ 89

Digitized by Google

ባቢ ሜት በብዛት ስለሚበትልና ገበሬ
ውም ሜት የመታም ልምድ ስላለው አብ
ዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፈው ሜት በመታም
ነበር ። ዛሬ በመንደር ከተሰባሰብን በኋላ
ግን አንደኛ ለሥራ እንዲያመቻቸው በአ
ንድ አካባቢ የሚያርሱ ገበሬዎች በወ
ንፈል የእያንዳንዱን ገበሬ ማሳ ስለ
ሚያርሱ አንዱ ከመካከላቸው ያለበቂ
ምክንያት ሊቀር አይችልም ። ከቀረም
ነገ የእሱን የሚያርስለት ስለማይኖር ለች
ግር ይጋለጣል ። በዚህ ላይ ቤተሰቡም
ቢሆን ዛሬ የእያንዳንዱን ሰው ሁኔታ በቅ
ርብ ስለሚያይ ሌሎቹ ለሥራ ሲሄዱ ያለ
ምክንያት መንደር ውስጥ ሲዘዋወር
ወይም በቤቱ የዋለ ወንድ ምን ሆንክ ?
ታመምክ እንዴ ? ሥራ ለምን አልሄድ
ክም ? እየተባለ ስለሚጠየቅ ሐፍረት ይሆ
ንበታልና ሰፈር አይውልም ። » ነገሩ እው
ነት ነው ። ጉረቤቶቹ እርሻ እየዋሉ ሲያ
ውደለድል የዋለ ወንድ ባለቤቱ ነገ የሌ
ሎቹ ቤት ተሟልቶ የኔ ቤት ባዶ እንዲ
ሆን ስለማትፈልግ ወደሥራ እንዲሠማራ
ትገፋፋዋለች ። ለሱም ቢሆን ሐፍረት
ነው የሚሆንበት ።

በአንድ ላይ ተሰባስቦ መኖርና መሥ
ራት የሥራን ባህል የሚያዳብር ስለመሆኑ
በአርሲ ክፍለ ሀገር በጭላሎ አውራጃ ፣
በገደብ አሳሳ ወረዳ የሚገኘው የታቀ ገበሬ
መንደርም ሌላው ምሳሌ ነው ። የታቀ
ገበሬ መንደር ታቀ 01 እና ታቀ 02 ተብሎ
በሁለት ገበሬ ማኅበር ይከፈላል ። በመን
ደር የተሰባሰበው በጥር ወር 1972 ሲሆን
በመጀመሪያ የተሠሩት ጊዜያዊ ግር ቤቶች
በ1973 በመንግሥት ድጋፍ በዋቢ ፕሮጄ
ክት አማካይነት ወደ ቆርቆሮ እንዲለወጡ
ተደረገ ። በዚህ መንደር የተሰባሰበው ኗሪ
በአብዛኛው ከብት አርቢ ስለነበር የእርሻ
ባህሉ እጅግ ዝቅተኛ ነበር ። በዚህ ላይ
በወቅቱ የነበረው የፀረ አብዮት ቅስቀሳ
ተጨምርበት በመንደር በተሰባሰቡበት
ጊዜ እንኳንስ ራሳቸው ለማረስና በመንግ
ሥት የታረሰላቸውን ስንዴና ገብስ ለማ



በዕቅድ የሠተራ መንደር ለልማት



Digitized by Google

ጫድ፣ ለቤታቸው መሥሪያ ከልዩ ልዩ ቦታ የመጣውን ዕቃ ከመኪና ለማውረድና ቤቱ ወደሚሠራበት አካባቢ ለማድረስ እንኳን በስንት ልመና ነበር። ዛሬ የታጥ መንደር ኗሪ የሚገኝበት ደረጃ የላቀ ነው። ገበሬው በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅቷል። በመንደሩ መሀል ባለው ቦታ ለልዩ ልዩ ማኅበራዊ ግልጋሎት ጽ/ቤቶች ተሠርተዋል። አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እስ 1 የተቀበሌው አኢወማና አኢሴማ የኪነት ቡድን በሚገባ ተደራጅቷል። የኪነት ቡድኑ የራሱን አባላት ከማዝናናት አልፎ በአካባቢው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በምርት መስክም ከፍተኛ መሻሻል አድርገዋል። ዛሬ የታጥ መንደር በክፍለ ሀገሩ ለሚገኘው የቢራ ብቅል ፋብሪካ መደበኛ እህል አቅራቢ በመሆን ይጠቀማል። ባለፈው ዓመት በሀገራችን በብዙ አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ የአካባቢው ገበሬም ሲቸገር የታጥ ገበሬዎች በነፍስ ወከፍ 25 ኪሎ እህል ርዳታ ከመስጠት ባሻገር በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበሬ እህል በመሸጥ ከፍተኛ ርዳታ አድርገዋል። በአሁኑ ወቅት የሁለቱም ገበሬ ማኅበራት መጋዘኖች ለዘርና ለመጠባበቂያ በተቀመጠ ስንዴና ገብስ ተሞልተዋል። የሚነገረው ስለመጋዘን መጥበብ ነው። ከአምስት ዓመት በፊት የራሳቸውን መንደር ለመሥራት ይሰንፉ የነበሩት ገበሬዎች፣ ዛሬ የአካባቢውን ገበሬ መንደር በመሥራት ከማገዝ ባሻገር በአዲሶቹ መንደሮች ለሚሠሩት ቤቶች የመሥሪያ ቁሳቁስ አስተዋጽኦ በማድረግ ተሳትፈዋል። ዛሬ የታጥ ገበሬዎች የዱር ስንፍናቸውን ልጆቻቸው በትያትር መልክ ሲያቀርቡት በትዝብት ከመመልከት በቀር ሁኔታውን ለማንጓት እንኳን ያፍራሉ። የእያንዳንዱ ገበሬ ገቢ የሚለካው በሥራው መጠን ስለሆነ ለሥራ ጉትጐታ እያስፈለገም። የእያንዳንዱ ጥረት ምርት ለማሳደግ ነው።

በገጠሩ መስፋፋት ያለበትና የእርሻ ምርታችንን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅና የገበሬውንም ሙሉ ጊዜ በሥራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው የመስኖ እርሻ ነው። «ኢትዮጵያ በ14 ከፍተኛና መለስተኛ ተፋሰሶች የተከፈለች ሀገር ናት። በእነዚህም ተፋሰሶች የሚያልፈው የውሀ መጠን በዓመት 5.1 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 75 በመቶ ወደ ሱዳን፣ 15 በመቶ ወደ ኬንያ፣ 6 በመቶ ወደ ሶማሊያ፣ 1 በመቶ ወደ ቀይ ባሕር የሚፈስ ነው። በዚህ መሠረት ሀገሪቱ ውስጥ የሚቀረው ውሀ ከ 3 በመቶ በታች ነው።»* ይህ ሁሉ የውሀ ሀብት እየባከነ ሀገራችን በዝናብ ጥገኝነት ተወስና ኖራለች። ገበሬው ተበታትኖ ባለበት ሁኔታ እያንዳንዱ ውሀ ገድቦ፣ ቦይ ቆፍሮ በመስኖ ለመጠቀም ዓቅም አይኖረውም። የገበሬው አሰፋፈር አመቺ ባለመሆኑ መንግሥትም በዚህ ዘኩል ርዳታ ለማድረግ ቢሞክር ወጭው እጅግ ከባድ ነው። ዛሬ ግን ገበሬው በመንደር በተሰበሰበባቸው አካባቢዎች የመስና እርሻ በሚያበረታታ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው።

ገበሬው በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ በሚገኝበት ሁኔታ ገንዘቡንና ጉልበቱን ለማስተባበር አመቺ ሁኔታ አለ። በባሌ ክፍለ ሀገር፣ በመንደዮ አውራጃ፣ በጐሮ ወረዳ ከሮቤ ወደ ጊኒር 77 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መልካ ቡታ የምትባል መንደር ትገኛለች። አካባቢው በሶማሌ ጦር ተመቶ ስለነበር መንደሩ በአጠቃላይ ወድሟል። የሶማሌ ጦር ድል ከተመታ በኋላ ገበሬው ኑሮውን እንደገና ሲመሠርት በመንደር እንዲሰበሰብ ተደረገ። አካባቢው በጣም ለም

---

* የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የዓሥር ዓመት መሪ ዕቅድ፣ 1977—86 ፣ አ.አ፣ መስከረም 1977 ገጽ፣ 311፣

Digitized by Google

ቢሆንም የዝናብ እጥረት ስለሚያጋጥመው እህሉ አንዳንዴ ይጠፋል ። የተተከለው ሙዝና ብርቱካን ጥሩ ፍሬ የሚሰጥ ሲሆን ዝናብ በሌለ ጊዜ ግን ለጉዳት ይጋለጣል።

በጣም ጥቂት ገበሬዎች በመንደሩ አጠገብ ከሚያልፈው ወንዝ መጠነኛ ውሃ በቦይ በመጠቀም አትክልት ማልማት ጀመሩ ። ከዚህ የተገኘው ውጤት የሚያበረታታ በመሆኑ ኮሕዝባዊት ኮሪያ በመጡ ባለሙያዎች ዲዛይን እንዲወጣና በግብርና የገጠር መሠረተ ልማት የአነስተኛ ግድብ መሥሪያ ዕቃዎች እንዲቀርቡ በመደረጉ ገበሬው በልዩ ልዩ የጉልበት ሥራ በመሳተፍ የመስኖውን ቦይ በመሥራት ላይ ይገኛል ። ይህ ሥራ ሲጠናቀቅ በአካባቢው ያሉ የግል ገበሬዎችና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በመጀመሪያ ደረጃ 50 ሄክታር ፣ ቀጥሎ በሚሠራው ማጠራቀሚያ አማካይነት 50 ሄክታር ፣ በድምሩ በ100 ሄክታር መሬት ላይ ልዩ ልዩ አትክልቶችን ለማልማት እንደሚቻል ይገመታል ። ይህ ጥረት በመካሄድ ላይ እንዳለ የታየ በመሆኑ ተጠቀሰ እንጂ አንድ የገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር እንዳሉት ዛሬ አምራች ባለበት ሁሉ መስና አለ ወደሚባልበት ደረጃ እያመራን ነው ። በያለበት በመስና የመጠቀሙ አዝማሚያ የወደፊቱን ብሩኅ ተስፋ ያመለክታል ።

«ኢትዮጵያ በመስና ሊለማ የሚችል ከ2 እስከ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሲኖራት በልማት ላይ የዋለው ግን 100ሺህ ሄክታር ያህል ወይም ከጠቅላላው 3 በመቶ ብቻ ነው። »* የገበሬው በመንደር መሰባሰብ ለልማት ሥራ የሚኖረውን አመቺነት ከዚህ ሁሉ አኳያ መመልከት ያሻል ። ገበሬው በየግሉ ስለመስና ሊያስብ አይችልም ። ቢያስብም ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም ። በተበታተነ ገበሬ መሀል የሚያልፍ ውሃም መሬትን በዕቅድና በአግባቡ ለማልማት አመችነት የለውም ። ስለዚህ መሬትን በዕቅድ ለማልማት በመጀመሪያ አሠፋፈርን በዕቅድ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል ።

አገራችን የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ 40 በመቶ በደን የተሸፈነች እንደነበረች ሲታወቅ ዛሬ ግን የደኗ መጠን ወደ 3 በመቶ ገድም ዝቅ ብሏል ። ምን እስኪቀረን ነው የምንጠብቀው ? የሚለው ጥያቄ ወቅታዊና አንገብጋቢ ነው ። ደን የአየር ሚዛን መጠበቂያ ነው ። አፈር እንዳይባክን መከላከያ ነው ። ለሰው ልጅ ጥቅም የሚውሉ የልዩ ልዩ መገልገያዎች ምንጭ ነው ። የምንመካባቸው የዱር አራዊቶቻችን ከለላ ነው። ያለፈው ትውልድ ደን የሚያልቅ መስሎ ስላልታየው ወይም ሲያልቅ ስለሚያስከትለው ጉዳት ባለመረዳቱ ለረባ ላልረባው ሲጨፈጭፈው ፣ በእሳት ሲያጋየው በመኖሩ ዛሬ ለዓይን ማረፊያ እንኳን ደን የምናየው በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ነው ። የዛሬው ትውልድ ስለደን ጥቅም በመጠኑ ስለሚረዳና ያለመኖሩንም ጉዳት በሕይወቱ ጭምር ከፍሎ ስላየ ለደን ደንታቢስ ሊሆን አይችልም ። ከሆነም ለጊዜው በሚደርስበት ጉዳት ብቻ ሳያበቃ የታሪክ ተወቃሽም ይሆናል ።

ደንን ለማልማትም የሕዝቡ ተሰባስቦ መገኘትና መሬትን በሥርዓት ከልሎ መጠቀም ለልማትም ሆነ ለቁጥጥሩ አመችነት አለው ። ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ በተለይ በ 1972 በተካሄደው የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ወቅት በየኮረብታውና በየሸንተረሩ ላይ የተተከሉ ልዩ ልዩ ዕፅዋት በአንዳንድ አካባቢዎች አድገው አንዳንዶቹ ለዱር አራዊትም ማንሠራራት ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል ። አንዳንድ የገበሬ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ያላቸውን የደን ይዞታ ተንከባክበው ወይም አልምተው ውጤታቸው ሲታይ ሰፊና የተጠናከረ ጥረት ቢደረግ ምን ያህል ጠቀሜታ ለማግኘት እንደሚቻል በጣም ግልጽ ነው።

በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በዓለምማያ ወረዳ የራሬ ጭላሉ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅ

* ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 313



Digitized by Google

በር መንደሩን የሠራበትን ማገርና ወራጅ ባሕርዛፍ ያገኘው ራሱ ካለማው ደን ነው። የባሌም ክፍለ ሀገር በመንደር ምሥረታው አንጋፋና በአገራችን የተረፈው የደን ርዝ ራዥ ከሚገኝባቸው ክፍላተ ሀገር አንዱ በመሆኑ መንደር በደን ልማትና ጥበቃ ላይ ያለው ጠቀሜታ በጉልህ ይታያል። ደሎ አካባቢ ካለው የተፈጥሮ ደን ሌላ ከጐባ ጊኒር መንገድ ግራና ቀኝ የሚታየው ጫካ በውስጡ ባለው ቁጥቋጦ ፣ ሐረግ ፣ በቅጠሉ ልምላሜ ደኑ ከመጥረቢያና መጋዝ ድምፅ እፎይ ለማለቱ አንድ ማስረጃ ነው። በደን ተከላ የገበሬው ተሳትፎም አንዳንድ አካባቢ ተስፋ የሚሰጥ ምልክት ይታይበታል። በገናሌ አውራጃ ከአዲስ አበባ ጉባ 310 ኪሎ ሜትር ላይ ሲደርሱ ገባ ብሎ የሚገኘው የኤዶ ገበሬ መንደር አንድ ምሳሌ ነው። መንደሩ ያለው ቅልጥጥ ያለ ሜዳ ላይ ነው። በአቅራቢያው አንድም ዛፍ አይታይም። መንደሩን አለፍ ተብሎ አንድ ረባዳ ቦታ ሲደረስ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ አዲስ በመውጣት ላይ ያለ 20 ሄክታር የባሕርዛፍ ተክል ተንጣሎ ይታያል። ሌላ 10.2 ሄክታር መሬት ለተከላ ተዘጋጅቷል። ነገሩ በሄክታር ሲታይ ወይም ከሌሎች የደን ቦታዎች ጋር ሲነፃፀር ቀላል ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ምንም ዛፍ በሌለበት በአንድ ገበሬ መንደር ይህን ያህል ማልማት አርአያነቱ ቀላል አይደለም።

ቁጥቋጦም የተጠናከረ ስለሆነ ዛሬ በሐረርጌ ፣ በአርሲና በባሌ ደንን እንደልብ ጨፍጭፎ ጋር መከመር ወይም ለገበያ መንገድ ላይ መደርደር የሚቻል አልሆነም። ደንን ለማልማት እንጂ ለማጥፋት ብዙ ጊዜ አይወስድም። ዛሬ በሥራና በኃላፊነት ላይ ያለ ሰው ወጣት በነበረ ጊዜ በየአካባቢው ፍራፍሬ ይለቅምባቸው ፣ እንጨት ይሰብርባቸው የነበሩ ደኖች ደብዛቸው ጠፍቶ ሲያገኛቸው የሚሰማውን ሐዘን በየራስ ኅሊና ማሰቡ በቂ ነው። ከአዲስ አበባ ሻሸመኔ መንገድ ግራና ቀኝ የነበረው የግራር ደን የዛሬ ሃያ ዓመት አካባቢ ጥቅጥቅ ያለ የነበረ ሲሆን ዛሬ ግራር አናቱ ሰፊ በመሆኑ ብቻ ከሩቁ ደን ይምሰል እንጂ ውስጡ ሲገቡ ግን በጣም ተመናምኗል። ዛሬም ቢሆን ምንጠራው ሙሉ በሙሉ አልተገታም። ዛፉ እየተፈለጠና እየከሰለ በመንገድ ላይ ባይደረደርም ከሹፌር ጋር በሚገባቡበት ዘዴ እየተቸበቸበ ነው።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከምትኮራባቸው ሀብቶች መካከል የቤት እንስሳትም ይገኛሉ። በከብት ሀብታችን በምሳሌነት የምንጠቀስ ነን። ሆኖም ገበሬው ተበታትኖ በሚኖርበት ሁኔታ እያንዳንዱ ያለውን እንስሳ በፈለገው አካባቢ ስለሚያሠማራ ግጦሽ ከመጠን በላይ ይጋጣል። በግጦሽ ተግጦ ማለቅ የተነሣ አፈሩ እየተሸረሸረ ያልቃል። አዳዲስ ቁጥቋጦዎችም ይረጋገጣሉ። ይህም ለደን ልማትና ለአፈር እንክብካቤ አመቺ አይደለም። ዛሬ ገበሬው በመንደር በተሰባበባቸው አካባቢዎች ለግጦሽ የተለየ ክልል ይወሰናል። የእንስሳት ስምሪት መልክ መያዝ ፣ በዕቅድና ከብዛት ይልቅ የተሻሉ ዘሮችን ለማርባት ጥሩ ዕድል ይሰጣል። በተለይ በአንዳንድ ማኅበራት አካባቢ በምርጥ ዘር ማዳቀል የሚታየው የዘመናዊ ከብት እርባታ ሊበረታታ የሚገባ ነው። አንዳንዱ አካባቢማ እያደለቡ ለገበያ ማቅረብም በስፋት እየተጀመረ ነው ፣ የዕድገት አንድ ምልክት ነው።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የመንደር ምሥረታው የአካባቢን መሬት ለእርሻ ፣ ለመኖሪያ ፣ ለደን ፣ ለግጦሽ በመከፋፈል በዕቅድ ለመጠቀም ያስችላል። በመሆኑም ከመንደር ምሥረታው ዋና ዋና ጥቅሞች አንዱና ከገበሬው ሕይወትም ጋር የሚሄደው መሬትን በዕቅድ ለመጠቀም መቻሉ ነው።

በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ያለው መሬት ለምነት የተለያየ የመሆኑን ያህል በአንድ ክፍለ ሀገር እንዲያውም በአንድ ወረዳና ቀበሌ ገበሬ ማኅበር እንኳን መሬቱ ሊውል የሚችለው ለተለያየ ግልጋሎት መሆኑ ግልጽ ነው። አንዳንዱ አካባቢ ሰው ለረጅም ጊዜ የኖረበትና የተጠቀመበት በመ

Digitized by Google



የተቆናጀ ሕይወት ለጎጆ ኢዱስትሪ መስፋፋትም ይበጃል ።

ሆኑ የአየሩ ጠባይ ተቀይሮ ፣ አፈሩ አልቆ ማኖር ከማያስችል ደረጃ ላይ ደርሷል ።

የገበሬው በመንደር መሰባሰብ እነዚህን ሁሉ ችግሮች በማገናዘብ የሚከናወን ነው ። እለበለዚያ በራሱ እንደምፍትሔ ተደርጎ ከተወሰደና ለም ባልሆኑ አካባቢዎች ያለውም እዚያው ከተሰባሰበ ፋይዳ የለውም። በዚህ በኩል በአርሲ ክፍለ ሀገር የተወሰደው እርምጃ ጥሩ ምሳሌ ነው ። በአርሲ የክፍለ ሀገሩ ማኅበረ ኢኮኖሚ ከተጠና በኋላ አንዳንዶቹ ቦታዎች በአየር መዛባት በተደጋጋሚ የሚጠቁና መሬቱም ለምነቱን ያጣ በመሆኑ ቢቻል በእነዚህ አካባቢዎች ያለው ሕዝብ በሌሎች አካባቢዎች በስግሰጋ እንዲሰፍር ፤ ይህ ካልተቻለ እዚያው በዚያው ከማስፈር ለጊዜው እንዲቆይ ተደርጓል ። አንድ ምሳሌ እንውሰድ ። የዶዶታ ወረዳ በጭላሎ አውራጃ የምትገኝና ከሸዋ ወደ ክፍለ ሀገሩ መግቢያ በር ናት ። ወረዳዋ 75% ቆላማ ፣ 25% ወይና ደጋ ስትሆን 48 ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ያሉባት ናት ። በተደረገው ጥናት መሠረት 24 የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውሃ የሌላቸውና መሬቱ በእሳተ ገሞራ ድንጋይ የተሸፈነ ሆኖ በመገኘቱ በዚያ አካባቢ መንደር እንዳይመሠረት ተደርጓል ። በጣም ለም በሆኑ አካባቢዎች ያለው መሬት ሰፊ በመሆኑ በ15 ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ስምንቱ ቀበሌዎች በስግሰጋ እንዲገቡ ተደርጎ 16 የገበሬ መንደሮች ተመሥረተዋል ። ይህም ችግር ላይ የነበረውን ገበሬ ወደ ለም አካባቢ ለማሰባሰብ አንድ መፍትሔ ሊሆን ችሏል ።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ጐልተው ከሚታዩት ችግሮች መካከል ትምህርት ፣ የጤና አገልግሎት ፣ መገናኛ ፣ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ ዘመናዊ ግልጋሎቶች ዘልቀው አለመግባታቸው ተዘውትሮ የሚጠቀስ ነው ። እነዚህ አገልግሎቶች ባላቸው ባሕርይ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በተናጠል ለማዳረስ የሚሞከሩ አይደሉም ። እንኳንስ በታዳጊ ሀገር ኢኮኖሚና በዳበሩት ሀገሮችም ቢሆን ሥርጭታቸው ከሕዝብ ብዛትና ክምችት ጋር



Digitized by Google

ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው ። በፍላጎት ደረጃ ሲታዩ መሠረታዊ ናቸው ። ካልተማረ ሰው የተማረ ሰው የበለጠ ያመርታል። ከበሽተኛ ጤነኛ በምርት ላይ የበለጠ ተሳትፎ ያደርጋል ። መገናኛ ያለበት አካባቢ ከሌለበት አካባቢ የተሻለ ግብይት ይኖረዋል ። በመሆኑም እነዚህን በአገሪቱ ባጠቃላይ ማዳረሱ ለዕድገታችን መሠረት ለመጣል ወሳኝነት እንዳለው ግልጽ ነው ። ገበሬው ተበታትኖ ባለበት ሁኔታ እነዚህን አገልግሎቶች ለማዳረስ መሞከር የማይጨበጥ ውጥን ይሆናል ። ስለዚህ የገበሬው ተሰብስቦ መገኘት ከዚህ ጠቀሜታ አኳያም ሊታይ ይገባል ።

የሕዝቡ በመንደር መሰባሰብ በእነዚህ አገልግሎቶች በሚገባ ለመጠቀም የሚያስችለው ለመሆኑ ትምህርትን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል ። በአገራችን የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መካሄድ ከጀመረ ዐሥራ አምስተኛ ዙር ላይ ደርሷል። በነዚህ ዙሮች ሁሉ በርካታ ወገኖቻችን ከማይምነት ተላቀዋል ። ዘመቻችንም በዓለም ደረጃ ተደናቂነትን ከማግኘቱም በላይ ተሸልመንበታልም ። ይህ ሁሉ ውጤት የተገኘው አብዮታዊው መንግሥትና በሙያው የተሠማሩ መምህራንና ተማሪዎች ማይምነትን ለማጥፋት ቆርጠው በመነሣታቸውና ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘልቀው በመግባታቸው ነው ። ይሁን እንጂ የሕዝቡ ተበታትኖ መኖር ከትምህርት ማዕከላት መራቅ ጋር ተዳምሮ እስከ አሁን ሊገኝ ይችል በነበረው ውጤት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አያጠያይቅም ። ዛሬ የገጠሩ ሕዝብ በመንደር በተሰባሰበባቸው ክፍላተ ሀገር ማይምነት ቀሺሞ ከነበረበት ጉራንጉር ለኢላማ በሚያመች ቅልጥጥ ያለ ሜዳ ላይ ወጥቷል ።

ሐላ እንዳዶ በአርሲ ክፍለ ሀገር በጢቾ አውራጃ ፣ ገቡዱ ወረዳ የምትገኝ አንዲት መንደር ናት ። በአዲሱ መንደር 354 ቤቶች ተሠርተዋል ። 2,345 ነዋሪዎች አሉበት ። ከዚህ ቀደም በአካባቢው ተደጋጋሚ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ተካሂዷል።በአዲሱም መንደር ለመሠረተ ትምህርት መስጫ አንድ መለስተኛ አዳራሽ ተሠርቷል ። አራት ዘማቾች ተመድበዋል ። ከመንደሩ ስንደርስ ተማሪዎች በትምህርት ላይ ነበሩ ። ክፍል ስንገባ ክፍሉ በተማሪ ተሞልቷል ። ለምን እንዲህ ሆነ ስንል ከዚህ ቀደም ተበታትነው ባሉበት ጊዜ ርቀቱ ስለሚያስቸግራቸውና ለቁጥጥርም አመች ባለመሆኑ ብዙዎች አይወጡም ነበር ። ዛሬ በደጃፋቸው ላይ ስለሆነ ለመማር አመች ሆኗል አሉን። ያን ያህል ጐልማሳ ማይምናንን በአንድ ላይ ማስተማሩ ችግር የሚፈጥር ቢሆንም ይህ ችግር ተማሪዎቹን በተለያዩ ፈረቃ በመከፋፈል የሚወገድ ነው ። ለማንኛውም ከዚህ የተሻለ ማይምነት ኢላማ ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ የለም ።

በመደበኛውም ትምህርት ቢሆን በመንደር መሰባሰብ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው ። በተለይ በባሌ ክፍለ ሀገር እንዳየነው ገበሬው ትምህርት ቤቶች የራሱ መሆናቸውን ዐውቆ በአስተዳደሩና በይዞታው የሚያደርገው ቀጥተኛ ተሳትፎ ተስፋ የሚሰጥ ነው ። ከዚህ ቀደም ሕዝቡ ቢበዛ ለትምህርት ቤት መሥሪያ ገንዘብ ከማዋጣት በስተቀር በአስተዳደሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ አልነበረውም ። ዛሬ ግን በትምህርት አመራር ኮሚቴ አማካይነት በቀጥታ ይሳተፋል ። ገበሬው ለትምህርት ቤቶች ሥራ ማስኬጃና አንዳንድ ሥራዎችን ማከናወኛ ገንዘብ ለማስገኘት መሬት አርሶ ፣ ዘርቶ ፣ አጭዶና ወቅቶ የበኩሉን ድጐማ ያደርጋል። ተማሪዎቹም በሥራው ይሳተፋሉ ።

በባሌ ክፍለ ሀገር በመንደዮ አውራጃ ፣ በሲናና ወረዳ የአበራ ገበሬ መንደር በዚህ ረገድ አንድ ምሳሌ ነው ። የአበራ ገበሬ መንደር እስከ 12 ኪሎ ሜትር ከሚርቅ አካባቢ የተሰበሰቡ ገበሬዎች የሚገኙበት 1,107 ቤቶችና 5,883 ነዋሪዎች ያሉበት ትልቅ መንደር ነው ። በሶማሌ ወረራ ጊዜ በአካባቢው ያለው ሕዝብ ዓለምገና በምት



Digitized by Google

ባለዋ ከተማ አካባቢ ተሰባስቦ ራሱን ሲከላከል ቆየ ። በመልሶ ማጥቃት የጠላት ወረራ ከተመታ በኋላ ሕዝቡ በከተማዋ አካባቢ ባለው ሰፈሚዳ ተሰባሰበ ። በወቅቱ በወረራውና በአየር መዛባት ምክንያት ችግር ስለነበር ሕዝቡ ከመንግሥት ዕርዳታ እያገኘ መንደሩ ተመሠረተ ። ዛሬ ከተማዋ ራሲ የገበሬ ማኅበሩ ስትሆን አንድ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት ተቋቁሟል ። ገበሬው ለትምህርት ቤቱ ወደ ስምንት ሄክታር መሬት አርሶ ዘርቷል ። ሰብሉ ሲደርስ ለዘር የሚሆን ይቀርና የተረፈው ተሸጦ ለትምህርት ቤቱ አገልግሎት ይውላል ። ወጭውን የትምህርት አመራር ኮሚቴ ይቆጣጠራል ። ገበሬው መሬት አርሶ ለትምህርት ቤቶች የማዋሉ ልምድ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ገበሬው በመንደር በተሰባሰበባቸው አካባቢዎች አንዱ ያልነበረ ልምድ የመዋዕለ ሕፃናት ጉዳይ ነው ። በጐበኘናቸው በሦስቱም ክፍላተ ሀገር መንደሮች በአካባቢያቸው በተገኘ ነገር መዋዕለ ሕፃናት ይሠራሉ ። አንዳንዶቹ የተማሩ የገበሬ ሚስቶችን አስተማሪ አድርገው ሲጠቀሙ ሌሎች ደግሞ ቀጥረው ያሠራሉ ። ለቀጠሯቸው መምህራን ወጭና ለሕፃናት ምሳ ጭምር ገንዘብ የማስገኛ ዘዴ ፈጥረው የሚጠቀሙ ጥቂት አይደሉም ። የገንዘብ ምንጮቻቸውም ከግብርና ጋር የተያያዙ ተጋባሮች ናቸው ።

የገበሬው በመንደር መሰባሰብ ያስገኛል ተብሎ ከሚታሰበው ጠቀሜታ አንዱ የጤንነት ጉዳይ ነው ። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት የሚደርሰው ሕዝብ ብዛት 20 በመቶ ያህል ነበር ይባል እንጂ ከጤና አገልግሎቱ ጠቅላላ በጀት 43 በመቶ የተመደበው ለሦስት ከተሞች ብቻ ነበር ። * ከአብዮቱ መቀጣጠል ወዲህ ግን በዚህ ረገድ በተለይ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ለብዙኃኑ ሕዝብ በማዳረስ በኩል የተደረገው ጥረት ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው ። ይሁን እንጂ አሁንም የተጠናከረ ትግል የሚጠይቅ ነው ።

የጤና አገልግሎት በባሕርዩ መንግሥት ብቻ ወይም እያንዳንዱ ግለሰብ በተናጠል በሚያደርገው ጥረት ብቻ የሚሳካ አይደለም ። የሕዝቡን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል። አንድን ምግብ ለመበከል የግድ በአካባቢ የዝንብ መንጋ መኖር የለበትም ። አንዲት ራቅ ካለ አካባቢ የምትመጣ የተበከለች ዝንብ ትበቃለች ። የጥቂት ሰዎች ጥንቃቄ አለመውሰድ ለብዙ ሰዎች ጠንቅ ይሆናል። በመሆኑም ከሁሉ አስቀድሞ ኅብረተሰቡን ስለመሠረታዊ የጤና ጥበቃ ማስተማር ተቀዳሚ ተግባር ነው ። ለዚህ ደግሞ ሕዝቡ በየሸንተረሩና በየአፋፉ ተበታትኖ በሚኖርበት ሁኔታ አይቻልም ። መሰባሰብ አስፈላጊ ነው ። ዛሬ መንደር በመመሥረት ላይ ባሉት ክፍላተ ሀገር ሕዝቡ ለጤንነት አጠባበቅ በተሻለ ተመቻችቷል ። በገጠሩ ከዚህ ቀደም የመፀዳጃ ቤት ጥቅም የማይታወቅ ሲሆን ዛሬ እያንዳንዱ መንደርተኛ ጉድጓድ ቆፍሮ መገልገል ጀምሯል ። በየመንደሩ ከገበሬው ከራሱ መካከል ወጥተው በጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች መጠነኛ ሥልጠና በቀሰሙ ነዋሪዎች አማካይነት የጤና አገልግሎት እየተስፋፋ ነው ። ክሊኒኮችን ለመሥራትም የገበሬው በመንደር መሰባሰብ አመች ሁኔታ እየፈጠረ ነው። በተለይ የሕፃናት ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል መቻል ጤናማ ዜጋን ለማፍራት አንዱ መነሻ መሆኑ ይታወቃል ። በ ዚ ህ በኩል እ-ኤ-አ በ2,000 ዓመት «ጤና ለሁሉም» በሚለው የተባበሩት መንግሥታት መርሐ ግብር መሠረት አባል ሀገሮች ከሚጠበቅባቸው የጤና አገልግሎቶች አ ን ዱ ለሆነውና ዛሬ በመላው ዓለም ለሚካሄደው የፀረ ስድስት ክትባት ምቹ ሁ ኔ ታ

*የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ፣ የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፣ አዲስ አበባ ፣ መስከም 1977 ፣ ገጽ 467


Digitized by Google

ተፈጥሯል ። ክትባቱ ስሙ እንደሚያመለክተው ስድስት በሽታዎችን የሚከላከል ነው ። አስጣጡም በተወሰነ ዕድሜ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ከበሽታዎቹ ነፃ ለመሆን በተወሰኑት ወቅቶች ሁሉንም መውሰድን ይጠይቃል ። ጥንቃቄ የሚያሻውም ነው ። ለዚህ መሳካት የሕዝቡ በተደራጀና በተሰባሰበ መልክ መገኘት እጅግ አስፈላጊ ነው ። የዚህን ክንውን ተግባራዊነት በጤና ጥበቃ የተደረገው ግምገማ እንደሚያሳየው በ1975 በባሌ ክፍለ ሀገር ክትባት ከጀመሩት ውስጥ 69% በማጠናቀቃቸው ክፍለ ሀገሩ አንደኛ ሲሆን ፣ በዓመቱ ከፋ ብልጫ ቢያሳይም ዘንድሮ በተደረገው ግምገማ ደግሞ አሁንም ባሌ 85.6% በማጠናቀቅ አንደኝነትን ይዟል ። ባለሙያዎች እንደሚሉት ይህ ውጤ በታዳጊ ሀገር ቀርቶ በለሙትም ቢሆን የሚናቅ ውጤት አይደለም ። በአዲስ አበባ 68% ፣ በሸዋ 60% ክትባቱን ሲያጠናቅቁ የሌሎች ክፍላተ ሀገር ውጤት ከዚህ በታች ነው ። የባሌ ይህን ውጤት ማስመዝገብ በክፍለ ሀገሩ በሥራው የተሰማሩትን ጥረት የሚያሳይ ቢሆንም ከሕዝቡ ቀደም ብሎ መሰባሰብ የመነጨ መሆኑም አያጠያይቅም ።

የጤንነት ጉዳይ ሲነግ ጤና ከንጹሕ ውሃ ተለይቶ የሚታይ አይደለም ። ውሃ ለመጠጥ ፣ ለምግብ መሥሪያ ፣ ለንጽሕና ወዘተ የሚያገለግል በመሆኑ ከሰው ሕይወት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። የዚያኑ ያህል በቀላሉ ሊበከልና ልዩ ልዩ የበሽታ ተዋስያንን ሊያስተላልፍ የሚችል በመሆኑ በንጽሕና የመያዙ ጉዳይ ወሳኝ ነው ። በታዳጊ ሀገሮች ያለው የሰው ልጅ የመኖር ተስፋ በጣም ዝቅተኛ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ በንጹሕ ውሃ ባለመጠቀም መሆኑ ይታወቃል ። የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት እንደገመተው በአፍሪካ ውስጥ «---ከሚሞቱት ሕፃናት ወደግማሹ ገደማ ንጹሕ ውሃ ባለማግኘትና በንጽሕና ጉድለት ነው ። በዚህ ላይ ከሩቅ ቦታ ውሃ ማመላለሱ ለአፍሪካ ሴቶች ትልቅ ሸክም ሆኖ ቆይቷል»* ። በዚሁ ጥናት ላይ እንደተጠቀመው « በአፍሪካ ውስጥ አንድ ሰው ይኖራል ተብሎ የሚገመተው ለ47 ዓመታት ብቻ ነው ። ይህም ቁጥር በዓለም እጅግ ዝቅተኛው ነው ። በሌላ በኩል በአሀጉራችን ገና አምስት ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱ ሕፃናት ቁጥርም እጅግ ከፍተኛ ነው ። ከሚወለዱት 1,000 ሕፃናት መካከል 150ዎቹ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ ። በአፍሪካ ውስጥ የጤና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች በጣም አነስተኛ ናቸው ። እ-ኤ-አ በ1977 ለ25,000 ሰዎች አንድ ሐኪምና ለ3,300 አንድ ነርስ ብቻ ነበሩ ። ለዚያውም አብዛኛዎቹ የጤና ባለሙያዎች ከነዋሪዎቹ 20 በመቶዎቹ ብቻ በሚገኙበት በከተሞች አካባቢ የተከማቹ ነበሩ ። »**

በኢትዮጵያ ያለውም ሁኔታ ይኸው ነው ። ለዚህ አንዱ ማስረጃ «በአሁኑ ወቅት ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት የሚያገኘው የገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ ከጠቅላላው የገጠሩ ሕዝብ 5.5 ከመቶ በታች ነው ። በቂና አስተማማኝ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው የከተማ ሕዝብም 19 በመቶ ነው ።» *** በዚህ ስሌት መሠረት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኝ ገና ሰፊ ጥረት መደረግ ይኖርበታል ማለት ነው ። ከዓቅም ማነስ ሌላ አብዛኛው የሀገራችን ሕዝብ ንጹሕ ውሃ ካላገኘባቸው ምክንያቶች አንዱ የገጠሩ ሕዝብ አስፋፈር የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ለማስፋፋት አመች ያለመሆኑና ለዚህ ተግባር የሕዝብ ተሳትፎ

---

* Accelerated Development in Sub Saharan Africa; an Agenda for Action, the World Bank, Washington D.C. 1981 p. 89.

** IBid; p. 87.

** የንብረተሰብአዊ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ፤ 1977—86 እ.ኤ. መስከረም 1977 ፤ ገጽ 311

Digitized by Google

እነስተኛ ሆና መቆየቱ እንደሆነ ልዩ ልዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ ። ስለዚህ የሕዝቡ በአፎፎሩ ስብሰብ ብሎ መገኘት የሕዝብንና የመንግሥትን ጥረት በማስተባበር ችግሩን ለማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚናረው የታመነ ነው ። ዛሬ ባለው አሰፋፈር ያለብን ችግር የንጹሕ ውሃ አለማግኘት ብቻ ሳይሆን ውሃ ራሱ በአንዳንድ አካባቢ በበቂ አለመገኘቱ ነው ። በአርሲና በባሌ በአንዳንድ አካባቢ እንደተመለከት ነው ወራጅ ወንዝ ባለመኖሩና በአንዳንድ ቦታ ያሉት ወንዞችም ቢሆኑ በክረምት ብቻ የሚፈሱ በመሆናቸው በርካታ ሕዝብ ውሃ የሚያገኘው የክረምቱን ጐርፍ በኩሬ በማጠራቀም ነው ። ወራጅ ወንዝ ባለባቸውም አካባቢዎች ወንዝ ድረስ ሄዶ ውሃ ለማምጣት የአራትና የአምስት ሰዓት ጉዞ የሚኬድባቸው ቦታዎች አሉ ። በጢቾ አውራጃ አሚኛ ወረዳ ስንገባ የወረዳዋ ፓርቲ ኮሚቴ ወረዳዋን ያስተዋወቀን ወረዳችን አንድም ወራጅ ወንዝ ፣ ከአንድ የመቃብር ሥፍራ ካልሆነ በስተቀር አንድም ደን የሌለባት ወረዳ ናት በማለት ነበር ። ወ ራ ጅ ውሃ የሌለበት የአንድ ወረዳ ክልል የሚናረውን የውሃ ችግር መገመት ይቻላል ። ከዚህ ይባስ ብሎ በባሌ ክፍለ ሀገር የዋቤ አውራጃ ዙሪያውን እያካለሉ ከሚወርዱ ወንዞች በስተቀር ምንም ወራጅ ውሃ የለበትም ። ከዚህ አኳያ ነው በነዚህ አካባቢዎች የውሃ ጥቅም የሚታየው ።

ታዲያ ምን እየተደረገ ነው ። ገበሬው በመንደር ከመሰባሰቡ በፊት ያለውን የውሃ ችግር በመገመት ጥልቅ ጉድጓዶችን በመቆፈርና ምንጮችን በማሻሻል አንዳንድ ጥረቶች ቢደረጉም ለተበታተነ ሕ ዝ ብ ብዙም ጥቅም ሊሰጡ አልቻሉም ነበር ። ዛሬ ግን ሕዝቡ በመንደር በመሰባሰቡ ጉድጓዶች በመቆፈርና ከምንጭ በቧምቧ በመሳብ የተደረገው ጥረት ትልህ ውጤት እያሳየ ነው ።

ሉዴ ቢቃ በአርሲ ክፍለ ሀገር በጭላሉ አውራጃ ፣ በዶዶታ ወረዳ የምትገኝ መንደር ናት ። ሉዴ ቡቃ የገበሬ መንደር ከመሆኗ በፊት ወደ ዴራ ፣ ናዝሬትና ጢቾ መተላለፊያ ስለነበረች ከተማነት ነበራት ።አዲስ መንገድ በሌላ በኩል ሲሠራ አንዳንዶቹ የከተማዋ ነዋሪዎች ወደሌላ አካባቢ ሲሄዱ የተቀሩት በእርሻ መተዳደር ጀመሩ ። መንደር ሲመሠረትም ቤቶች በመንደር ፕላን ተሠሩ ። በመንደሩ ውስጥ ሦስት ቦታ የውሃ ማከፋፈያዎች (በዚያ አካባቢ ቢርካ ይባላሉ) አሉ ። ከእያንዳንዳቸው በአንድ ጊዜ አራት ሰው መቅዳት ይችላል። ውሃው ከየት መጣ ብለን ብንጠይቃቸው ከዚያ ጉብታ ሥር አሉን ። ለምን ከቅርብ አልገባላችሁም ተብለው ሲጠየቁ እዚህ አካባቢ ምን ውሃ አለ ፤ ከዚህ ቀደም እንቀዳ የነበረው ከኤላዎች (ከኩሬዎች) ነበር አሉን ። ኩ ሬ ው ሲደርቅ ከቀለጣ ወንዝ ነው የሚቀዳው ። የቀለጣ ወንዝ የት-አካባቢ ነው ? ስ ን ል ያውና ብለው ውሃ ለመቅዳት ሰው ይሄዳል ተብሎ ከማይገመትበት ርቀት ላይ አሳዩን ። በግምት ከ15 ኪሎ ሜትር አያንስም። ከዚያ ውሃ ለማምጣት ገና ወፍ ሲንጫጫ ተነሥቶ የበረታ ወደሰባት ሰዓት ይመለሳል ። በዚህ ሁኔታ የነበረውን የውሃ ችግር መገመት አስቸጋሪ አይደለም ። እንዲያ የኖረ ሰው ዛሬ ንጹሕ ውሃ ከደጁ ሲያገኝ ምን ይሰማዋል ? ውሃ ሲቀዱ ካገኘናቸው ነዋሪዎች አንዷ ወይዘሮ ድንቄ ዋቀዮ ነበሩ፤ ወይዘሮ ድንቄ ዕድሜአቸው 55 ገደማ ይሆናል ። እዚያው ተወልደው ያደጉ ናቸው ። ከተማዋ በነበሩበት ጊዜ ጠላ እየሸጡ ይኖሩ ነበር ። ዛሬ ከተማዋም መንደር ሆናለች ። እሳቸውም ዓቅም አንሶአቸዋል ። እንደነገሩን ዛሬ የሚኖሩት በአካባቢው ገበሬ ዕርዳታ ነው ።

ውሃ ከየት ይቀዱ ነበር አልናቸው ።

ከቀለጣ አሉን ።

እንዴት ይሄዳሉ ?



Digitized by Google

ንጹሕ ውሃ በቅርቡ

ሴሊት ተነሥተን እንሄዳለን ።

በየቀኑ ?

የለም በሁለት ቀን አንዴ ነው ። ለዚያውም ቀደም ብለን ካልደረስን ቦታው ስለማያመች ተራውም ችግር ነው በማለት ትዝ እያላቸው አስረዱን ።

አሁን ውሃ ከዚህ ሲቀዱ ምን ይሰማዎታል ?

ዓለም ነዋ ! ሌላ ምን እላለሁ ፤ ዓለም ነዋ ! አሉ ።

እውነትም ዓለም ።

በዚህ አካባቢ የገባው ውሃ በአኢሴማና በጀርመን ሴቶች ማኅበር ኅብረት ነው ። ዛሬ በዶዶታ ወረዳ ከሚገኙት አሥራ ስድስት መንደሮች አሥራ አራቱ ንጹሕ ውሃ ገብቶላቸዋል ። ተመሳሳይ በርካታ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ። ዛሬ በሐረርጌ፣በአርሲና በባሌ መንደር በተመሠረተባቸው አካባቢዎች ዓቅም በፈቀደ መጠን ውሃ ለማስገባት የሚደረገው ጥረት ቀላል አይደለም ። ጉድጓዶች መቆፈር ፣ ምንጭ ማሻሻል ፣ ከሩቅ በቧንቧ ማስገባት በስራው ይካሄዳል ።

ለገጠሩ ነዋሪ ንጹሕ ውሃ ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት በሚመለከት በግንባር ቀደምትነት መጠቀስ የሚችለው የባሌ ክፍለ ሀገር ነው ። ባሌ በቅድመ አብዮት በተፈጥሮ ሀብቷ ካልሆነ በቀር በልማት በማንኛውም መለኪያ ኋላቀር ከሆኑት ክፍላተ ሀገር አንዷ ነበረች ። ዛሬ ግን አይደለችም። በመሠረተ ልማት በኩል በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ። ከነዚህ አንዱ ለገጠሩ ሕዝብ ንጹሕ ውሃ ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት ነው ። በየመንደሩ የተቆፈሩ በርካታ ጉድጓዶች ይቅሩና ከሩቅ በቧንቧ የገቡ የውሃ አገልግሎቶች በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም ። ከነዚህም ውስጥ በጎሮ ወረዳ ከዳዲሞስ ተራራ ሥር ካለው ምንጭ በቧንቧ 58 ኪሎ ሜትር ተጉዞ ጎሮ ከተማ ድረስ የተወሰደውና በመንገድ ላይ ያሉትን ወደ 18 ገበሬ መንደሮችንና ሁለት ከተሞችን የሚያጠጣው የቧንቧ ውሃ ሥራ አንዱ



Digitized by Google

ነው ። የውሃው መነሻ ከከፍታ ሥፍራ ላይ በመሆኑ እነዚህን መንደሮች ሁሉ ለማጠጣት የሚጓዘው በስበት ኃይል በመሆኑ ለቁሳቁስና ለሠራተኛ ከወጣው በቀር ሌላ ወጭ አልተደረገም ። ነዋሪው በቦይ ቁፋሮና በመንገድ ጠረጋ በጉልበት ተሳትፏል ።

ሌላው የሚዮ ጋስራ የውሃ ፕሮጀክት ነው ። የፕሮጀክቱን ወጭና ሙያን የሚጠይቅ ሥራ የሚሸፈነው በተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅትና በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሲሆን ሥራውን የሚመራው የሚዮ ጋስራ ውሃ ፕሮጀክት ነው ። ውሃው የሚነሣው ከዲንሾ ወረዳ ፣ ሜሌ ከሚባለው አካባቢ ከምትገኘው ሜሌ ምንጭ ነው ። በሕዝቡ የሥራ ተሳትፎ በኩል እስካሁን 49,909 ሰዎች ተሳትፈዋል ። ሥራው ሲጠናቀቅ ዋናው መሥመር ብቻ 68.65 ኪሎ ሜትር ተጉዞ ለ22 የገበሬ መንደሮችና ለአንድ ከተማ ግልጋሎት ይሰጣል ። በዚያን ጊዜ ግልጋሎት የሚያገኘው ሕዝብ ብዛት 40,416 ይሆናል ። ከዚህ ውስጥ እስካሁን የ48 ኪሎ ሜትር ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን በ11 ገበሬ መንደር የተሰባሰቡ 21,548 ሰዎች ውሃ ገብቶላቸዋል ።

ከላይ የተገለጸው የቧንቧ ሥራ መነሻ ከሆነው ከሜሌ ወንዝ አምስት ኪሎ ሜትር ገደማ ርቆ ከሚገኝ ሌላ ምንጭ ደግሞ በመጀመሪያ ከአዳ ርቢ ፣ ከዚያም ከአዳ በልዩ ድረስ የሚዘረጋ የ78 ኪሎ ሜትር መሥመር ጥናት ተገባዶ የምንጩ ጠረጋ ተጀምሯል ። እስካሁን በባሌ ክፍለ ሀገር ከገጠሩ ነዋሪ 26.5 በመቶ ንጹሕ ውሃ ያገኛል ። ይህም አዲስ በመገባት ላይ ያሉትን ሳይጨምር ነው ።

ዛሬ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ንጹሕ ውሃ የሚያገኘው ሕዝብ 5.5 ከመቶ ፣ ከጠቅላላው ሕዝብ ደግሞ 11.5 በመቶ ከመሆኑ ጋር ሲነፃፀር ጉልህ ውጤት ነው ። ክፍለ ሀገሯ ለዚህ የበቃችው ምን ተገኝቶ ነው ? ትላንት ከሀገሪቱ በኋላ ቀርነት ትጠቀስ የነበረችው ባሌ ያጋጠማት ተአምር የለም ። እንዲያውም ሕዝቡ በሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት በመጠቃቱ ተበታትኖ ከፊሉም ተሠውቶ ፣ ሀብቱ እንዳለ ተዘርፎ ችግር ላይ በመውደቁ በጣም ተጎድቷል ። ባሌ ዛሬ በልማት እርምጃ አንደኛ ተጠቃሽ ለመሆን የበቃችው ጦርነቱ እንዳበቃ ሕዝቡ በመንደር በመሰባሰቡና አመቺ ሁኔታ በመፈጠሩ ፣ በዚህም አማካይነት በመልሶ ማቋቋሙ ተግባር መንግሥት የሰጠው ትኩረትና የዓለምአቀፍ ድርጅቶችም ድጋፍ ለፍሬ እንዲውል በመደረጉ ነው ። በነገራችን ላይ የክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ የሆነችው ጎባ የቧንቧ ውሀ የገባላት በዐሥረኛው የአብዮት በዓል ወቅት ነው ። ይህ ለክፍለ ሀገሩ በኋላ ቀርነት መቆየት አንዱ ማስረጃ ሲሆን ፣ የገጠሩ ሕዝብ ንጹሕ ውሀ በማግኘት ከኢትዮጵያ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘ መሆኑ ደግሞ ለዛሬው ውጤት ማስረጃ ነው ። ስለዚህ የሕዝቡ በመንደር መሰባሰብ ሁለገብ የሆነውን የንጹሕ ውሀ ግልጋሎት ከማግኘት አኳያም የሚታይ ነው ።

በአጠቃላይ በመንደር የተሰባሰበው ሕዝብ ከኋላቀር አኗኗር ለመላቀቅ በሚያደርገው ጥረት ብዙ ውጤት እያገኘ ነው ። ገበሬ መንደር ሂዶ የኤሌክትሪክ ብርሃን ማየት ቢያንስ ትናንት ገጠር ተወልዶ ከተማ ላደገ ሰው ታላቅ ለውጥ ነው ። በአገራችን የገጠር መንደሮች ኤሌክትሪክ መግባት ጀምሯል ። ዶታ ወረዳ የሄጦሳ ገበሬ መንደር አንዱ ማስረጃ ነው ። የሄጦሳ ገበሬ መንደር በአብዛኛው በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር የተደራጀ ነው ። ገበሬው በመንደር መሰባሰብ የጀመረው ቀደም ሲል በመሆኑ በክፍለ ሀገሩ የመንደር ምስረታ በተስፋፋ መልክ ከመጀመሩ በፊት በዚህ መንደር 116 አባላት ተሰባስበው ነበር ። በመንደሩ አዲስ ከተሠሩት 51 ቤቶች በስተቀር ሌሎቹ በሙላ ሃያ አራት ሰዓት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኛሉ ። ለአዲሶቹ ቤቶችም ቢሆን ግምት ወጥቶ ገንዘቡ ስለተከፈለ በቅርብ ቀን እንደሚገ



Digitized by Google

ባላቸው ታውቋል ። ሁለት ቤቶች በኤሌክትሪክ የሚሠራ ምጣድ አስገብተዋል ። በሁለት ቦታ እያንዳንዱ ለዐሥር ቤቶች የሚያገለግል የባዮ ጋዝ ማመንጫ መሣሪያም ለሙከራ ተተክሏል ። በመንደሩ ውስጥ ሲዘዋወሩም ሆነ ቤቱ ውስጥ ሲገቡ በምንም ዓይነት የገጠር መንደር አይመስልም ። የገበሬውን አኗኗር ለመለወጥ የሚደረገው ጥረት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ዛሬ በየቤቱ ማድ ቤት ፣ መፀዳጃ ቤት ፣ የቆሻሻ መጣያ እየተሠራ ነው ። በማድ ቤት ውስጥም ቢሆን እንደቀድሞው በግልጽ ምድጃ በጭስ ከመታፈን ለመገላገል የቁምና ዝግ ምድጃ መሥራት እየተለመደ ነው ። ለዚህ አንድ ጥሩ ምሳሌ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ፣ በወበራ አውራጃ በደደር ወረዳ ፣ የዱዴሳ ቁጥር 3 ገበሬ ማኅበር መንደር ነው ። ገበሬ ማኅበሩ ፣ ከዚህ ቀደም በ9 መንደሮች የሚኖር ሲሆን ዛሬ በአራት መንደሮች ተሰባስቧል ። ከነዚህ መካከል ከቀቦ ከተማ 15 ኪ- ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው አዲስ ዓለም የሚል መጠሪያ የተሰጣት አንዷ ናት ። አዲስ ዓለም የተባለችበት ምክንያት ቤቶቹ በሞላ በቆርቆሮ የተሠሩ በመሆናቸው ነው ። አዲስ ዓለም ቀቦ ላይ ሆነው ሲመለከቷት ከግዶ



መንደራችን ዘመናዊ አኗኗርም እያስተማረን ነው ።



Digitized by Google

ባለው ተራራ ጥግ ታንጣላ እዩኝ እዩኝ የምትል መንደር ናት ። ገበሬው ከሐረር መገንጠያ 6 ኪ- ሜትር በራሱ ጉልበት የመኪና መንገድ አውጥቷል ። የግብርና ሚ/ር መሠረት ልማት መንገዱን አሻሽሎ ለመሥራት የቅያስ ሥራ ጀምሯል ። መንደሩ የተሠራው ተራራ ጥግ ነው ።

በጭቃ ብሎኬት የተሠራ የሕፃናት መዋያ አለ ። ይህን መንደር ተደናቂ የሚያደርገው በሩቁ የሚታየው ውበቱ ብቻ አይደለም ። በመንደሩ ያሉት 325 ቤቶች በሙላ ቁም ምድጃ አላቸው ። በብዙ ቤቶች ዝግ ምድጃ እየተሠራ ነው ። ከዚህም በላይ ሌሎች መንደሮች የቁም ምድጃ እንዲሠሩ የመንደሩ አኢሴማ ሊቀ መንበር የሆኑት ጓድ ራዚያ አሕመድ እያስተባበሩ ነው ። በዚህም መሠረት ከአካባቢው ወደ 12 ኪ-ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ጨለንቆ ሐራ መንደር በአንድ ቤት የቁም ምድጃ ተሠርቶ መገልገል ሲጀምሩ ቃጠሎ አስነሣ ማለትን በመስማታቸው ጓድ ራዚያ ሌሎች 40 ሴቶችን በማስተባበር ሂደው 17 የቁም ምድጃ በመሥራት የአካባቢውን ሴቶች አስተምረውና እንዴት እንደሚሠራ አሳይተው ተመልሰዋል ።

ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው እንዲሉ ሁሉም የሚያምረው መረዳዳት ሲኖር ነው ። በቆቦ አዲስ ዓለም መንደር እንደነበርን ዝናብ ስለጣለ መጠለያ መፈለግ ግድ ነው ። ስለዚህ በአንዱ ቤት በራፍ ተጠልለን ። ቤቱ በጣም ትልቅ ነው ። እንዴት ግንባሯ ላይ ጨሌ ያሠረች ጠይም ወጣት በር ላይ ቆማለች ፤ ስሟ ሐጀራ አሊ ይባላል ። ባለቤቶች አሉ ወይ ስንላት አዎ አሉ አለችን ። ወደቤት ገባን ። አብራን ገባችና ሳሎኑ መሐል ቆመች ። ሳሎኑ ሰፊ ነው ። በሳሎኑ መሐል ባለው ሰፊ መደብ ሰፋፊ ነት ተነጥፏል ። የቤቱ ግድግዳዎች በሙላ በአዳዲስ የስፌት ዕቃዎች ተጊያጌጠዋል ። ሁኔታው ስላጠራጠረን ያንቺ ቤት ነው ወይ ? ስንላት አዎን አለቺን ። መቼ ገባሽ ስንላት መንደሩ ገና እንደተሠራ አግብቼ መጣሁ አለች ። ገና ትዳር ስትጀምሪ በመንደር በመኖርሽ ምን ይሰማሻል ? በሠርጌ ዕለት መንደርተኛው ሁሉ ወጥቶ እየዘፈነ ፣ እያጨበጨበና በእልልታ አጅቦ ስላስገባን የኔ ሠርግ ከማንም የደመቀ ነበር ። ስለዚህ በጣም ወድጄዋለሁ አለች ። ከዚያች የ18 ዓመት ወጣት አንደበት የወጣ ንጹሕ አገላለጽ ነው ።

የገጠሩ ሕዝብ በመንደር መሰባሰብ በኢኮኖሚውና በማኅበራዊ ግልጋሎቶች ረገድ



በጭቃ ጡብም ቤቶች ይሠራሉ ።



Digitized by Google

ከሚሰጠው ጥቅም ያላነሰ በማኅበራዊ ደኅንነት በኩልም አስተዋጽኦ እንዳለው የተሠወረ አይደለም ። ሕዝቡ ተበታትኖ ይኖር በነበረበት ጊዜ እንኳንስ እንደአስ ፈላጊነቱ ለጋራ ጥቅም በወል መሠማራት ይቅርና እርስ በርሱ በውል ለመተዋወቅ ሁኔታው አመች አልነበረም ። በተለይ በኅብረተሰቡ ውስጥ የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበቱ አረጋውያን ገንቢ ልምዳቸውን ለማካፈልና በሌላም መልክ ጠቃሚ የኅብ ረተሰቡ አባል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቀርቶ ዕድለኞች ካልሆኑ በስተቀር ለብቸ ኝነት የሚዳርጉ ነበሩ ። ይህ የሚያስከት ለው ጭንቀት ቀላል አይደለም ። ሰው ማኅ በራዊ ነው ። በመሆኑም ከሰዎች ጋር መሥ ራትና መኖር ፣ ሐሳብ መለዋወጥ ያስፈልጋል ። አንድ ችግር ቢደርስበት ሰዎች ሊደ ርሱለት ይጠብቃል ። በተለይ የዕድሜ ማነስ ሲኖር ሁኔታው ይበልጥ አሳ ሳቢ ይሆናል ።

አቶ መሚ ፈጀራ የተባሉ የ80 ዓመት ... ደህና ገልጸውታል ። በጉርሱም ... ፣ በባቢሌ ወረዳ የቢይቱላ ቀበሌ ገ/ ማኅበር ነዋሪ ናቸው ። እዚችው መን ደር ተወልደው ብዙ ያዩ ናቸው ። አሥራ ሁለት ልጆች ወልደው ስምንቱ በሕይ ወት አሉ ። ከነዚህ መካከል ሁለቱ አሁን ትምህርት ቤት ገብተዋል ። በመንደር በመሰባሰብዎ ምን ይሰማዎታል ? ብለን ስንጠይቃቸው እኔ መንደሩን ሲሠሩ ታምሜ እንቅስቃሴውንም እምብዛም አላጤንኩ ትም ። ድኜ ስነሣ ሌላ አገር የወሰዱኝ መሰለኝ ። ይህ የምታዩት ሜዳ ቁጥቋጠ ነበር ። ዓቅም ስለሌለኝ ርቄ አልሄድም ፤ ከብዙ ዘመዶቼ ተራርቄ ነበር ። ዛሬ ይኸው አንድ ላይ ሆነን እያንዳንዱ ቤት ሐዘን ሲኖር ፣ ሰው ሲታመም እኔ እንኳን በደ ካማ ዓቅሜ እደርሳለሁ ። በፊት እሰጋ ነበር ። አሁን በሰው መሐል ስለሆንኩ እፎይ ብዬ እንደልቤ እተኛለሁ ። እዚሁ ከጉድጓድ ወጥቶ ንጹሕ ውሃ እንጠጣለን ፤ የሚቻል ቢሆን ልጅነት በገዛሁ አሉ ።

ሌላ ያነጋገርነው ወ/ሮ ሀቢባ አብዱላ ሂ ነበር ። ሀቢባ አብዱላሂ ከሐረር ባቢሌ መንገድ ላይ የሚገኘው የሐረር ጉዳ ገበሬ መንደር ነዋሪ ናቸው ። መንደሩ የሚገኘው ሸረፍ ... በሚባል መለስተኛ ተራራ ሥር ነው ። ቤቶቹ በጥላ የተከደ ኑት ስንዳር በሚባል ረጃጅምና ሰፋፊ ቅጠል ነው ። መንደሩ ከሩቅ ሲታይ በረ ድፍ የተነጠፈ የማሽላ አገዳ ይመስላል። ጠጋ እያሉ ሲሄዱ ነው የቤትነቱ ቅርጽ ተለይቶ የሚታየው ። ወደ መንደሩ ጉራ ስንል አንደኛው ቤት በራፍ ላይ አንድ አጭር ፣ ሽበት ጣል ጣል ያደረገባቸው ፊታቸው ከስተር ያለ ሴትዮ ተቀምጠ ዋል ። እንደተለመደው ጠጋ አልንና ሰላ ምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስማቸውን ጠየ ቅን ። ወ/ሮ ሀቢባ እዚያው አካባቢ ተወ ልደው ያደጉ ናቸው ።ባለቤታቸው ሞተው አንድ ልጃቸውን ራሳቸው እያለፉ ነው ያሳደጉት ። ዛሬ ልጃቸው አሥራ አራት ዓመት ሞልቶታል ። እኛ ስንደርስ እቤት አልነበረም ። እርሻ ሄዷል ። ስለአካባቢው ሁኔታ ስንወያይ በመሐሉ ስለመንደር ተነሣ ። እንዴት ነው ብለን ጠየቅናቸው ። ቤቴ የነበረው ከሸረፍ ባቦ ጥግ በወዲያ ኛው በኩል ነበር አሉና በእጃቸው አቅ ጣጫውን አሳዩን ። ይኸ አሁን ቤት ያለ በት ቦታ ሁሉ እንደዚህ አልነበረም ። በመኪና ተመንጥሮ ነው እንዲህ መልክ የያዘው ። ልጄን ለማሳደግ በየቦታው እየ ዞርኩ መገበያየት ነበረብኝ ። ከገበያ ስመ ለስ በተለይ መሸት ሲል ይህን ቁጥቋጠ አልፌ መሄድ ቀላል አልነበረም ። በዚህ ላይ አካባቢው አንበሳ አለው ።ዛሬ ለሥራ ስንሄድ ቤታችን እንኳን ጠባቂ አያስፈ ልገውም ። በመንደሩ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ካሉ የሁሉም ቤት ይታያል አሉን።

በሦስቱ ክፍላተ ሀገር የገጠር ነዋሪዎች በመንደር እንዲሰባሰቡ ያስፈለገበትን ምክንያትና ከዚሁ አኳያ እስካሁን የተገኙ አንዳንድ ጥቅሞችን ለመጠቃቀስ ተሞክ ሯል ። ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች



Digitized by Google

አጠቃላይና በሌሎችም አካባቢዎች ከምላ
ጉደል የሚሠሩ ሲሆኑ ፤ በነዚህ አካባቢ
ዎች ለየት ብሎ የሚታየው ሌላው የፀ
ጥታ ጉዳይ ነው ። እንደሚታወቀው ከብዙ
ዓመታት ጀምሮ «ታላቋ ሶማሊያን» የመ
መሥረት ከንቱ ምኞት የተጠናወተው
የሶማሊያ መንግሥት ዋና የጥቃት ዒላማ
በተለይ ሐረርጌና ባሌ ናቸው ። በነዚህ ክፍ
ላተ ሀገር በኩል አንዳንዴ ሰርጎ ገቦችን
በማስገባት በሌላ ጊዜ ደግሞ በቀጥታ በመ
ውረር ብዙ ጥፋት አድርሷል ። በተለይ
አብዮታችን እንደተቀጣጠለ አጋጣሚውን
መጠቀሚያ በማድረግ በከፈተብን ጦር
ነት በምሥራቅና በደቡብ የአገራችን
ክፍል ለጊዜውም ቢሆን አንዳንድ አካባ
ቢዎችን በቁጥጥር ሥር እስከማድረግ
ደርሶ እንደነበር ይታወሳል ። በወቅቱ
የአካባቢው ሕዝብ የንቃትና የድርጅት
ዓቅሙ ዝቅተኛ በመሆኑ ጠላት እንደ
ልብ ለማወናበድ ጥሩ አጋጣሚ ነበረው።
በዚህ ላይ የሕዝቡ ተበታትኖ መገኘት
በተናጠል ለማጥቃትና ለመከፋፈልም ረድ
ቶታል ። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አካባቢ
ሕዝቡ ተራ በተራ ከሚጨርሱን ባለ ዓቅ
ማችን ሰብሰብ ብለን እየተዋጋን እን
ሙት በማለት በራሱ አነሣሽነት በአመቺ
ቦታዎችና አነስተኛ የገጠር ከተሞች አካ
ባቢ ተሰባስቦ መከላከል ጀመረ ። ሕዝቡ
በዚህ መልክ ተሰባስቦ የተከላከለባቸው
አካባቢዎች ከጠላት ጉዳት ቢደርስባቸ
ውም ጠላት እጅ ሳይወድቁ ሊቆዩ ችለ
ዋል ። በተለይ በመንደር ምሥረታው
ሥራ አንጋፋ በሆነችው በባሌ ክፍለ ሀገር
በዚህ መልክ የተሰባሰቡ መንደሮች በር
ካታ ናቸው ።

በተለይ ከፍተኛ የጠላት ጥቃት ከደረሰ
ባቸው አውራጃዎች አንዱ በሆነችው
በዋቤ አውራጃ በጊኒር ወረዳ አቃቂ ፣
ኤቢሳ ፣ ለቦሚ ፣ ቀበና የተባሉ መንደሮች
በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው ።
ሁኔታዎችን በማስመልከት የኤቢሳ ገበሬ
መንደር ሊቀ መንበር የሆኑት ጓድ ቱሉ
ማን ጠይብ የሚከተለውን አጫውተው
ናል።«ይህ መንደር የተመሠረተው በ1969
ነው ። በወቅቱ አካባቢው ሁሉ በጠ
ላት ስለተያዘ ሕዝቡ ተሰዶ እዚህ ሜዳ
ላይ ቤት እየሠራ ተሰባሰበ ። ዙሪያውን
ምሽግ ቆፍረን ባለን መሣሪያ ጠላትን መከ
ላከል ጀመርን ። ብዙ ጊዜ ጠላት ሙከራ
ቢያደርግም ሊገባ አልቻለም ። አንድ ጊዜ
ግን በጣም ተጠናክሮ መጥቶ መንደሩን
በከፊል አቃጠለብን ፤ ወደ ሰባት ሰዎች
በውጊያው ሞቱ ። ከሞቱት መካከል የሕ
ዝባዊ ሠራዊት አዛዥ ሻምበል ይገኙ
በታል ። መጠነኛ ከብቶች ተዘርፈውብ
ናል ፣ ጥቂት ቤቶችም ተቃጥለውብናል ፣
መንደራችን ግን አልተያዘችም ።

«በአብዮታችን ታሪክ ውስጥ የመንደር
ምሥረታ አነሣሥ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው
ማለት ይቻላል ። በዚህ መልክ በተለያየ
አካባቢ የተሰባሰበው ገበሬ ጦርነቱ እንዳ
በቃና ጠላት እንደወጣ ወደ ቀድሞ መን
ደሩ ለመሄድ መፈለጉ አልቀረም ። ግን
በወቅቱ ሌላ ችግርም ነበር ። በ1971 በደ
ቡብ ክፍላተ ሀገር በደረሰው ድርቅና በተ
ለይ በጠላት ቤቱ ተቃጥሎ ሀብቱ ተዘ
ርፎ በዱር በገደሉ የቆየው ሕዝብ ሲመ
ለስ ከፍተኛ ርዳታ ያስፈልግ ነበር ። ጠላ
ትም ቢሆን በመደበኛው ጦርነት ተሸ
ንፎ ይውጣ እንጂ ያሠለጠናቸውን ሰርጎ
ገቦች ትቶ ስለሄደ የፀጥታውም ሁኔታ
ቢሆን አስተማማኝ አልነበረም ። ስለዚህ
በማናቸውም ረገድ ለሕዝቡ የሚያስፈል
ገውን ርዳታ ለማቅረብ ካለው አመቺነት
አኳያ ገበሬው እንደቀድሞው ተበታትኖ
መኖሩ ቀርቶ አመቺ የሆኑ አካባቢዎች እየ
ተመረጡ በመንደር እንዲሰባሰብ ተደረገ።
ገበሬው ጥቅሙን ተረድቶ እንዲያከናው
ነው የተደረገ በመሆኑም ውጤቱ ሊሠ
ምር ችሏል ።

በዚህ መልክ የተሰባሰበው ገበሬ ዛሬ
በየፈርጁ የልማት ሥራውን በአስተማማኝ
ለማካሄድ ከመቻሉም ሌላ ፣ ራሱንና አካባ
ቢውን ለመጠበቅ ከምንጊዜውም በተሻለ



Digitized by Google

ሳሙናንም በጋራ ጥረት ወደማምረት

ሁኔታ ላይ ይገኛል ። በትጥቅ ደረጃም ቢሆን በተለይ የአብዮቱን ዓላማ እየተገነዘቡ እጃቸውን የሰጡ ይዘው የገቡትና መንግሥትም ያስታጠቃቸው ራሳቸውን ለመከላከል በበቂ ደረጃ ላይ እንዲገኙ ረድቷቸዋል ። የአካባቢ የፓርቲ ፣ የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶች አካላት እንደሚሉት መንደር እፎይታ አስገኝቷል ። በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በጋራ ሙለታ አውራጃ እጃቸውን እየሰጡ የገቡ እንዳሉት በወንበዴ ላይ ከባድ መድፍ የተተኮሰው በመንደር ምሥረታ ነው ። ከመንደር ምሥረታ መጀመር ጋር የእኛ ትኩስ መብላት እያከተመ መጣ ሲል አንዱ ወንበዴ የነበረም ገልጾታል ። በዚህ ምክንያት ነው በዚህ አካባቢ መንደር ምሥረታ ሲታቀድ ፀረ መንደር ቅስቀሳ በማድረግና ሲመሠረትም ቤቶች እስከማቃጠል በመድረስ ፀረ አብዮት ኃይላት የተረባረቡት።

መንደር ያስገኘው ጠቀሜታ ይኸ ብቻ አይደለም ። በተለይ በሐረርጌና በአርሲ የመንደር ምሥረታው አዲስ በመሆኑና ከሌላ አካባቢ ልምድ የተገኘበትም ከመሆኑ ሌላ የቅርብ የፓርቲ አመራር ይሰጠዋል ። እያንዳንዱ አካባቢ ለጓዶች በኃላፊነት እየተከለለ ተሰጥቷል ። በዚህ የተነሣ ከክፍለ ሀገር እስከ ወረዳ ያሉ የፓርቲ ካድሬዎች የራሳቸውን ክልል ሥራ በቅርብ ይከታተላሉ ። ከገበሬው ጋር አብረው ውለው በማደር ያስተባብራሉ ። በዚህም ምክንያት መንደር እኛን ገበሬዎችን ብቻ ሳይሆን ከባለሥልጣኖችም ጋር ይበልጥ አንድ አድርጎናል ይላሉ አንዳንድ ገበሬዎች ። በእርግጥ የካድሬዎች በገበሬው መሐል ዘልቆ መግባትና አብሮ መሥራት በሕዝቡ ዘንድ የፓርቲውን ተቀባይነት ከፍ አድርጎታል ። አንድ የገበሬ መንደር በጣም አስቸጋሪ በሆነ አካባቢ በራሱ ጉልበት የመኪና መንገድ በማስገባቱ አንድ ጓድ እንዲህ መሥራት እየቻላችሁ ለምን እስካሁን ቸል አላችሁ ብሎ አንዱን ገበሬ ቢጠይቀው ገበሬው መለሰና እመካከላችን ገብታችሁ ካስተባበራ

ቾሁን ምን ያትተናል ። እናንተ ሳትመጡ ቀያችሁ እንጂ ይኼኔ ምን ያህል በተራ መድን ነበር አለ ።

ገበሬውን ለልማትና ለዕድገቱ ለማስተባበር አመቺ ሁኔታ ለመፈጠሩ አንድ ሌላ ማስረጃ በመካሄድ ላይ ያለው የሕዲሪኢ ምሥረታ ነው ። ገበሬው በመንደር በተሰባሰበባቸው አካባቢዎች በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ለውይይት ማደራጀት በጣም ቀላል ነበር ። ጊዜና ጉልበት አልባከነም ። ሁሉም በደጁ የመብቱ ሙሉ ተጠቃሚ ለመሆን ችሏል ። ቀድሞ ለአንድ ጉዳይ ለመሰባሰብ ከጉዳዩ ይልቅ ብዙውን ጊዜ አስቸጋሪው ተበታትኖ የሚኖረውን ገበሬ ጥሪው እንዲደርሰውና እንዲሰባሰብ ማድረጉ ነበር ። ዛሬ ይህ ችግር ተወግዷል ። በተቆጠበ ጊዜ ብዙ ቁምነገሮችን ለመፈጸም ተችሏል ።

## የመንደሮች አመሠራረት እንዴት ?

መንደርን ለመንደርነቱ ብቻ በመውሰድ መተቸት እንደየተቸው አመለካከትና አቋም ሐሳብ (ጭብጥ የሌለው ሐሳብ)ከመሰንዘር ባሻገር ከዚህ የሚመነጨው እውነት እጅግ የተመጠነ ነው ። እንዲህ ዓይነቱ ሀገር ላይ በጅቷል ፤ የለም እንዲህ ዓይነቱ ላይ ደግሞ አልበጀም ማለቱም ብቻውን ብዙም እኛ ላለንበት እውነታ አያቀርብም ። እርግጥ አንዳንድ አጠቃላይ እውነታዎች በተለያዩ ቦታዎችም ቢሆን ከተግባር ተመሳሳይነታቸውን ማረጋገጥ አይቻልም ማለት አይደለም ። ሆኖም የጊዜን፣ የሥፍራንና የሁኔታን ልዩ ባሕርያት ባለመቀበል በበጐም ሆነ በክፉ ጥቅል አቋም መውሰድ ትክክል አይሆንም ።

የመንደር ምሥረታ በሀገራችን የተጀመረው የሕዝባዊ አብዮታችን ዓላማ ተገራፊዎች ሲያውኩና ድንገተኛ አድርገው ለማቅረብ እንደሞከሩት አሁን አይደለም። በመሠረቱ መንደር ለሕዝባችን እንግዳ አይደለም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ በታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ የሰው ልጅ አንዱ የአኗኗር ባሕርይ ነው ። ለየት ያለ ነገር ቢኖር በዚህ ረገድ በፓርቲያችን አመራር የተቀነባበረ ጥረት ማድረጋችን ነው። ለዚያውም ገበሬው በመንደር መሰባሰቡ ለመጭው የልማት ጥረታችን መሳካት አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልናል እንጂ በራሱ ግባችን አይደለም ። ትኩረታችን ከዚያ በኋላ መቀጠል ያለበት ሥራ ላይ ነው ። እውነተኛ ፍርድም መስጠት የሚቻለውም ያኔ ነው ።

ጠለቅ ተብሎ ሲታይ ተቺዎቻችንን እንደየማንነታቸው ያሳሰባቸው ልዩ ልዩ ምክንያት ቢኖርም ፣ የጋራዎቹ ሥጋት ገጠሩ ለሶሻሊዝም መመቻቸቱ ነው ። በእርግጥ አልተሳሳቱም ። ይህን ፓርቲያችንና አብዮታዊው መንግሥት በፕሮግራምና በዕቅድ በግልጽ ያመለከቱት ጉዳይ ነው ።

ለማንኛውም ትግሉ በመንደር ምሥረታው የሚወሰን ሳይሆን ፣ ከዚያ ባሻገር መንደርን ለፍሬ ማብቃቱ ላይ ነውና በተጠናከረ መልክ ፣ በዕቅድና በብልሃት መቀጠል ይኖርበታል ። በሐረርጌ ፣ በባሌና በአርሲ ምሥረታው የተገባደደና በሌሎች አንዳንድ ክፍላተ ሀገርም ያላነሰ ርምጃ የሚታይ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማጠናቀቅ ጊዜ የሚጠይቅ ነው ። ያልጀመሩ ክፍላተ ሀገር መኖራቸውም መዘንጋት የለበትም ። በእርግጥ በሁሉም ቦታ በአንድ ጊዜ የግድ መጀመርና መጠናቀቅ ያለበትም አይደለም ። እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ከአጠቃላዩ መመሪያና ከራሱ ልዩ ባሕርይ በመነሣት መቼ መጀመር ፣ እንዴት መራመድና ለግብ መብቃት እንዳለበት በጥልቀት አስተውሎ የማቀድ ኃላፊነት አለበት ። የሦስቱ ክፍላተ ሀገር ልምድም የሚያሳየን ይህንኑ ነው ። እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የጀመረው በተለያየ ወቅት ሲሆን ፣ በራሱ በአንድ ክፍለ ሀገር ውስጥም ቢሆን በሁሉም አካባቢ በአንዴ አልተጀመረም ። በሌሎቹም ክፍላተ ሀገር



Digitized by Google

በብሔራዊ የመንደር ምሥረታ መመሪያ መሠረት ስልቱ የተለየ ሊሆን አይችልም ።

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው የገበሬው በመንደር መሰባሰብ ሥራ በቅድሚያ የተጀመረው በባሌ ክፍለ ሀገር ነው ። በአሁኑ ወቅት በክፍለ ሀገሩ በ 562 መንደሮች 789,891 ሕዝብ ይኖራል ። በባሌ የገጠሩ ሕዝብ ቁጥሩ 929,284 ሲሆን ፣ በመንደር የተሰባሰበው 85% ነው ። በጦርነት ሚገሥት በክፍለ ሀገሩ ሕዝቡን በመንደር ለማሰባሰብ ቀደም ተብሎ የታሰበ ባለመሆኑ በጥናት የተደገፈ አሠራር አልነበረም ። ችግሩን ለመወጣት እንዲምል እመች የመሰለ ቦታ እየተመረጠ ሕዝቡ እንዲሰባሰብ ተደረገ ። ስለአሰፋፈሩም ሆነ ለአንድ ሰው መሰጠት ስለሚገባው ክልል ፣ በአንድ መንደር በአማካይ ሊኖር ስለሚገባው የነዋሪ ብዛት ወዘተ. የወጣ መመሪያ አልነበረም ። አብዛኛዎቹ መንደሮች ከ 300 እስከ 500 ቤቶች ሲኖራቸው በአንዳንድ መንደሮች የቤቱ ቁጥር 1000 ይደርሳል ። የቤቶቹ ቁጥር ሲበዛ ኗሪው ይበዛል ። እያንዳንዱ ቤተሰብ የሚኖረው የእርሻ መሬትም ከአካባቢው ይርቃል ። በተለይ በባሌ ነዋሪው በርካታ ከብቶች ስላሉት ብዙ ሰው በአንድ መንደር ሲኖር የግጦሽ አካባቢም ያንኑ ያህል ይርቃል ። ከእነዚህ የባሌ መንደር ምሥረታ ቀደምት ልምዶች ለመማር ተችሏል ። በባሌም ቢሆን አልፎ አልፎ የታየ እንጂ አጠቃላይ ችግር አልነበረም ። ልምዱ እዚያው ክፍለ ሀገር ውስጥ በቅርብ ለተቋቋሙት መንደሮች በጣም ረድቷል ።

በ1971 በመጋቢት ወር በወሎ ክፍለ ሀገር በደረሰው ድርቅ ሳቢያ 7,316 አባወራዎች ወደ ባሌ ሄደው ሁሉም መልካ እዳ በሚባለው ሥፍራ ላይ ለጊዜው እንዲያርፉ ተደረገ ። በዚያው ዓመት መጨረሻ ወደ ሀረዋ መዛወር ጀመሩ ። ሀረዋ ላይ ሲሰፍሩ አሁንም የርዳታ ማስተባበርያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ልምድና ዓቅም በቂ ስላልነበረ ተሉ ውጤት ለማየት አልተቻለም ። በ1977 ግን የተፈጥሮ ችግር መቋቋሚያ ኮሚቴ በሰጠው አመራር መሠረት የፓርቲ አካላትና መንግሥታዊ ድርጅቶች ተረባርበውበት ሥራው በአራት ወር ተጠናቀቀ ። ዛሬ የሀረዋ መንደሮች ለዓይነት የሚታዩ ናቸው ። ይህ የልምድና የጥናት ውጤት ነው ።

በሐረርጌና በአርሲ ገበሬውን በመንደር ማሰባሰብ አስፈላጊ ያደረጉት ምክንያቶች በአብዛኛው ቀደም ሲል ስለመንደር ጠቀሜታ በገለጽናቸው ነጥቦች ተወስተዋል። የክንውኑም ጊዜ ይለያያል ። የዚያን ያህል ከራሳቸው አካባቢም ሆነ ከባሌ ልምድ ለመቅሰምና ዝግጅት ለማድረግ ጊዜ ነበራቸው ። አርሲ ክፍለ ሀገር በጭላሉ አውራጃ በገደብ አሳሳ ወረዳና በጢቾ አውራጃ በአሚኛ ወረዳ የመንግሥት እርሻዎች ሲቋቋሙ የአካባቢውም ሕዝብ በአገባቡ ሰፍሮ የምርት ተግባሩን እንዲያካሂድ በመጀመሪያ በዕግግኮ በ1972 ተመሥርተው ፣ በኋላ በ« ዋቢ ፕሮጀክት » አማካይነት በ1973 የተጠናከሩ መንደሮች ለእንግሙጥሩ የጥናት መሠረት ሆነዋል ። በሐረርጌም በመጀመሪያ መደበኛ የገበሬ መንደር የተመሠረተው በወበራ አውራጃ ከደደር 70 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ በመልካ በሉ ወረዳ ነው። በዚህ ወረዳ ወንበዴዎች ችግር ይፈጥሩ ስለነበረ 10,000 ሰዎችን በ3 መንደሮች የማሰባሰቡ ሥራ ድሬ ቁሩ ፣ በሬዳና ሸዋበር በሚባሉ ቦታዎች በሐምሌ ወር 75 ተጀምሮ በጥር ወር 76 ተጠናቀቀ ። የዚህ መንደር አሠራርና ልምድ ለመነሻነት አገልግሏል ።

በሐረርጌ ሕዝቡን በመንደር የማሰባሰቡ ጥያቄ ለብዙ ጊዜ ሲነግ ቆይቶ በመጨረሻ የክፍለ ሀገሩ ኢሠፓ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ገበሬውን በቶጠኑ መንደሮች የማሰባሰቡ እንቅስቃሴ እንዲጀመር ታኅሣሥ 23 ቀን 1977 ባደረገው ስብሰባ ውሳኔ አሳለፈ ። በውሳኔው ላይ ተመርኩዞ ልዩ ልዩ ጥናቶች ፣ ለምሳሌ የቀድሞ የሐረርጌ ገበሬ



Digitized by Google

አኗኗር ፣ የሐረርጌ ሕዝብ አሁን ያለ
በት ከተጠና በኋላ የመንደር ምሥረታው
ስልት ተቀየሰ ። በዚህም መሠረት በስ
ምንቱ ዶጋማ አውራጃዎች የሚገኘውን
ገበሬ በራሱ ፈቃደኝነት በተመረጡና
በተጠኑ መንደሮች ለማሰባሰብ ዝርዝር
መመሪያ ማዘጋጀት ተጀመረ ። የክፍለ
ሀገሩ ፓርቲ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ አባላ
ትም አውራጃዎችን በቀጣና ተከፋፍለው
የማስተባበር ሥምሪት በማድረግ የመን
ደር ምሥረታው በፓርቲ አካላት ሙሉ
አመራርና የማስተባበር ተሳትፎ ሥር እን
ዲውል ተደረገ ። ከቦታ አመራረጥ ጀምሮ
የመንደር ፕላንና የቤት አሠራርን ያጣ
መረ መመሪያ ተዘጋጅቶ በ18/ 5/ 77
ለየአውራጃዎቹ ተሰራጨ ። መመሪያው
እንደተሠራጨም የክፍለ ሀገሩ ኢሠፓ
ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ራሱን በአውራጃ
ቀጣናዎች በመደልደል በመመሪያዎች
ላይ ማብራሪያ ሰጠ ። ይህንኑ በመከተል
የአውራጃና የወረዳ ፓርቲ ኮሚቴዎችም
ገበሬ ማኅበራትን በቀጣና በመከፋፈል
እስከ መንደር ለቅስቀሳ ሥራ ተሠማሩ።
የቅስቀሳው ሥራ ከተከናወነ በኋላ ቦታ
ዎች ተመርጠው የቅየሳውና የግንባታው
ሥራ በየካቲት ወር 77 ተጀመረ ። የአን
ደኛው ዙር መንደር ምሥረታ ሥራ
መጋቢት 30 ቀን 1977 ተጠናቀቀ ።
በዚህ ወቅት በ6 አውራጃዎች በ23 ወረ
ዳዎች ፣ በ312 ገበሬ ማኅበራት 9002
ነባር መንደሮች በ2365 አዲስ መንደሮች
ተሰባሰቡ ። 182,000 ቤቶች ተሠርተው
815,277 ሕዝብ በአዲስ መንደር መኖር
ጀመረ ። በመጀመሪያው ዙር ያለውን
የሥራ ሂደት ለመከታተልና ችግሮችን
አጥንቶ ለመፍታት በየደረጃው ሁለት ጊዜ
የቡድን ግምገማ ሥምሪት ተደርጓል ።

ከነዚህ የግምገማ ሥምሪቶችና ጓድ መን
ግሥቱ ኃይለ ማርያም ክፍለ ሀገሩን በጐ
በኙ ጊዜ ከሰጡት ማበረታቻና አብዮታዊ
አመራር ፣ እንዲሁም የኢ.ሠ.ፓ ማዕከላዊ
ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ባሳለፈው
ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ በክፍለ ሀገር ደረጃ
ነሐሴ 23 ቀን 77 የአንድ ቀን ሴሚናር
ተሰጠ ። በዚህ ሴሚናር የመንደር ምሥ
ረታው ባልተጀመረባቸውና ተጀምሮባቸ
ውም በከፊል ባልተጠናቀቀባቸው አው
ራጃዎች የመንደር ምሥረታው ሂደት
የእርሻ ሥራን በማይሻማ መልኩ ተጀ
ምሮ የካቲት 30/78 ለማጠናቀቅ ጥረት
እንዲደረግ ውሳኔ ተላለፈ ። በዚህ መሠ
ረት ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ በመካ
ሄድ በቤት አሠራርም ሆነ በመንደር
ፕላን በሁለተኛው ዙር የተሠሩት ከአን
ደኛው ዙር የተሻሉ መሆናቸው በአካባ
ቢው ይነገራል ። በሁለተኛው ዙር የሕ
ዝቡም ሥነ ልቦና በተሻለ ሁኔታ የተዘ
ጋጀ በመሆኑ የአሠራር ቅልጥፍናም ሊገኝ
ተችሏል ። በአጠቃላይ በሐረርጌ በ8
አውራጃዎች ፣ በ31 ወረዳዎች ፣ በ1265
ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት 3427 መንደሮች
ተመሥርተው 1,654,224 ሕዝብ በአሁኑ
ወቅት በአዲስ መንደሮች ይኖራል ።

በአርሲ ክፍለ ሀገር ለመንደር ምሥረ
ታው የተደረገው ዝግጅት ደግሞ ጠንከር
ያለ ነው ። በዚህም መሠረት ፣

1ኛ/ በዋቤ ፕሮጀክት የተሠሩ መንደ
ሮች ላይ በወቅቱ በተከሰቱትን ችግ
ሮችና አሁን መንደሮቹ የደረሱበ
ትን የዕድገት ሁኔታ በማጥናት ፣

2ኛ/ በ1975 በአርባ ጉጉ አውራጃ በጐ
ሎልቻ ወረዳ ከተመሠረቱ አም
ስት መንደሮች ልምድ በመነሣት ፣

3ኛ/ አንድ ከፍተኛ የክፍለ ሀገሩ ቡድን
በሐረርጌ ፣ በሸዋና በባሌ የጥናት
ጉብኝት በማድረግ የተለያዩ ልምዶ
ችን ለመቅሰም ችሏል ።

ከነዚህ ልምዶች በመነሣት ለመንደር
ምሥረታው ዕቅድ የሚያወጣና አፈጻጸ
ሙን የሚከታተል ሁሉንም የፓርቲ ፣
የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶችን ያካ
ተተ አንድ የመንደር ምሥረታ ኮሚቴ በክ
ፍለ ሀገር ደረጃ ተቋቋመ ።



Digitized by Google

ክፍለ ሀገሩ ለአሠራር እንዲያመች በአ
ራት ዞን ተከፍሎ ይኸው የኮሚቴ አወቃ
ቀር እስከ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ድረስ ተዘ
ረጋ ። ከዚያ በኋላ አጠቃላይ የክፍለ ሀገሩ
ማኅበረ ኢኮኖሚ ጥናት ተጀመረ ። ይህ
ጥናት የክፍለ ሀገሩን የመሬት ስፋትና
አቀማመጥ ፥ የሕዝቡን ብዛት በዕድሜና
በጾታ ፥ በአካባቢው የሚገኙ እንስሳትን
ዓይነትና ብዛት ፥ የአየር ጠባይ ፥ በአጠቃ
ላይ በአካባቢው ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፥
ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ያጠቃለለ
ነበር ።

ከዚህ በመነሣት መንደር ሊመሠረትባ
ቸው የሚችሉና የማይችሉ አካባቢዎች
ተለይተው የክፍለ ሀገሩ የመንደር ምሥ
ረታ ካርታ ተሠራ ። ሕዝቡን በመንደር
ለማሰባሰብ የሚቻልባቸው ቦታዎች ከታ
ወቁ በኋላ መንደሩ የሚመሠረትባቸው
ሥፍራዎች በቀበሌ የመንደር ምሥረታ
ኮሚቴ ተመርጠው ለወረዳ ከዚያም ለክ
ፍለ ሀገር ተላለፉ ። ከዚህ በመነሣት የመ
ንደር ምሥረታው ከነውንም ቅድሚያ
ሊሰጣቸው የሚገቡ ቦታዎች ተለይተው
ታወቁ ። ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ
አካባቢዎችን በመለየት ፥ የእህል አሰባሰ
ብንም ወቅት በማገናዘብ በቆላማው አካ
ባቢ ከታኅሣሥ 1 እስከ ጥር 30 ፥ በደጋው
ደግሞ ከጥር 1 እስከ የካቲት 30 መንደር
ምሥረታው እንዲከናወን ዕቅድ ወጣ ።
በዚህ ወቅት በ807 ቀበሌ ገበሬ ማኅበ
ራት 870 መንደር ለመመሥረት ታቅዶ
በ839 ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት 1009 መን
ደሮች ተመሠረቱ ። ለመሥራት የታቀ
ዱት ቤቶች 199,719 ሲሆኑ ፥ የተሠሩት
193,497 ናቸው ። የተሰባሰቡት የቀበሌ
ገበሬ ማኅበራትና የተሠሩት መንደሮች ከዕ
ቅድ በላይ ሆነው የተገኙት በመንደር
ማሰባሰብ ከተጀመረ በኋላ ገማሹም ለመ
ሰባሰብ በመፈለግ ፥ ሌሎቹም እናንተ የቀ
ራችሁት ሌላ ቦታ ሊወስዱአችሁ ነው
የሚል ቅስቀሳ በመጀመሩ በመስጋት ወደ
ኋላ አንቀርም በማለት በራሳቸው እየመጡ
ለመንደር ምሥረታ ኮሚቴ በማመልከታ
ቸው ከዕቅድ ውጭ መንደሮች በመሠራታ
ቸው ነው ። የቤቶች ቁጥር አንሶ የሚገ
ኘው አንዳንድ ቦታ በእናቲ እጥረት ያል
ፈረሱ ቆርቆር ቤቶች በመኖራቸው ሲሆን፥
ገማሹ ገበሬ በመንደር ከመሰባሰቡ በፊት
የነበሩት ትንንሽ ቤቶች ሁሉ ተቆጥረው
ስለነበርና ዛሬ እነሱን አሰባስቦ አንድ
ትልቅ ቤት በመሥራቱ ነው ።

በአርሲ ክፍለ ሀገር ከሌሎች ልምድ ለመ
ቅሰም የተደረገው ጥረት አሠራሩን በዕ
ቅድ ለመምራት የተሻለ ዕድል ሰጥቷል።
በክፍለ ሀገሩ የመንደር ምሥረታ ኮሚቴ
አማካይነት የሰው ኃይል ጥናትም በመ
ደረጉ በአንድ ገበሬ መንደር ምን ያህል
ሰው ለየትኛው የሥራ መስክ ቢሠማራ
በተወሰነው ጊዜ ሠርቶ ሊጨርስ እንደሚ
ችል ሁሉ የጊዜ ሰሌዳ ወጥቷል ። ለም
ሳሌ በጭላሎ አውራጃ በገደብ አሳሳ ወረዳ
የግመዳ ቱሌ ገበሬ ማኅበር ካለው የሥራ
ኃይል 20% ቤት ለመፍረስ ፥ 50% ለማ
ጓጓዝ 30% ለመሥራት የተጠቀሙበት
አመዳደብ ለወረዳው ዕቅድ ማስፈጸሚያ
ሆኖ አገልግሏል ።

በክፍለ ሀገሩ የተደረገው ዝግጅት ያስገ
ኘው አንዱ ጥሩ ልምድ የመረጃ (የሪኮርድ)
አያያዝ ነው ። ከክፍለ ሀገር እስከ ቀበሌ
ድረስ ባሉ የመንደር ምሥረታ ጽ/ቤቶች
የአካባቢው ካርታ ፥ በመንደር የተሰባሰ
በው ሕዝብ ብዛት፥የቤቶች ፥ ቁጥር ፥ የእንስ
ሳት ብዛት ፥ የኮሚቴ አወቃቀርና የአባ
ላት ስም ጭምር ተመዝግቦና በቻርት ተዘ
ጋጅቶ ይገኛል ።

በቤቶች አሠራርም ቢሆን በሐረርጌ ከአ
ንደኛው ዙር በሁለተኛው ፥ በአርሲም
ደረጃ በደረጃ የተሻለ ልምድ እየተገኘ
ሄዷል ። በሐረርጌ በመጀመሪያው ዙር
በተለይ ቆርቆር ቤቶችን በሚመለከት
ሥራ ላይ የዋለው ዘዴ አፍርሶ መውሰድ
ሲሆን ፤ ይህ ጊዜና ጉልበት ከማባከኑም
በላይ ቆርቆሮውን ስለሚበሳሳውና ግገ



Digitized by Google



ዘላኑንም ኅብረተሰብ በመንደር ምሥረታው ተሳትፎ እየጀመረ ነው

ሩም ስለሚሰበር እንዱን ክንፍ እንዳለ
ነቅሎ በመውሰድ ችግሩን ለማቃለል ተች
ሏል ። ከዚሁ በማገር በአርሲ ጣሪያ
ውን እንዳለ ተሸክሞ መውሰድ በመቻሉ
የበለጠ ችግሩ ሊወገድና ቅልጥፍና ሊኖረ
ውም ችሏል ። በእርግጥ ለዚህ የመሬቱ
አቀማመጥና የሚኬድበት መንገድ ሁኔ
ታም ይወስነዋል ። አርሲ ሜዳማና ደን
አልባ መሆኑ ጣራውን እንዳለ ለመውሰድ
አመች ነው ። በግር ቤት አከዳደንም ቢ
ሆን ብዙ ልምዶች ተገኝተዋል ። በጉርሱም
አውራጃ የመንደራቸውን ስም እስከመጻፍ
ሲደርሱ ፤ ባሌ ሀረዋ የተሠሩ መንደሮች
አከዳደን ደግሞ በከፍለ ሀገሩ ገበሬ ቀድሞ
ባልተለመደ ሁኔታ የተዋበ ነው ።

እስካሁን ማየት እንደሞከርነው እነዚህ
ሦስቱም ክፍላተ ሀገር መንደር ምሥረታ
የጀመሩት በአንዱና የየክፍለ ሀገሩን ክልል
በሞላ ባቀፈ መልክ አይደለም ። የመን
ደር ምሥረታው ኅላግ የገበሬውን ሕይ
ወት ለመቀየር መንደርደሪያ በመሆኑ እስ
ፈላጊ ወደአልሆነ ችግር ውስጥ ሊጥለው
አይገባም ። በመሆኑም ሁኔታው እየታየ ቅድ
ሚያ የሚሰጣቸው አካባቢዎች በቅድሚያ
እየተሰበሰቡ ከነሱ በማገር ሌሎችን ማሰ
ባሰብ መሞከሩ ጥሩ አማራጭ ነው ። የተ
ደረገውም ይኸው ነው ። በአንዳንዶቹ አካ
ባቢዎች በውሀ እጥረት ፣ ባለው ባህልና በመ
ሳሰለው ምክንያት ምሥረታው ጊዜ የሚጠ
ይቅ ነው ። ለምሳሌ በሐረርጌ፣በጅጅጋ አው
ራጃ መጠነኛ ዘላኖች ቤተሰባቸውን አንድ
ቦታ ትተው ከብቶችን ብቻ ይዘው እንዲዘዋ
ወሩ ለሙከራ በደሳ ቤት በመንደር እን
ዲሰባሰቡ ተደርጓል ። ከጅጅጋ ወደ ምሥ
ራቅ 20 ኪ· ሜ ገደማ የተመሠረተውን
ቃቡራሌ መንደር ተመልክተን ነበር ።
መንደሩ የተመሠረተው ቅልጥጥ ካለ ሜዳ
ላይ ሲሆን ፣ ወደ 70 ቤቶች አሉ ። በእር
ግጥ አካባቢውም ያው ስለሆነ አላስደነቀ
ንም ። የመጀመሪያ ጥያቄአችን ነፋሱን
እንዴት ይችሉታል ነበር ። በእርግጥ
አሁን ያሉበት ንፋስ ያስቸግራቸዋል ።



Digitized by Google

ተደም ሲል ግን በቤታቸው ዙሪያ እንደበ
ረትና እንደ አጥር ሆና የሚያገለግል የቁ
ልቋልና የታሜ ተክል አጥር ነበራቸው ።
ለአውሬ መከላከያ ቁጥቋጦም ያጥራሉ ። እነ
ዚህ እስከሚወጡ አዲሱ መንደር ማስ
ቸገሩ አይቀርም ። ኩበት በአካባቢው ስላ
ላየን ከብተቻቸሁ የት አሉ አልናቸው፤
በጋ ስለሆነ ሣርና ውሀ ወደሚገኝበት ወን
ዶች ይዘው ሄደዋል ። አሁን ግን ስለዘ
ነበ መመለሻቸው ነው አሉን ። ውሀ የሚ
ያገኙት ከኤላዎች (ጉርፍ ከሚጠራቀምባ
ቸው ጉድጓዶች) ነው ። በየመንገዱ ሸለቆ
ተከትለው የተሠሩ ጉድጓዶች አሉ ። በእ
ርግጥ በዚህ አካባቢ የተሠሩት ለሙከራ
ነው ። የዘላኑ ችግር ከሦስቱ ክፍላተሀገር
በተለይ የባሌና የሐረርጌ ነው ። ሙሉ
በሙሉ በከብት ርባታ የሚኖረውን ክፍል
ለማሰባሰብ በተቀነባበረ ጥናት ላይ የተ
መሠረተ ጠንካራ ጥረት ይጠይቃል ።

በሦስቱ ክፍላተ ሀገር እንደታየው የመ
ንደር ምሥረታው በሥራ ክፍፍል ተገባ
ርን በተቀላጠፈ መልክ ለማከናወን ተጨ
ማሪ ገፊት ፈጥሯል ። በሙያ ማስፋፋት
ረገድም አስተዋጽኦ አድርጓል ። ለምሳሌ
በአናኒ በኩል ብዙ መንደሮች የተጠቀ
ሙት በአካባቢው ያለውን ወጣት በማሠ
ልጠንና መማሪያ በመገዛት ነው ። በአብዛ
ኛዎቹ መንደሮች እንደተነገረን ቤት ማፍ
ረሱና መሥራቱ ዘዴንና ልምድን የሚጠ
ይቅ በመሆኑ በአብዛኛው የሚከናወነው
በአረጋውያን ነው ። የማጋዙን ሥራ ወጣ
ቶችና ሴቶች ያከናውናሉ ። በተለይ ሴቶች
ለሚሠራው ሕዝብ ምግብ ከማዘጋጀት ሌላ
ቤቱን በመምረግና ውስጡን በማዘጋጀት
ያከናወኑት ተግባር በቀላሉ የሚገመት አይ
ደለም ። በዚህ በኩል አንድ ምሳሌ መጥ
ቀስ ይቻላል ። ወ/ሮ አማኔ በሺር አርሲ
ክፍለ ሀገር ፣ በጭላሎ አውራጃ በዶዶታ
ወረዳ የአሚኛ ዳቦ መንደር አኢሴማ አመ
ራር አባል ናቸው ። በቀበሌው በኩል ሴቶ
ችን በማስተባበር ፣ በኑሮ ዘዴ ሠልጥነው
በማሠልጠን ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በሬን ለማጓጓዝም

Digitized by Google

ቤቱ በመንደር ምሥረታ ስላደረገው አስተዋጽኦ ሲናገሩ በመጀመሪያ ለሚሠራው ሕዝብ ምግብ ያዘጋጃል ። ከዚያም በአንድ ላይ ወግ በማጋዝ ጭቃ ያቦካና በየዕለቱ የሚሠሩትን ቤቶች በዚያኑ ዕለት መርጎ ያድራል አሉን ። ተዘዋውረን እንደተመለከትነው 249 አባወራዎች ሲኖሩ በመንደሩ ያለው የቤት ቁጥር 260 ነው ። 11 ቤቶች ለዓቅመ ደካሞች የተሠሩ ናቸው። በመንደሩ ቢያንስ ከውስጥ ያልተመረገ ቤት የለም ።

ታዳጊ ሕፃናት ሳይቀሩ ለመንደሩ ሥራ ድርሻቸውን አበርክተዋል ። አፈር በመደልደል ፣ የክዳን ግርችንና ዕቃ በማቀበል ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም ። በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በጉርሱም አውራጃ ፣ የቢይቱላ መንደር ታዳጊ ሕፃናት የሠሩት ሥራ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ። እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ከመፈጸም አልፎ የመንደሩ ቤቶች በሞላ የተሠሩበትን 15,000 ገመድ የገመዱት ታዳጊ ሕፃናት ናቸው ።

ቀያሾችንም በሚመለከት ኃይል የተገኘው ከየአካባቢው ነው ። በወረዳ ደረጃ ቀያሾች ተመድበው ከየቀበሌው ለተመረጡ ወጣቶች ትምህርት ተሰጣቸው ። የቻለ ሜትር ገዛ 1 ያልቻለ በገመድ በመጠቀም ቀጥ ያለ እንጨት ተቆርጦ ተላጦና አልፎ አልፎ ቀይ ቀለም ሲቀባ ጃሉ ሆነ ። በዚህ መልክ ቅየሳው ሲከናወን በወረዳው የተመደቡት ሁኔታውን እየተቆጣጠሩ ያስተካክላሉ ። በአርሲ በሄጦሳ ወረዳ ከኢተያ በስተምዕራብ የምትገኘዋን የኡላ ዳዌን መንደር ስንመለከት አንድ ጃሉና ሜትር የያዘ ሱልጣን ቡርቃ የተባለ ወጣት አገኘን ። ምንድነው ሥራህ ስንለው ሚሊሺያ ነበርኩኝ አለን ። በመጋቢት 1973 እጋዴን ውስጥ በጥይት ተመቶ ነው የተመለሰው ። ሱልጣን የጦር ጉዳተኛ በመሆኑ ማረስ ስለማይችል እርሻውን የሚያርሱለት ገበሬው ነው ። እሱ በጥበቃ ሥራ ያገለግላል ። በመንደር ምሥረታው ጊዜ በወረዳ ግብርና ሠልጥኖ ዛሬ የመንደሩ ዋና ቀያሽ ሆኖአል ። በቅየሳ ሥራ ብዙ መንደሮች በተማሩ ወጣት ነዋሪዎችና በመምህራን ተጠቅመዋል ።

በመንደር ሥራው የቁሳቁስ እጥረት እንደሚያጋጥም በመገንዘብ ፣ በተለይም የደን ሀብት እንዳይባክን የተቻለው ጥንቃቄ ተደርጓል ። በግር ቤቶች በኩል መፈክሩ «ቤት ሥራ እንጨት ግን አትቁረጥ »በመሆኑ 90% ያህል የተጠቀሙት በተድጦው ፍራሽ ነው።

በነዚህ ክፍላተ ሀገር ከታየው ልምድ መንደር ሲመሠረት ሊጤኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ የመሬት ጥበት ጉዳይ ነው ። ይህ በሐረርጌ በጉልህ ይታያል ። መንደር የተመሠረተው አብዛኛውን ደጋማ በሆኑ ስምንት አውራጃዎች ነው ። የሐረርጌ ክፍለ ሀገር የቆዳ ስፋትና የሕዝቡ ቁጥር ሲነፃፀር የመሬት ጥበት ጉዳይ የሚነገም አይመስልም ። ሆኖም ቆላማ አውራጃዎች አብዛኛውን ሰው ያልሠፈረባቸው ሜዳዎች ሲሆኑ ደጋማው ክፍል ግን እጅግ የተጨናነቀ ነው ። በመሆኑም የመንደር ምሥረታው የእርሻን ቦታ እንዳይሻማ ለማድረግ በአብዛኛው ለአንድ የግል ገበሬ የተሰጠው የግር ክልል 500 ካሬ ሜትርና ከዚያ በታች ነው ። 300 ካሬ ሜትር የተሰጠባቸው አካባቢዎችም አሉ ። እዚህ ላይ ይህን መጠቆም ያስፈለገበት ምክንያት ከመንደር ምሥረታው ጋር ችግሮችን በዘላቂነት ለማስወገድ አብሮ ትኩረት መስጠት ጠቃሚ መሆኑን ለማመልከት ነው ። የእርሻ መሬት እየተጣበበ መሄዱ ሊያጋጥም የሚችል በመሆኑ ከወዲሁ ተገቢ ስልት መቀየስ አስፈላጊ ነው ።

በእነዚህ ክፍላተ ሀገር እንደተረዳነው በገበሬው ውስጥ በመሥራት አዲያ ወላፉ የገበሬውን ሥነልቦና አስተዳጥ ማዘጋጀትና በተግባርም ሙሉ ተሳታፊ ማድረግ ነው ። በባሌ ክፍለ ሀገር ቀደም ሲል ጀምሮ ለመንደር ምሥረታ የተፈጠረውን እመች ሁኔታ ትተን የሁለቱን ክፍላተ ሀገር ብንመለከት የመንደር ምሥረታው ሊሳካ የቻለው



Digitized by Google

በተደረገው የተጠናከረ የማስተማር ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ይህም ተግባር በተለይ በጠላት ይነዛ የነበረውን አፍራሽ ወሬና ፕሮፓጋንዳ ከመቋቋም ጋር የተለየ ትኩረት ጠይቋል። ሥር ሥሩን ይናፈሱ ከነበሩት የጠላት አሉባልታዎች ጥቂቱን እንመልከት። አንድ ላይ ከተሰበሰባችሁ በኋላ ማናቸውም የግል ሀብታችሁ ይወረሳል ፤ ልጆቻችሁ ተሰብስበው ወደሌላ ይወሰዳሉ፤ ሴቶቻችሁ በግድ ለሌሎች ይሰጣሉ ፤ ገበሬ ያለከብት ሽታ እንዴት ይኖራል ወዘተ - የሚሉ ይገኙባቸዋል። በተለይ መስጊዳችሁ ሊፈርስ ነው እየተባሉ በአንዳንድ ሼኮች ነን ባዮች በሚደረገው ቅስቀሳ የተወናበዱ አንዳንድ ገበሬዎች ከብቶቻቸውን መሸጥ ፤ ከአካባቢው መሸሽ ሁሉ ጀምረው ነበር። ገና ከአምስት ዓመት በፊትም በዋቤ ፕሮጀክት አማካይነት የገበሬው ደሳሳ ጎጆ በቆርቆሮ እንደተቀየረ ገበሬውን ከዚያ ለማስወጣት ቆርቆሮ ቤት ገደ ቢስ ነው ፤ ስለሚንኳኳ ልጅና ጥጃ ስለሚደነግጡ አያድጉም እየተባለ አንዳንዶቹ በዚያው አካባቢ ሣር ቤት እየሠሩ እንዲገቡ ሁሉ አድርገው ነበር።

የጠላት ፕሮፓጋንዳ በተለይ ከገበሬው ሥነ ልቦና አኳያ ቀላል ባለመሆኑ በሐረርጌ የፓርቲ ካድሬዎች መንደር ተመሥርቶ እስኪያልቅ ከገበሬው ባለመለየት አብረው እየዋሉና እያደሩ በወቅቱ ፀረ አብዮት ቅስቀሳውን እያከሸፉ በመሄዳቸው ምሥረታው ሊሳካ ችሏል። በአርሲ ከመንደር ምሥረታው ኮሚቴ ጥረት በተጨማሪ ባለፈው ዓመት በነበረው የአየር መዛባትም ሆነ ቀደም ባለው ጊዜ በዋቤ ፕሮጀክት የተሰባሰቡት ገበሬዎች የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ መገኘታቸው ለቅስቀሳው ቁሳዊ መሠረት በመሆን አገልግሏል። በዚህ ላይ ሴሚናሮችን በማዘጋጀት ፤ በገበሬው መካከል ሆኖ ስለትክክለኛው ነገር በማስረዳት የተከናወነው ሥራ ቀላል ባለመሆኑ ጠቅላላው የመንደር ምሥረታ ተግባር ሊሠምር ችሏል።

## ማጠቃለያ

በሐረርጌ ፤ በባሌና በአርሲ ዛሬ በመንደር መኖር የሚያወያይ ጉዳይ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ኑሮ አንዱ ገጽታ ሆኗል። ገበሬው ስለመንደር የሚናገረው ከሰማው ሳይሆን ከራሱ ልምድ ነው። በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው መንደር ወደዋናው ግባችን ማለትም የገጠሩን ሕይወት ወደ መቀየሩ መረማመጃ በመሆኑ ከምሥረታ በኋላ ያለው የክትትል ሥራ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በቅስቀሳ ወቅት የገበሬው መሰባሰብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ተጠቃቅሷል። ከዚህ አኳያ ዛሬ ከገበሬው ሊመጣ የሚችለው ግፊት ከዓቅም በላይ እንዳይሆንም አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በተቀዳሚ በእራሱ በገበሬው ተሳትፎ አንገብጋቢ ለሆኑት በወቅቱ ምላሽ መስጠቱ ቸል ሊባል አይገባም። ገበሬው በራሱ አነሣሽነት ሊሠራ የሚያስባቸው ነገሮች በጥንቃቄ ሊታዩና ከዕቅድና ከዓቅም ጋር እየታዩ ሊበረታቱ ይገባል። ብዙ ድካም ጥቂት ውጤት ብቻ የሚያስገኝ ከሆነ ወደፊት ለመራመድ አያደፋፍርምና።

በጢቾ አውራጃ ፤ በአሚኛ ወረዳ የደሮሌ ገበሬ ከክፍለ ሀገሩ ዕቅድ ውጭ በመንደር ተሰባስቧል። በአካባቢው የውሃ ችግር በመኖሩም ገበሬው በራሱ አነሣሽነት 10,470 ብር አዋጥቶ ውሃ እንዲቆፈርለት እየጠየቀ ነው። በባሌ ክፍለ ሀገር አንድ መንደር ክሊኒክ በማሠራት ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲረከብ እየጠየቀ ነው። የነዚህ ዓይነቶች ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንዱ ዓቅምን ይጠይቃል። እንደውሃ ዓይነቱ ችግር ደግሞ ከዓቅም ባሻገርም የመገኘት ያለመገኘትም ጉዳይ አለ። ስለዚህ የልማት ሥራ ቆርጠ መነሣትን የሚጠይቅ የመሆኑን ያህል እያስተዋሉና ዓቅምን እየገነቡ በቅደም ተከተል መራመድን ይሻል።

የገበሬው በመንደር የመሰባሰብ ፋይዳ ተቀዳሚ ውጤት የእራሱ የገበሬው ሕይ



Digitized by Google

ዉት መለወጥ ነው ። የዚህም አዝማሚያ
ከመንደር ምሥረታው ማግሥት ጀም ር
ሊጠበቅ የሚችል በመሆኑ አሁንም ገበሬ
ውን የጉዳዩ ዋንኛ ባለቤት በማድረግ ባስ
ፈለገው ሁሉ በየአቅጣጫው መረባረብ
እጅግ አስፈላጊ ነው ። ይህም ርብርብ እንደ
መንደሩ ምሥረታ የአጭር ጊዜ ሳይሆን
ለአስተማማኝ የልማት እርምጃ መንደንደ
ሪያ የሚሆን ውጤት እስኪገኝ መቀጠል
ያለበት ነው ። ብዙ መሥዋዕትነት ሊጠይ
ቅም ይችላል ። ነገር ግን ገጠሩን በአፋጣኝ
ለመለወጥ ሌላ የተሻለ አማራጭ ያለ አይ
መስልም ።



Digitized by Google

# የአካባቢ ትምህርት ጠቀሜታ

አበበ ወርቁ

ኅብረተሰብ ቁሳዊና ኅሊናዊ ፍላጐቱን ለማርካት በሚያካሂደው ማኅበራዊ እንቅስቃሴ በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ጉልተው የሚታዩ የአካባቢ (Ecological) ለውጦችን እያስከተለ ነው ። አንዳንዶቹ ለውጦች ለሰው ልጅ ሕልውና መጠበቅ ፣ ለፍላጐቱ መሟላትና ለዕድገቱ መፋጠን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ ካልተወገዱ በስተቀር በሰው ልጅ ላይ ችግር ሊፈጥሩ መቻላቸውን ሳይንሳዊ መረጃዎች በአጽንኦት ይገልጻሉ ። በአሁኑ ጊዜ አካባቢያዊ ችግሮች እየበዙና አሳሳቢ እየሆኑ መጥተዋል ። ችግሮቹን ለማስወገድ ከሚያስችሉት መፍትሔዎችም አንዱ የሰውንና የተፈጥሮን ግንኙነት አግባብ ያለው ወይም ጤናማ ማድረግ ነው ። የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ለመመሥረት የተፈጥሮን ባሕርይ ፣ ተፈጥሮ ለሰው ሕልውና መሠረትና ለዕድገቱ አስፈላጊ መሆኗን ፣ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለው መስተጋብር በምን ሁኔታ ቢካሄድ ጤናማ ሊሆን እንደሚችል በትክክል መገንዘብ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። ይህንኑ ግንዛቤ ለማስገኘትም የአካባቢ ትምህርትን (Ecological Education) ማስፋፋትና በጥልቀት ማካሄድ መወሰድ ከሚገባቸው እርምጃዎች አንዱ ነው ። ስለአካባቢ ትምህርት ጠቃሚነትና ሚና ከማየታችን በፊት ሥነ አካባቢና የአካባቢ ትምህርት ምን እንደሆኑ እንመልከት ።

ሥነ አካባቢ (Ecology) የሚባለውን ጽንስ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት በ1866 ኧርንስት ሃይከል የሚባል ጀርመናዊ የሥነ እንስሳት ተመራማሪ ነው ።[1] ሃይከል ሥነ አካባቢ ማለት ሕይወት ያለው ነገር ከአካባቢው ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያጠና ሳይንስ ነው ብሎታል ። * በሃይከል ትርጉም መሠረት ሥነ አካባቢ የሰው ልጅ ስለ ሕይወት ያለው ዕውቀት አካል ነው ። በአሁኑ ጊዜ የሥነ አካባቢ ትርጉም ሰፍቶ ኅብረተሰብም ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት ጭምር የሚያጠቃልል ሳይንስ ሆኗል ። በዚህም ምክንያት ዛሬ ሥነ አካባቢ ማለት አንድ አካል ወይም ሥርዓት ከአካባቢው ጋር የሚያደርገውን መስተጋብር የሚያጠና ሳይንስ ነው ። [2]

ምሁራን ሥነ አካባቢን በተለያዩ ፈርጆች ይከፋፍሉታል ። ለምሳሌ የሰው ልጅ በግብርና ሥራው በአካባቢ ላይ የሚፈጥ

* ኢኮሎጂ የሚለው ቃል የመጣው ኢኮስ (Oikos) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው ። ኢኮስ ማለት መኖሪያ ወይም ቤት ማለት ነው ።

Digitized by Google

ረውን ተጽዕኖ ግብርና ነክ ሥነ አካባቢ
(Agricultural Ecology) ፥ አካባቢ በኅ
ብረተሰብ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ
ሰብአዊ ወይም ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ
(Human or Social Ecology) የሚሉ
አሉ ። [3] ይሁን እንጂ ሁሉም ምሁራን
በክፍፍሉ አይስማሙም ። አንዳንድ ምሁ
ራን ሥነ ማኅበራዊ አካባቢ ኅብረተሰብ
ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን መስተጋ
ብር የሚያጠና የሥነ አካባቢ አካል የሆነ
የዕውቀት መስክ ነው ሲሉ ሌሎች ግን
ሥነ ማኅበራዊ አካባቢ ምንም እንኳን
ይህንኑ መስተጋብር የሚያጠና ቢሆንም
ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው የሚል አቋም
አላቸው ። [4]

ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ የሚለውን ጽንሰ
ሐሳብ ያስተዋወቁት ከተሞች በአካባቢ
ያቸው ላይ ስለሚደርሱት ተጽዕኖ ተመራ
ማሪ የሆኑት አር ፓርክ ፥ ኢ በርገስ እና አር
ዲ. ማክኬንዚየ የሚባሉ አሜሪካውያን
ሳይንቲስቶች ናቸው ። ሳይንቲስቶቹ
በቃሉ መጠቀም የጀመሩት በ1920 ዎቹ
ውስጥ ሲሆን ፥ የመጀመሪያ ትርጉሙም
የሚያመለክተው ከአካባቢ በተዛመደ
ሁኔታ ስለከተሞች አመሠራረትና አሠ
ራር የሚያጠና ንድፈ ሐሳብን ነበር ። [5]
በአሁኑ ጊዜ ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ራሱን
የቻለ ሳይንስ ነው በሚሉ ምሁራን አስተ
ያየት ይህ ሳይንስ በ1960 ዎቹ መጨረሻ
ከማኅበራዊ ሳይንስ ፥ ከሥነ ሕይወትና
በአጠቃላይም ከተለያዩ የሳይንስ ፈርጆች
ዕውቀት በማገናኘትና በማዋሃድ አንድ
ራሱን የቻለ ሳይንስ ለመሆን ችሏል ።
ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ የተፈጠረው ቀደም
ሲል በተለመደው ሁኔታ ማኅበራዊና ተፈ
ጥሮአዊ ሕግጋትን በመነጣጠል ሳይሆን
አጣምሮ በማጥናት የአካባቢን ሁኔታ የሚ
መረምር የዕውቀት መስክ አስፈላጊ ከሆነ
በት ደረጃ ሲደርስ ነው ። የዚህ ሳይንስ
የትኩረት መስክም ሰው የአውደ ሕይወት
አጠቃላይ የዕድገት ሕግጋትን ለኅብረ
ተሰብ አመች የሆነ ተፈጥሯዊ የዕድገት
ሁኔታ ለመፍጠር በሚጠቀምባቸው ሁኔታ
ዎች አንፃር ማጥናት ነው ይላሉ ። [6] ማኅበ
ራዊ ሥነ አካባቢ ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው
በሚሉ ምሁራን አስተያየት ይህ ሳይንስ
ከሌሎች ሳይንሶች የሚለይበት አንዱ ምክ
ንያት በዚህ የትኩረት መስኩ ነው ። በተ
ጨማሪም ሀ/ በተፈጠረበት ምክንያትና
ዓላማ ፥ ለ/ የወደፊት ሁኔታዎችን ሲተን
ብይ በሚያተኩርበት ጉዳይ ፥ ሐ/ በሳይን
ሶች ክፍፍል ውስጥ በሚይዘው ሥፍራ
የራሱ ባሕርያት ጐልተው የሚታዩ መሆ
ኑን እንደሚከተለው ያብራራሉ ።

ሀ/ ከማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ሳይንስ
በፊት የነበሩ የተፈጥሮ ሳይንሶች ሁሉ
የተፈጠሩት በመሠረቱ የሰው ልጅ ተፈጥ
ሮን ለማወቅና ለመቆጣጠር ፥ የነበረውን
ፍላጐት ለማርካት ነው ። ኅብረተሰብ በአ
ሁኑ ጊዜ የገጠመውን የአካባቢ ችግር ለመ
ፍታት ተፈጥሮን በመቆጣጠር ለሰው
ጥቅም ማዋል ብቻ በቂ አልሆነም ። ተፈ
ጥሮን የግዴታ መንከባከብ ፥ ማኅበራዊ እን
ቅስቃሴን ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር ማጣጣም፥
በዚህም ሂደት ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያ
ደርሰውን ጥፋት ሁሉ ማቆምና ለሰው
ዕድገት መሠረትና አመች ሁኔታ የሆነውን
ተፈጥራዊ አካባቢ መጠበቅ አስፈላጊ ሆነ ።
ቅድመ ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ሳይንሶች
በተፈጠሩበት ዓላማና ባሕርይ ምክንያት
ይህን ዓይነቱን ችግር ለመፍታት በሚያ
መች መንገድ የተቀነባበሩና በዚሁ ላይ
የሚያተኩሩ አይደሉም ። ለዚህ ችግር አል
ባት ማግኘት እንዲረዳ ማኅበራዊ ሥነ
አካባቢ ተፈጠረ ። በመሆኑም ይህ ሳይንስ
የተጀመረበት ምክንያት እንደሌሎች የተ
ፈጥሮ ሳይንሶች ሰው በተፈጥሮ ላይ ያለ
ውን የበላይነት ለማስፈን ሳይሆን ለሰው
ሕይወት ሕልውና አመች የሆነ ተፈጥ
ሯዊ ሁኔታን ለመንከባከብ ፥ ሰው በተፈ
ጥሮ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለማስወ
ገድ ነው ። [7] መሠረታዊ ዓላማውም ኅብ
ረተሰብ በዕድገት ሂደቱ ከአካባቢ ጋር

Digitized by Google

የሚያደርገው መስተጋብር አዲስና ጤናማ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ መርዳት ነው ። [8]

ለ/ ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ እንደሌሎች የዕውቀት መስኮች ሁሉ በሚያጠናው መስክ ወደፊት ሊደርሱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ይተነብያል ፤ አሸጋገር ለማየት ይጥራል ። በትንበያው የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ግን ከሌሎች ሳይንሶች የተለየ ባሕርይ እንዲይዝ አድርገውታል። ሌሎች ሳይንሶች የሚተነብዩት የሰው ልጅ ማኅበራዊና ተፈጥራዊ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አዳዲስ ዘዴዎችን ለመፈለግ ሲሆን ፥ ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ግን ኅብረተሰቡ በወደፊት የዕድገቱ ሂደት ውስጥ በሚጠቀምባቸው የተፈጥሮ ሀብቶችና በአጠቃላይ በአውደ ሕይወት ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ የሚገጥሙትን እንቅፋቶች ለማሳየት ፥ ለማወቅ ነው ። [9] ይሁንና እንቅፋቶቹን አሳይቶ እንዴት ሊወገዱ እንደሚችሉ አይጠቁምም ማለት አይደለም ። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ነገር ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ማኅበራዊ ዕድገት በአጠቃላይ ሊያድግ የሚችልበትን ሁኔታ የሚመረምር ሳይሆን በዚሁ ዕድገት ሂደት ውስጥ የሚገጥሙትን ተፈጥራዊ ሁኔታዎች የሚያጠና ሳይንስ በመሆኑ የሚያተኩረው በዚህ ረገድ ዕንቅፋቶችን በመለየቱ ላይ መሆኑ ነው ።

ሐ/ የማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ሌላው ባሕርይ በተለመደው የሳይንስ መስኮች አከፋፈል (ማለትም በማኅበራዊና በተፈጥሯዊ ሳይንሶች ) ውስጥ በትክክል በዚህኛው መስክ ነው ተብሎ ሊመደብ አለመቻሉ ነው ። ለምሳሌ ኢ. ቪ. ጊሩሶቭ በሚባሉት የሶቭዬት ኅብረት ምሁር አስተያየት የማኅበራዊ ሥነ አካባቢ መፈጠር ካርል ማርክስ በማኅበራዊና በተፈጥራዊ ሳይንስ መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ የሚመጣ መሆኑን በመገንዘብ ወደፊት «ማኅበራዊ ሳይንስ ተፈጥራዊ ሳይንስን እንደሚጨምር ሁሉ ተፈጥራዊ ሳይንስም -- ማኅበራዊ ሳይንስን ይጨምርና አንድ ሳይንስ ይኖራል ።» [10] በማለት የተነበየው ተግባራዊ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። [11] በዚህም ምክንያት ምሁራን ይህ ሳይንስ ማኅበራዊ—ተፈጥራዊ ሳይንስ ተብሎ ሊጠራ ይችላል ይላሉ ። የሚያጠናው መስክ የኅብረተሰብንና የተፈጥሮን ግንኙነት ወይም መስተጋብር በመሆኑ የሚያተኩርባቸው ሕግጋትም የግድ ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ባሕርያት ያላቸው የኅብረተሰብንና የተፈጥር ግንኙነትን የሚገልጹ ናቸው ። በመሆኑም ሳይንሱ የሚያጠናቸው ሕግጋት «ማኅበራዊ አካባቢያዊ ሕግጋት» ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ ። [12]

በዚህ ጽሑፍ ስለማኅበራዊ ሥነአካባቢ አመጣጥና የትኩረት መስኮች ስናወሳ ይህ የዕውቀት መስክ ራሱን የቻለ ሳይንስ ሆኗል ወይም መሆን አለበት ከሚል መደምደሚያ ለመድረስ አይደለም ። እንደሚታወቀው የሳይንሶች ዕድገት በመሠረቱ የሚወሰነው በማኅበራዊ ታሪካዊ ፍላጐት ነው ። [13] ዛሬ ኅብረተሰብ ያጋጠመው አካባቢያዊ ችግር በተለያዩ ሳይንሶች መጠናትን የሚጠይቅ ነው ። በዚህ ሂደትም ምናልባትም የአካባቢን ችግር ወይም የሰውንና የተፈጥሮ ግንኙነት የሚያጠና አዲስ የሳይንስ ዓይነት ወይም ዓይነቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ ። ከነዚህም ሳይንሶች አንዱ ማኅበራዊ ሥነአካባቢ ሊሆን ይችላል ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰብአዊ አካባቢ ራሱን የቻለ አንድ ሳይንስ ሳይፈጠርለት የአጠቃላይ የሥነአካባቢ ሳይንስ አንዱ ፈርጅ ሆኖ ሊቆይ ይችል ይሆናል ። ይህ ጉዳይ ወደፊት ከኅብረተሰብ ዕድገት ጋር የሚታየው የሳይንሶች መራራቅና መቀራረብ ሂደት መልስ የሚያገኝለት ጥያቄ ነው ።

እዚህ ላይ ዋናው ነገር ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው በማለትና የዚህን ሳይንስ ልዩ የትኩረት መስክ፥ ዓላማ ፥ የወደፊት ትንበያና የሚያጠናቸውን ሕግጋት ባሕርይ ለማብራራት የሚ

Digitized by Google

ቀርቡት ሐሳቦች በአጠቃላይ የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግርን ለመፍታት ለሚደረግ ጥናት ጠቃሚ መሆናቸውን መገንዘቡ ላይ ነው ። ማለትም ማኅበራዊ አካባቢን የአጠቃላይ አካባቢ ሳይንስ አንዱ የትኩረት መስክ አድርጐ ፣ ወይም ነጥሎ ለማጥናት እላይ የተጠቀሱትን የማኅበራዊ አካባቢ ጥናት ባሕርያትን መገንዘብ በመስኩ ለሚደረግ ምርምር ውጤታማነት ይጠቅማል ።

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢ ችግር ላይ የሚያተኩር ሳይንስ አለ (ወይም ማኅበራዊ ሥነ አካባቢ ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው ካልን የሚያተኩሩ ሳይንሶች አሉ) ቢባልም ፣ ሌሎች ሳይንሶችም የአካባቢን ችግር በሚመለከታቸው አንፃር እያጠኑና ለችግሩም መቃለል አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ። አያሌ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ተመራማሪዎች ከኢንዱስትሪ ምርት የሚወጣ ቆሻሻ የአካባቢን አየር እንዳይበክል ለማድረግና እስከ አሁንም የተደረገውን ብክላ ለማጥፋት ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ግኝት እየፈለጉ ነው ። የሥነ ሕይወት ተመራማሪዎች ጥልቀትና ስፋት ያለው የአካባቢ ምርምር እንዲደረግና ወደፊት የሚቋቋሙ እንዱስትሪዎችም በምርምር በተገኘ መረጃ ላይ ተመሥርተው እንዲሠሩ ፣ በማንኛውም የትምህርት ተቋም የአካባቢ ትምህርት እንዲሰጥ እያሳሰቡ ነው ። ኢኮኖሚስቶች ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ሳይደርስ የአካባቢ ብክላ ሊወገድ የሚችልበትን መንገድና የኢኮኖሚ ዕቅድ ሲወጣ ወደፊት በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ እያጠኑ ፣ የተፈጥሮ እንክብካቤና ልማት በዝቅተኛ ወጭ ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ተጣምሮ የሚካሄድበትን ዘዴ ለመቀየስ እየጣሩ ነው ። በእነዚህና በሌሎችም የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አንፃር የአካባቢ ችግርን ማጥናት አካባቢያዊ ኢኮኖሚክስ(Ecological Economics) የሚባል የምርምር መስክን ፈጥሯል ።

የማኅበራዊ አካባቢ ችግር የጂኦግራፊ ተመራማሪዎችንም የሳበ መስክ ሆኗል ። በዚህ መስክ የሚያተኩረው የጂኦግራፊ ዕውቀት ታሪካዊ ጂኦግራፊ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ፣ የሚያጠናውም የማኅበራዊ ቡድንና የተፈጥራዊ አካባቢ ግንኙነትን ነው ። [14]

የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የአስተሳሰብን አጠቃላይ የዕድገት ሕጎጋት የሚያጠናው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍናም የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነቶችን አጠቃላይ ሕጎጋት ለማጥናትና በመስኩ ለሚካሄዱ ጥልቅ ምርምሮችም ዲያሌክቲካዊ የምርምር ስልትን የሚያስጨብጥ የሳይንስ መስክ ነው ። ሌሎችም አያሌ የሳይንስ ዓይነቶች ስለአካባቢ ችግር መፈታት ወይም ቁጥጥር ሥር መዋል አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ። ለምሳሌ የፖለቲካ ሳይንስ ዛሬ የሚታየው የአካባቢ ችግር ምን ያህል ከፖለቲካ ሥርዓት ፣ ከመደቦች ጥቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን ፣ ለአካባቢ ችግር እልባት ማግኘት የሚካሄደው ትግል በአጠቃላይ ሠርቶ አደሮች ከብዝበዛና ከጭቆና ለመላቀቅ ከሚያደርጉ የመደብ ትግል ጋር ተጣምሮ መካሄድ ያለበትና እንዴትስ እንደሚካሄድ ፣ መንግሥታት በጋራ ሆነ በግል አካባቢያዊ ችግሮችን ሊያቃልሉ ወይም ሊያስወግዱ ስለሚችሉባቸው ዘዴዎች ሐሳቦችን ያቀርባል ።

በአጠቃላይ ባለንበት ወቅት በተለይም ከ1970ዎቹ ጀምሮ አካባቢ በተለያዩ የሳይንስ ዓይነቶችና ፈርጆች ጥልቅ ምርምር እየተደረገበት ነው ። በዚህ መልክ የተገኘውና የሚገኘው ዕውቀት የአካባቢ ዕውቀት (Ecological Knowledge) ስለ አካባቢ ሁኔታ የሚሰጠው ትምህርትም የአካባቢ ትምህርት (Ecological or Environment Education) ተብሎ ሊጠራ ይችላል ።

የአካባቢን ችግር በየአቅጣጫው በዝርዝር ማጥናት በመስኩ ጥልቀት ያለውና የዳሰረ ዕውቀት ለማግኘት ማስቻሉ የሚ



Digitized by Google

ያከራክር አይደለም ። ይህ ዕውቀት ችግሩን በትክክል ለመረዳት ፣ ወደፊት ሊደርስ የሚችለውንም ለመተንበይና በቁጥጥር ሥር ለማዋል እንዲቻል አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ከወዲሁ ለመዘጋጀት እንደሚጠቅም መገመት ይቻላል ።

ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች በእርግጥ የተግባር መመሪያና የችግሩ መፍቻ መሣሪያ እንዲሆኑ አመች ሁኔታ ሊፈጠርላቸው የሚችለው በኅብረተሰብ ዕድገት ወደ ላቀ ደረጃ መሸጋገር ነው ። ከዚህ መደምደሚያ ለምን መድረስ እንደተቻለ በ«መስከረም» ቅጽ 5. ቍ. 22 የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር በሚል ርዕስ ዘርዘር ያሉ ነጥቦችን በማቅረብ ለማሳየት ተሞክሯል። እንደገና አንመለስበትም ። ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ወደላቀ ደረጃ ማለትም ወደ ኮሚኒስት ሥርዓት እስከሚሸጋገር ድረስ በአካባቢ ችግሮች ላይ የሚደረግ ምርምር ግኝት ችግሩን ለማቃለል ምንም ውጤት አያመጣም ማለትም ትክክል አይሆንም ። አንዳንድ የአካባቢን ችግር ሊያቃልሉ የሚችሉ ግኝቶችን (ለምሳሌ የአካባቢ ብክለን ለመከላከል በቁጠባ ላይ የተመሠረተ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ቴክኖሎጂያዊ ግኝትን ) ካፒታሊስቶችም ቢሆኑ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ወይም በተለያዩ ግፊቶች (በተራማጆች የመደብ ትግል ወዘተ. ) ምክንያት በምርት ሂደት የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይኖራል። ከዚህም በተጨማሪ የመስኩ ዕውቀት እየተስፋፋ መሄድ ለውጥ ፈላጊዎችና ደጋፊዎቻቸው የችግሩን ክብደትና መሠረታዊ መንሥኤ በሚገባ ተረድተው ለመፍትሔ እንዲታገሉ ይረዳቸዋል ። በአጠቃላይ ዛሬ የሚታየውን የአካባቢን ችግር ለመፍታት የሚያስችል አመች ሁኔታ ለመፍጠር በመጀመሪያ መሠረታዊ ማኅበራዊ ለውጥ ማድረግና ኅብረተሰብን ወደተሻለ የዕድገት ደረጃ በማሸጋገር ነው የሚለው መሠረታዊ ሐሳብ ሳይረሳ የአካባቢ ትምህርት የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች በአራት አጠቃሎ ለማየት ይቻላል ። እነርሱም 1/ የተፈጥሮ ሀብትን መከባከብ ፣ 2/ ይህንኑ ሀብት ማልማት ፣ 3/ ከተፈጥሮ ወይም ከአካባቢ ችግር ጋር የሚዛመደውን አስተሳሰብ ወይም ፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳ መቋቋም 4/ የተፈጥሮ ዕድገት ሕግጋትን መረዳትና ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከነዚህ ሕግጋት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ናቸው ።

### 1. የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ

ከተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ አንፃር የአካባቢ ትምህርት ሦስት ተግባራት አሉት ማለት ይቻላል ። አንደኛው ተግባር መላው የአካባቢ ሀብት ማለትም ዕፅዋት፣ እንስሳት ፣ አፈር ፣ ውሃ ፣ ወዘተ - ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ትውልድ ሕልውና መሠረት መሆናቸውን ማስገንዘብና እያንዳንዱ ግለሰብ ኃላፊነት ተሰምቶት ለተፈጥሮ ሀብት መጠበቅ የግልም ሆነ የወል እርምጃ እንዲወስድ ማሳመን ነው ።

የሰው ልጅ ሕልውና መጠበቅና ዕድገት ያለተስማሚ የተፈጥሮ ሀብት ፍጹም አይታሰብም ። የተፈጥሮ ሀብት ያለአግባቡ መባከንና መበከል የሰውን ሕልውና አደጋ ላይ ይጥላል ። ስለዚህም አንድ ግለሰብ ፣ ወይም ቡድን ለተፈጥሮ ሀብት የሚያደርገው እንክብካቤ ለሰው ልጅ ማሰቡንና እንክብካቤ ማድረጉን በተጨባጭ የሚያሳይበት ተግባር መሆኑን ሊረዳው ይገባል ።

በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ወይም ከእነጭራሹ ማለቅ ያስከተለው ችግር እልባት ካላገኘ ወደ ሀገር አቀፍ ችግር ደረጃ ሊሸጋገር የሚችል ነው ። ይህም የሕዝቡን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን በማስገንዘብ አስፈላጊውን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለማድረግ እንዲቻል የአካባቢ ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል ። «የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ፣ ብልጥ ያለቅሳል » ይላሉ አበው ። ይህ አባባል በአስተሳሰቡ



Digitized by Google

ያልዳበረውና የዚህን የተፈጥሮ ሀብት ጠቃሚነት ያልተረዳው ወገን ሀብቱ ሲወድም በዝምታ ሲመለከት ፣ ነገር ግን የተፈጥሮ ሀብቱ መባከን የሚያስከትለው ችግር የገባው እጅግ የሚያሳስበው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ። የአካባቢ ሁኔታ ትምህርት የተፈጥሮ ሀብት ለመንከባከብ ባህላቸው ዝቅተኛ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማንቃትና ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ በአጠቃላይም ሕዝቡ ስለተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የሚኖረው ዕውቀት የበለጠ የዳበረ እንዲሆን ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል ።

ሁለተኛ ፣ ተፈጥሮ ለሰው ሕልውና መሠረት ብቻ ሳትሆን ሰብአዊ አእምሮን ለማበልጸግና ለመቅረጽም አስተዋጽኦ ታደርጋለች ። የተፈጥሮ ውብ ገጽታ ፣ የመሬት ፣ የተራሮች ፣ የኮረብቶችና የደኖች አቀማመጥ ፣ የእንስሳት ዓይነቶች ፣ ሰው ስለተፈጥሯዊና ማኅበራዊ ክስተቶች የበለጠ እንዲመራመር ፣ ሁኔታዎችን እንዲያገናዝብ ይገፋፉታል ። የተፈጥሮንና ማኅበራዊ ዕውቀቱን እንዲያስፋፋ ፣ ሕይወትን በሰፊው እንዲተረጉም ይረዱታል ።

ሦስተኛ ፣ ተፈጥሮ ለሰው ልጅ ሕልውና መሠረትና ለአእምሮው ማዳበሪያ ብቻ ሳትሆን በሕይወቱ ውስጥ ላለው አስደሳች አስተሳሰብ ፣ ለትዝታውም ምንጭ ናት ። ለምሳሌ ሰው በተፈጥሮ ከሚያያቸው አረንጓዴ ገጽታዎች ፣ ከአበቦች ያሸበረቀ መልክ ፣ ከአእዋፍ ውብ መልክና ዝማሬ ፣ ከወንዝ ፏፏቴዎች ፣ በብሩህ ሰማይ ከሚታዩ ከዋክብትና ከሌሎችም የአካባቢ ገጽታዎች ውጭ የሆነ ፣ ወይም እነኝህን የተፈጥሮ ገጽታዎች የማይጨምር የሰው ልጅ አስተሳሰብ ምን ያህል የተራቆተና ደሀ እንደሚሆን በዓይነ ኅሊና በማስተዋል ለመገንዘብ ይቻላል ።

ዛሬ ስለ ሀገራችን የተፈጥሮ ገጽታ ስናስብ ትውስ ከሚሉን ነገሮች መካከል ፣ በዕፅዋት የተሸፈኑ ተራሮችና ኮረብቶች፣ የተዋቡ ሐይቆችና ወንዞች ፣ አስደሳች የዱር አራዊትና ሌሎችም የሚመስጡ ገጽታዎች ናቸው ። እነዚህን የተፈጥሮ ገጽታዎች የተገፈፈች እናት ሀገር ለማየት ቀርቶ ለማሰብ እንኳን የሚያሳዝን ፣ የሚያስጨንቅ ነው ። በብዙ አካባቢዎች ደኖች እንዳልነበሩ ሆነዋል ። ብርቅ የአራዊት መንጋዎች አልቀዋል ፣ ወይም ተሰደዋል ። በአንዳንድ አካባቢ ለም አፈሯ ተሟጦና መሬቱ ተራቁቶ ይታያል ። ዛሬ ከዚህ አኳያ ተጠናክሮ መካሄድ ያለበት ትግል ችግሩ እንዳይስፋፋ መቆጣጠርና እያደርም የተገፈፈው የተፈጥሮ ሀብት እንዲመለስ ማድረግ ነው ።

በሀገራችን የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ አመች ሁኔታ የፈጠሩ በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል ። ለምሳሌ መሬት ፣ ደንና ውሀ የጠቅላላው ሕዝብ ሀብት በመደረጋቸው ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ተግባራዊነት የተመቻቸ ነባራዊ ሁኔታ አለ ። ነገር ግን ሕዝቡ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መሆኑ ብቻውን የዚህን ሀብት እንክብካቤ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አያስችልም ። የሕዝቡ ንቃት መታከል አለበት ። ከዓለም የሶሻሊዝም ግንባታ ልምድ ለመማር እንደተቻለው አንድ ሕዝብ የንብረት ባለቤትነት መብትን መቀዳጀቱ ታላቅ ድል ቢሆንም ፣ የንብረቱ ትክክለኛ ተጠቃሚነት ግን አብሮ ወዲያው እውን የሚሆን አይደለም ። ሕዝቡ የብሔራዊ ሀብት እውነተኛ ባለቤት መሆኑን ተገንዝቦ በአግባቡ እንዲጠቀምበትና እንዲያዳብረውም ለማድረግ የሚያስችለውን አመለካከት ለመቅረፅ ረጂም ጊዜ ይጠይቃል ።

በዕድገቱ ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ባለና ሳይንሳዊ አስተሳሰቡ ባልዳበረበት እንዲሁም የአድኃሪ ፕሮፓጋንዳ በሚናፈስበት ኅብረተሰብ ውስጥ ብሔራዊ የተፈጥሮ ሀብትን በወል የመንከባከብ ባህል የቱን ያህል ዝቅተኛ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም ። ስለዚህ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ በሚገኝ ፣ ነገር ግን አብዮት በተፈጥሮ ሀብቱ



Digitized by Google

ላይ ባለቤትነትን ባተዳጀው እንደኛ ባለው ኅብረተሰብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ለማስገኘት ልዩ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ። በዚሁ መሠረት የሕዝቡን የባህል ደረጃ ከፍ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት ። የአካባቢ ሁኔታ ትምህርት ግቢይ የመፍትሔነት ሚናም እዚህ ላይ ነው ።

## 2. የተፈጥሮ ሀብት ልማት

የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ከተፈጥሮ ሀብት ልማትና ዕድገት ጋር ተዳምሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ። ተፈጥሮ ሰው ሁልጊዜ ለፍላጐቱ ማርኪያ ፣ ለሕይወቱ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ሁሉ የሚዛቅበት መስከ ተደርጐ መወሰድ የለበትም ። በሰው ተጽዕኖ ምክንያት ሊያልቅ ወይም ሊበላሽ የሚችል ነው ። ዛሬ የሰው ልጅ በአካባቢው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ በሁለት አቅጣጫ ማየት ይቻላል ። እነዚህም አንደኛ የአንዳንድ የተፈጥሮ ሀብት መመንመን ፣ ሁለተኛ የተፈጥሮ ሀብት መበከል (Pollution) ናቸው ። የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መፈጠር ሰው የተፈጥሮ ሀብትን በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት እንዲጠቀምበት በማድረጉ እያሌ የተፈጥሮ ሀብቶች ለምሳሌ ነዳጅ ፣ ብረት ፣ ወዘተ. ከከርሠ ምድር እየተሟጠጡ ነው ። የዓለም ሕዝብ ብዛት በተለይም በታዳጊ ሀገሮች እየናረ መሄድና ከዚሁም ጋር የተዛባ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መስፋፋት ለለም አፈር ፣ ለውሀና ለሌሎችም የተፈጥሮ ሀብቶች መመንመን አስተዋጽኦ እያደረገ ነው ። ከኢንዱስትሪና ከሌሎችም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚወጡ ቆሻሻዎችም የአካባቢን አየር እየበከሉ ነው ። ችግሩ እየተባባሰ የመሄድ አዝማሚያ ስላለው ዛሬ የሰው ልጅ ሕልውናውን ለመጠበቅ የግዴታ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብ ብቻ ሳይሆን ለሕልውናው ተስማሚ የሆነ አዲስ የተፈጥሮ ሀብት ማምረት ፣ አዲስ አካባቢ መፍጠር አለበት ።

አዲስ አካባቢ መፍጠር ወይም አዲስ የተፈጥሮ ሀብት ማምረት (Ecological Production) ለሚለው ቃል ምሁራን ተመሳሳይ ትርጉም አይሰጡትም ። [15] እንዳንዶቹ አዲስ አካባቢ መፍጠር ማለት ተፈጥሯዊ አካባቢን በሙሉ ወይም በከፊል ማምረት ነው የሚሉ አሉ።በአንዳንዶችም አስተያየት አካባቢን ማምረት ማለት በተፈጥሮ ከተሰጠው የተለየና ለኅብረተሰብ ዕድገት ጠቃሚ ፣ ለሰው ሕልውናና ሥራ ተስማሚ የሆነና ከዚህ በፊት ያልነበረ አካባቢ መፍጠር ነው ። አካባቢን ማምረት ማለት አጠቃላይ የምርት ሂደት በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አድርጐ ፣ ከአካባቢ ጋር አጣጥሞ ማካሄድ ነው የሚሉም አሉ። አካባቢን ማምረት ወይም መፍጠር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በመሠረቱ የመነጨው ለሰው ልጅ ሕልውና መጠበቅና ለዕድገቱ ዋስትና ማግኘት አመቺ የሆነ የአካባቢ ሁኔታ በሰው ኃይል የመሥራትን ነባራዊ አስፈላጊነትን ለመግለጽ ነው ። ከዚህ ሐሳብ በመነሣት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አካባቢን ማምረት ሲባል ፣ አንደኛ ዛሬ እየተመናመነ በመሄድ ላይ ያለውን እንዲሁም ከዚህ በፊት ለሰው ልጅ ጥቅም በመዋል ወይም በተፈጥሯዊ ለውጦች (ለምሳሌ በአየር ለውጥ) ወይም በሁለቱም ምክንያቶች የጠፉ ፣ ሁለተኛ ፣ እስከዛሬ ያልነበረ የአካባቢ ሁኔታን በሰው ሠራሽ ዘዴ መፍጠርን ለማመልከት ነው ። በመሆኑም በረሃማ አካባቢዎችን ማልማት ፣ ሰው ሠራሽ ዝናብ ማዝነብና የመሳሰሉት አካባቢያዊ ምርት ቢባሉ ስህተት አይሆንም ። ይህ ምርት በምድር ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ፕላኔቶች ፣ በጨረቃና በመሳሉት አካላት ላይ ፣ በሕዋ ውስጥ በአጠቃላይ እነጋገር የሰው ልጅ ሊደርስ በሚችልበት በማንኛውም ሥፍራ የሚካሄድ ሊሆን ይችላል። ይህን ለማድረግ ዛሬ በየአቅጣጫው የሚካሄደው የአካባቢ ምርምርና ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ።

Digitized by Google

### 3-የፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳን መቋቋም

እያሌ የቡርዧ ምሁራን የአካባቢን ችግር በሚመለከት የተለያዩ አስተያየቶችንና ንድፈ ሐሳቦችን ያቀርባሉ። ከሚያቀርቧቸው ሐሳቦች ውስጥ ችግሩን ለመረዳትና እልባት ለማግኘት የሚረዱ ቢኖሩም ተስፋ አስቆራጮችና የተሳሳተ «መፍትሔ» ጠቋሚዎችም አሉ። አንዳንድ የአካባቢ ተመራማሪ የቡርዧ ምሁራን ለአካባቢ ችግር መሠረታዊ መንሥኤ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው ከሚል ሐሳብ በመነሣት ለችግሩ እልባት ለማግኘት የሰው ልጅ የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ ዕድገቱን ማቆም አለበት የሚል ሐሳብ ያቀርባሉ። በአካባቢ ችግር ምክንያት የሰው ልጅ ፍጻሜ አይቀሬ ወደሆነ ጥፋት እያመራ ነው የሚሉም አሉ። ለምሳሌ ማሽን የሰውን ልጅ አጥፊ ነው የሚል አመለካከት ያለው ኦስዋልድ ስፔንግለር የሚባለው ጸሐፊ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍሯል፤ «---ወደ ሕይወታችን ፍጻሜ የሚያደርሰን ጎዳና ላይ ያለማወላወል በመጓዝ ላይ ነን። ቢሆንም ሌላ አማራጭ ስሌለን ተስፋ ሳይኖረንና ለመዳን ሳንጓጓ እስከመጨረሻው ድረስ መታገል ነው።»[16]

በተጨማሪም የሰው ልጆች በተፃራሪ መደቦች በመከፋፈላቸው ምክንያት የሚያካሂዱትን የርዕዮተዓለምና የፖለቲካ ትግል በመተው ከአካባቢ ችግር ላይ እንዲያተኩሩ የሚገፋፉ የቡርዧ ምሁራንም እያሌ ናቸው። በቀኝ አክራሪነቱ የታወቀው ዝብግኒው ብርዝኒስኪ የተባለው አሜሪካዊ ፖለቲከኛ «በርዕዮተዓለም ላይ የሚደረገው ትኩረት ለአካባቢ ችግር ለሚደረገው ትኩረት ቦታውን እየለቀቀ ነው»[17] ብሏል። ነገር ግን በተግባር እንደሚታየውና በአካባቢ ችግር ላይ በተካሄዱ ሳይንሳዊ ጥናቶች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ዛሬ የዓለም ሕዝብ በአካባቢ ችግር ወጥመድ ውስጥ የገባው ወደተሻለ የዕድገት ደረጃ ባለመሸጋገሩ በተለይም ለዕቅዳዊና ለተሟላ የተፈጥሮ አጠቃቀም እንቅፋት የሆነውን የምርት መሣሪያዎች የግል ባለቤትነትን ባለማስወገዱ ነው።[18] ስለሆነም ለችግሩ መፍትሔ የሚገኘው የጭቁኖችን የመደብ ትግል የበለጠ በማጠናከር፣ ወደተሻለና በዓይነቱ ወደላቀ የዕድገት ደረጃ በመሸጋገር እንጂ የርዕዮተዓለም ትግልን በማስወገድ አይደለም። ዛሬ የአካባቢ ችግርን ለመፍታት እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች አንዱ ለችግሩ እልባት መገኘት በሚታገሉ ብዙኃን ዘንድ ይህ ግንዛቤ አለመኖሩ ነው። አሜሪካዊ ኮሚኒስት ጋስ ሆል እንዳሉት፣ «የአካባቢን ብክለት በመቃወም የሚታገሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለሶሻሊዝም በመታገል አካባቢያቸውን ለማዳን ገና ዝግጁ አይደሉም።»[19] ግንዛቤውን ለማስገኘትና በአጠቃላይ በአካባቢ ችግር ላይ በመነሣት የሚነዛውን የተሳሳተ ተስፋ አስቆራጭ አስተሳሰብ ለመዋጋት በማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ አካባቢያዊ ትምህርት ማስፋፋት አንዱ መፍትሔ ነው።

ዛሬ ሀገራችን ከምትገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የአካባቢ ሁኔታ ትምህርት በሰፊው ማካሄድ በአጠቃላይ ስለአካባቢ በቡርዧ ምሁራን የሚነዛውን የተሳሳተ አመለካከት ብቻ ሳይሆን የአብዮቱን ድሎች በማጥላላትና ችግሮቹን በማጉላት የሚነዛውን የፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳ ለመቋቋምና ለማክሸፍም ይረዳል። የውስጥና የውጭ አድኃሪዎች በተለያዩ የቅስቀሳ ዘዴዎች በመጠቀም በሀገራችን የተከሰተውን የከፋ የአየር ለውጥና ድርቅ አብዮቱ ያስከተለው ክስተት አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል። መሠረታዊ መንሥኤው ተፈጥሯዊ መሆኑንና የመቋቋሚያው ዓቅም ማነስም ምክንያት የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ጭቆናና ብዝበዛ ቀጥተኛ ውጤት የሆነው ኋላቀርነት መሆኑን በመሸፈን፣ መፍትሔውም ሥር ነቀል ለውጥ ማካሄድ መሆኑን ሕዝቡ እንዳይገነዘብ ለማድረግ አደናጋሪ ፕሮፓ



Digitized by Google

ጋንዳ ያካሂዳሉ ። በሃይማኖት ትምህርት
ስም ጭምር ከፍተኛ የሥነ ልቦና ጦርነት
ከፍተዋል ። በአብዮቱ ወገኖች በቂና አስ
ፈላጊው የማክሸፍ እርምጃ ካልተወሰደ
በስተቀር ይህ ፕሮፓጋንዳ በሕዝብ ዘንድ
በተወሰነ ክፍልና ደረጃም ቢሆን ተቀባይ
ነት እንዲያገኝ የሚያስችሉት ሁኔታዎች
የሉም ማለት ያዳግታል ። ከነዚህም መካ
ከል ፣ ሀ/ ከሀገራችን የዕድገት ዝቅተኛነ
ትና ከወቅቱም የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ
የተነሣ በርካታ የኑሮ ችግሮች መኖ
ራቸው ፣ ለ/ ለሕዝባዊ ጠቀሜታ የሚ
ረዱ አብዮታዊ እርምጃዎችን ሁሉ በአ
ጭር ጊዜና በቀላሉ ለመገንዘብ ከባድ
መሆኑ ይገኙበታል ። እነዚህን ሁኔታዎች
ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክር ።

ሀ/ ሰፊው ሕዝብ ችግሮች ሲፈራረቁበት
በቆራጥነት ለመቋቋምና ለመፍታት ሕይ
ወቱን ጭምር ለመስጠት ዝግጁ እንደሚ
ሆን ተደጋግሞ የሚታይ ሐቅ ቢሆንም ፣
አንዳንዴ ከሱ ውስጥ የተወሰኑት ክፍሎች
በነዚህ ችግሮች ምክንያት የመማረርና
ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊያሳድርባቸው
ይችላል ። ታዋቂው የሶቭዬት ምሁር ላፕ
ቴቭ እንዳለው «በማኅበራዊ እንቅስቃሴ
ውስጥ የሚፈጸም ጥፋትና የፍትሕ መጉደል
ዓለምን በአጠቃላይ ፣ ተፈጥሯዊ ዓለምን
ጭምር የማውገዝ (ምንም እንኳን ይህ ማው
ገዝ ራስን እንደ መኮነን ቢሆንም) ፍላጐ
ትን ሊፈጥር ይችላል ።»[20] በአንዳንድ
ማኅበራዊ ችግሮች በመማረርና ተስፋ
በመቁረጥ ለምዝብሮች ነፃነት መካሄድ
ካለበት የነፃነት ትግል መድረክ መውረድ
ለሕዝባዊ ትግል መዳከም አስተዋጽኦ ማድ
ረግ ስለሆነ አድኃሪዎችን የሚጠቅም
አቋም ነው ። በተጨማሪም የዚህን ዓይ
ነት አቋም የያዙ ሰዎች ለአድኃሪ አስተሳ
ሰብ ለመጋለጥ ራሳቸውን የሚያመቻቹ
ይሆናሉ ። አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን
ትክክለኛ የትግል መሥመሩን ከሳተ የሱን
ችግር ወደሚያባብሰው የአድኃሪዎች አስ
ተሳሰብ ወጥመድ ውስጥ በመግባት ለነሱ
ዓላማ ተፈጻሚነት ይቆማል ።

በዚህ አንፃር በሀገራችን የተፈጥሮ ችግር
ብዙ ጊዜ መደጋገሙ ፣ አልፎ አልፎም
መባባሱና በስፋትም ብዙ አካባቢዎችና
በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠርቶ አደሮችን *
የነካ መሆኑ በአያሌ ሰዎች አእምሮ ላይ ያስ
ከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን
ጉዳት ተጽዕኖ መገመት ይቻላል ። ጉዳት የሚ
ደርስበት አርሶ አደር የችግሮቹን መንሥኤ
በትክክል ለመረዳት የሚያስችለው ሳይን
ሳዊ ዕውቀት የለውም ። አያሌ ገበሬዎች
የችግሮቹ መንሥኤ ፍርጃ እንጂ በዕውቀት
ሊደረስበትና መፍትሔ ሊገኝለት የሚችል
ተፈጥሯዊ ክስተት አይመስላቸውም ።[21]
በዚህም ምክንያት ራሳቸውን ያስጨን
ቃሉ ፣ ስለወደፊት ኑሯቸው የስትና ማግ
ኘት ይጠራጠራሉ ፣ ተስፋ የመቁረጥ ስሜ
ት ሊያድርባቸው ይችላል ። በገጠር የኢኮ
ኖሚ መናጋት የሚያስከትለው ማኅበራዊ
ችግር በከተማ የሚኖሩ ሠርቶ አደሮችን
ኑሮም ይነካል ። ከእነሱም ውስጥ የችግር
ችን መንሥኤ በትክክል የማይረዱና በዚ
ህም ምክንያት ለተሳሳተ አቋም መያዝ የሚ
ጋለጡ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ። በተ
ጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚ
ዎች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገ
ኙና ለሕዝባዊ ዓላማ ከልብ ያልቆሙ እንዲ
ሁም ሌሎች አድኃሪ ኃይላት በቀጥታም ሆነ
በተዘዋዋሪ የሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ችግርና
የሚያናፍሱት ወሬ በተወሰኑ የአብዮቱ
ወገኖች ዘንድ ጉጂ ስሜትን ሊፈጥሩባ
ቸው ፣ በዚህም ምክንያት ለዕድገታቸውና
ለተሟላ ነፃነታቸው ከሚያካሂዱት ትግል
ሊያዘናጓቸው ይችላሉ ።

---

* በኢትዮጵያ የ1977 መረጃ እንሚያመለክተው ከ9 ሚሊዮን ያላነሱ የገጠር ኗሪዎች በድርቅ ምክ
ንያት ኑሯቸው ተናግቷል ። ከነዚህ ውስጥ 7,5 ሚሊዮን የሚሆኑት የዕለት ርዳታ ማግኘት
የነበረባቸቸው ነበሩ ። የገጠሩ ኢኮኖሚ መቃወስ በከተማ ሠርቶ አደሮች ላይ የሚያስከትለው
የኑሮ ውድነትም አለ ።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ችግሮች እንዲሁም የአድኅሮት ኃይላት የሚያካሂዱት ፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ሕዝብ ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ጉጂ ተጽዕኖ ለመቋቋም ሕዝቡ በትግሉ ሂደት ውስጥ የገጠሙትን ችግሮች መንሥኤ በትክክል እንዲረዳ ፥ በራሱ በመተማመን ለመፍትሔአቸው እንዲታገልና አልባት እንዲሰጣቸው የሚያስችሉ ብዙ እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም ችግር የለም ለማለት አይቻልም ። ይህን ችግር ለመቋቋም ከሚያስችሉት መሣሪያዎች አንዱ ስለአካባቢ ተገቢ ትምህርት ማስፋፋት ነው ፤ በዚህም ሕዝቡ ራሱንና ተፈጥሮን በበለጠ ተረድቶ ለችግሮች አልባት እንዲሰጥ ፥ ከኋላቀር አስተሳሰብ እንዲላቀቅና በርትቶ ከታገለ ፍትህና ነፃነት የሰፈኑበት ኅብረተሰብ ሙሉ በሙሉ ሊገነባ የሚችል መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል ።

የአካባቢን ትምህርት አስፈላጊ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት ለሕዝባዊ ጠቀሜታ የሚወሰዱ አብዮታዊ እርምጃዎችን ሁሉ በቀላሉ መገንዘብ ከባድ መሆኑ እንደሆነ ከላይ ተመልክቷል ። በማንኛውም ሕዝብ ውስጥ በአብዮታዊ ትግል ሂደት የሚወሰዱ አብዮታዊ እርምጃዎችን ጠቃሚነት የሚጠራጠሩ ቡድኖች ሊኖሩ ይችላሉ ። ጉጂ ቢሆንም እንኳን ለብዙ ጊዜ የለመዱትን የአሠራርና የኑሮ ሁኔታ በአስቸኳይና በቀላሉ መለወጥን የሚቃወሙባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ ። ይህ ዓይነት አቋም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የገጠመ ጉዳይ ነው ። አንዳንድ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ምንም እንኳን በአብዮቱ ሂደት ከራሳቸው ትግል ብዙ የተማሩና እየተማሩ ፥ ልምድ እያካበቱ የመጡ ቢሆንም በፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት ከሳይንሳዊ አስተሳሰብ ተገልለው በመቆየታቸው እንዲሁም ሆን ተብሉ አእምሯቸው በአድኃሪ አስተሳሰብ እንዲመረዝ በመደረጉ ምክንያት የማኅበራዊ ችግሮችን ውስብስብነትና እነሱንም ለመፍታት የሚወሰዱ አብዮታዊ እርምጃዎችን ጠቃሚነት ሁሉ በግልጽ ለመረዳት የሚያስችላቸው ዕውቀት ገና አልቀሰሙም ፥ ቢቀስሙም ገና በቂ አይደለም ። በአጭሩ የዳበረ ዕውቀት አለመኖር ለዚህ ዓይነቱ ችግር ያጋልጣል።

ሌላው መንሥኤ ደግሞ ለማንኛውም ሕዝብ ቢሆን አዳዲስ ክስተቶችንና ችግሮችን በፍጥነት ጠንቅቆ መረዳት ከባድ መሆኑ ነው ። የአንድ ኅብረተሰብ የዕውቀት መሠረት የራሱና የወረሰው የልምድ ክምችት እንዲሁም በዚህ ዕውቀት ላይ በመመሥረት በሚያደርገው ማመዛዘን የሚደርስባቸው መደምደሚያዎች ናቸው ። ማኅበራዊ እንቅስቃሴና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በየጊዜው አዳዲስ ክስተቶችን ፥ ከነሱም ጋር የተያያዙ መፍቻሔ ሊፈለግላቸው የሚገቡ አዳዲስ ችግሮችን ይፈጥራሉ ። ሁሉንም ችግሮች በቀላል መረዳት እጅግ ከባድ የሚሆንበት ጊዜ አለ ። ይህም ብቻ ሳይሆን የተሳሳተ አቋም መፍትሔ ይሆናል ብሎ መደገፍም ይኖራል ። በዚህም ምክንያት ለችግሮች ትክክለኛ መፍትሔ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎችን በጥርጣሬ ማየት ወይም አለመደገፍ ያጋጥማል ። በእርግጥ በረጅም የትግል ሂደት አንፃር ሲታይ ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱት አብዮታዊ እርምጃዎች እያደር በሚያስገኙት ውጤት ምክንያት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታቸው አይቀርም ።

አንዳንድ ሰዎች ለጊዜው በትክክል ተረድተውና አምነውባቸው ሳይሆን በተጠርጣሪነት ተግባራዊ ከሚያደርጓቸው ጠቃሚ እርምጃዎች ትምህርት ይቀስማሉ ። በአጠቃላይም ሰፊው ሕዝብ « የሥራውን ፥ የትግሉን ፍሬ የበለጠ ሲያይ ፥ የፈታውንና የሚፈታውን ችግር ከባድነትና ውስብስብነት የበለጠ በግልጽ ይረዳዋል ። » [22] ይሁን እንጂ የታሪክ ሂደት ውስብስብ ችግሮችን ግልጽ በማድረግ ለትክክለኛ አቋም ምስክርነት የሚሰጥ ቢሆንም በማኅበራዊ የዕድገት ደረጃዎች አንፃር ሲታዩ አዳዲስ አስ



Digitized by Google

ቸጋሪና ውስብስብ ችግሮችንም ይፈጥራል፤ ስለሆነም በኅብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ በፊት ግልጽ ያልሆነው ጉዳይ የበለጠ ግልጽ ሲሆንና ሕዝቡ ሲረዳው አዲስ ግልጽ ያል ሆነና በብዙ የሕዝብ ወገኖች ዘንድ መጠራጠርን ወይም መደናገርን የሚፈጥር ክስተት መኖሩ አከራካሪ አይደለም ። የዕውቀት እንቆቅልሽም ( Paradox of Konwledge ) የዚህ ዓይነቱ ክስተት መኖር ነው። ሰው በታሪክ ሂደት ውስጥ የበለጠ ዕውቀት ሲያከማች ፤ ነገሮችን የበለጠ ሲረዳ አዳዲስ የማያውቃቸው ነገሮች ይገጥሙታል ። ማወቁ ፤ አለማወቁን የበለጠ ያስገነዝባል። መፍትሔውም የዕውቀት አቀባሰም ስልትን በአግባቡ መቀየስና የበለጠ ለማወቅ መታገል ነው ። ለዚህም ትግል መሳካት የአካባቢ ትምህርት አንዱ መግሪያ ነው ።

በተለይም ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የገጠመውን የአካባቢ ችግር ለመፍታት ፤ ሀልውናውን ለማስከበርና ዕድገቱን ለማፋጠን በትግል ውስጥ የገጠሙትን ውስብስብ ችግሮች የበለጠ ለመረዳት በአእምሮ ያለውን ኋላቀር አስተሳሰብ ለማስወገድና የሚነዛበትን የሥነ ልቦና ጦርነት ለመመከት የአካባቢ ትምህርት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ።

## 4- የተፈጥሮ ሕግጋትን መረዳት

ሠርቶ አደሮች የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብና ማልማት አስፈላጊ መሆኑን የሚያስገነዝብ ዕውቀት ከቀን ተቀን እንቅስቃሴያቸው ፤ በቀጥታ ከተፈጥሮ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ፤ በሌላ አገላለጽ በልምዳቸው ሊያገኙ ይችላሉ ። ምንጊዜም ዕውቀት የሚጀምረው ሰው ከሱ ውጭ ከሆኑ ነገሮች ጋር በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት በሚያደርገው ግንኙነት ወይም ጥናት ነው። ሰው በስሜት ሕዋሳቱ አማካይነት ከነገሮች ጋር በቀጥታ በመገናኘት የነገሮችን ምንነት ለመገንዘብ የሚያስችለውን መረጃ ያገኛል ። በዚህ ደረጃ የሚያገኘውም ዕውቀት ዳሰሳዊ ዕውቀት * (Emperical Knowledge) ይባላል ።

ዳሰሳዊ ዕውቀት የሰው ልጅ በልምድ የሚቀስመው የመጀመሪያው የዕውቀት ደረጃ ነው ፤ ስለነገሮችና ክስተቶች ትክክለኛ መረጃ ሊያስገኝ የሚችል ቢሆንም ውሱን ነው ። የነገሮችን ውስጣዊ ባሕርይ ምንነትና ግንኙነት በየፈርጃቸው ለይቶና አበጥሮ ለማወቅ ፤ የዕድገት ሕግጋታቸውን ለመረዳት አያስችልም ። የነገሮችን ውጫዊ ገጽታ ነው የሚያንፀባርቀው ። ነገር ግን የሰው ልጅ ዕውቀት መቅሰም ዋና ዓላማ የነገሮችን ውስጣዊ ባሕርይና የዕድገት ሕግጋትን መገንዘብ ነው ። ምክንያቱም «የሕግጋት ፤ የነገሮች ውስጣዊ ምንነት ዕውቀት ብቻ ነው ለሰው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መመሪያ በመሆን ሊያገለግል የሚችለው ።» [23] የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ረቂቃዊ ዕውቀት (Abstract Knowledge) ይባላል ።

ረቂቃዊ ዕውቀት ወይም አርቅቆት ( Abstraction ) በዳሰሳዊ ዕውቀት ላይ በመመሥረት የነገሮችንና የክስተቶችን ገጽታዎች በየፈርጃቸው በመለያየትና በመተንተን ፤ እርስ በርሳቸው በማገናዘብ ለዳሰሳዊ ዕውቀት ድብቅ የሆኑትን ጥልቅ ባሕርያቸውን ለመረዳት ፤ የሚገዙአቸውን የዕድገት ሕግጋት በጥልቀትና ሰፋ ባለ ሁኔታ ለመገንዘብ ይረዳል ። ነገሮች መስለው እንደሚታዩበት ሁኔታ ብቻ መቀበል ስህተት ላይ ይጥላል ። ምክንያቱም ከውጭ ሲታይ የነገሮች ምንነት አንዳንዴ

---

* ይህ ዕውቀት ዳሰሳዊ የተባለበት ምክንያት ሰው ስለነገሮችና ክስተቶች በአጠቃላይ ስለውጭው ዓለም የሚቀስመው ዕውቀት የሚያገኘው ግንዛቤ እንደ ባየው ብቻ ሳይሆን በተወሰነ ሥርዓት ከክስተቶች መደጋገም የተነሣ የሚያገኘው በመሆኑ ነው ።( ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገብ ቃላት ፣ እ-ኢ-ገጽ 427 )



Digitized by Google

የእውነተኛ ባሕርያቸው ተቃራኒ ሆኖ የሚገለጽበት ሁኔታ አለ ። ለምሳሌ ሰዎች ለረጅም ጊዜ ፀሐይ መሬትን ትዞራለች ብለው ያምኑ ነበር ። ዛሬም ቢሆን የሚያምኑ ብዙ ናቸው ። በእርግጥም በዓይን ሲታይ ነገሩ ይመስላል ። ሐቁ ግን መስሎ የሚታየው የተገላቢጦሽ ነው ፤ መሬት በፀሐይ ዙሪያ ትዞራለች እንጂ ፀሐይ መሬትን አትዞርም ።

በተጨማሪም የነገሮችን ባሕርይ ትክክለኛ ገጽታና ምንነት የሚገልጽ መረጃ እንኳን ቢገኝ ፣ የተገኘውን መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች በማጤንና በሱ ላይ ተመሥርቶ የሚወሰደው እርምጃ የሚያስከትላቸውን ልዩ ልዩ ውጤቶች አስቀድሞ በመተንበይ ማኅበራዊ ጠቀሜታቸውን ወይም ጉጂነታቸውን ማጣራት ያስፈልጋል ። [24]

በአንድ አቅጣጫ ሲታይ ጠቃሚ የሚመስለው ነገር በተለያዩ አቅጣጫዎች ሲታይና ሲገመገም ግን ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል ። በዚህ ዓይነት ጥንቃቄ የሚካሄድ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ነው ከግብታዊነት ለመላቀቅ የሚያስችለው ።

ስለግብታዊ አሠራር ሲወሳ አንድ መታወስ ያለበት ጉዳይ አለ ። ይኸውም ማኅበራዊ ችግርን ለመፍታት በግብታዊና በዕቅዳዊ አሠራር መካከል ያለውን ልዩነት የመገንዘብ ጥያቄ ነው ። አንድን ማኅበራዊ ችግር በዕቅድ ማስወገድ ማለት ችግሩን ለማስወገድ አስቦና አቅዶ መሥራት ብቻ አይደለም ። ችግርን ለመፍታት አስቦና ሊከተል የሚችለውንም ውጤት በዓይነ ኅሊና አሻግሮ በማየት ወይም አውቀዋለሁ ብሎ በማሰብ መሥራት በማንኛውም የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ ያለና ሰው ከሌሎች እንስሳት ወይም ፍጡራን የሚለይበት አንዱ ባሕርይ ነው ። ይህ ባሕርይ ብቻውን አንድን ማኅበራዊ ችግር በዕቅዳዊ አሠራር መፍታትን ወይም ማስወገድን ላያስገኝ ይችላል ። ምክንያቱም ማኅበራዊ ችግር በዕቅድ ተፈታ ለማለት የሚቻለው ይከናወናል ተብሎ በታሰበው ግብና ይህንኑ ግብ ተግባራዊ ለማድረግ በሚካሄደው እንቅስቃሴ አማካይነት በሚገኘው ውጤት መካከል ከሞላ ጎደል መቀራረብና መጣጣም ሲኖር ነው ። በአጭሩ ማኅበራዊ ችግር በዕቅድ ተፈታ ለማለት የሚቻለው ግብና ውጤት ሲመሳሰሉ ነው ። የሁለቱ መጣጣም የማኅበራዊ ችግር በዕቅዳዊ አሠራር እልባት ለማግኘት ወይም ላለማግኘቱ ፣ አንድ ኅብረተሰብ በዕቅድ ለማደግ ወይም ላለማደጉ ዋነኛና ወሳኝ መለኪያ ነው ። [25]

በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ዕውቀትና ጥንቃቄ የተሞላበት አሠራርን ይጠይቃል ። ይህም አሠራር በነገሮች ሕግጋት ፣ ባሕርይና ምንነት ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ነው በእርግጥ ነባራዊ ሁኔታን በማንፀባረቅ የተግባር መመሪያ ሊሆን የሚችለው ። የአንድ ክስተት (ማኅበራዊ ወይም ተፈጥሯዊ ችግር ጭምር ) ምንነት ታወቀ ማለትም የክስተቱን አመጣጥ ፣ የሚገዙትን ሕግጋት ፣ ወሳኝና መሠረታዊ ባሕርይ ወደፊትም የሚይዘውን አቅጣጫ መረዳት ነው ።

የክስተቱን ምንነት ለማወቃችን ምስክሩም የታዋቂውን ክስተት ሂደት በሚፈለገው አቅጣጫ ለመምራት [26] ወይም በሰው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቆጣጠር የሚኖረን ብቃት ወይም የዕውቀት ችሎታ ነው ። የዚህ ዓይነት ዕውቀት የሚገኘው ደግሞ ከሥነ አካባቢና ከሌሎችም ሳይንሶች ነው ። የሳይንስ ዕውቀት ልዩ ባሕርይ በተግባር የተገኘውን ዕውቀት በከፍተኛ ደረጃ በማካተት የተፈጥሮና የማኅበራዊ ክስተቶችንና ሂደቶችን እውነተኛ ውስጣዊ ባሕርይና ሕግጋት ፣ በንድፈ ሐሳብና በአርቅቆት መግለጽ ነው ። [27] መሠረታዊ ተግባሩም የነገሮችን ምንነት ማወቅ ነው ። [28] በአጠቃላይ ሥነ አካባቢንና ሌሎችንም የአካባቢ ሁኔታን የሚ



Digitized by Google

መረምሩ የሳይንስ ዕውቀቶችን በአካባቢ ትምህርት በማቀነባበር ማስፋፋት ጠቃሚ መሆኑ ግልጽ ነው ።

## የአካባቢ ትምህርት ማስፋፊያ መንገዶች

የአካባቢ ችግር መፍትሔ ማግኘት የሕዝብን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል ። ለዚሁ ችግር መፍቻ የሚሰጠው ትምህርትም ለመላው ሕዝብ መሆን ይገባዋል ። ስለዚህ ትምህርቱ በመገናኛ ብዙኃን (ጋዜጦች ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና በመሳሰሉት) በቤተሰብ ፣ በትምህርት ቤቶች ፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችና በኪነታዊ ሥራዎች አማካይነት መተላለፉ አስፈላጊ ነው ።

የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ልማት በቀጥታ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች፣ የግብርና ሚኒስቴር ፣ ብሔራዊ የውሃ ሀብት ልማት ኮሚሽን ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ወዘተ- በጋዜጦች ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ የሚረዱ ተከታታይ ትምህርቶች ለመስጠት መጠነኛ ጥረት እያደረጉ ነው ።

ጋዜጣ ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የአካባቢ ሁኔታን የሚመለከት ትምህርትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ሊኖራቸው ይችላል ። እነኝህ የመገናኛ አውታሮች በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ በርቀት ፣ በሥራ ባሕርይ የአካባቢ ትምህርት ለመቅሰም ችግር የገጠመውን የኅብረተሰብ ክፍል ለማስተማር ያስችላሉ ። በተጨማሪም በእነኝህ አውታሮች የሚተላለፈው ትምህርት እንደየኅብረተሰቡ ክፍል የንቃት ደረጃና ሥነልቦናዊ አመለካከት በቀላሉ ሊዘጋጅና ሊለዋወጥ የሚችል ነው ። በዚህ ረገድ በተለይ ለማይምነት ተዳርጎ በኖረው ሕዝባችን ዘንድ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አስተዋጽኦ ምን ያህል የጎላ እንደሆነ ለመገመት አያስቸግርም ። በተለይም ብዙ ቋንቋዎች በሚነገሩባትና የሥነጽሑፍ ዕድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኝባት ሀገራችን የአካባቢ ትምህርትን በተለያዩ ቋንቋዎች በመገናኛ ብዙኃን ማስተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ። ይሁን እንጂ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አውታሮች ውሱንነት ትኩረት ተሰጥቶት ዓቅም በፈቀደ መጠን እየተቃለለ መሄድ ይኖርበታል ። ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል የትምህርት ሚኒስቴርን የአካባቢ ሬዲዮ ጣቢያዎች በይበልጥ አጠናክሮ ማንቀሳቀስም ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል ።

የሬዲዮና የቴሌቪዥን እጥረትን ለማቃለል ጥረት ማድረግ ሌላው ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው ። ከእጥረትም ባሻገር የብዙኃኑ ሕዝብ የመግዛት ዓቅምም ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ ሕዝቡ በጋራ ዓቅሙ ለመጠቀም በሚችልበት መልክ የተደራጀ በመሆኑ በተለይ በገጠርም የገበሬው በመንደር መሰባሰብ ለማናቸውም አገልግሎቶች መዳረስ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው ። በዚሁ ሁኔታ በመጠቀም ሬዲዮና ቴሌቪዥን ደረጃ በደረጃ ለማዳረስ ይቻላል ።

ቤተሰብም እንደአካባቢ ትምህርት ማሠራጫ አካል ሊያገለግል ይችላል ። እስከዛሬም ቢሆን ትምህርቱ ትክክለኛ ግንዛቤ አግኝቶና ታስቦበት አልተካሄደም እንጂ ማንኛውም ቤተሰብ ሕፃናትን ስለማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ሲያስተምር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለተፈጥሮ ሀብት ትምህርት መስጠቱ አይቀርም ። በአሁኑ ጊዜ ግን ትምህርቱ ታስቦበትና ዓላማው ግልጽ ሆኖ ቢካሄድ የበለጠ ውጤት ያስገኛል ። ሕፃናትን ለማስተማር ቤተሰቡና የአካባቢው ሕዝብ ስለተፈጥሮ ያለው ዕውቀት የወሳኝነት ሚና አለው ። በዚህ አንፃር ሲታይ በሀገሪቷ ውስጥ የመሠረተ ትምህርት መስፋፋት ፣ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት እና በትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የአካባቢ ትምህርት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቤተሰብ ለሕፃናት የሚሰጠውን የአካባቢ ትምህርት የሚያግዝ ይሆናል ። በተጨማሪም የአካባቢ ትምህርት በሙዓለ ሕፃናትና በአፀደ ሕፃናት ሊሰጥ ይችላል ።



Digitized by Google

ትምህርት ቤቶች ፣ እንደሌሎቹ የትምህ ርት ዓይነቶች ሁሉ የአካባቢ ትምህርትን በጥልቀት ለማስገንዘብና ተግባራዊ ለማ ድረግ የሚያስችሉ ማዕከሎች ናቸው ። በኢ. ትዮጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይህ ትምህርት ከ2—3 ክፍል ድረስ እራሱን ችሎ የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ በላይ ባሉት ክፍሎች ግን ከሌሎች የትም ህርት ዓይነቶች ለምሳሌ ከሳይንስ ፣ ከጂኦ ግራፊና ከባልትና ትምህርት ጋር ተዳብሎ የሚሰጥ ነው ።

ከአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተ ጨማሪ የተለያየ ደረጃ ባላቸው የትምህርት ተቋሞችና ዩኒቨርስቲዎች የአካባቢ ትምህ ርት ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር ግን ኙነት ካላቸው ሳይንሶች ውስጥ በመጠቃ ለል ይሰጣል ። ለምሳሌ በአሥመራ ዩኒቨር ስቲ እራሱን የቻለ ዲፓርትመንት ሆኖ ባለ ሙያዎችን በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ በማስ መረቅ ላይ ባለው የበረሃ እርሻ ትምህርት ክፍል ፣ በዓለማያ ዩኒቨርስቲ በአፈር ሳይ ንስ ትምህርት ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጂኦግራፊ ፣ በጂኦሎጂ፣ በባዮሎጂና በሌሎ ችም ከሥነአካባቢ ሳይንስ ጋር የቅርብ ተዛ ምዶ ባላቸው ሳይንሶች ውስጥ ከሞላ ጐደል በመጠቃለል እየተሰጠ ነው። የወንዶ ገነት የደን ልማት ትምህርት ተቋም ፣ የአምቦ መ ለስተኛ የእርሻ ኮሌጅና ሌሎችም ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የአካባቢ ትምህርትን በተለያዩ የሳይንስ መስኮች ውስጥ በማካ ተት እያስፋፉ ነው ። በተጨማሪም የሕን ፃው ሥራና ዝግጅቱ በቅርብ ጊዜ ተጠናቆ የውሀ ልማት ባለሙያዎችን በባችለር ዲግሪ ደረጃ ያሠለጥናል ተብሎ የሚጠበ ቀው የአርባ ምንጭ የውሀ ቴክኖሎጂ ኢን ስቲትዩት የአካባቢን ትምህርት ለማስፋ ፋት አንዱ መድረክ ይሆናል ። እንዲሁም ከተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ልማት ጋር በቀጥታ በተገናኙ ሳይንሶች አያሌ ኢትዮ ጵያውያን በውጭ ሀገሮች እየሠለጠኑ ነው። ለምሳሌ በ1978 መጨረሻ 70 ኢትዮጵያ ውያን በውሀ አጠቃቀምና ልማት በባችለር ዲግሪ ደረጃ እንዲሠለጥኑ ወደ ሕንድ ተል ከዋል ።

በአንድ ሀገር ውስጥ የአካባቢ ትምህርት አሰጣጥ ስፋትና ጥልቀት እንደየሀገሩ የተፈ ጥሮ ችግርና እንደሚሰጠው ትኩረት ሊለ ያይ ይችላል ። ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት በሞስኮ ዩኒቨርስቲ ከ1948 ጀምሮ በማንኛ ውም መስክ የሚሠለጥን ተማሪ የግዴታ መውሰድ ያለበት ልዩ የተፈጥሮ እንክብካቤ ትምህርት (Commen course) ይሰጣል ። በዚችው ሀገር በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ ተገቢ አጠቃቀምና ልማት ትምህርት የሚ ሰጡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ተከፍ ተው የበሰሉ ባለሙያዎች እየሠለጠኑ ነው ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች (በዩኒቨርስቲ ጭምር) በተለያዩ ሳይንሶች ውስጥ በመጠቃለል የሚሰጠው የአካባቢ ትምህርት በሀገሪቷ ውስጥ ካለው የትም ህርቱ አስፈላጊነትና በሌሎችም ተራማጅ ሀገሮች ለትምህርት ከሚሰጠው ትኩረት አንፃር ሲታይ በቂ አለመሆኑ ይታመናል።

ለአካባቢ ትምህርት መስፋፋት የአካ ባቢ ችግር አሳሳቢነትን በጥልቅ ከተረዱ ምሁራን ከፍተኛ የሥራ ድርሻ ይጠበቃል። እንደሚታወቀው ያሉበት ኅብረተሰብም ሆነ የዓለም ሕዝብ በአጠቃላይ የገጠመው የአካባቢ ችግር ጉልቶ ከመከሰቱ በፊት በቅ ድሚያ የተረዱ ፣ ለሰው ልጅ አሳሳቢነቱን የገለጹ ፣ ችግሩን ሕዝቡ በትክክል እንዲ ረዳውና ኃይሉን አስተባብሮ እልባት እን ዲያገኝለት የሚጥሩ ፣ አስተሳሰባቸውን በሳ ይንሳዊ አመለካከት የቀረጹ የሕዝብ ወገን ምሁራን ናቸው ። በዚህ አንፃር በኢትዮጵ ያም የአካባቢን ችግር ለመፍታት ምሁራን ሊጫወቱ የሚችሉትን ሚና ለመገመት አያዳግትም ። ለሕዝብ ለቆሙ ምሁራን በየ ሠለጠኑበት ሙያ ዛሬ ይህ ሕዝብ ሕልው ናውንና ዕድገቱን ከሚፈታተነው የአካ ባቢ ችግር እንዲላቀቅና ለተሻለ የኑሮ ሁኔታ እንዲያበቃ ታግሎ ማታገል ታላቅ ታሪካዊ ኃላፊነት ነው ።



Digitized by Google

በሀገራችን ስለአካባቢ ትምህርት መስፋ ፋትና የተግባር መግሪያ መሆን ሲኖግ መረሳት የሌለበት ጉዳይ በመላ ሀገሪቷ የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ ፣ ለማልማትና ተፈጥሮን የበለጠ ለማወቅ የሚያደረገውን እንቅስቃሴ ለማቀነባበር ፣ የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር ነው ። በሀገሪቷ ውስጥ በአካባቢ ትምህርት አሰጣጥና ምርምር ሂደት ውስጥ የሥራ መደራረብ ለማስወገድ ፣ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ ፣ የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብና ለማልማት ፣ በቀጥታ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት በታቀደላቸው መሠረት የሥራ ድርሻቸውን መወጣታቸውን ለመቆጣጠርና ከጥላ ጉደል አንድ ወጥ አመራር ለመስጠት የሚያስችል መንግሥታዊ አካል ገና አልተመሠረተም ። አንዳንድ በመወሰድ ላይ ያሉ እርምጃዎች ግን በቀላሉ እውን ለማድረግ እንደሚቻል ይጠቁማሉ ። በአሁኑ ጊዜ የማስተባበሩን ተግባር ብሔራዊ ማዕከላዊ ፕላን ጽ/ ቤት ሥር የሚገኘው የፊዚካል ፕላኒንግ መምሪያ በአጠቃላይ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ ይታወቃል ። ይሁን እንጂ ከጉዳዩ መውሬታዊነት አኳያ የበለጠ የትርብ ክትትል ለመስጠት የሚያስችል ዘዴ መፍጠሩ እንደሚጠቅም ይታመናል ።

የአካባቢ ትምህርት መስፋፋት ዛሬ ሀገሪቷ ለገጠማት የአካባቢ ችግር አስተማማኝና ዘላቂ መፍትሔ ማግኘት በአጠቃቀም ዕድገቷን በሳይንሳዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ለማድረግ ፣ ሕዝቡ የላቀ ሳይንሳዊ ዕውቀትን እንዲቀስምና የተግባር መመሪያው እንዲያደርገ ለማስቻል አማራጭ የለውም።

## የግርጌ ማስታወሻ

1. Yu. P. Trusov, "The Ecological Approach and Problems of Moulding the Noosphere, an article in *Philosophy and the Ecological Problems of Civilisation* (Moscow: Progress Publishers, 1983), p. 58. See also *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 29, p. 280.
2. Yu. P. Trusov, p. 59.
3. *Great Soviet Encyclopedia* Vol. 29, p. 280.
4. *Ibid*, p. 284.
5. E.V. Grusov, "The Normative Character of Ecological Knowledge," an article in *Philosophy and the Ecological Problems of Civilisation*, p. 209. See also *Great Soviet Encyclopedia* Vol. 29, p. 284.
6. E.V. Girusov, p. 209.
7. *Ibid.*, p. 210.
8. *Ibid.*
9. *Ibid.*
10. Karl Marx quoted by E.V. Girusov, p. 209.
11. E.V. Girusov, p. 209.
12. *Ibid.*, p. 211.
13. M.G. Chepikov, *The Integration of Science* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 25.
14. *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 29, p. 284.
15. See E. T. Faddeev, "The Problem of Econogical Production," an article in *Philosophy and Ecological Problems of Civilisqtion*, p. 115.
16. Oswald Spengler, as quoted by T.I. Oizerman, "Historical Materialism and the Ideology of 'Technical Pessimism'" an article in *Philosophy and and the Ecological Problems of Civilisation* p. 350.



Digitized by Google

17. Z. Brzezinski, *Between Two Ages*, New York, 1970, p. 61 quoted by G. Khozin, *The Biosphere and Politics* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 46.

19. G. Hall, *Ecology. Can We Survive Under Capitalism?*, New York, 1972, p. 93 as quoted by G. Khozin.

20. I. Laptev, *The Planet of Reason* (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 34.

21. Mesfin Woldemariam, *Rural Vulnerability to Famine in Ethiopia*: 1958 1977 (New Delhi: Vikas Publishing Pvt. Ltd., 1984), pp. 141-143.

22. *Philosophy in the USSR: Problems of Historical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 142.

23. V. Afanasyev, *Marxist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 158.

24. See *Fundamental of Marxist-Leninist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 189.

25. Alexander Spirkin, *Dialectical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1983), p. 108.

26. *Fundamentals of Marxist-Leninist* Philosophy, p. 509.

27. *Ibid.*, p. 192.

28. I. Laptev, pp. 102-103.



Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 071 108 976
Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

BSPP

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

BSPP

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google